# መሪሳ

(የመ ቼት ፊልሞ)

@BOOKALEM

የመጻሕፍት አለም
የቴሌግራም ቻናሉን ይቀላቀሉ

@BOOKALEM

የተለያዩ አዳዲስ እንዲሁም ነባር መፅሐፍትን በአነስተኛ ሜጋባይት ያገኙበታል

Description

የተለያዩ መፅሐፍትን በአነስተኛ ሜጋባይት
የሚያገኙበት ቻናል····· @BOOKALEM

t.me/BOOKALEM

@BOOKALEM

# ወሪሳ

## (የውድቅት ፈለጎች)

ዓለማየሁ ገላጋይ

@BOOKAlEM

© የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያ እትም - ሐምሌ 2007ዓ.ም
ሁለተኛ እትም - ነሐሴ 2007ዓ.ም
ሦስተኛ እትም - መስከረም 2008ዓ.ም
አራተኛ እትም - ኅዳር 2009ዓ.ም

## የደራሲው ቀደምት ስራዎች

- ✓ እጥቢያ
- ✓ ትበላ
- ✓ ሰብሐት ገብረእግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት
- ✓ ኩርቢት
- ✓ የፍልስፍና አፅናፍ
- ✓ ኢህአዴግን እከስሳለሁ
- ✓ መልክአ-ሰብሐት
- ✓ የብርሃን ፈለጎች

ዋና አከፋፋይ፡- 0923797954/0936959644

# ምስጋና

ለመዐዛ ግርማ እና
ለቤተልሔም እመነሸዋ

@BOOKALEM

# ምዕራፍ አንድ

## 1 - ትውውቅ

እንደ ኢየሱስ በወንበዴዎች መካከል ተቸንክሬአለሁ፡፡

ላይኛው ጉረቤቱ ጡጫው ቀርቶ ግልምጫው የሚያደባይ ማጅራት መቺ፡፡ ታችኛው ተጉራባቼ ከአይን የፈጠነ ከምናምን የቀጠነ ሞጭላፋ፡፡

ይሄን ሳስብ ተናዘዝ፣ ተናዘዝ፣ ይለኛል፡፡ እንደው ለወጉ ነው እንጂ የአማርኛ አስተማሪ ምኑን ይናዘዛል? ወር መጻሬሻዬ እንኳን ተረት አይደል?

ቢሆንም መናዘዝ አይከፋም፡፡ ቢያንስ ቤተዘመድ ሃብት ያለኝ መስሎት በሐሜት ከመቧጨቅ መትረፉ አንድ ነገር ነው፡፡

"እኔው ሞቼ እኔ ቴስ ጠርቼ" አሉ፡፡ ሳቁ መጣ፡፡ የጣዕር ድምፅ የመሰለች ሳቅ አፈተለከች፡፡ ደነገጥኩ፡፡ ስሰቅ የሞላልኝ መሰሏቸው ያለችኝን ሊጣ ነፍስ እንዳይናጠቁኝ፡፡

እንግዲህ ላይ ላዩን ላየኝ ነፃ እመስላለሁ፡፡ መንፈሴ ግን እንደ ጃኬት ግራና ቀኝ በአንራባቾቼ ተጨምድዳለች፡፡ እራሴን በተራቡ ድመቶች አንፃር እንደተንጠለጠለ ቋንጣ ቆጥሬዋለሁ፡፡ ዕድሜ የሆንኝ ድመቶቹ ከተሰቀልኩበት ለማውረድ እስኪዘይዱ ድረስ ማሰላሰላቸው ነው፡፡

መብራት ሲጠፋ ጨለማ ውስጥ ብዙ አይኖች ይታዩኛል፡ እንደ ድመት ዓይን ብርሃን የሚታለበ ብሌኖች የገና መብራት መስለው "ብልጭ ድርግም" ይላሉ፡፡ "በስመአብ" ብዬ መብራት አበራለሁ፡፡ ምንም የለም፡፡ የሚጃ አክስቴ ትርክምክም ዕቃዎች እንደ ባለጌ ባልቴት በባዶ እፎቻቸው የሚስቁብኝ ይመስሉኛል፡፡ የዛገ ጎድጓዳ ሳህን፡ ትሬይ፡ በቡና እተላ የጠቆረ ረከቦትና ስድስት ተራ ሲኒዎች፣ ጀበና፡ ማንከሽከሻ... የአክስቴ መንፈስ ያረፈባቸው ስለሚመስለኝ አውጥቼ ለመጣል አልደፈርኩም፡፡

የሥራ ዝውውር የጠየኩበትን አረገምኩ፡፡ እርሲ ነገሌ ውስጥ ኩየራ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለሁ ሲሻኝ ሽልሜ፡ ሲከፋኝ ተራግሜ ነፍሴ ሳትጨማደድ እኖር ነበር፡፡ በግዛ እጄ በአዲስ አበባ የሥራ ቅያሪ ስብብ ስላሜን በጦርነት ሰወጥኩ፡፡

"ዶሮ ጭራ ጭራ፣ መታረጃዋን ካራ" አሉ፡፡

በብላ ተባላ ዘመን፡ ብላ ተባላ ሠፈር ገባሁ፡፡ ጤነኛ የሌለበት፡፡ የሚሰማው ሁሉ የሚያባትት፣ ሥማቸው እራሱ ላፉቱ፡ ጨልፌ፡ ቀማው፡ ደምሰው፡ ጎመጄ፡ አጋደለች.... ምናምን የሆነበት፡፡

አክስቴን መርገም አማረኝ፡፡ ይሄን ቤት ያወረሰችኝን፡፡ ምን ታወርሰኛለች፣ ልጇ ክከርቸሌ እስኪወጣ ቤቱን እንድጠብቅለት ተናዘዘችብኝ እንጂ፡፡

ለመሆኑ የልጇ መፈቻ መቼ ነው? እስላሁት፡፡ ገና ድፍን ስምንት ወራት ይቀሩታል፡፡

"እኔ የምሞተው ባሬ ማታ፣ ገብስ የሚደርሰው ለፍልሰታ" አሉ፡፡

እንኳን ስምንት ወር ስምንት ቀንም እንጃ፡፡ ለነገሩ እዚህ ክገባሁ እኮ ሃያ ሰባት ቀን ሞልቶኛል፡፡ ማን ያውቃል?

የሠፈሩ ምስጢር ሳይገለጥልኝ በፊት እንደ መንተባረርም፡ እንደ መጠየፍም ቃጥቶኝ ነበር፡፡ ፊት ለፊቴ ወዳሉ አሮጌ ጭልፊት መሳይ ባልቴት ሄጄ ያላንዳች ሰላምታ ጥያቄዬን መዠረጥኩላቸው፡፡ ቀሚሳቸውን ይዞ የቆመው ህፃንም ሳይታዘበኝ አልቀረ፡፡





"ማን ይሉታል ሠፈሩን?" አልኳቸው፡፡

"ወሪሳ ሠፈር ይባላል" አሉኝ፣ በነጠላቸው ጫፍ አፋቸውን እያበሱ፡፡

"ምን ማለት ነው እሱ?" ትንሹ ልጅ ለማዳ ቢጤ ነው መሰል ተጠግቶኝ የሱሪ ጨርቄን መጎተት ጀመረ፡፡ አዘቅዝቄ አየሁት፡፡ እቀፈኝ በሚል እጁን እንከርፍፏል፡፡ ጥቂት እንገራግሬ እንሳሁና አቀፍኩት፡፡ እንገቴ ውሽቅ አለ፡፡ የሀመምተኛ ልጅ ትኩሳትና ሁኔታ አለው፡፡

"ወሪሳማ" ባልቴቷ ማብራራት ያዙ "ወሪሳማ፣ ወረረ፡ ዘረፈ፡ በዘበዘ ማለት ነው፡፡"

ደንገጥ አልኩ፡፡ "ታዲያ ይሄ እንዴት ለሠፈር ሥም ይሰጣል? ስፈዝ ነውም" ልጁ እንትልፍ የወሰደው ያሀል አድፍጧል፡፡

"እረ እንዲያም አይደል"

"እና?..."

"የወንዶች ሠፈር ሆኖ እንጂ"

"ማለት?"

ባልቴቷ እንደጭልፊት ጋደድ ብለው በጎን እያዩኝ በጥያቄ መሰሉ፡፡

"ነጥቆ የሚበላ ወንድም አይደል?"

አተኩሬ አየኋቸው፡፡ የደከሙ ባልቴት ይሁኑ እንጂ ሁኔታቸው እኔን ለንጥቂያ የቋመጡልኝ አስመስሏቸዋል፡፡ ምን ላይ እንደተጣድኩ ያኔ አወቅኩ፡፡ መውረር፡ መዝረፍ፡ መበዝበዝ ግዳይ የሆነበት ሠፈር፡፡ ልጁን አወረድኩት፡፡ ገና መሬት እንዳስነካሁት ባልጠበኩት ቅልጥፍና 'ሽርርርር' ብሎ አሮጊቷን አልፏቸው ወደ ጭለማው ቤታቸው ገባ፡፡ እኔም ነገሩ ሁሉ ተምታቶብኝ ወደ ቤቴ፡፡

ከቆይታ በኋላ የኪስ ቦርሳዬን ብፈልግ አጣሁት፡፡ አልደነገጥኩም፡፡ ብዙ ጊዜ እዚያው ትምህርት ቤት 'ሎከሬ' ውስጥ እየዘነጋሁት እመጣለሁ፡፡



@BOOKALEM

ነገሩ እንዲያም አልነበር፣ ጠዋት ወደ ሥራ ልሄድ በሬን ስከፍት መታወቂያዬንና የተለያዩ ማስታወሻዎቼን ተበታትነው ደጄ ላይ አገኘኋቸው፡፡

## 2 - ትውውቅ ሲጠብቅ

ከመስሪያ ቤት ሞዴል ለመውሰድ ተገደድኩ፡፡

የቦርሳዬ መሰረቅ ግን አሁንም እንቆቅልሽ ነው፡፡ ወሮሳዎች ጣሪያ ላይ ሆነው ቦርሳዬን እንደምንብኝ ብለው ጠሩት? ያም ሆነ ይህ ኑሮዬ ድንገተኛ ጥፌ እንዳረፈበት ሁሉ ደንግጧል፣ ዞሮበታል፡፡ ለተወሰነ ሳምንት ወይም ወር በጊዜ ወደ ቤት እየገባሁ ካላረጋጋሁት፣ እንደዞረበት ሊቀር ነው፡፡

ወደ ቤቴ ለመግባት ስጣደፍ የበሬን ቁልፍ አጣሁት፡፡ ሱሪ ኪሴን፣ ኮት ኪሴን፣ ሸሚዝ ኪሴን...

በዚህ መካከል አንድ የአዛውንት ድምፅ ሰማሁ፡፡

"ደግም አይደል፣ ጥሩም አይደል..."

ዞር አልኩ፡፡ እኛ የንጥቂያ አፍለኝነታቸው ያልበረደላቸው ባልቴት ከአንድ አዛውንት ጋር በር ላይ ቆመዋል፡፡ አዛውንቱ እንደተጠፈጠፈ ቆርኪ ሰፋት እንጂ ቁመትና ውፍረት የላቸውም፡፡ ግርማ ሞገስ ባለው ገሳጭ ድምፅ ቀጠሉ...

"ሰው እንዴት እግዚሐሩን ይዳፈራል?"

ቁልፌን ሳለማግኘት እየለገምኩ አዳምጣለሁ፡፡

"ሰው እንዴት የፈጣሪውን ትዕዛዛት ይጥሳል? ሰው መሆን እምን ላይ ነው? ከጥጆች፣ ከዳክዬዎች፣ ከውሾች... በምን ተሻለ?"

"ጎሽ!" አልኩ በልቤ፡፡ ከሰዶምና ጎሞራህ ሎጥ እንደተገኘ እንዲሁ ከወሮሳም እኚህ አዛውንት በፃድቅ ገሳጭነት ቆመዋል ማለት ነው፡፡ ከለላ - ጥጋት መሰለው ታዩኝ፡፡

ቀጠሉ - አዛውንቱ "አሁን እኔን ለምሳሌ ውሰዱ፤ አትግደል የሚል ትዕዛዙን ፈፅሞ አልተላለፍም፡፡ የዶሮ ነፍስ በእጄ አልፎ





አያውቅም፡፡ ለምን ብዬ? ያናደደኝ ቢኖር ኮረንቲ እንዲይዘው፣ መኪና እንዲደጠው እመኛለሁ፡፡ ተግቼም እጠልያለሁ፡፡ ይሄ ካልያዘልኝ ለዱርዬ ጥቂት ብር ሰጥቼ አስገድለዋለሁ፡፡ ከዚህ በተረፈ ነፍስ በእጄ አልፎ አያውቅም፡፡"

ቁልፌን በጥድፊያ ማፈላለግ ጀመርኩ፡፡ ለመሆኑ ባልቆለፈው ምን እንዳይጠፋ ነው? ወሮሳዎችን ቁልፍ ያቆማቸው ይመስል... አገኘሁት፡፡ ከፈትኩ፡፡ ገባሁ፡፡ ነገሮች ተደበላለቁብኝ፡፡ የወሪሳ ሠፈር ቅጥ አንባር አልገባኝ አለ፡፡ በሩን ዘግቼ በጭላንጭል ወደ ውጭ አየሁ፡፡ አዛውንቱና ባልቴቷ መካከል ያ እንደ እፉዬ ገላ የቀለለ ትንሽ ልጅ ከመቆሙ ሌላ የተለወጠ የለም፡፡ ወጋቸውም ቀጥሏል፡፡

"አንዳንድ ጠላቶቼ" ይላሉ አዛውንቱ "አንዳንድ ጠላቶቼ ሌባ ነው ይሉኛል፡፡ ከኋላዬ ምን እንደሚወራ አውቃለሁ፡፡ አሁን እኔ "አትስረቅ" የሚለውን ትዕዛዙን እጥሼው ነው የምሰርቀው? በፍፁም! የሰው ሃቅ ወደ እኔ አልፎብኝ አያውቅም፡፡ ለምን ብዬ? እርግጥ የወደቀ ካገኘሁ የማነው? አልል ይሆናል፡፡ ይሔ ግን ሌባ አያሰኘኝም፡፡ አንዳንድ ዝንጉዎች ልብሳቸውን ሽቦ ላይ አስጥተው ቤታቸው ይቀመጣሉ፡፡ ይሄኔ ልብሱን ከሽቦው ላይ አነሳለሁ፡፡ ይሄማ ሌብነት ነው፡፡ ጎትቼ መሬት እጥለዋለሁ፡፡ እና እግዚአብሔር ችግሬን አይቶ፣ ፀሎቴን ሰምቶ በቸርነት እጄን እንደዘረጋልኝ ቆጥሬ ከመሬት አነሳዋለሁ፡፡ 'የወደቀ አንሱ የሞተ ቅበሩ' አይደል እስተንተረቱስ? እና ሰው እንዴት የፈጣሪውን ትዕዛዝ ይጥሳል? ሰው መሆኑ እምን ላይ ነው?"

ድንገቴ ስራ አካላቴን ወረረኝ፡፡ ኧረ ምንድነው ጉዱ?

በብላ ተባላ ዘመን፣ ብላ ተባላዎች መካከል ተገኘሁ፡፡

እርሷ ነገሌና ኩየራ ትምህርት ቤት አይኔ ላይ ተንከራተተ፡፡ ከላይ እሳት፣ ከታች እሳት፣ ከጎን እሳት፣ ከኋላ እሳት..... ወሪሳ፡፡

"አንተም ከፉ ነበርክ ከፉ አዘዘብህ፣
እንደ ገና ዳቦ እሳት ነደደብህ፣" የተባለው ማን ነበር?

የሁለቱ ጎረቤቶቼ ድምፃቸውም አይሰማ፡፡ እንዳደፈጠ ድመት ለሽ ብለዋል ማለት ነው፡፡ ድንገት ጉብ! ሊሉብኝ?

እንግዲህ ጭዳ መሆኔ ነው፡፡ ፍርሃት እንደሥጋ ዘመድ እራስጌዬ ግርጌዬ እያለ ይከተለኝ ጀመር፡፡ ብትት ብትት ያደርገኛል፡፡ ሁለቱ አጎራባቾቼ ቤት ከጣሪያ ወርዳ መሬት የምታርፍ ዝንብ ዳና እንኳን በጉልህ ይሰማኛል፡፡ ግን ምናምኒት ድምፅ የለም፡፡ ያም ሆነ ይህ ብዙ የፍርሃት እኗኗር ስልቶች እነድፍ ጀመር፡፡ ማምሸት ዋነኛው የማይታሰብ ነው፡፡ መጠጣት መተው፣ በሞዴል ብር ቤቱን ሳሳድስ የነበረውን መተው፡ ነባር ዕቃዎቼን ማምጣት መተው፡ የደላው መስሎ ለመታየት አደርግ የነበረውን ጥረት መተው፣ የተማርኩ የተመራመርኩ እያልኩ መብለጥለጤን መተው… እንግዲህ በእነዚህ ጥረቶቼና በመላእኩ ተራዳኢነት፣ ባቄላ ተፈላ ውሃ የሚያተርፈው እትርፍኝ ይሆቼን ስምንት ወር…

## 3 - የትንሣኤው መለከት

የረፋዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መገባደጃ ላይ ነው፡፡ እያስተማርኩ ሳለ ሰው ይፈልግሃል ተባልኩ፡፡ ስወጣ ያስጠራኝን ሰው አይቼ ደነገጥኩ፡፡ እንደ ኩይሳ የአፈር ቱልል መስሎ ተከምሯል፡፡ የላይኛው ጎረቤቴ፡፡ በጡሜ ሳይሆን በግልምጫ የሚያደባየው፡፡ መስሪያ ቤት ድረስ መጥቶ በማን አለብኝነት ማጅራቴን ሊሰኝ?

"ጤና ይስጥልኝ" አለኝ፡፡

(ጤናማ አንተ ስጠኝ እንጂ ለማን "ሪፈር" ትልከኛለህ?) አልኩ በልቤ፡፡

"የመካሻ እናት ነዎት አይደል?"

"አዎ" አልኩ፡፡ (መካሻ የታሰረው የአከስቴ ልጅ ነው፡፡)

"ይጠይቁታል?"

"አዎ"

"መፈቻው ደርሷል ይባላል"





"አዎ" የሆነ የአለኝታነት ስሜት ተሰማኝ፡፡

ኩይሳው የሰራውን ኪስ ደባብሶ "ይህቺን ይስጡት" አለ እጁን እየዘረጋ፡፡ "ከወሪሳ ሠፈርተኞች የተዋጣ ነው፡፡"

የህልም ትብብሉ'ሽ በመካከላችን ተከናወነ፡፡ ላምን አልቻልኩም፡፡ በወረቀት የተጠቀለለ ዳጎስ ያለ የብር ቅርፅ እጄ ላይ ለሽ ብሎ ተኝቷል፡፡ ኩይሳውን ከኋላው ስመለከተው ሁለመናውን በትከሻው ጋርዶት እህያ የማይችለው ዝናብ የመጣ መሰለኝ፡፡

## 4 - ትንሣኤ

ለካ ሳይታወቀኝ እኔም ወሪሳ ላይ ጥላዬን ጥዬ ኖሯል፡፡ የአከስቴ ልጅ የአካባቢው የጎበዝና የጎበባዝት አለቃ፣ የታፈረ፣ የተከበረ፣ አድራጊ ፈጣሪ፣ ብዙ ግባር ያለው (መቼም ወሪሳ ላይ አይታረስ)

ወሪሳ ላይ መፍራት ቀርቶ ማስፈራራቱ ገነነ፡፡ ትክ ብሎ ያየኝን፦

"መካሻን ጠየከው?" እላለሁ፡፡

ቅልስ፣ ምልስ ይልና "አዋተቼያለሁ" ነው መልሱ፡፡

"እድሜ ለእኔ ለአጎቱ ገንዘብ አላጣም፡፡ ሰው ነው ያጣው….." ወግ እንደ ቶክራ ማሽበሪያ አደርጋለሁ፡፡

መጠጣት፣ ማምሸት ተጀመረ፡፡

ፍፁም ወሪሳዊ ሆንኩ፡፡

ጋባገሮቼን ተማምኜ እጠጣለሁ፣ ደጋፊዎቼን ተማምኜ እስከራለሁ፣ የመካሻውን ሥም ተማምኜ እጠጣለሁ፡፡ ወሪሳ ቁርጥ የበፈቷ እርሲ ነገሲ፡፡

## 5- ከትንሣኤ መልስ

መባጠጤ በዛ መሰል፡፡ አንድ ሌሊት ድንገት ስባንን በድንጋጤ ድርቅ ብዬ ቀረሁ፡፡



@BOOKALEM

ከአልጋዬ ፊትለፊት አንድ ሰው የባፍ ጥላ መስሎ ቆሞ ነበር፡፡ መቼም መልአክ ሊሆን አይችልም፡፡ መልአክ ወሪሳ ሠፈር ምን ሊያደርግ?

መብራት ሳበራ እጄን ሰሰድ፡-

"ተው!" አለኝ፡፡

ተውኩ፡፡

በቀደደው ግድግዳ ሥር የሚገባውን ብርሃን ውጦ ያስቀረ ፀለም ያለ ፊት አለው፡፡ በገባበት ተዳዳ ሹልክ ብሎ ወጣ፡፡

ስለዚህ ሰው እንደተንጋለልኩ አሰብኩ…

"በመጀመሪያ እንዴት አባቱ ደፈረኝ" የሚል እብሪት መጣብኝ፡፡ "እኔ የመካኝ እንትኑ!" በኋላ ግን የማያዋጣኝ ሆኖ ተውኩትና ስለሁኔታው አሰላስል ጀመር፡፡

መቼም ቤት ሰርሳሪ ሊሆን አይችልም፡፡ ምን ሊያገኝ ሲለፋ አደረ? በወዲያ ከመዞር ብሎ በቤቱ ውስጥ ለማቋረጥ ያሰበ መንገደኛ መሆን አለበት፡፡ ካልሆነም ጠቋሚ አሳስቶታል ወይም ሲጠቆም ተሳስቷል፡፡

በደንብ ሳስበው ግን ሁኔታው ስጋት አጫረብኝ፡፡ መካኝን የሚፈሩ እንዳሉ ሁሉ ማጥቃት የሚፈልጉ ቢኖሩስ? በግዴየለሽነት እንደ እሮጌ ልብስ አውልቄ የጣልኳት ፍርሃት ተመልሳ መጣች፡፡ እናስ? ያ የጭዳንት ፍርሃቴ መልሶ አስደገደገኝ፡፡ ብዙ አይኖች ጭለማው ላይ እንደ ሌት ኮከብ ይጣቀሱኝ ጀመር፡፡ ይሄ ሁሉ አለልክ መባጠጤ ያመጣው እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ ከድንበሬ አልፌ ብዙ አጥቅቻለሁ፡፡ መመለስ፡ ወደ ድንበሬ፡ ወደ ቦታዬ…፡፡

## 6 - የማስተካከያ እርምጃ

"እንደምን አደራችሁ?" አለወትሮዬ "ሳይ፡ታቹ፡ ግራ፡ ቀኝ"

"እዘሀር ይመስገን" ባልቴቷ መለሱ፡፡

የተነደለውን ግድግዳ መለስ ብዬ አየሁት፡፡ እኔን እንዲህ ነድሎኝ ቢሄድ የማን ያለህ ይባል ነበር? አሰብኩ፡፡ ወደ ሥራ ስሄድ ያየሁትን ሁሉ በናፍቆት እያቀፍኩ ሰላም አልኩ፡፡





"እንዴት ናችሁ ታዲያ? እማን ነው? እሰይ!…"

ከሥራ ስመለስ ከንትር ግሮሰሪ ጎራ ብዬ ከዚህ ቀደም የጋበዙኝን ሁሉ ጋበዝኩ፡፡

"ዛሬ እንዴት ነው የመካኝ እንትን?" ሲሉኝ

"ደስ ብሎኛል" አልኩ፡፡

ወደ ቤቴ ስመለስ የጐልፊቷን ባልቴት በር እንኳኩቼ "ቡኒች ቡና አፍሉ" አልኳቸው፡፡ እንደ ወፍ ጥርስ የሌለው መንቁር አፋቸው ውስጡ እስኪታይ ፈገግ ብለው ተቀበሉኝ፡፡

ሲጋስኑቱን አብዝቼ አከናወንኩ፡፡ ወሪሳዎች የሚቅሙበት ቦታ ድረስ ሄጄ ጫት ገዛሁላቸው፡ ሲጀራ አክልኩላቸው፡፡

መካኝ ስሙም ሳይነሳ እራሴን ብቻ ይዤ ወሪሳን ዞርኳት፡፡

## 7 - ትውልድ

ሌፋቱ ሜዳ ላይ አልቀረም፡፡ እያንዳንዱ ወሪሳዊ እንደ አንድ ወሪሳዊ ይመለከተኝ ጀመር፡፡ አንድ ቀን ጫት ላይ ይሔን ሰምቼ ገረመኝ፡፡

ወሬው የተነሳው የባልቴቷ የልጅ ልጅ ልጅ… (ስንተኛ እንደሆነ እንጃ) ጫት የሚቃምበት ቤት መጥቶ ነው፡፡ ዘንጧል፡፡ እንደጥጥ ዘለላ የሌለው ቀይ ፀጉር እራሱ ላይ ብን ብን ይላል፡፡ "ስታድግ ምን ትሆናለህ በለው" አሉኝ፡፡

"ማሙሽዬ ስታድግ ምን ትሆናለህ?" አልኩት፡፡

"ሌባ" አለኝ በኩራ፡፡

"ለእሱ ነው እንጂ ሌባ ከሆነ ቆይቷል" አሉ ጫት ቃሚዎቹ፡፡

"እንዴትን?" አልኳቸው፡፡ ይሄን ነገሩኝ፡፡

የወሪሳ ጎረምሶች ይዘውት ወደ ባቡር መንገድ ይወጣሉ (አሁንም ለመሄድ ነው የመጣው) ትልቅ ሰው፡ ኮት የለበሰ ይጠብቅና፡-

"አባባ አሻግሩኝ" ይላል፡፡



@BOOKALEM

"ማሙሽዬ ወዴት ልትሄድ ነው?" ይሉታል፡፡

"እማዬ ጋ"

ሊያሻግሩት እጁን ሲይዙት፡-

"እፈራለሁ እቀፉኝ" ይላል፡፡ እጁንም ለመታቀፍ ያንከረፍፋል፡፡ ሰውየው ምንተፍረታቸውን ሲያቅፉት እንገታቸው ውስጥ ተወሽቆ እንጀታቸውን እየበላ የኮት ኪሳቸውን ይበዘብዛል፡፡ የኪስ ቦርሳ ወይም ብር ይዞ ይወጣል፡፡

ይደነቃል ወይም ይስቃል ብለው ይሄን ሲነግሩኝ እኔ ግን ፈዝዤ ቀረሁ፡፡ ይሄ እቶዬ ገላ የሆነ ልጅ እኔንም .... እቀፈኝ ያለኝ፡ እንገቴ ውስጥ ውሽቅ....

## 8 - ታሪካዊቷ ወሪሳ

ወሪሳዊነቴ ከፀደቀ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሥራ እንደወጣሁ ወደ ቤቴ አመራሁ፡፡ ሠፈሩ ጭር ብሏል፡፡ ፊት ለፊት ያሉት ባልቴት በሰፌድ ላይ ምስር ክክ እየለቀሙ ነበር፡፡ አይናቸው ስለደከመ ፊታቸውን ለሠፌዱ አቅርበው በአፍንጫቸው የሚለቅሙ መስለዋል፡፡ ቀና ብለው አይተውኝ ፈገግ አሉ፡፡ የልጅ-ልጅ-ልጅ ልጃቸው እንኳን ወደ ባቡር መንገዱ ተሰማርቶ የለም፡፡ ወሪሳ በሰው ሐራራ እያዛጋ ነው፡፡ የወር መዳረሻ ስለሆነ እንደ አንድ የአማርኛ መምህር መጠን ተረት ለመመዝበር አቆበቆብኩ፡፡

ባልቴቷን ቀረብኳቸው፡፡

"ለመድከ?" ሲሉ ጠየቁኝ፡፡

"ለመድኩ እንጂ አሁንማ ቤተኛ ሆኛ"

"ታዲያ የለመደ በዚህ ሰዓት እዚህ ምን ያደርጋል? በስራ መውጫ? በግርግር? ተው ተው አልለመድክም፡፡ አሁንም ወር ተወር እየቆጠርክ በመኖር ላይ ነህ? አትሞኝ! በዚህ ኑሮ ውድነት እንደ ራስ ተወዛውዞ አይቻልም፡፡ አልፎ አልፎ ....ኧ?" በአይናቸው ጠቀስ አደረጉ፡፡ ነገራቸው ገብቶኛል፡፡

"ኧረ እኔስ...."





"አትሞኝ! በዛሬ ዘመን ሰዉ ሁሉ የሰው ፈላጊ ሆኗል፡፡ አሁን ገበያ ሄደህ ለምንድነው ዋጋ አውርድ አታውርድ የምትከራከረው? ብትችል በነፃ ይዘህ ለመምጣት ነው፡፡ ሌላኮ አይደለም፤ ሌብነት በነፃ ገዝቶ መምጣት ነው፡፡ ንግድ ደግሞ ከተቻለ በእጥፍ ሸጦ ስንጥቅ በማትረፍ አለማምቶ መስረቅ ነው፡፡ እኔኮ ዋዛ ባልቴት እንዳልመስልህ እያሃሃሃሃ...." ጥርሶቻቸው የሰመጠበት የሚመስል የጥቁር ጉድጓድ ድርድር የድዳቸው ሜዳ ላይ አለ፡፡ አብሬ ሳቅሁ፡፡

"ለመሆኑ" አልኳቸው "ይሄ ሠፈር ወሪሳ የተባለበት ምስጢሩ ምንድነው?"

"እንዲህ ነው እንግዲህ" አሉ ባልቴቷ ሰፌዳቸውን ከጭናቸው ላይ እንስተው ፊት ለፊት እያስቀመጡ፡፡

"የእኔ አያት ይቺን መንደር የቆረቆረ እሱ ነው፡፡ በአጤ ምኒልክ ጊዜ፡፡ አባ ወሪሳ ይባላል፡፡ የፈረሦ ስሙ ነው፡፡ የፈረሦ ስሙን ያገኘው ተዋግቶ አይደለም፡ ዘርፎ ነው፡፡ ሁሉቱም ያው ነው፡፡ የተዋጋ ይዘርፋል፤ የዘረፈ ይዋጋል፤ ሁለቱም የጀግና ሥራ ነው፡፡ አባ ወሪሳ ተከታዮች አሉት፡፡ ዘራፊዎች፡፡ ከመንደር ወጣ ብሎ ዘርፎ መመለስ ነው፡፡

"ከኋላ አጤ ምኒልክ ይሄን ሰምተው ተወኝ ብዬሃለሁ፡፡ ኋላ ትጣላኛለህ፡፡ ወላዲትን አልምርህም፡፡ በሌባ ደንብ እጅህን አቆርጣለሁ አሉት ይባላል፡፡

"አባ ወሪሳ ማንን ሊፈራ፡፡ ኧረ ወዲያ! አትዝረፍ ብሎ ነገር! መዝረፍ ወንድነት መሰሉኝ፡፡ ሰራህን አውልቅ ይባላል? አለ አሉ፡፡

"ከኋላ ጭንቅ ሆነ፡፡ ሁለቱማ ተተያዩ፡፡ አለቅን እንግዲህ አለ አገሬው ተሁኖ ሁኖ እግዜሀር ማብረጃውን ከላይ ላከ፡፡ ኑጭ በግ ለመስዋዕት እንደወረደው ተምሳሌት ሣሊያንም እንዲያ ዱብ! አሌታወጀም ዛዲያ? እናስ? አባ ወሪሳ 'መቼስ ለመዝረፍም ቢሆን አገር መኖር አለበት' በሚል ምኒልክን ተከተለ፡፡

"አጤ ምኒልክ 'አባ ወሪሳ አሁን በለጥከኝ' አሉ ይባላል፡፡

አባ ወሪሳ ጦርነቱን የጀመረው የአድዋው ውጊያ ገና ድምጡም ሳይሰማ ነው፡፡ ተከታዮቹን ይዞ ከጣሊያን ያገኘውን



@BOOKALEM

ዘራርፎ ወደ ሠፈሩ፡፡ ጉድ ተባለ፡፡ ጣሊያንም ግራ ተጋባ፡፡ ማታ ያኖረው አዱኛ ለጠዋት አይገኝም፡፡ ሲመሻሽ ያደራጀው ለጠዋት የለም፡፡ ምንድነው ጉዱ? ተባለ እሰብሰ፡፡ ሲታይ ደግሞ አበሾቹ አያማርባቸው፡ ሰልዱቶ የ,ጋገረውን ብሲት፡ የጠመቀውን ጥጢት፡ እለት እለቱን እንዲያ - እንዲያ ቀጠለ፡፡ የሰፉትን እየለበሱ፣ በጌጣቸው እየደመቁ... ቁልጭ!

"እጤ ምኒልክ ይሄን ሲያይ "ያስቀመጡት እንቅርት ያገለግላል" አሉ ይባላል፡፡

"ኋላ ደግሞ ሊናከሱ፡፡ አድዋው ተፈጣጥሞ እዚህ ተተገባ በላይ እጤ ምኒልክ (መቼም ዘዴኛ አይደሉ)'አባ ወሪሳ ና ተሠናብተኝና አገርህ ግባ "ንጂ" ብለው ላኩበት፡፡

"አባ ወሪሳም (መቼም ሲፈጥረው ቆቅ አይደል?) 'ጥሊያንን አርዶን ተሰንባብትን መስሎኝ' አይልም፡፡ እ-ሻ-ሻ-ሻ-ሻ-ሻ"

እሳሳቃቸው አስፈኝ ሳቅሁ፡፡

"መቼም ሁን ያለው አይቀርም፣ ነገር አብራጅ ጠፍቶ ተካረሩ. ተካረሩ፡፡ በሁለቱ ጠብ ተንቀራጣጩ በዛ፡፡ ማን ደፍሮ ሁለቱን ሃይ ሊል? እቤት! እቤት! እቤት! እንደተባለ፣ እነሱም እንደተፏከሩ በመጨረሻ ጦር ተሰዶ እንደተፈራው ሳይሆን ቀረና አባ ወሪሳ ገፈርሳ ላይ ተያዘ፡፡ ተዚያ በሳይማ ቁርጡ ሲለይ ደሞ እንቀራባጩ በዛ፡፡

"ያ - አባ ወሪሳ ዝረቱ እያለ አዘዘ፣
ቀን ጠሞበት ኖሮ ገፈርሳ ተያዘ፡ ተብሎ ተዘፈን፡፡

"እጤ ምኒልክ አባወሪሳን ያህል ሰው በእግረሙቅ ታስሮ ተፊታቸው ሲቀርብ 'ወግዱ ፍቱት አላማረባችሁም፡፡ አባ ወሪሳን ተራ ዘራፊ ማድረጋቸው ነውን?' አሉ ይባለል፡፡

"አባ ወሪሳ ተፈታ፡፡ እንቀራባጩ ሁሉ ኩም አለ፡፡ የአባ ወሪሳ ተከታዮችም ፍርድ ተለለላቸው፡፡ የኋላ ኋላ ለቤተ መንግሥቱ ንተተር ያለውን ይሄን ትብታ መርጠው እዚህ ሥፈር ኢሉት፡፡

"ጃንሆይ፡ እኔስ ወዳገሬ...." አለ፡፡

"እንግዲህ አገሬን ማለት ቀረ ምሽትህም ትምጣና እዚሁ ታንተው ትሁን፡፡ ወዲያ ወዲህ የለም" አሉ እጤ ምኒልክ





"እመሊስ? እመሊን ሲያውቱት ጃንሆይ"

"አረጀህኮ አባ ወሪሳ፡፡ በእባውንትንትህ እንዳትምህ ተዚሁ ሥራ እንጂ" አሉ፡፡ ልብ-ሰልብ ተዋውተዋል፡፡ ተግግቁ፡፡

"ተዚያ ወዲህ የድብቅ ፈታዱን ተገን አድርጎ የከተማ ዝርፈያውን ቀጠለ፡፡ አገር እየሠለጠነ ህዝብ እያገነገነ ሲሄድ ማን እለብኝነቱ ቀርቶ እፋራምነቱ ተተከቶ ዝርፈያው በማዘናጋት ይከናወን ጀመር እልሃለሁ፡፡ እንዲህ ነው ወሪሳ ሠፈር የተቆረቆረችው እ-ሻ-ሻ-ሻ-ሻ-ሻ"

አብሬ እንደጅል ሳቅሁ፡፡ በሣቃችን መካከል ከፀጉሬ ላይ ጉድፍ አነሱልኝ፡፡ እናትነታቸው ጠናብኝ፡፡ ኮሌታዬን በእጃቸው አይበለባ መታ መታ አድርገው አራገፉልኝ፡፡ ወደ ቤቴ ገባሁ፡፡ ታሪኩ እጅግ ገርሞኛል፡፡ እሱን ሳስብ ቆይቼ ለመተኛት ኩቴን ሳወልቅ ቀለለኝ፡፡ የውስጥ ኪሴን ብፈትሽ በርሳዬ አልነበረም፡፡ አልተጨነኩም ምንም ስለሌለው መታወቂያዬን ጠዋት በር ላይ እንደማገኘው አልተጠራጠርኩም፡፡

## 9 - የጀግንነት ውሎዎች

ወሪሳ ላይ ሌብነት ሥራ ብቻ አይደለም፡፡ መዝናኛም ነው፡፡ የሌብነት ገድሉ በመንፈሳዊ ኩሸት ተብለጥልጦ ይቀርባል፡፡ አንድ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ እየተቃመ ብዙ «የጀግንነት» ውሎዎች አደመጥኩ፡፡ ጉድ ነው ያልኩት የፓርላማን ሰዓት እያቴ ያወረሱኝ ነው ብሎ የሸጠ ሌባ ገድሉ ሲቀርብ ነው፡፡ ቀብድ የሰጡት ባላገሮች ሰዓቱን ለመውሰድ እህያ ይዘው መጥተው ከፖሊሶች ጋር እንደተንታረኩ ተወራ፡፡ ይላቃል፡፡

...ደግሞ፡ እውቶቢስ ውስጥ መነፅሩ የተሰረቀ ሰው በፖሊስ ሲያስፈትሽ ሌባው የሰረቀውን መነፅር አድርጎ "ስማ እንጂ" ይለዋል ተሰራቂውን፡

"ምናሉኝ?" ይላል፡፡

"መጀመሪያውኑ መጠንቀቅ፣ እንደኔ አታደርገውም ነበር?"

"መች እንዲህ ይሆናል ብዬ ገመትኩ?" ሲል

"ለሌላው ጊዜ ተጠንቀቅ" ብሎት እንደሄደ ይወራል፡፡ ይሳቃል፡፡

ቀጣዩ ገድል ከባልቴቷ ጋር ሲያወሩ የነበሩት አባውንት ነው፡፡ የተጠፈጠፈ ቀርጪ የሚመስሉት አባውንት መግፈሪያዊ ሳይኖራቸው መሮከቶ መካከል ሲንጠራወዙ ነው አሉ፡፡ አንድ ባላገር ቢጤ ይመጡና "አባቴ" ይሏቸዋል፡፡

"ጌትዬ" ይላሉ በአላቸው ዘዬ

"ይሄ የዕድር ዕቃ የሚሸጥበት የት ነው?"

"የድግስ ማለትዎ ነው?"

"አይ አድራችን የደረጀ፤ የነበረ ነው፡፡ ባዲያ ዕቃው ሁሉ በዕድሜ ብዛት ነኩቶ አልቆብኝ እሱን ለማስተካካት ነበር፡፡"

"ትርፖሬሽን ነዋ"

"የት ነው እሱ ደሞ?"

"እኔም ወደዚያው ነኝ፡፡ የድግሥ ዕቃ ለመግዛት፡፡"

"እንዋብ እንግዲህ"

ይዘዋቸው የሄዱት ወደ አማኑኤል የአእምሮ ሆስፒታል ነበር፡፡ ካርድ የሚያወጡ ሰዎች ተሰልፈዋል፡፡

"ይሄ ነው" አላቸው

"ድንቅ" አሉ

"በሉ እንሰለፍ፤ ለመሆኑ የቀበሌ መታወቂያ አልዎት?"

"የገበሬ ማህበር ነው"

"አይ የእርሶ ነገር፤ ይሄ ለአዲስ አበባ ነዋሪ በቅናሽ የሚሸጥበት ቦታ ነው፡፡"

"ምን በጀኝ ይላሉ ባዲያ?"

"አይ፤ በሉ ከእኔ ጋር አዳብዬ እመዘግብልዎታለሁ፡፡ እዛች ይቆዩኝ፡፡ ምን ምን እንደሚፈልጉ ይንገሩኝማ"

ነገሩዋቸው፡፡

"ሦስት ብረት ድስት፤ ሁለት ትሪ፤ አምስት ጎድጓዳ ሳህን፤ አርባ ኩባያ...."





"ንሱ ብፋን ይስጡኝማ" አሉ፡፡ ሰጧቸው ተቀበሉ፡፡ ባላገሩ ጥቂት እራቅ ብለው እንዲጠብቁ ነገረዋቸው፤ "እጭበርባሪው ብዙ ነው ተማንም አያውሩ አዳፋ የለበሰ ሲያዩማ ያጀበጅባሉ፡፡"

"ድንቅ"

ወረፋው ደርሶ የመታከሚያ ካርዳቸውን በመታወቂያ አውጥተው ተመለሱ፡፡ ባላገሩን ጠርተው "ንሱ፤ ይሄንን ካር ይያዙና ነገ ጠዋት አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ በከፈልነው መሠረት ዕቃችንን ተረክበን እብስ ነው፡፡"

"ወላዲቷ ለጭንትዎ ትድረስልዎ እንጂ ሌላ ምን እላለሁ"

"እሮ እግረ መንገዴንጂ ለርስዎ ብዬ አልወጣሁ አልወረድሁ፡፡ ይልቅስ ነገ እዚችው ይምጡማ፡፡"

ተሰያዩ፡፡

አባውንቱ የወሬውን መጨረሻ እንዲያጠና ፍራንክ ሰጥተው አንድ የወሬ ወጣት ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ላኩ፡፡

ባላገሩ አባውንቱን ፈልገው ስላጡ የታካሚዎች ወረፋ ጠብቀው ገቡ፡፡ ካርዳቸው ታይቶ ለቃለ መጠይቅ ቀረቡ፡፡

"ለምን መጡ?" ሐኪሙ ጠየቀ፡፡

"ከቱም ሳታውቁት ቀርታችሁ ማለት ነው? ይልቅ ንሱ ስጡኝና ልሂድ፡፡ ሦስት ብረት ድስት፤ ሁለት ትሪ፤ አምስት ጎድጓዳ ሳህን፤ አርባ...."

ሐኪሙ ከኋላቸው ያሉትን ነርሶች ጠቅሶ አሲያዛቸው፡፡ የፊጥኝ ታስረው መርፌ ተወጉ፤ ወደ ህክምና...፡፡ ተሳቀ፡፡

## 10 - ማነሽ ባለሳምንት

ሳቅ የጥዋ ማህበር ጠባይ አለው፡፡ በአንዱ ላይ ለአስራአንድ ተሆኖ ይሳቃል፡፡ ሌላው ይተጥላል የጥዋ ማህበሩን ለማውጣት፡፡ ሲል ሲል ዙሩ እኔ ጋ ደረሰ፡፡

የፈዙ መነሻ ቤቱ ሰርሳሪ መግባቱ ነው፡፡ ሜት ቃሚው ሁሉ "እኔ የሰማሁት" እያለ አወራ፤ አውካካ፡፡ ወሬው ሰብጥርጥር

ነው፡፡ ለያኘር ለገናኘር ያስቸገረ፡፡ እኔ እንዲመች አድርጌ ላቅርብላችሁ፡፡ (ለዚህ መምህርነቴ ጠቅሞኛል፡፡)

<u>አንድ</u>

መካሻ እናት ቤት ሰርሳሪ ገባ፡፡ የሰረሰረበትን ድጅኖ እንደያዘ የቤቱን ዙሪያ ገባ ቢመለከት ምንም የረባ ዕቃ አጣ፡፡ ዕቃ ከጠፋ በልቼ ልሂድ ብሎ ሊሚቱን ቢከፍት ባዶ ሆኖ አገኘው፡፡ ፓስታ ተቅሎ ይሆናል ብሎ ድስቱን ቢከፍተው ሽረሪት አድርቶበት አየ፡፡ በዚህም፡-

ሀ- በሀዘኔታ አለቀሰ ያሉ አሉ፤

ለ- ቀስቅሶ ይሄን ድጅኖ ሽጠህ ብላ ብሎ ሰጠው ያሉ አሉ፡፡

ሐ- አምስት ብር ቀዳዳ ሰሀን ላይ አስቀምጦለት ወጣ ያሉ አሉ፡፡

<u>ሁለት</u>

መካሻ እናት ቤት ሰርሳሪ ገባ፡፡ ሴሊቱን ሲለፋ አድሮ ሊነጋጋ ሲል ቀድዶ ገባ፡፡ በድካም እያለከለከ ቢመለከት እሱ ከቀደደው የማይተናነስ ሌላ ነባር ቀዳዳ በትይዩ ግድግዳ ላይ ተመለከተ፡፡ በልፋቱ ተናደደ፡፡ ይበልጥ ያናደደው ደግሞ ቤቱ ውስጥ ምንም ባለመኖሩ ነበር፡፡ ስለዚህ የመካሻን እናት ቀስቅሶ፡-

ሀ- መከረው ያሉ አሉ፤

ለ- ሰደበው ያሉ አሉ፤

ሐ- ገረፈው ያሉ አሉ፡፡

በዚች ቀልድ ጥሎሽነት ከወራሳዎች ጋር እንዳልለይ ሆኜ ተቀላቀልኩ፡፡ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆንኩ፡፡ በብላ ተባላ ዘመን የብላ ተባላ ሠፈር ሠፈርተኛ ሆንኩ፡፡





# ምዕራፍ ሁለት

## 11 - ግርሻ

"እንቅልፍ ለምኔ"ን መተወን ጀመርኩ፡፡

ፍርሃት እንደ ክፉ በሽታ አገረሸብኝ፡፡ የአክስቴ ልጅ መካሻ ፍርዱን ሊያጠናቅቅ 5 ወራት እንደቀሩት ነው አሉ፡፡ ከዚህ በፊት ጥርሱን ያረገፈውና የዘረፈው አንድ ሰው የታሰረ ጥየቃ ከርቸሌ መሄድ፡፡ እዚያው ማረሚያ ቤት መካሻን የእስረኞች ካቦ ሆኖ ከወዲያ ወዲህ ሲል አየው፡፡ የተዘጋ ክሱን ቀስቅሶ፣ መጥሪያውን አበጃጅቶ፣ በማረሚያ ቤቱ በኩል እንዲደርሰው አደረገ አሉ፡፡ ቢያንስ የአምስት ዓመት እስር ይጠብቀዋል ሲሉ ሰምቻለሁ አንድ የወረሳ ሰፈር የሌቦች ህግ አማካሪ፡፡ ከሰላዬን ተገፍፌ ለወረሳ ፀሐይና ዝናብ ተጋለጥኩ…

ወረሳዎች እኔም ላይ የቆየ ክሳቸውን ቀሰቀሱ፡-

ያ የአፈር ቴሌል የመሰለ ተንሪባቹ ኩይሳ ደጄ ላይ ተኮምሮ ጠበቀኝ፡፡ ፈገግ ብዬ ቀረብኩት፡፡ እሱ ግን ድድ የመሰለ ድፍርስ አይኑን አፍጥጦ፣ ለሠላምታ የዘረጋሁለትን እጄን ወዲያ አለው፡፡

"ም-ምነው?" አልኩት

"የሌቦች ሠፈር አልክን አሉ"

"መቼ? የት? እንዴት?…" አፍ ያልፈታ ልጅ መሠልኩ፡፡ እሱን የሚያህል ፍርሃት ተከመረብኝ፡፡



@BOOKALEM

"ማሀተም ያረፈበት ማስረጃ ይዤልህ ልምጣ?"

"ኧረ ምን በማህ?፡፡

"ታዲያ?" ብድግ አለ

"እኔ እንደሆን አፌ-ብርጨ ነኝ፡፡ ትንሽ ስጠጣ...." እውነቱን ለመናገር የወራሳን የሴቦች ሠፈርንት ከልቤ ዘንግቼው ባላውቅም በእፌ ማውጣቱ ትዝ አይለኝም፡፡ ባሬስ የቱርጡ መጥቷል፡፡ ሳልናዘዝ... ኤዲያ! እንደ ጥቁር ጉም ከእናቱ ትንሽ ራቅ ብሎ እንዣበበብኝ፡፡ አሁን ካሁን የጥቁር እጅ በጤ ዘነበብኝ በሚል ነፍሴ ተጨነቀች፡፡

"ለዚህ አፍህ ዋጋህን ታገኛለህ፡፡ አሁን ያበደርኩህን ብር መልስ"

"የምን ብር?

"መኪኛን የምጠይቅበት ብር እጣሁ ስትል ትምህርት ቤት ድረስ መጥቼ አላበደርኩህም? እክክክክ...."

"እ? አ-ዎ-ልጂ" እንደ ወረቀት ጨምድዶ፣ ኪሱ ከቶኝ፣ ወደ አንድ ሰዋራ ቦታ ወሰደኝ፣ በሚሎሎቶ ሲጥለኝ፣ ወንዝ ላይ አርፌ፣ ዓይኔ፣ ጆሮዬ፣ የእግሬ ጣቶች፣ ጡቴ፣ እንብርቴ፣ ቁርጭምጭሚቴ..... ተበታትነው ሲንሳፈፉና እንዱ ገላዬ ሌላኛውን ሲናፍቅ ታየኝ፡፡

"እኮ ወዲህ በል" አለኝ እርቦ የመሰለ መዳፉን ፊቴ ላይ ደቅኖ

ጊዜ ለመግዛት "ደሞዝ...." አልኩት

"መቼ ነው?"

"ሳምንት ቢቀረው ነው"

"እጠብቃለሁ፣ ታዲያ ወለዱንም እንዳትረሳ... ከዚያ በኋላ ደግሞ የአፍ እዳህን ትከፍላለህ" ብሎኝ ሂደ፡፡

ይኸው ለአንድ ሳምንት ዕድሜ "እንትልፍ ለምኔ"ን እየተወገኩ እገኛለሁ፡፡





## 12 - ማስተባበያው

የብር ዕዳና ዳገት እያረፉ ይወጡታል፡፡ መቼም እንደ "ልፋ ያለው ቢነግድ አይተርፈው" ሆኛለሁ፡፡ እኔን የጨነቀኝ የአፍ ዕዳው በምን ይወራረዳል? .

አንድ ሁለት ቀን እውጥቼ እውርጂ ዘዴ መጣልኝ፡፡

የተጠቀሰብኝ እንቀፅ ሌባ ብለሃል አይደል? ክሱን በድርጊት ማስተባበል እችላለሁ፡፡ ለምሳሌ የቤቱን በር ሳልዘጋ ወለል እንዳለ ትቼ ወደ ሥራ መሄድ፡፡ ወሪሳዎች እንዳመንኳቸው ይገባቸዋል፡፡

· በዚህ ዘዴ ሁለት ቀን ተጠቀምኩ፡፡ የእን ቤት መሰስ ብሎም ያየ ወሪሳዊ የለም፡፡ ለነገሩ ወና ቤት ለመጨፈር አይገቡ፡፡ ማስተባበያ ዘዴዬን ቀየርኩ፡፡ ትምህርት ቤት ሎከር ውስጥ ቆልፌ ያስቀመጥኳቸው ልብሶቼን አንድ በአንድ እያመጣሁ አጥቤ ደጅ ማስጣት፡፡ በሬን ዘግቼ በቁላንጭል የሚሆነውን እያለሁ፡፡ ይሄ ዘዴዬ ያዘልኝ፡፡ ፊት ለፊቴ ያሉት ባልቴት ግራ ቀኝ ሳይሉ፣ ከእላቸው በማይጠበቅ ቅልጥፍና ላጥ አድርገውት ይሄዳሉ፡፡

ሌላ አጥቤ አሰጣለሁ፡፡

የልጅ ልጃቸው እየዘለለ አልደርስበት ያለውን፣ ባልቴቷ አውርደው ይሰጡታል፡፡

ሌላ ልብስ ውሃ ውስጥ ነክር አድርጌ አሰጣለሁ፡፡ እኒያ የተጠፈጠፈ ቆርኪ የመሰሉት አዛውንት ይመጡና መጀመሪያ ልብሱን ጎትተው ይጥላሉ፣ ቀጥሎ ፈጣሪያቸውን ያመሰግኑና አንስተው ጋቢያቸው ስር ሸጉጠው ይሄዳሉ፡፡

ወሪሳዎች የማስተባበያ ድርጊቴን ይቀበሉት አይቀበሉት ሳላውቅ ልብሶቼ ተገባደዱ፡፡

ያንኑ ሰሞን ባልቴቷ ሌባና አዛውንቱ ሌባ በእኔ እሰርቅ በእኔ እሰርቅ ተጣሉ፡፡ መጣላታቸው ለእኔ በጀ፡፡ ወሪሳዎች በምን እንደተጣሉ ደረሱበት፡፡

ተሳቀ....

...በቀጣዩ ቀን ባልቴቷ ደጄን ቆረቆሩ፡፡ ያ ኩይሳ መስሎኝ ደነገጥኩ፡፡

"በሠላም?" አልኳቸው፡፡

"የሆነውን ሰምተህ የለም?" አሉኝ ጥፍጥሬ "የመሰሉ አንዳንድ ጥርሶች አልፎ አልፎ አፋቸው ውስጥ ይታዩኛል፡፡

"የቱን?" አልኩ፡፡

"እኔና ያ-የሽማግሌ ቀላል፡ መጣላታችንንን?"

"የቱ ሽማግሌ?" ወዲያው ስማቸውን ለማወቅ የዘይድኩት ነው

"ጆቢራው ነዋ!"

የልጅ ልጃቸው ቀሚሳቸውን ፈልፍሶ እኔን አየኝ፡፡ አየሁት፡፡ እቀፈኝ እንደማለት እጁን አንከረፈፈ፡፡ እምቢ ብል ወሬሳዎች ጠረጠርከን፡ ሰደብከን ሊሉ ነው፡፡ እንስቼ ታቀፍኩት፡፡ እንግቴ ስር ውሽቅ አለ፡፡

"መቼም አንተም ልብስ አስጥተህ ማስጣትህን አልተውክ፡ እኛም.... (ጠቀስ አደረጉኝ) አልተውን፡፡ ስለዚህ ማንም ባዕድ ከሚበላው እንዴ በፌስታል እደጅ ብታስቀምጥልኝ እኔ እናትህ እጠቀም ነበር ለማለት ነው የመጣሁት" አሉኝ፡፡ ግራ ተጋባሁ፡፡ "ኧረ ግድ የለም፡ እምቱቼ በእጅዎ እሰጥዎታለሁ" አልኩ

"ኧረ ንቬ'ቱ፡ እኔን ለማኝ ማድረጉ ነው'ዴ? ባይሆን እንዳሳወቀ ሰው በር ላይ ቁጭ አድርገውና..." (ጠቀስ አደረጉኝ)

"ድንቅ"

ሲሄዱ እርደታ ተሰማኝ፡፡ ወዲያው ትዝ ብሎኝ ኩት ኪሴን ብዳብስ ቦርሳዬ የለም፡፡ ግድ የለም፡፡

በዚህ መካከል ልጄ አውርደኝ አለኝ፡፡ ሥራውን አጠናቋል ማለት ነው፡፡

"ድንቅ" ብለው ሊመለሱ ሲሉ

"እኔ እምለው" ብዬ እቤቴታዬን አወረድኩት፡፡ "አሁን እኔ ወሬሳን እንዲያ ብዬ የምሳደብ ነኝ?"

"ብትሳደብስ? ያኮራናል እንጂ አያሳፍረን"





ሊያወጣጡኝ መሰሎኝ "ኧረ እኔ" አልኳቸው፡፡

"ተወው ወዲያ፡ እኔ እሰጠንቅቀዋለሁ፡፡ ሜፍህ አይደር ስም፡፡ እምቢ ካለ የልጅ ልጅ ልጄን ያውቀዋል፡፡"

"ከኩይሳው የሚበልጥ?" አልኩ

"ተዚህ አይቆጥረውም" አሉኝ የጥፍራቸውን ሥር በሌላ ጥፍራቸው እየሰቀሰቁ "እሱን ለእኔ ተወው፡ ብቻ ፌስታሉን"

## 13 - ማስተካከያ

ሌብሱን በፌስታል አድርጌ እምጥቻለሁ፡፡ ግን እንዳሉኝ በር ላይ እንዳስቀመጥኩ ከእነ እባ ሞጭልፊዎቹ አንዱ ከእይን በፊጠን፡ ቅልጣፌ ሳጥ ቢያደርገውስ? ባልቴቷ ቃል የገቡልኝን የኩይሳን ነገር ሊያጥፉት አይደል? ኧረ እንዲያውም በተቃራኒው ጠላቴ ሆነው ኩይሳውን "በለው! ብላው" እያሉ ሲገፋፉት ይችላሉ፡፡

ምን ባደርግ ይሻለኛል?

በዚህ መካከል ደጃፌ ተቆረቆረ፡፡ ባልቴቷ የመጡ መሰሎኝ ደስ አለኝ፡፡ የመጣው ሰው በበሩ ሳንቃ ስንጥቅ ውስጥ ፅላሎቱ ይታየኛል፡፡ እንደ ባልቴቷ ሹክክ ያለ ቅርፅ የለውም፡፡ ከደጃፌ ተርፎ ወደ ግድግዳው ገፋ ያለ ሰውነት አለው፡፡ ኩይሳው ይሆን? ደነገጥኩ፡፡

ደግሞ ተቆረቆረ፡፡

በሩን ገፋ አድርጎ ከመግንጠሉ በፊት ተንስቼ ከፈትኩ፡፡ ፊቱን ማየት ስላስፈራኝ አቀረቀርኩ፡፡ በሩ ስር ያስቀመጥኳት የታሰረች ፌስታል በሳንቃው እየተገፋች ሸርተት ስትል ኩይሳውን ፈርታ ገሸሽ የምትል መሰለችኝ፡፡

ጥላው እላዬ ላይ ተንጠርብቧል፡፡

ቀና አልኩ ኩይሳው ሳይሆን እንደ ነጠላ እርብ እንጂ ውፍረት የሌላቸው እዛውንቱ ጆቢራው ናቸው፡፡ ቀለል አለኝ፡፡

ለጥቂት ጊዜ ተፋጥጠን ቆምን፡፡ ፊታቸው ሲቀርበኝ እንደማላውቀው ገባኝ፡፡ የተከፈሰ እፍንጫ አላቸው፡፡ ፊታቸው ላይ



@BOOKALEM

ጉብ ብሎ የሚታየው አፍንጫቸው እንደ አድባር በአይኖቻቸው በቅንድቦቻቸው በጆሮዎቻቸው ተከቧል፡፡

"ቤት ለእንግዳ አይባልም?" አሉኝ

እንደታሰረችው ፌስታል ሸርተት ብዬ መንገድ ለቀቅኩላቸው፡፡ ገቡ፡፡

እንደ ቤት አከራይ ተንጠረበቡብኝ፡፡ ዙሪያ ገባውን በኩራት ገረመሙ፡፡ ንቀት ያደረባቸው መሰሉ፡፡

"ቁጭ ይበሉ'ጂ" አልኩ፡፡

"ምን ላይ?" የሽሙጥ ፈገግታ አሳዩኝ፡፡

እውነትም መቀመጫ ቀርቶ ለመቀመጫ የሚሆን ዕቃ እንኳን የለም፡፡ ብረት ድስቱን በእቶ ደፍቼ ለመቀመጫነት አመቻቸሁት፡፡ ቂጡ ጥላሸት በመሆኑ ግራ ተጋባሁ፡፡ አሲጋው ጫፍ ላይ እንዲቀመጡ ጋበዝኳቸው፡፡ የተንዘረፈፈ ጋቢያቸውን እንደ ቆሚስ ሰብስበው ተቀመጡ፡፡

"ዘመኑ ተበላሽቷል" ሲሉ ጀመሩ፡፡ "ሁሉም የሰው ሐብት ማታረ ሆኗል፡፡ ሁሉም ትዕግስት አጥቷል፡፡ ነፍስ በእጁ የሚያልፈው፣ እፉ የሚያዳልጠው በዝቷል፡፡ ትናንት ነው ተትናንት በሱቲያኳ ይህቺ ተንራባችህ ሰደበቺኝ"

"ማን?" አልኩ እንዳልሰማ

"ወ/ሮ ጉዶ፡"

የባሏቴድን ስም እስከዛሬ አላውቅም ነበር፡፡ "ምን ብለው?"

"ምን ያላለችው አለ? ኧረ ተወኝ እኔ ባልሆን ምላሴን አድጡት ክፉ በተናገርኩና ፈጣሪዬን ባስቀየምኩ ነበር፡፡"

ያለፈ ማብራሪያቸው ትዝ አለኝ፡፡ ዝም...

"ስድብ ሐጢያት እንደሆነ ከእኔ ቀድሞ የተረዳ'ጂ እንደኔ የተገበረው የለም፡፡ ምላሴ በሰው ላይ አለፎ አያውቅም፡፡ ለምን ብዬ? የሰደበኝ ቢኖር ለተሳዳቢ እንዲዳርገው እመኛለሁ፡፡ ይሄ ካልሆነም በእጅ ምልክት አንዳንድ አናዳጅ ነገሮችን ባል አደርግበ





ታለሁ፡፡ ከዚህ በተረፈ ምላሴ በሰው ክብር ላይ አልፎ አያውቅም፡፡ ሌላው ቀርቶ ምላሴንኳ በሰው ላይ አላወጣም፡፡ የእጅ ምልክቶችን ባል ማድረግ ከሐጢያት አልተፃፈምና በእሱው እጠቀማለሁ፡፡"

ግራ ብጋባም ጭንቅላቴን በእውንታ ነቀነቅሁ፡፡

የተቀመጡበትን ቆንጥንጥ ብለው አደላደሉ፣ ጋቢያቸውንም ትከሻቸውን ከፍ ዝቅ አድርገው አመቻቹና ቀጠሉ፡፡

"እኔ እንደ እሷ አይደለሁም፡፡ በስተርጅና ዘመኔ ፈጣሪዬን የሚያስቀይም ነገር አልሰራም፡፡ ወደሱው መሄጃዬ ደርሷል፡፡ እሷ ግን ሥራዋ ሁሉ ሌላ ነው፡፡ ሆን ብላ ሐጢያት መሥራቷ ሳያንስ ታሪካችንንም ማዛባት ይዛለች"

"እንዴት?" በሰፊው ለማድመጥ ቀለቤን ለወሬው ሰጥቼ የተደፋው ድስት ላይ ተቀመጥሁ፡፡

"አሁን ሰታ ለሌሎች የምትነፋውን ውሸት ታሪክ ብላ ደገመችልኝ፡፡ ተይ'ጂ ጉዶ አልኳት አለሳልሼ፡፡ ይሄን ሰፈር የቆረቆረው አባ ወሪሳ አይደለም፡፡ በፊት አባ ቀማው በኋላ አባ ንጠቀው የተባለው የእጤ ምኒሊክ ዘመነኛ ነው፡፡ አባ ወሪሳ እኮ የኖረው በእጤ ኃይለሥላሴ ዘመን አሁን ነው አልኳት፡፡ እፍጥጣ ምን ሲደረግ አትልም?

"እሺ ተሆኑሆንና ማን ቢወልድ ማ ሆኖ ነው አባ ወሪሳ ይሄን ሰፈር የቆረቆረው? አልኳት፡፡

"እዚህ ላይ ትክክል መጣች፡፡ ደረደረች፡፡ ከእጤ ቴዎድሮስ ዘመን እንሲታ በስትክክሉ መጣች፡፡ መጨረሻ ፈጠጠች፡፡"

"እንዴ?" አልኩኝ በታሪኩ ተመስጬ "እንደ ነገሥታቱ እነሱም የሥልጣን ተዋረድ....."

"እነሱስ ነገሥታት አይደሉም ወይ? ምን ይጎድላቸዋል?"

ሲያፌጡ ፈራሁ፡፡ በወሪሳ ሰፈር የተከሰሰኩበት የእፍ ዕዳ ትዝ አለኝ፡፡

"እንግዲህ ታሪክ የደረሰበት የመጀመሪያው ሌባ አባ ላፌው ነው፡፡ በእጤ ቴዎድሮስ ዘመን ንጉሡ ፊት ቀርበ ለእኛም ሙያ



@BOOKALEM

እውቅና ይሰጠው፡ ሥራችን ተመዝግና እንሾም፡ እንሸለም እለ ይባላል፡፡

"እይ አባ ላፈው' አሉ እጤ ቴዎድሮስ 'ነገሩንስ ሆንና ስንት ተከታይ አለህ?'

"እስር ሺህ ይደርሳሉ፡ ጃንሆይ' አለ፡፡

"ድንቅ ነው፣ ድንቅ፡፡ ለዛሬው እንተን ሾመናል፡፡ ንሱ ቀሚስ ስጡት፡፡ ደግሞ የጎበዝ አለቆችህንና ተከታዮችህን ተፈታችን እያቀረብክ እንድታሾም እንድታሸልም ይሁን' አሉት፡፡

"አባ ላፈው ነገር ያውቃል፡፡ እጤው የዋዛ አይደሉም፡፡ ስንቱን ላፎቱ እጁን እንዳስቆረጡ ደርሰበታል፡፡ ኋላ ሹመቱንና ሽልማቱን ተቀብሎ ወደ ሰፈሩ፡፡

"በቀጣዩ ቀን ሁለት ጎበዝ አለቆቹንና ጥቂት ተከታዮቹን ወደ ንጉሡ ላከ፡፡ አሁንም እጤ ቴዎድሮስ እስኪጠራቀሙላቸው ሾመው ሸልመው ላኩ፡፡ አሁንም እንዲያው ጥቂት ተፈታቸው እስቀርቦ ንጉሡ መላው ዘራፊ እንዳይደነብርባቸው ሰግተው ሾሙ ሸለሙና

"አባ ላፈውን ስትሉት፡ እንተም ደክምክ፣ ለእኔም ሥራ አበዛህ እንዴ የሚሸለሙና የሚሾሙትን ይዘህ ና' የሚል መልዕክት ላኩበት፡፡

"አባ ላፈው እንዲህ ዋዛ ጭሮሱት ጥጪት መላኩን ተወው፡፡ እሱ ደጅ አዝማች ተብሏል፡፡ በሱ ሥር ሁለት ግራ አዝማችና ሁለት ቀኝ አዝማች እሹሟል፡፡ ተዚህ በላይ ምን ማረግ አለ?

"ንጉሡን ተላላ ስላደረጋቸው ተበሳጩ ሜት ፈረሴን እሉ አሉ፡፡ 'አባ ታጠቅን አምጡልኝ'

"ያ ሁሉ መኳንንት ሃይ ሃይ ብሎ እስቀራቸው፡፡ እኛ እንበቃም ወይ? ተባለ፡፡ ደሞ ለዘራፊ ንጉሥ ይዝመት? ይሄ ለሚሰማውስ ደግ ነው?

"ንሱ እጁን አስረችሁ አምጡልኝ ይባላል፡፡

"አባ ላፈው የት ሊገኝ፡፡ እዚህ ሲሉት እዚያ፣ እዚያ ሲሉት እዚህ ነው እሱ እንደሆን፡፡ ያኔ ነው እንግዲህ የጎንደር አዝማሪ እንዲህ ብሎ የዘፈነው፡፡





የታለ አፋልጉኝ ያን አባ ላፈው፡
ተንጉሥ ላይ ቀሚስ ያጭበረበረው፡፡፡

"ግሩም ነው" አልኩ፡፡

"ይሄን ተትምህርቱ አላገቡትም?"

"ኧረ በጭራሽ?"

"አብደዋላ፡ አባ ጭጭልፍም ተትምህርቱ የለም?"

"የለም"

"አባ መዝብርም?"

"እንደውም?"

"አባ መንትፍም?"

"የለም ሰሎት"

"አባ ንጠቀውሳ?"

"ስሙንም ዛሬ መስማቴ ነው"

"እይ ኢትቢያ፡ አሁን አባ ንጠቀውን ያለ ሰው ትዘነጊ?"

"ትልቅ ታሪክ ነበራቸው?" አልኩ፣ ለወሬ ጭምጩ እየተቁነጠነጥኩ፡፡ የተቀመጥኩበት ድስት ከመሬት ጋር እየተፋፋቀ ዘግናኝ ድምፅ አሰማ፡፡

"የስን ያህል ማን ሰራ? ይሄ ሰፈራችንኮ ፊት አባ ንጠቀው ነበር፡፡"

"ታዲያ እንዴት ወረሳ ተባለ?"

"እጤ ኃይለሥላሴ ናቸው አሉ፡፡ 'በንጉሥ እገር አባ ንጠቀው ትሉ? በሉ ተይሩ አሉ' አሉ፡፡ ያኔ የነበረው አባ ወረሳ ነበር፡፡ እሱ ቀየረው ትርጉሙ ግን አንድ ነው፡፡ ንጉሡ ተላላ ናቸውና ትዛዜ ተፈጠመ መስሏቸው ደስ ተሰኙ አሉ፡፡"

"ግሩም ነው አልኩ" ጨዋታቸው እንዳይቋረጥብኝ ለማበረታታት ያልኩት ነው፡፡

"ይልቅ አባ ንጠቀውን አንድ ታሪክ ላጫውትህ"

"እ-ሺ" ተቁነጠነጥኩ፡ ያ ዘግናኝ የድስት ድምፅ ተከተለ፡፡

"አባ ንጠቀው በአጤ ምኒልክ ገፈርሳ ላይ አልተያዘም?"

"አዎ"

"ይሄ ተትምህርት ገብቷል'ዴ?"

"አ-ይ ወ/ሮ ጉዶ ነግረውኛል፡፡ ብቻ አባ ወረሳ ነው ያሉኝ"

"እዉን ተዋት፣ ዘባራቂ" ብለው አፋቸውን ስላዳጠው እማተቡና ቀጠሉ፡፡

"አባ ንጠቀው ይሀቺ ቦታ ለማረፊያ ተሰጥታው ቁጭ እንዳለ አጤ ምኒሊክ አንድ አይን-ቁራኛ መደቡበት ይባላል፡፡ ያ አይን ቁራኛ እዚሁ እየኖረ አባ ንጠቀው ሥር/ሥር ይላል፡፡ ሲወጣ መውጣት፣ ሲገባ መግባት፡፡ ኧረ ተወኝ ቢሉት ወዴት፣ አላሳውስ አለው፡፡

"በኋላ አንድ ቀን ስለ ዛር ወሬ አወራው፡፡ ስለውቃቢ ደገመው፡፡ አንዳንዱ ውቃቢ ምስ ዝርፊያ ነው፡፡ ምሱን ካጣ መላውን ሰው ይፈጃል አለው፡፡

ሊፈራ ነው ጭራሽ እያንገራበበ ሳቀ፡፡

"ተው ኋላ አይሆንም፣ ተውቃቢዬ ትጣላላችሁ ያሳብድሃል፣ ጨርቅህን ጥለህ ትበራለህ" አለው፡፡

"ሲባ ውቃቢ ባገኝ እሱንም እኾፈድደዋለሁ አይልም? ተጉለቴ ነው፡፡ እቀፈድደዋለሁ ማለቱ ነው ኋላ ልናይ አለ አባ ንጠቀው ተጎንሀ ታገኘዋለህ

"ቀን ላይ አባ ንጠቀው ረጅም አጣና አምጡልኝ ብሎ አዘዘ፡፡ አጣናውን ሰንጥቆ አቀጠነና ጫፉ ላይ ከአጣናው ለአመል ስፋት ያላት ቆርቆሮ መታበት፡፡ ተጉለቴው ለእዳሪ ሲወጣ አጣናውን ይዞ ተከተለው፡፡ እስቲቀመጥ ከበስተኋላው አድፍጦ ጠበቀ፡፡ ቂምጣውን አውልቆ ቁጢጥ ሲል አባ ንጠቀው አጣናውን ሰደድ አድርጎ ቆርቆሮውን እስፉ አስቀመጠ፡፡ ቆርቆሮዋ በቂጡ ትክክል እንደረጋች ሲያረጋግጥ ዝም ብሎ ጠበቀ፡፡ ሰውየው ተፀዳድቶ እንደጨረሰ አጣናውን እንስቶ የተደበቀበት አኖረው፡፡ ሰውየው ቂምጣውን ታጥቆ መለስ ቢል አሩን አጣው፡፡ ደነገጠ፤ ታዲያ የት ሄደ?-በእግሩ ቢዳብስ የለም፡፡ ቂጢጥ ብሎ ቢመለከት





አልታይህ አለው፡፡ በቃ ሮጦ 'አርቹ ጠፋ!' አለ፡፡ እራሱን ማመን ተሳነው "ጉድ! ጉድ!" ማለት አበዛ፡፡

"እና ተገኘ?" ወረሳዎች መጠየቅ አበዙበት፡፡ ማላገጫ ሆነ፡፡

"የለም፣ ጠፋ" እያለ ይመልሳል፡፡ ከሩሁ እንዳልሆነ አባ ንጠቀው ገብቶታል፡፡ እውነትም ወርም ሳይደፍን ጨርቁን ጥሎ አበደ፡፡

በዚህም ለአባ ንጠቀው ተዘፈነ፡፡

"የአባ መንትፈው ልጅ፣ አባ ንጠቀው
ጠላቱን አር ሰርቆ እሚያሳብደው!"

ሁለታችንም ተያይዘን ሳቅን፡፡

"እንግዲህ እየመጣሁ እጫውትሃለሁ" ብለው ለመሄድ ተነሱ፡፡ እኔም ለመሰናበት ተነሳሁ፡፡ የተቀመጥኩበትን ድስት ገርመም አድርገው "ተጥላሽቱ ነው የተቀመጥከ?" አሉኝ፡፡

እይ የኔ ነገር?

"ተው አንተ ልጅ ተቀልብህ ሁን" ብለው "ጨርቅ እምጣ ላራግፍልህ" አሉኝ

"እኔ እራግፈዋለሁ"

"ጥላሸት ሲራገፍ በዴ አለው ይልቅ ዙር" ብለው ደረቴን ደገፍ አድርገው እራገፉልኝ፡፡

"ብል ደህና እደር እንዲሁ ሲመቸኝ እየመጣሁ እጫውትሃለሁ" ብለው ወጥተው ሄዱ፡፡

የነገሩኝ ታሪክ አዝናንቶኛል፡፡ አሁን እኔ ምኔ ነው የአማርኛ አስተማሪ? ለዛቸው? እውቀታቸው? ማስታወሳቸው?.....

አንዳች ነገር አይኔን ቀለለው፡፡ ከቀልቤ ሆኜ ሲታኝ በፌስታል ያሰርኩት ልብስ የለም፡፡ ክው ብዬ ቀረሁ፡፡ የደነገጠችው ልቤ ስትፈራገጥ ቦርሳዬን አስታወሰችኝ፡፡ እጄን ስሰድ የለም፡፡ ለኩይሳ ለመስጠት ያዘጋጀሁት ብር እዚያ ውስጥ ነበር፡፡ በተሰፋ መቁረጥ መሬት ቁጭ አልኩ፡፡



@BOOKALEM

## 14 - አንድ ለእናቱ

"ዕዳና ገል ተሸራርፎ ያልቃል" ይባላል፤ ታዲያ የገንዘብ ዕዳ እንጂ የአፍ ዕዳ አይደለም ተሸራርፎ የሚያልቀው፡፡ በገንዘብ ወይም በንብረት ለመጣ ጥቂት በሰጪት ከማለት ውጪ ይሁንኝ ብዬ ስናደድ የምውል ሰው አይደለሁም፡፡ የትናንቱ የአባውንቱ ድርጊት ግን አብሮኝ አደረ፡፡ ተወኝ ብለው ሊተውኝ አልቻለም፡፡ ከሆዴ አልወጣ ብሎ ሳንሳሳው ያደርኩት የፌስታሉ ጉዳይ ነበር፡፡ እሮጊቷ ይሄን ሲሰሙ ከኑይሳው ጋር አወሻኩተው ያጋድሉኛል፡፡

ተስፋ መቁረጥ ተሟሟነኝ፡፡

ወደ ሥራ ልሄድ ራስጌዬ ያኖርኩትን ሱሪ ባየው ቂጡ እንደጠለሸ ነው፡፡ ቅያሪ የለኝ፡፡ የግዴን ከሥራ ልቀር ነው፡፡ ለከሰዓቱ ክፍለ ጊዜ እንዲደርስልኝ አለቅልቄ አሰጣሁት፡፡ ቂል አይደለሁ እውጪ የማሰጣው፤ እዚያው ቤቴ ውስጥ አልጋዬ ግርጌ ላይ አሰጣሁት፡፡

ያ ከአይን የፈጠነ፣ ከምናምን የቀጠነ ጎረቤቴ ትውስ ሰላለኝ ሱሪዬን በቁራኛ መጠባበቅ ያዝኩ፡፡ እዚያው አልጋ ላይ ቁጭ ብዬ አይኔን ሳላረግብ እጠብቃለሁ፡፡

በመሃሉ፣ ሱሪው ከመድረቁ በፊት ያፈጠጥኩበት አይኔ ደረቀ፡፡ ጨፈን፣ ጨፈን አድርጌ አረጣጠብኩና ለማፍጠጥ ስዘጋጅ ማፍጠጫዬን አጣሁት፡፡ አላመንኩም፡፡ አይኔን አሸት አሸት አድርጌ በድጋሚ ብመለከት የተለወጠ ነገር የለም፡፡ እርጥብ ሱሪዬ፣ አንድያ ሱሪዬ፣ መከራዬ.....

እራሴን ተጠራጠርኩ፡፡ እራሴ ከእእው ላይ ካልሰረቀ በቀር ዝር ያለ ሰው አልነበረም፡፡

ብድግ ብዬ ራሴን ወደ ውጭ አስገግኩ፡፡ ወፍ የለም፡፡ ወሪሳዎች ለሥራ የሚጣደፈውን ሊያጣድፉ ተሰማርተዋል፡፡

"ታዲያ?"

እሩ እንደተሰረቀብት ተጉለቴ ማበድ ከጀለኝ፡፡

"ሁለተኛ ግፍ፣ ልብሴን ይገፍ ጀርባዬን ይገርፍ" አሉ፡፡





## 15 - ሽኮኮ

ረፋዱ ላይ የእማማ ጉዶ የልጅ ልጅ...ልጃቸው መጣ፡፡ እጄን ኪሱ ከትቶ እያፏጨ ነበር፡፡ በቅጡ መናገር ሳይችል ማፏጨት? ገረመኝ፡፡

ቁንጥላቴን ብቻ ከበር አውጥቼ ጠራሁት፡፡ "አቡሽ" መጣ፡፡

"ስራ አይተሃል?"

እንደ ትልቅ ሰው ታዝቦኝ ሄደ

በገዛ እጄ የአፉን ዕዳ አጠናከርኩት፡፡ ሥጋት ገባኝ፡፡

ጥቂት ቆይተው እማማ ጉዶ በሩን ቆረቆሩና "ቤቶች? ሥራ አልሄድክም እንዴ?" አሉኝ፡፡

ራቁቴን ስለሆንኩ እንዳይገቡ በሩን ተደግፌ እነጋገርኳቸው፡፡

"ምን እሄዳለሁ? ሱሪዬን አጥቤ ከቤቴ ባሰጣው....." እየዘፈንኩ ነው እንዴ? እራሴን ታዘብኩት፡፡

"ሱሪዬን አጥቤ ከደጄ ባሳጣው፤
ወዳኝ ነው መሰለኝ ተራምዶው አለፈች፡" የቂሎች ዘፈን ነው፡፡ እእስ ምንድንኝ? እንደመነሜኑዬ ከጀለኝና የሆነውን ሁሉ ለእማማ ጉዶ ነገርኳቸው፡፡

"ጥቂት ብር አለህ?" ልግባ ሳይሉ ያሉበት ሆነው ጠየቁኝ፡፡

"ኧረ የለኝም፤ እሱንም ትናንት...." ብዬ ዝም አልኩ፡፡ የፌስታሉ ጉድ ሊዝረከረክና እማማ ጉዶን ሊያስቆጣ ሆነ፡፡

"ግድ የለም እእ አበድርሀና ሽኮኮ ገዝቶልህ ይመጣል" አሉኝ፡፡

"ሽኮኮ? እሱ ደሞ ማነው?"

"የተከነነች ነፍስ ከኪያል ያመጣልሃል፤ ቆይ ላጥራልህ"

ስለዚህ ደሳሳ የሰማሁ ይመስለኛል፡፡ እዚያ ጫት ቤት፡፡ አዎ ልክ ነው፡፡ የወሪሳ ደሳሳ እሱ ነው፡፡



@BOOKALEM

እማማ ጉዳ እንዳሉት ጥንት ሲባ ነበር፡፡ አሁን ግን ድለላ በልጦበታል፡፡ ክፍት ቤት እንኳን ካገኘ ዘው የሚለው ለመስረቅ ሳይሆን ለመደለል ነው ይባላል፡፡ ዋጋ ያወጣል ያለውን ዕቃ ያንሳና ይወጣል፡፡ መስረቁ አይደለም፡፡ መደለሉ ነው፡፡ አዙሮ ሸጦ ዕቃው ወደጠፋበት ሰው ይሄድና ይሄን ያህል ተሸጧል፣ የድለላዬን ይሄን ያህል ቀንሻለሁ ብሎ የሚደርሰውን ይሰጠዋል አሉ፡፡

እማማ ጉዶ ሽኩን አስከትለው መጡ፡፡ በበሩ ሰንጥቅ አየሁት፡፡ ሽኩ የቆላ እንጨት ይመስላል፡፡ ሁለመናው ተንጨፍርሯል፡፡ እርጥበት አይታይበትም፡፡ ዓይኑ እንኳን የደረቀ ነው፡፡

"ምን አስቸኩለው?" ይላል "ሲሸጥ የሚደርሰው ይሰጠዋል"

ስለማን እንደሚያወራ ግራ ገባኝ፡፡ "እሰጥቸዋለሁ፡፡ እንደተሸጠ እምጥቼ አፍንጫው ላይ እወረውርለታለሁ፡፡"

የእኔው ጉድ ነው፡፡ ሱሪዬን ከአይኔ ስር ላፍ ያደረገኝ አይኑ ደረቁ ሽኩ ኖሯል፡፡ ተሆነ በላይ መበላጨት ምን ሊፈይድ? ደግነቱ ሱሪው አልተሸጠም፡፡"

ከሽኩ ጋር ተደራድሬ፣ የድለላውን አስር ብር ከእማማ ጉዶ ተበድሬ ሰጠሁ፡፡ ሱሪዬን፣ አንድ ለእናቱ ሱሪዬን ከሽኩ እጅ ተረከብኩ፡፡ ገና አልደረቀም፡፡ የት ላስጣው? ከላዬ ላይ እስኪሰርቁኝ አጥልቄው ይድረቅ፣ በሚለው ወንኩ፡፡

## 16 - እንዳደረከኝ - ልሁን

ለክስዓቱ ክፍለ-ጊዜ ከቤቴ ስወጣ ሽኩ ሲንደረደር መጣ

"ሱሪው ተስማማህ?" አለኝ፡፡

የገዛ ሱሪዬ መሆኑን ተጠራጠርኩ፡፡ ቢሆንም ጭራሴን በአዎንታ ነቀንቅኩለት፡፡

"አልሰፋህም? አልጠበበህም?"

አሁንም እራሴን ነቀነኩለት፡፡

"ደንበኛ እንሆናለን" አለኝ

እራሴን ግራ ቀኝ እማታሁበት፡፡





"የምትፈልገው ሲኖር አስታውሰኝ"

እንደ አካሉ ድምፁም የተንጨፈረረ ነው፡፡ ጆሮ ይፍቃል፡፡ ቢሆንም የምፈልገውን ሲጠይቀኝ አለኝታነት ተሰማኝ፡፡ እኔ የምፈልገው ከአፍ ለዳ መላቀቅ ነው፡፡ ለዚህ ሽኩ ምን እትርቦት ይኖረዋል?

ስፈራ ስቸር ነገርኩት፡፡

"ኩይሳ ያልከኝ ያንተን ጎረቤት ነው?" አለኝ፡፡

እራሴን ላይ ታች ወዘወዝኩለት፡፡

"ኡ ታዲያ እሱማ ዝም ብለህ እንዳደረገህ መሆን ነው"

"ምን?"

"እም!"

ዞረብኝ፡፡ ቀን ገደቤ ነገ ነው፡፡ ብሩን በሞዴል ተበድሬ እንደሰጠሁት ይገድለኛል፡፡ ተናዘዝ ተናዘዝ አለኝኝ፡፡

"ለማንኛውም አፈላልጌ ልጠብቅህ"

ህይወት ሱሪ አይደል የት ያፈላልገልኛል?

* * *

የመጨረሻዋ ቀን አዳሬን ሳማትም ወደ ቤቴ እየሄድኩ ነው፡፡ ሞዴል የወሰድኩትን ብር ይዣለሁ፡፡ ነገ በጠዋት ኩይሳው በሬን ይቆረቁራል፡፡ እከፍታለሁ፡፡ የእንጨት ገበቴ እጄን ፊቴ ላይ ይደቅናል፡፡ ብሩን አስተምጣለሁ፡፡ የእንጨት ገበቴውን ይጨብጣል፣ ጣቶቼን ሲሰበስባቸው ቡጢው ጉቶ ይመስላል፡፡ እንግዲህ በዚያ ጉቶው ነው ፊቴ ላይ የሚለኝ፡፡ ሲደግመኝ የኩቱን ክሳድ ይዞ ከወደኩበት ሲያነሳኝ የለሁም፡፡ በባህላችን አስከሬን ክቡር ነው፡፡ በእርጋታ አስተምጠኝ ካማተበ በኋላ ይሔዳል፡፡ ፍትሐቱም በኩይሳ ማማተብ ይጠናቀቃል፡፡

ወራሳዎችን ተሰናበት ተሰናበት አለኝ፡፡

ደግሞም እንደነብሁቹ "ወዮልሽ ወራሳ" ማለት አማረኝ "ፍፃሜ መጥቷል፣ ተንቅቶብሻል ወራሳ! እነሆ ቀን ደርሷል፡፡ በወራሳ



@BOOKALEM

የምትቀመጥ ሆይ፣ ተራህ ደርሷል፡፡ ጊዜ መጥቷል፣ ቀን ቀርቧል፣ የሽብር ቀን ነው እንጂ በተራራማዋ ወሪሳ ላይ ያለ እልልታ አይደለም፡፡ አሁን በቅርብ መዓቴን እፈስብሻለሁ፣ ቁጣዬንም እፈፅምብሻለሁ፡፡ እንደ መንገድሽም መጠን እፈርድብሻለሁ፡፡ ጉስቁልናን በአንድ ምስኪን የአማርኛ መምህር ላይ ፈፅመሻልና ጉስቁልናሽንም ሁሉ አመጣብሻለሁ፡፡"

በራሴ ትንቢት ተፅናናሁ፡፡

ከዚህች ዓለምና ሕዝቧ የተረኝን ነገር ፈልጌ ፈልጌ አጣሁት፡፡ ብቻ አንድ የተረት መጽሐፍ ብጽፍ ምኞቴ ነበር፡፡ ይሄ ደግሞ የብዙዎቹ አማርኛ መምህሮች ህልም ነው፡፡ አልሆንም፡፡ እራሴ የኩይሳው ተረት መሆኛዬ ደርሷል፡፡

ቤቴ መዳረሻ ላይ "አንተን ነው፣ ስማ" የሚል ድምፅ ሲከተለኝ ከሐሳቤ ነቃሁ፡፡ መልአከ ሞት መሰለኝ፡፡ ምን አስቸኮለው? አንድ ሌሊት መጠበቅ ተሳነው? ልወቅሰው ዞር አልኩ፡፡ መልአከ ሞት ሳይሆን መልአከ ሞት የሚመስለው ሽኩኩ ኖሯል፡፡

ቆሜ ጠበቅሁት፡፡ ባያታክተኝ፣ የመጨረሻ ቀኔን በሠላም ባሳልፍ ምናለ? ሆድ ባሰኝ፡፡ እልቅስ እልቅስ አለኝ፡፡

"ያ ያልከኝን አግኝቼልሃለሁ" አለኝ

ጎንበስ ብዬ ሱሪዬን አየሁ፡፡ እሱ፣ ታዲያ ምንድነው ያገኘልኝ? ኩይሳው ከገደለኝ በኋላ እርጥብ ነፍሴን እምጥቶ የድለላ ሊቀበለኝ?

"ባለጋራህ አንድ የሚፈራቸው ሰው አሉ፡፡"

"ማናቸው? እናና?" የምለው ጠፋኝ፡፡

"እምቋርቋር ይባላሉ፡፡ ድሮ እሳት የላሱ ጠበቃ ነበሩ፡፡ ኩይሳውን ከአንዴም ሦስቴ ከርቸሌ አውርደውታል"

"እናን"

"ነገ ቤታቸው ሄደን...."

"ከሞትኩ በኋላ?" አልኩት፡፡

"እንግዲያው አሁን እንሂዳ፣ ለእኔ የድለላዬን....."





"እሱ ግድ የለም፡፡ ግን ሰውየው ማነው ያልከኝ ስማቸውን?"

"እምቋርቋር"

"እ--- የእምቋርቋር ቤታቸው የት ነው?"

"እሪ በከንቱ"

"እ?"

ደገመልኝ፡፡ የሰፈሩ ስም ያስፈራል፡፡ ቢሆንም፣ ሲያልቢሆንም ከኩይሳው መገላገያ ካገኘሁ እሄዳለሁ፡፡

"እንሂድ" አልኩት ሠፈሩን እንደሚያውቅ እየቀደምኩ፡፡

## 17 - እምቋርቋር

እምቋርቋር፣ እምቋርቋር፣ እምቋርቋር ምን አይነት ስም ነው? እንደአማርኛ መምህርነቴ ይህን ስም ለመፍታት ይሄን ያህል ማሳደድ አልነበረብኝም፡፡

እምቋርቋር፣ ይምቋርቋር፣ ይቋርቋር ዘንድ.... አባቴ ትዝ አለኝ፡፡ በሩ ላይ ተቀምጦ ግስ ሲያረባ፣ የሚያረባቸውን ዶሮዎች በመሃሉ "እ-ሽ" እያለ፣ የረባም ልጅ ባይኖረው እፊቱ ኮልኩሎ "ግስ እርቡ" ይላል፣ እርቡ ጠባብ የሆነውን ነጠላውን ትከሻው ላይ ጣል አርጎ፣ ከሚያረባቸው በጎች አንዱን እሞሌ ጨው እያላሰ....

"እምቋርቋር፣ ይምቋርቋር፣ ይምቋረቋር ዘንድ....."

እሪ በከንቱ የወሪሳ አጎራባች መንደር ነው፡፡ አቆልቁለን የእሪ በከንቱን ወንዝ ሻገር እንዳልን መንደሯ የገጠር ገበያ መስላ ትታያለች፡፡ የኮልት ዳስ የመሳሰሉ እንደነገሩ ቤቶች ይበዟታል፡፡

ከወደወሪሳ አቅጣጫ ስለመጣን እሪበከንቱዎች በአይነቁራኛ እያዩ መዳረሻችንን ይታዘቡ፡፡ ትልቅ ቤት አጠገብ ደረስን፡፡

"ቤቶች" አለ ሽኩኩ

አንዲት ደዘደዝ ልጅ እግር ብቅ ብላ ካየችን በኋላ "አባዬን ገደሉት? ወይኔ አባዬ...." እያለች ልታለቅስ አኮበኮበች፡፡ አንድ አራት የሚሆኑ ማቲዎች እሰሯ ተኮለኮሉ፡፡



@BOOKALEM

"ኧረ እኛ እሳቸውን ፈልገን...."

"ነው'ንዴ?" ብላ የተንጠረበበ እንባዋን ዋጠች፡፡ እንደ ማር ስልቻ የሚዋልል ገላዋን ሰፊ ተሚስ ከታዋለች፡፡ የሆንግ ተራዳ የመሳሰሉ እግሮች አሏት፡፡ እጆቿ የኩይሳውን አስታወሱኝ፡፡ ገበቴ እጅ፡፡

"የሉም?" አሳት

"ጠጅ ቤት ብሎ ወጣ" አለች

ወደዚያው ለማምራት ፊታችንን መለስን፡፡ ያቺ ግርንድስ ወደ ቤቷ እንዳልገባች ቀልቤ ነግሮኛል፡፡ ትከብዳለች፡፡ ዞር ስል በር ላይ ቆማ ስታጤነን አየኋት፡፡ ፈገግ አለችልኝ "አይ ፊትና ከንፈር" አልኩ በሆዴ "ይቦጭትሽ!"

አንድ ሦስት ጠጅ ቤቶችን እንዳሰስን አገኘናቸው፡፡ እንደ ኩይሳው ግርንድስ መስለውኝ ነበር፡፡ የኩይሳውን አውራጣት ነው የሚያክሉት፡፡ ከእሳቸው ይልቅ ያቺ ደዘደዝ ልጃቸውን በተማመንኩ ደግ ነበር፡፡

እምጳርጵር ሁከተኛ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ በአንድ ጊዜ ከቀጂው እና ከጠጪ ጋር ሲጣሉ ነው ያገኘናቸው፡፡

"እእን? እእን? አንድ ብርሌ እጭበረበርከኝ? ጥሩ፡ አንተ ደሞ ዝም በል በፊት ቢሆን ስታየኝ ሽንትህ ይመጣ ነበር፡፡ አንተስ ብትሆን..."

በልብ ከኩይሳው እኩያ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ እንዲያውም ባይበልጡ፡፡

"ምን ነበር?" ጠጃቸውን ከብርሌ ፊንጠት አድርገው፡፡

"ይሄ ወንድሜ" ብሎ ሽኩኩ ዘለግ ያለ ነገር ነገራቸው፡፡ እንዴም አልተያዘልኝም፡፡ የእኔ አማርኛ አስተማሪነት አሁንስ አጠራጠረኝ፡፡ እምጳርጵር ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁና ከለፍ አገደም እእን እየማተሩ አድምጠው

"ጥሩ ነው" አሉ፡፡ "አልፎ አልፎ እንዲህ ሀግ አማካሪነቱን ተመክተው የሚመጡ ሰዎች መንፈሴን ተውድቀት ይታደጓታል፡፡





መንግሥት ዲፕሎም ተሊላችሁ ወገዱ ይበለን እንጂ አውቀቱ ያለው እኛጋ ነው፡፡ ዳኞቹም ወንበሩን ይያዙት እንጂ ማታ ማታ እኛኑ ተለማምጠው ባማከሩን መሠረት ነው ውሳኔ የሚሠጡት፡፡ እራስ ሳይጠኛ ጉተና አሉ፡፡"

እምጳርጵር ሲያወሩ ይቁነጠነጣሉ፡፡ ከመቁነጥነጥም በላይ መከለፍለፍ ሊባል ይችላል፡፡ ፈራኋቸው፡፡

"ያ አመለኛ ነው ባሊጋራህ?"

"አዎ እምጳርጵር" አልኳቸው

"በገደለህ" አሉኝ

"እ?"

"በገደለህ አልኩህ፡፡ ምን ያልሰማ ትመስላለህ? እሬ ዛሬጢ ነህ እምጳርጵር ትለኝ?"

"ይቅርታ" አልኩ የምለው ግራ ገብቶኝ፡፡

"ስሜ እምብርብር ነው፡፡ የመንደር ወሽካታ ነው እምጳርጵር የሚለኝ፡፡ በዚህ የቀንሳ አንድ ሦስቱን ፀጉሩን አስላጭቼ ከርቸሌ ሰድጄዋለሁ፡፡"

እራሴን ነቀነቅሁ፡፡

ወደ ጠጅ ቀጂው ዞረው "ና አንተ" አሉት "ለእንግዶቼም ቅዳ"

ጠጅ ጠጥቼ አላውቅም፡፡ እንቢ ማለትም አልቻልኩም፡፡ አመጠኛን በአመጠኛ አጠፋለሁ ስል እኔ መካከል ቤት እንዳልጠፋ ሰጋሁ፡፡

"እንግዲህ ሰውየውን በገጀራም ሆነ በጩቤ ብትገድለው ሁኑ አንድ ነው፡፡ ጨካኝ፣ ነውረኛ ተብለህ መቅለብህ አይቀርም፡፡ ህጋዊ አገዳደል የሚባል የለም፡፡ ከፍርድ የሚያስመልጠው ተደብቆ መግደል ብቻ ነው፡፡"

እኚህ አውራጣት የሚያህሉ ሰው አውራዶሮ ኩራት ቅርም ሳይላቸው ስለወንጀል አፈፃፀም ያማክራሉ፡፡ ፈራኋቸው፡፡



@BOOKALEM

"እኔ እኮ ልገድለው ሳይሆን እንዳይገድለኝ...."

"እእስ ምን አልኩ? እንዳይገድልህ የምትከላከለው በመግደል ነው:: ልክሰስ እትል በምን ማስረጃ? እጅ ጠብቅ ብታስፈርመውም......"

ዞር ብዬ ሽኩኑን አየሁት:: የቀረበለትን ብርሌ እንደ እንጀራ እናት ጡጦ አፉ ላይ ለግቶታል::

"ሌላ አማራጭ የለም?"

"ይኖራል" አሉኝ

"ምንድነው?"

"እኔን ከእሱ ጋር ማጣላት"

"እ?"

"ሰምተሃል፣ ደሃው ነው፣ ከፍያው ሚኒን ይልብሃል እንጂ ተቻልከው አሄድለታለሁ:: በሚዳ ስጣላና ስካሰስ የኖርኩ ሰው ነኝ:: ጠብ ኑሮዬ ነው::"

ትክ ብዬ አየኋቸው:: የዱር ድመት ይመስል ስለጠብ ሲያወሩ ተንፍፍተው ይገዝፋሉ::

"እየጠጣህ"

"እሺ" እንሰቼ ቀመስኩት:: ይጣፍጣል:: ደግሜ አስቀመጥኩት "ምን ያህል ይላሉ?"

"ያገር ዋጋ ነው እሪ በከንቱዎች ያውቁታል:: አንተን ግን ቀልቤ ስለወደደህ መቶ ሃምሳ ትከፍላለህ::"

"እሱስ ይሁን፣ ግን እርስዎ ከተጣሉት አጠገቡ አይደርስም?"

"ምን ይላል ደሃ፣ መቼ ፋታ እሰጠዋለሁና:: እሱን ለእኔ ተወው:: ጠበኝነትን ከአባቴ የወረስኩ ሰው ነኝ:: የሰባት ጠበኛ ዘር ነኝ::"

አባቴ "የሰባት ቂስ ዘር ነኝ" ሲል እሰማ ነበር::





"አሁን እድሜው እየተጫነኝ የያዝኩትን ጠብ ማጥበቅ ተሳነኝ እንጂ በፊት አንተን ሳህልማ፣ ጠብ እቤቴ ተመጣ መጣ ታልመጣም ነምለል፣ ነምለል እያልኩ ጠብ ወዳለበት እብስ"

ተጓ ጋር ጠብ ሳያነሱ ቶሎ ተዋውዬ መለያየት ፈለኩ::

"ጠጣ"

"አሁን ተብድ ልስጠትና...."

"ምን አስቸኮለህ? ጠብ ጥደህ ነው የመጣሽው?"

"አይ"

"በል ጠጣ"

"እሺ"

ሽኩቱ ደጋግሟል:: ደረት አይኑ ተጎልጉሎ መጨፈን ተስኖታል:: ጭራሽ ደረት እንዴ?

ከፍርሃት ለመገላገል ቢረዳኝ በሚል እእም ጠጁን ደጋገምኩ:: በዚህ አጋጣሚ ጠጅ ለፍርሃት ፍቱን መድኃኒት መሆኑን ለሚፈሩ ሁሉ መንገር እፈልጋለሁ:: ጠጅ ተምን ይሠራል? ተማርና ተጊሾ ያላችሁ ውድቅ ተደርጎባችኋል:: ጠጅ የሚሠራው ተትዕቢትና ተስብሪት ነው:: የጠጅ ስካርስ? መወላገድ ያላችሁ ውድቅ ሆኖባችኋል:: ጠበኝነት ነው::

መጀመሪያ ሽኩቱን "አንተ እኮ ደፍረኸኛል" እላኩት ሱሪዬን በማስታወስ

አይኑን መጨፈን ተስኖት ፊጥጦ ፊቴ ላይ ተደቀነ:: በጣቶቼ ሽፍሽፍቱን ዝቅ አድርጌ ልጨፍንለት ይሆን?

ሒሳቡን እኔ ከፍዬ ወጣን::

እምጵርጵር ቢደክሙም የሚያወሩት አይሳታቸውም::

"ለሌባ መድኃኒቱ እኔ ነኝ:: ገና ትክ ብዬ ሳየው ሰራ አካላቱ ይፈርሳል" ይላሉ::

ቤታቸው ስንደርስ ድፍን ሃምሳ ብር አውጥቼ ዘረጋሁላቸው::

"ምን?" አሉኝ



@BOOKALEM

"ቀብድ"

"ገንዘቡን ወዲያ በለውና ጠላቶቻችንን በጋራ ልናጠቃ ተማምለን የለም እንዴ?" አሉኝ

"ተማማልን እንዴ?"

"እንግዲያስ"

ሸኩ ብሩን ሲያይ የበለጠ አይኑ ፈጦ ቀረ:: እንዳይፈርጥ::

"ግቡና እኔ ቤት እደሩ:: ነገ አንድጋ ሄደን ያንን ሽንታም እናንጸረጽረዋለን"

በስካር ለዘብታ ለምን እምጸርጽር እንደተባሉ ተገለፀልኝ::

"ማንን ፈርቼ እዚህ የማድረው?" አልኳቸው

"ነሽ የእኔ ልጅ: ታዲያ ቤትህ ገጀራ አለህ?"

"ኧረ የለኝም"

"ጩቤስ?"

"በፍፁም"

"ቆይ ትርፍ አለኝ ልስጥህ" ብለውኝ ወደ ውስጥ ገቡ

ሸኩን የማንጠልጠል ያህል እያጣደፍኩ ጉዞ ወደ ወሪሳ ሆነ:: ብዙም ሳንጓዝ ከኋላችን የአንዲት ሴት ድምፅ ሰማን:: ስለጨለመ አላየናትም:: ስትቀርብ የእምጸርጽር ልጅ መሆኗን ለየሁ::

"አባዬ ለማንኛውም ይሄን ያዙ ብሏችኋል" አለች እያለከለከች:: ገጀራ ነበር:: ገና እጄ ሳስገባው ፍርሃቱ ጨርሶ ጠፋ::

ለካ የጎደለኝ ልብ አልነበረም:: ገጀራና ጠጅ እንጂ:: የጠጅ ፈረሴን ጭኜ ገሰገስኩ:: ሸኩ ስካሩ ጠፍቶ በጥርጣሬ ይከተለኛል::

ወሪሳ እምብዛም አልተሟሟቀችም:: ገጀራውን ይዤ ያየ ወሪሳዊ ክፉቱ ገለል ይልና የማደርገውን ለማየት በርቀት ይከተለኛል::





የልብ ልብ ተሰምቶኝ የትናንት ትንቢት ጭንቅላቴ ውስጥ ይመላለስ ጀመር::

"መዓቱ በብዙዎች ሁሉ ላይ ነው:: አንድስ እንኳ ወደሌብነት የሚሄድ የለም:: ገጀራ በውጭ: ስድብና ማንጓጠጥ በውስጥ አለ:: በሚዳ ያለው በገጀራ ይሞታል:: ከእኔ የሚሸሽ ይሆናል...."

ደጄ ላይ ደረስኩ:: ልገባ ካልኩ በኋላ አንዳች ነገር ገፋፍቶኝ ወደ ኩይሳው ቤት ጠጋ አልኩ:: ምናልባት የሚከተሉኝ ወሪሳዎች ወደቤቴ ስገባ ለዚህ ነው እንዴ በማለት አሳንሰው እንዳያዩኝ ይሆናል:: ያም ሆነ ይህ በያዝኩት ገጀራ በሩን ቆረቆርኩ::

ሲወጣ ምን እለዋለሁ? እሳርፍበታለሁ? ተማረክ እለዋለሁ? ተናዘዝ እለዋለሁ? ሁለተኛ ላትደርስብኝ ማለልኝ እለዋለሁ? ምን እለዋለሁ?... ለማንኛውም ኩይሳው የለም::

ወደቤቴ መለስ ስል ትከሻዬን ከበደኝ:: ሰዐር እማማ ጉዶ እሎሌቀው ያዩኛል:: በቆንጨራው ዛትኩባቸው

"ጠብቁኝ: እጠብቅዎታለሁ" አልኳቸው ሸኩክ ብለው ገቡ:: የልጅ ልጅ ልጃቸው.... እስራቸው ቆሞ ኖሮ አየሁት "አንተም ጠብቀኝ" አልኩትና እጠገቢ ያለውን ቅጠላቅጠል በቆንጨራ ቀንጣጥሼ ገባሁ::

## 18 - የፍርሃት መዳረሻ

በማለዳ: ወፍ ሳይንጫጫ ጭንቅላቴ ተንጫጭቶ ቀሰቀሰኝ:: የስካር ክፍያው ራስ ምታት ነው:: ልቤንም ያጥወለውለኛል:: እንደሚስት ታቅፌው ያደርኩት ቆንጨራ ግኗል:: የማታ ሁኔታዬ ሁሉ በብዥታ ትውስታ እየተቆራረጠ እእምሮዬ ላይ ተሰልፎ አለፈ::

"ሙኝ የማታውቅ ወፍ እስቲ: እሰቴ ትላለች" ይባላል::

ፍርሃትና ሃፍረት ወረደብኝ::

እንግዲህ ኩይሳ ደጄ መቆርቆሩን ሲሰማ [illegible] ይሆናል:: በሩን እንደመጋረጃ ገልጧት ይገባል:: [illegible]

"በል ተነስ እንግዲህ ታጠቅ" ይለኛል

"ምነው ኩይሳው? እኔ ብሳሳት አንተ ትሳሳታለህም" እለዋለሁ፡፡

"ያለ ደም ስርየት የለም" ይለኛል፡፡ (እንዲህ እንኳን አይልም፡ እንደው ወጊ እንጨት እንጨት እንዳይል ካልሆነ በቀር)

"ኃጢያ እያለ?" እለዋለሁ "ስህተት በደም? እንዴት ያለ ፍርድ ነው?"

"እኛ ወሪሳዎች የኖርነው በዚህ ህግ ነው፡፡ በዚያው ትዳኛለህ፡፡ ተነስ ታጠቅ"

ታልቀረልኝ ብዬ ሱሪዬን አጣው ብርድልብስ ውስጥ እንዳለሁ አጠልቃለሁ፡፡ እነሳለሁ፡፡ ኩይሳው ወደ መፋለሚያቸን ይመራኛል፤ እከተላለሁ፡፡ ቆንጨራ እያያዜ መሬት ለመሬት እየጎተተኩ ነው፡፡ ብረቱ ይሰማኛል፡፡ ኩይሳው ይሄዳል፤ ወሪሳን መሀል ለመሀል ሰንጥቆ ያልፋል፡ መንደሩን ይጨርሳል፤ አሰፋልቱን ይጨርሳል፡ ጅረቱን ያቋርጣል፤ አረሁን ያልፋል፡ ቆላ ይወርዳል፤ እኔና ቆንጨራዬ እንከተለዋለን፡፡ ከተማ እናገኛለን፤ ገበያ እናቋርጣለን፤ ባህር እንቀዝፋለን፤ ጠፍ መሬት እናገኛለን፤ ገጠር እንገባለን.... መለስ ብዬ ሳየው የቆንጨራዬ ዱካ የምድር ወገብ ሰርቷል፡፡

ልንፋለም እንዘጋጃለን፡፡ ሰውነታችን አይታዘዝልንም፡፡ ከድካም ሳይሆን ከእርጅና፡፡

"እያ ኩይሳ" እለዋለሁ ከዕድሜ ብዛት በዛገ ድምፅ

"ማን ልበል?" ይለኛል ያኔ ኩርሲ የሚያክለው እጁ ሟሾ በወፍቆ የታሰረ የአንድ ብር ቅቤ መስሏል፡፡

"ዘነጋሽኝ?"

በዚህ ሀሳብ ተጠምጄ የጭንቀቴንና የጭንቅላቴን ንዝንዝ ረስቼው ነበር፡፡ ደጃፌ ተቆርቁሮ ወደ እውነቱ መለሰኝ፡፡

ጥሳ ይታየኛል፤ ግዙፍ ጥላ

"መጣ" አልኩ ሳልታጠቅ የተኛሁበት እንዳይዘኝ፤ እሚሟቱ እንኳን ቅጥ እንዲኖረው ሱሪዬን አጠለቅሁ፡፡ አሊጋው ጫፍ





ተቀምጬ ትንፋሽ ለማሰብ ከጀልኩ፡፡ ግን ድጋሚ ለሰስ ባለ መልኩ ተቆረቆረ፡፡

ሊያዘናጋኝ ነው፡፡ ደጃፍ ቁርቆራው ላይ ለዘብ ማለቱን አይቼና ተዘናግቼ ስከፍት መጆ እጁን ሊጭንብኝ፡፡

ተጠንቅቄ ከፈትኩ፡፡ ኩይሳው ሳይሆን እሳውንቱ ሴባ ነበሩ፡፡ ፊታቸውን አጤንኩ፡ ፍርሃት ይዘዋል፤ እጃቸውን አጤንኩ ፊስታል ይዘዋል፡፡ ዘረጉልኝ፡፡

"እኛ ብንሳሳት አንተ ትሳሳታለህ?" የት ነበር ይሄን ንግግር የሰማሁት? ፊስታሉን ተቀበልኩ፡፡ ኪሳቸው ገብተው ብር አወጡ፡፡ ዘረጉልኝ ተቀበልኩ፡፡

ሲፈሩ ሲቸሩ "የወደቀ አንሺ እንጂ ሴባ አይደለሁም" አሉኝ፡፡ "ያው እንደምታውቀው ፊስታሉን ጥለኸው ነበር፡፡ አነሳሁ፡፡ ትንሽም የተሳሳትኩት ቦርሳው ላይ ነው፡፡ መሬት ሳልጥል፡ ሳላመሰግን ይዤ መሄዴ ጥፋት ነበር፡፡"

* * * *

በቀጣዩ ቀን ኩይሳውም እማላጅ ሳክብኝ፡፡ ለካ ይሄን ሁሉ ቀናት በፍርሃት ቤቱ አልገባም ኖሯል፡፡

"እንግቱ ይቆረጥ! ወይ እኔ፤ ወይ እሱ" አልኩ፡፡

"እረ ተው፤ እርስት አልተናጠቃችሁ፤ ሚስት አልተቃማችሁ" አሉኝ

ስማደረደር እንጂ እራሴ እማላጅ ልኬ በታረኩት ነበር፡፡

"ሃይ፤ ሃይ፤ ሃይ" አሉ እማላጆቹ

"ይሁን" አልኩኝ፡፡

ኩይሳው መጥቶ እግሬ ላይ ወደቀ፡፡ እሰሬ ጉድባ መስሎ ተከመረ፡፡

"አሁን እግሬን ዘርጥጦ ጭጭ ቢያደርገኝስ?" የሚል ሀሳብ ይዞኝ አስጨነቀኝ፡፡

## 19 - የሡላም ልዑክ

እምጻርጵር ምን እንዳገረሸባቸው እንጃ በአራተኛው ቀ፣ ወሪሳ ሡፈር ድረስ መጥተው ደነፉ፡፡

"ማ አባቱ ነው የልጄን ባል? የታለ ኩይሳው?" አሉ፡፡

"ኧረ ተዉ ነገር በርዷል" ተባሉ፡፡

"መጀመሪያውኑ ምን ሲደረግ ተቆሰቆሰ? አንድ ጠብ ጀምሮ ማፈግፈግ አልለመደብኝም፡፡ ገጥመናል ገጥመናል" አሉ፡፡

"ይተዉ እንጂ ኧረ ደግም አይደል?"

"መጀመሪያ አስቀፈድደዋለሁ - እንደለመደ፡፡ ከዚያ እገድለዋለሁ እንዳልለመደ፡፡ ቅጣቱ ሁለት ነው፡፡"

ኩይሳው የእኔን ውንቀት ምናምኒት ሳያስቀር ተረከበኝ፡፡ ፊቱ ገርጥቶ፡ ትከሻው ከድቶት መጣ፡፡

"አማልደኝ እኒህን ሰውዬ" አለኝ፡፡ ቢያሳዝነኝም ወደ ቀንደ ማሽበሩ ዳግመኛ እንዳይመለስ አድርጌ መሸኘት አለብኝና "እሳቸው ሰው ይሰማሉ እንዴ?" ስል አንገራበብኩ፡፡

"አንተን ይሰሙሃል፡ የልጃቸው ባል ነህ አሉ" እጄን እንደ ዶሮ አጣቢ አየር ላይ አንቸፈቸፈ፡፡

"እሱስ ነው፣ ግን....አንተ....."

"እኔ ምን? ከእንግዲህ? ኧረ የዛሬን አውጣኝ"

"እሞክራለሁ"

"እ-ሺ፡ እግዚሐር ክጉድ ያውጣህ" ብሎ ከቤት ሲወጣ ስለ "በሩን ልዝጋው?" አለኝ፡፡

"ተወው" አልኩት

"እሺ ደህና እደርልኝ..."

በጀርባዬ ተንጋልዬ ተኛሁ፡፡ ነፃነት ተሰማኝ፡፡ የበላይነት ትርፉ ይሄው አይደል?





## 20 - ሽግግር

ለአማላጅነት እኔ ሳልሄድ ራሳቸው አምጻርጵር ወሪሳ ሡፈር መጥተው ያንን መፈለል በወሪሳውያን እንዴ ተወጡት፡፡

"ምድሪ ሊባ እያንዳንድሽ ፋይልሽ እጇ ላይ ነው፡፡ ፈርሚ መላክ ነው" አሉ፡፡

ጠቀስ አድርጌአቸው ወደ ቤት ገባሁ - ተከተሉኝ፡፡

"እየሸልኝ ጠቤን?" አሉ "አልነክስም ከነከስኩ አልለቅም፡፡ ጊንጥ ነኝ፡፡ ጠብን በዘርማንዘሬ አውቀዋለሁ"

"ጥሩ" እንደማለት እራሴን ነቀነኩላቸው፡፡

"ገራ እንኳን አመጣጤ ወዳንተ ነበር፡፡ በቃላችን መሠረት አንድ ባላጋራዬን በጋራ እናቀምሰዋለን፡፡"

"የምን ባላጋራ?"

"ቃል ተገባብተን? ጠላትህ ጠላቴ ተባብለን?"

"ይልቅ አማላጅ እርስዎ ዘንድ ተልኬአለሁ" አልኳቸው፡፡

"ማን ላከህ?"

"ኩይሳው"

"ምን አለ?"

"ይተዉኝ እያለ ነው ይተዉት"

"አልተውም፣"

"እንዴ ለእኔ ሲሉ ተማሉት፡ ጠባዩን ካሻሻለ......"

"እ-ይ እንግዲህ፣ እንዴ ጠብህን ወደ እኔ አዙረሃል፡፡ በቃ የምን ጠቤን መልሱልኝ ነው? ሞኝ ወርውረው ቢስቱት ያልጎዱት ይመስለዋል" ሲሉ ተረቱብኝ፡፡

"ሳይሆን....."

"እንዴ በቃ አልነኩ እኮ፡ እኔ በጠቤ ማሌቃ ሲገቡብኝ አልወድም፡፡"

"ኧረ እምቢ..."

"እ? እቡቲ ጨርሳት? ዛሬ እንጫረሳለን፡፡" ተቁነጠነጡ፡፡ ነገር ሲያገኙ እንደሚሆኑት ሰውነታቸው ተቆጥቶ ተነፋፋ፡፡ ፊራጓቸው፡፡

ዝም አልኩ፡፡

"ይልቅዬ ዛሬ ማታ እዚያው ጠጅ ቤት ናና ያንን ባላጋራዬን፣ ባላጋራችንን..."

"እ?"

"እደብ እናስገዛዋለን"

"ዋእርሶ ባላጋራ የትየለሌ፤ እኔ ዕድሜዬን ሙሉ ስወራከብ ልኖር ነው?"

"ኧረ ተው ጎረምሳው፣ ጠብ ይሰለቻል እንዴ? ዋ! ስንት ክፉ ቀን አለ መሰለህ ሁለት ቀን ሙሉ ሳትጣላ የምታሳልፍበት ተመስገን ማለት ነው"

"ወይ ጉድ! እንዴ ተጣልተውልኛል! እንዴ መጥቼ ዕዳዬን አወራርዳለሁ፡፡ ተዚያ በኋላ ላለው እኔን ምንም አይመለከቱኝም፡፡"

"እሱን ግድ የለም፣ ብቻ ማታ ና" ሄደት ብለው ተመለሱና "ደግሞኮ ዕዳ ካልከው ሲጣውን አይመለስም ወለድ አለበት፡፡"

ከፈሪው ኩይሳ ወደ ደፋሩ ኩይሳ እንደተዘዋወርኩ ገባኝ፡፡

አመሻሽ ላይ ሽኩኩን ልከው "ቀጠሮችን ቀርቷል፡፡ ሰውየው ሞቶ አደረ" አሉኝ፡፡ የተሰማኝ እረፍት ይህ ከእንዲህ የሚባል አይደለም፡፡





# ምዕራፍ ሦስት

## 21 - ወረራ

እምጰርጵር ብቻቸውን ወሪሳን ወረሩ፡፡

እናቱ የትንሽ ልጅ ራስ የሚያህል የፀብ ዱላ ታጥቀው ይንጠረበባሉ፡፡

"ባላጋራዬን ውለዱ!"

ወሪሳ ምጥ ይጠናባታል፡፡

"ይሄን ሰፈር ወና ነው የማደርገው፡፡ እንደ ህዝብ ቆጠራ በመደዳ ነው የወንጀል ሪከርዳችሁ ያለኝ፡፡ በቤተሰብ፣ በቤት በመደዳ፣ አባት ነህ፣ እናት ነሽ፣ ልጅ ነህ፣ የልጅ ልጅ ነሽ፣ አያት፣ ቅድመ አያት... የሞቱት ሁሉ አይቀሩኝም፡፡ እንደገና ተቆፍረው እንዲቀበሩ አስፈርድባቸዋለሁ"

ወሪሳ እራደች፡ በእድሜ የእምጰርጵር እኩያ ተመርጠው ጆቢራ ተላኩባቸው፡፡

"እንዳትቀርብኝ!" ዱላቸውን ወደ ጆቢራው አነጣጠሩ፡፡ "የዝንጀሮ መነኩሲ፣ የሰንበሌጥ እንካሲ አለ፡፡ እንዳትቀርበኝ፡፡"

የመጣውን ሁሉ አያስቀርቡም፡፡

"ባላጋራዬን ውለዱ"

ወሪሳን አስጨንቀው ያዙ፡፡ ጆቢራ ስላልተሳካላቸው አቀርቅረው ተመለሱ፡፡ እላቸውን ተከቶ የእማማ ጉዶ የልጅ ልጅ... ልጅ ቀረባቸው፡፡ እቀፉኝ እንደ ማለት እጁን እንከረፈፈላቸው፡፡



@BOOKALEM

"አንት የእይዋ ግልገል፣ ዞር በል ካጠገቤ" አሉት እሱም ላይ ዱላቸውን እየነቀነቁ፡፡ የልጅ ምላሹ በደረቱ ይላሻ! ዘወር እኮ ዘወር"

ልጅ መስሎ የሄደው እዋቂ ሆኖ ተመለሰ፡፡

እምጴርጵር ቢያናድዱኝም አደንቅኋቸው፡፡ እራሴን እየሁባቸው፡፡ ጀቢራ በእባውንትነት፣ ልጁ በህፃንነት እሞኝተውኛል፡፡ እምጴርጵር ግን እእንም ወረሳንም በሌጠው ተገኙ፡፡

እምጴርጵር በወረሳ ላይ "እይዋ ጣረሞት ይዟት፣ ትጫወታለች ድመት" እንደተባለው ሆኑ፡፡ እስጨነቁ፡፡

* * *

በሦስተኛው የእምጴርጵር ወረራ ላይ እንዴት እንደተከናወነ ያላወኩት ነገር ሆነ፡፡ እምጴርጵር ወረሳውያንን ጥቂት እንጴርጵረው እንደቆዩ ከረንቲ የያዛቸው መሰለ፡፡ የደረት ኪሳቸውን፣ የሱሪ ኪሳቸውን፣ ከፈታተሹ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ፈዘው ቆሙ፡፡

እምጴርጵር ሲመጡ ጀምሮ እይቻቸዋለሁ፡፡ ማንንም ወረሳዊ አላስጠጉም፡፡ እንደ እኔ አልታተቀፉም፣ የሱሪ ጥላሸታቸው እንዲራገፍ አልተስማሙም፡፡ እናግ ተአምር ሆነብኝ፡፡

እምጴርጵር በደከመ ድምፅ "መጠሪያዬን መልሱ" አሉ፡፡ ቤታቸው ጥለው የመጡ መሰሉኛል፡፡

"መጠሪያዬን"

የእምጴርጵር ድምፅ የእሽናፊነት ግርማውን እጥቶ ተልፈስፍሷል፡፡ በወረሳዎች ፊት የተንበረከኩ መሰለኝ፡፡

"መጠሪያዬን"

ሂጄ ቤታቸው ጥለው እንደመጡና ማንም እንዳልቀረባቸው ልነግራቸው ሳኮበኩብ የእማማ ጉዶ የልጅ… ልጅ ወደ እምጴርጵር እመራ፡፡ በእዋቂ ትዝብት ካያቸው በኋላ አንድ በእድሜ ብዛት የተኰኘረጎረች ቡና አይነት የኪስ ቦርሳ አውጥቶ ሰጣቸው፡፡ እምጴርጵር አላመኑም፡፡ ተስገብግበው ከፈቱት፡፡ ፊታቸው ፈካ፡፡





ኩኩመታቸው እጥረት የተነሳ የልጁን ግንባር ሳሙት፡፡ ልጁን ለመሳም እጅግም አላጎነበሱም፡፡ የወደቀ ዱላቸውን እንስተው ወረሳን ለቅቀው ሄዱ፡፡

ተአምር ሆኖብኛል፣ ድግምት ሆኖብኛል፣ እስማት ሆኖብኛል… ወረሳዎች የእምጴርጵርን ቦርሳ እንደ ድመት ውርርርር ብለው ጠሩዋት? እንደ ቡችላ እባበሏት? እንደ ዶሮ "ኩልኩል" አሏት? …እውነቱ ተተባዘረብኝ፡፡ ስጠይቅ የሚነግረኝ አጣሁ፡፡ የእምጴርጵር ወገን አድርገው ወረሳዎች እንደሚግለሉ ብለውኛል፡፡ በመጨረሻ ምዬ ተገዝቼ የሆነውን ነገሩኝ፡፡ የእስራረቱን ዘዴ ያመጣው "ድቂሱ" ነው አሉ፡፡ ድቂሱን አውቀዋለሁ፡፡ ጫት የሚታምበት ቤት ካንዴ ሁለቴ አይቼዋለሁ፡፡ ፈጣን፣ ቀዥቃዣ ስለሆነ ተቀምጦ እንኳን ሙሉ ገፅታውን ለማየት የሚያዳግት ነው፡፡ እይኑ፣ እፉ፣ እፍንጫው፣ ጆሮው… ሁለመናው በእንቅስቃሴ የተሰከቱ ናቸው፡፡ ሲያወራ ቃላቱ እጥብቆ ለመያዝ የሚያዳግት ፍጥነት አላቸው፡፡

እና … ድቂሱ እምጴርጵርን እጨናቸው፡፡ ሁልጊዜም አንድ ቦታ ቆመው ነው ወረሳን የሚዘልፉት፡፡ ድቂሱ እጢኖ፣ አውጥቶ እውርዶ አንድ ድምዳሜ ላይ ደረሰ፡፡

ተሆን ልምሖ ሜዳ ላይ ክር እሰረ፡፡ ክሩ ሜዳ ላይ መንጠቆ እንጠለጠለ፡፡

"ዛሬ ድቂሱ አሳ ሲያጠምድ ነው" ብለው ወረሳዎች ተዘባበቱ "እረ በክንቱ ወንዝ ዓሣ አለ እንዴ?"

የመሰላቸው ከፍጥነቱ የተነሳ አልተደመጠላቸውም፡፡ ብቻ ድቂሱ አንድ ቤት ተጠግታ የቆመች ስልክ እንጨት ታቅፎ ወደ ላይ ተሳበ፡፡ ጣሪያ ላይ ወጣ፡፡ ለካ እምጴርጵር ሲመጡ አይቶ የጠቆመው ኖሯል፡፡ እደፈጠ፡፡

እምጴርጵር ዘለፋቸውን የሚያከናውኑበት ጉብታ ተቆጣ ጠሩ፡፡ ድቂሱ ሰገግ ብሎ ከእናታቸው ያያቸዋል፡፡ እምጴርጵር ዘለፋቸውን ቀጠሉ፡፡ ድቂሱ እስሌቶ እስሌቶ ማስገሪያውን ጣል አደረገ፣ የእምጴርጵር ኮት ከፊት ዘጋ ትላለች፡፡ እስተካከላት፣ የውስጥ ኪሷ ላይ እንጣጥረ፡፡ ሰደደ፣ ቦርሳዋ እንደ ዓሳ እየተፈራገጠች መንዝዞ እወጣት፡፡



@BOOKALEM

## 22 - እሪ በከንቱዎች

ጀቢራ በሬን ቆርቁረው "መሪኛው" አሉኝ፡፡

"የምን መሪኛ ነው?" አልኳቸው

"ወሪሳዎች መሬ ነው ሲሉ ሰማሁ፡፡"

"ኧረ እኔ አገሬ መራቤቱ አይደለም"

"ቆንጨራ ይዘህ በመሮከርህ እንጂ መች በሀገርህ ሆነና፡፡ ይልቅዬ..." አሉ ወደ ውስጥ እየዘለቁ "ብቸኝነትህ ይበቃል፤ በአንድ ልብ ወሪሳዎችን ተቀላቀል፡፡"

"እኔ መች እንቢ አልኩ? ስተርብ መሰረቅ ነው፤ ስቀርብ መሰረቅ ነው፡፡"

"አይ ያንተ ነገር፡ እሾህን በእሾህ ሲባል አልሰማህም፡፡ ሰራቂ ብትሆን ማን ይሰርቅሃል፡፡"

"እንዴት፤ እንዴት?"

"ሌባ ሌባን አይበሊጠው፤ ምላጭ ምላጭን አይቆርጠው ሲባል አልሰማህም?"

በረጅሙ ተንፍሼ ዝም አልኩ፡፡

"ይኸውልህ፤ ወሪሳ ውስጥ እንደ እሪ በከንቱዎች እርስ በእርስ መጣቆስ የለም፡፡ ወሪሳዎች ግብሩ ከግብራቸው፤ ጠባዩ ከጠባያቸው ያልገጠመውን ነው የሚያጠቁ፡፡ ተደባለቃቸው፡፡ እለቱን መደባለቅ ቢያቅትህ ምሰላቸው፡፡"

"እሺ"

"ባል በርታ" ብለውኝ ሊወጡ ሲሉ...

"የአምጸርጽር ነገር እንዴት ሆነ?" አልኳቸው፡፡ መለስ ብለው...

"እንዴት ነው እንዴት ሆነ?" አሉኝ

"አልተመለሱም?"

"የእነሱን ነገር ተወው፤ የስብሰቱ እርሻ የጠብ መነሻ አሉ፡፡ ጠበቃ በነበረበት ጊዜ የቂሙ መዋጫ አድርገን ነበር፡፡"





"እንዴትም እንደቸኮሉ ባውቅም ቢያሟጡቱኝ ወድጃለሁና ነገር ማሰናሰሌን ቀጠልኩ፡፡

"ነገሩ ረጅም ነው፡፡ የእሱ አባትና የኔ አባት ደመኞች ነበሩ፡፡ ደመኝነታቸው በሌላ አይደለም የአምጸርጽር አባት ጠብ፡ ሁከት፡ ክስ... ይወዳል፡፡ ታዲያ ነጋ ጭቅጭቅ ነው፤ ጠባ ማመልከቻ ነው፤ ክስ ያስፈረደበትን የወሪሳ ሰው ተከርቸሊ ድረስ ሄዶ ሲላ መጥሪያ ይሰጠዋል፡፡

"በዚህ የኔ አባት እንጀታቸው ያራልና ሱታሉታውን ከወሪሳ መርጠው ሌት ወደ እሪ በከንቱ ይሰዳሉ፡፡ የሌላው ሳይነካ የአምጸርጽር አባት ቤት ወና ሆና ያድራል፡፡

"ሲደጋግም እንዲህ የሚያደርግኝ አባ ሰተቱ ነው ማለት ጀመረ፡፡ አባ ሰተቱ የእኔ አባት ናቸው፡፡ ጃንሆይ ድረስ የታወቁ፡፡ ይሄ የኛ ሰፈር ሰሙ አባ ንጠቀውም አልነበር?"

እራሴን በአዎንታ ነቀነኩላቸው

"ጃንሆይ በንጉሥ አገር የምን አባ ንጠቀው ነው? ቀይሩ ሲሉ ወሪሳዎች ሁሉ እኛ የምንወደው አባ ንጠቀው ነበር፤ ንጉስ ካልፈቀዱ አባ ሰተቱ ይባልልን አሉ፡፡ ይሄኔ አባ ወሪሳ ግልቃ ግብቶ ነው በራሱ ስም ያደረገው፡፡ ንጉሡም ተሳላ ናቸውና 'ተሰቴቴስ ወሪሳ ይኛላል' አሉ፡፡ በዚህ የትንሳ ከጉዶ ጋር ቂም እንደተዋረሰን አለን፡፡ ተአንገት በላይ ሆድ ለሆድ እየተዋወቅን እንክ-እንክ እንባባላለን፡፡ እቧ የወሪሳ የልጅ ልጅ አይደለች?"

"አዎ"

"ብቻ አንዱን ይገር አንዱን ሆነ እንጂ ጃንሆይ አባ ሰተቴን በደንብ ያውቋቸዋል፡፡ በወሪሳ በኩል ወደ ግምጃ ቤትም፡ ወደ ባንክ ዲ ሮማም ሲሄዱ ተዚሁ እኛ ደጅ ታስ ጥላ ሥር አረፍ ብለው ነው፡፡ ጃንሆይ ለሰበቡ ግምጃ ቤት፤ ባንክ ዲ ሮማ ይላሉ እንጂ የሚመጡት ተአባቱ ዘንድ ነበር ይባላል፡፡"

"ቂጭ ይበሉ" አልኳቸው ጀቢራን፡፡ ወሰድ መለስ በሚያደርግ ማመንታት ውስጥ ሆነው እሊጋው ጫፍ ላይ ተቀመጡ፡፡ "እሺ?" አልኳቸው፡፡



@BOOKALEM

"የኛ አባ ንጠቀው ሰፈር ነበር አላልኩህም? እሪ በከንቱ ደግሞ "መሸ በከንቱ" ነበር፡፡ የአምጻርጵር አባት ለአመሌ ማመልከቻውን አሰናድቶ አባ ሰተቴን ጉድ ልሰራው ነው ማለት አበዛ፡፡ ተው ቢሉት አልሰማም፡፡ ተአውራጃ ጠቅላይ ግዛት... ቢል ቢል አንቀበልም አሉት፡፡"

"ለምን?"

"እንዴ? ንጉሱ ተበቅሎ ወርደው የሚያናግሩትን ማን ሊዳኝ?" እንዲያ በከንቱ ክፍ ዝቅ ሲል በመሀሉ ማን ይመጣል ማርሻል ቲቶ፡፡"

"እሺ?"

"ጊዜው መጥፎ ነበር፡፡ የጎጃም ገበሬ አምጧል፣ የትግሬ ገበሬ አምጧል፣ የባሌ ገበሬ አምጧል፣ ሁሉም ግብር እንከፍል ባይ ሆኗል፡፡ ያላመጠውም ግብር እስቲጠየቅ አኩብኩቦ ነው ያለ፡፡

"እንዲያ ወዲያ ሰሞን ደሞ ልዑል መኮንን በመኪና አደጋ ሞተው ለተሰካሩ የተገኘው ሁሉ ሲገዛ፣ ሲቀቀል፣ ሲገነፈል፣ ሲባላ... የተረፈም አልተገኘ፡፡ እንግዲህ በዚህ መካከል ያ ቂናማ ፈርጅ ሲንከረፈፍ የመጣ ማርሻል ቲቶ መቼም ቅንጡ ነው፣ ያገኘውን አይበላ አይን ፈጥጥ፡፡

"ጃንሆይ ንባ በጅሮንድ ብር አምጣ ቢሉት እየተልሞሰሞሰ ዝም፡፡ "ምን ሆነሃል?" ቢሉትስ ኧረ ጉድ ሆነናል ጃንሆይ ምናምኒት የለም፡፡

"ባንኮ ዲ ሮማ አትሄድም ወይ?"

"ኧረ እዚያም የለ"

"በጉዱ ወጣሁ" አሉ አሉ ጃንሆይ፡፡

"እናስ ምን በጀን? ይሄ ነጫጭባ ሰማችንን ሊያጠፋው አይደለም ወይ?"

"አይን ፍጥጥ"

"ጃንሆይ ጊዜውን ያውቁታልና ወደ የትኛውም ገበሬ መልእክት አላኩም፡፡ በሉ ንሱ የአዲስ አበባ አጥቢያ ሹማምንትን ጥሩልኝ አሉ፡፡





"ሁሉም መጥቶ ተፈታቸው ተኮለኮለ፡፡ ለወሪሳም አባ ወሪሳ ስላልተገኙ አባ ሰተቴ ሄደዋል፣ ለመሸ በከንቱም የአምጻርጵር አባት አለ፡፡ ጃንሆይ እንዲህ ሆንን ሳይሉ በደፈናው ጠየቁ፡፡

"እንዴት ነው የመሬት ግብር የምትሰበስቡት? ለመሆኑ እጃችሁ ላይ ምን ያህል ብር አለ? የንላው አጥቢያ ሹም ታንተ ይጀመር"

"የንላው ተነስቶ ስምንት መቶ ጎላ ሰብስበን ነበር ለልዑል ተዝካር ለመቀቀያ ይፈለጋል ተብሎ አስገብተናል፡፡"

"በል ተወው ቁጭ በል፡፡ የተረት ሰፈሩት?"

"እኛም የተገኘውን ተረት ማሰባሰቢያ እናውላለን፡፡ ገንዘብ ዛሬ ቢጠፋ ነገ ይገኛል፡፡ እንደዜ ተጠፋ የማይገኝ ተረት ነው አይደለም?

"በል ተወው ቁጭ በል፡፡ ዶሮ ማነቂያ?"

"ኧረ እኛም ተቸግረናል፡፡ እናት እናት ዶሮዎቹ ተወስደው ሚስቶቹ ቀርተዋል ምን እናድርጋቸው ስንባባል ነው የተጠራሁት፡፡"

"ቁጭ በል - አሮጌ ቄራ?"

"ያንኑ ሰባ ሰንጋ እያንከላወስን ነበር ያለነው፡፡ ሁሉንም ለልዑሉ ተዝካር ቤተመንግስት አስገብተን....፡፡

"ጃንሆይ ተከዙ ጭንቅላታቸውን ይዘው እንዳቀረቀሩ....

"ኧረ አልተጠራንም?" አለ አባ ሰተቴ ቤቱ ጉም፣ ጉም፣ ጉም፣ አለ፡፡

ጃንሆይ ቀና ብለው "ማነህ አንተ?" አሉ፡፡

"አባ ሰተቴ ነኝ ጃንሆይ"

"አንተንስ አልዘነጋንም፣ አውቀን ነው፡፡ የምታስተዳድረውን እያወቅን ተየት አምጣ እንልሃለን?"

"እዳሪ ያረሰ ለልጁ አነረሰ ይባል የለም ወይ ጃንሆይ

"እንዴት? እንዴት? አሉ ጃንሆይ

"ነገር አበዛሁብዎ ጃንሆይ ለማንኛውም እኛ ዘንዳ ስላሳ ሺህ ጠገራ ብር አለ፡፡"



@BOOKALEM

"አይደረግም"

"እ-ይ ጃንሆይ ኩራትና ሀብት አይገኙ አንድነት ይባላል።"

"ቤቱ እርጭ አለ። ጃንሆይ ራሳቸውን ይዘው አቀረቀሩ። የሚገርም እኮ ነው። አሁን ምን ይሁን ነው የምትል አባ-ሰተቴ? አሉት።

"ብሩ ተርሶ ዘንድ ባደራ ይቀመጥልን። ይሄን ተባሬ ነገ እንነግርዎታለሁ ስል" አለ አባ-ሰተቴ። ጃንሆይ ብር እንደቸግራቸው የገባው እሱ ብቻ ነው።

"ብል እሱን በኋላ እንመከርበታለን። እኛ የአንተ ብር አስቀማጮች ነን? ልብ ለልብ ተዋውቀው ፈገግ ተባባሉ

"ጉባኤው ሲያበቃ አባ ሰተቴን ብቻውን አስቀርተው "ብሩን እኛ ግምጃ ቤት አስገባ። ጊዜ ሲተናልን እንመልሳለን። ብድር ነው አሏቸው አሉ።

"አባ ሰተቴ ፈገግ ብለው

"ጃንሆይ፤ እኔም የሀገሬ አደራ አስቀማጭ ነኝ። አበዳሪም ተበዳሪም የለም። ሁሉም ባለአደራ ነው" አሏቸው ይባላል።

"ጃንሆይ እርግጥ፤ እርግጥ አሉ

"የእኔ ነገር አንዱን ይገፍ አንዱን አይደል? የእሪ በከንቱዎቹን ሳልነግርህ። ጃንሆይ አይናቸውን እየማተሩ

"ተሆንስ ሆነና" አሉ ተሆንስ ሆነና መሸ በከንቱዎች ወካያቸውን ለከዋል?

"አዎ ጃንሆይ" አለ የአምጳርጵር አባት።

"ዛሬ ችሎት የለህ ሆኖ ነው? አሉት ጃንሆይ ቤቱ ሁሉ አውካካ። በነገረኝነቱ ወጋ ሲያደርጉት ነው።

"አንተስ እንዴት ነው?"

"ገንዘብ እግር አብቅሎ ቁልቁል ሲወርድ እያዩት ጃንሆይ" አይልም።

"ልብ ያለው አንቆ አስቀረዋ። እናንተ መሸ በከንቱዎች አይናችሁ ከነገር፤ እጃችሁ ከበትር አይቦዝን። እንዳው እሪ በከንቱ አሏቸው።





"እለቱን ሰፈሩ እሪ በከንቱ ተብሎ አደረ። እንግዲህ ተዚያ አንስቶ ፊት አባቴ፤ አሁን ደሞ እሱ ነክሰው ይዘውናል። የወሪሳ ሰው ወጥቶ ባይገባ ደስታቸው ነው። ታዲያ አንተም ወሪሳን አልፈህ እሪ በከንቱ ስትሄድ ከጠላት ቆጥረንህ ነበር። በኋላ እውነቱ ተገለጠልን።"

ጀቢራ ከቤት ከወጡ በኋላ ቤቱን ፈተሽኩ፤ ኪሴን አሰስኩ፤ ምንም የጠፋኝ አልነበረም። በዚሁ ወሪሳዎችን ተቀላቅዬ ከወሪሳዎች እንደ አንዱ እንደተቆጠርኩ አወኩ።

## 23 - ጅማሬ

ጠዋት ደጃፌ ተቆርቁሮ ስከፍት አንዲት ግርንድስ ሴት ቆማለች። እራሴን አስጨንቄ ማን እንደሆነች አወኩ። የአምጳርጵር ልጅ ናት።

ምኗም አምጳርጵርን አትመስልም። ትከሻዋ እንደ ቋጥኝ የተከመረ ነው። ጡቶቿ እንደ ግሬደር ከባድ ነገር ከፊቷ ገለል የምታደርግበት መጋፈያዋ ይመስላል።

"አወከኝ?" አለችኝ።

እራሴን ወዘወዝኩላት። ይቺን ሴት አምጳርጵር እንዴት ልጀ ብለው ተቀበሉ? በማለት እያሰብኩ ነበር። ምልናባት የጀቢራ ልጅ ብትባል ያሳምን ይሆናል። አምጳርጵርና ጀቢራ የሚናከሱት የእሷን ልጅነት በየልቦናቸው ይዘው ይሆን እንዴ?

"ምነው? በደህና?" አልኳት

"አባዬ ይሄን ስጪው ብሎኝ ነው" አለች።

አምጳርጵር ተኩራርተው የሚቀመጡበት መዳፍ ባለው ቀኝ እጁ የተቋጠረ ጎድጓዳ ሰሀን ይካለች። እሷ ጋ ሆኖ ትንሽ የመሰለኝ ወደኔ ሲዛወር ከበደኝ።

"ምንድነው?"

"ትናንት ማህበር ነበር። ቋጥረና ውሰጂለት አለኝ።"

"አትገቢም?"

"አ-ይ አባዬ ይገድለኛል።"

የተሽኮረመመች መሰለኝ። ግቢ ያልኳት ለምን መሰሏት ይሆን?

"አባዬ እንዳለ፣ መቼም የጦር ታልኪዳናችን እንዲ ፈርሷል። ምነው በአባትንት እንኳን አልጠየቅም ወይ?"

"እመጣለሁ፣ ኧረ እመጣለሁ" ጎድጓዳ ሰሀኑ እጄን ሊገነጥለው ደረሰ።

እየተሽኮረመመች ፊቷን አዙራ ሄደች። መሬት የተንቀጠቀጠና የተንቀረቀበኩ መሰለኝ። እንድ እግሯን መሬት ላይ በደንብ መትከሏን ካረጋገጠች በኋላ ሌላኛው እግሯን ስለምታነሳ፣ ስትራመድ እጅግ ትዘገያለች።

"እችን ልጂ ማለታቸው እምጳርጽር ተሸወዱ" አልኩ።

የልቤን የሰማች ይመስል ዞር አለች። ደነገጥኩ። ፊቷ ላይ ግን መሽኮርመም እንጂ መታዘብ አላነበብኩም።

## 24 - አዲሲቷ ወሪሳ

እምጳርጽር የላኩልኝን ቋጠሮ ወሪሳዎች ጫት የሚቅሙበት ቤት ሄጄ ፈታሁት። አልጫና ቀይ የበግ ወጥ ነው። በጠዋት ጫት የጀመረው ወሪሳዊ ሁሉ እየተጉመጠመጠ ገባበት። ሁሉም እንደ ባህሪው እበላሉም ይወሰናል። ድቂሱ ከምኔው ጠቅልሎ ከምኔው እንደጎረሰ ለማጤን የሚከብድ ፍጥነት አለው። ሸከክ በዚህ ጠቅልዬ እንዲህ አድርጌ እንበቼ እንዲህ ብጎርስ እያለ ከቆየ በኋላ የሚተገብር ይመስላል። ከማውቃቸው ውጭ በቅጡ ያልተግባባኋቸውን እንኳን በአባባላቸው ባህሪያቸው ለመገመት ችያለሁ። ለምሳሌ "ፈላስፋው" የሚሉት ወጣት በአንድ እጅ ጎርሶ በአንድ እጁ ፂሙን እያሻሸ ይመሰጣል። ያለው ድባብ ያስፈራል ሁለት ያህል እንደጎረሰ ተነሳ።

"ፈላስፋው አትበላም?"





"ቢቃ፣ ለመኖር ብቻ"

እንዲጋመሰን እንዷት ወንድ የምትመስል ሴት ገባች። ወንድ ያስመሰላት አለባበሷ ነው። መልኳ ለትም ያለ ቆንጆ "ሙፍን እኛንም ምሰይ" አሏት፣ ተተሳተለችን። አለባበሷ ብቻ ሳይሆን አበላሏም የወንድ ነው።

"ሴሽ አላችሁ?" አለች፣ ሙፍን

"ሴሽ" ሲጋራ መሆኑን ያወኩት ድቂሱ አውጥቶ ሲሰጣት ነው።

የአዲሱ የወሪሳ ትውልድ በቅጡ የማይገቡ ቃላቶች አሉት። ባእድ እንዳይረዳ ሲፈለግ ጠመዝማዛ መንገድ ያለው ቋንቋ ይጀምራል። ስለዚህ መፍትሄ ሆኖ ያገኘሁት ቃላቶቹን ከሸክኮ ላይ መማዛት ነበር። በቃላት አሰር ሳንቲም ከመቶ በላይ መዘገብኩ። መከከላቸው ሰገኝ ወረቀት የማገለበጥ መሰዬ ከቃላት መፍቻዬ ላይ እገናዝባለሁ።

የመጀመሪያ ቀን ምግቡን በሉተን እንደጨረሰን ወንዳ ወንዷ ሙፍን ሲጋራዋን እየሳበች

"ቶማር ነው እንዴ?" አለች። (ሰላይ ነወይ ማለቷ ነው)

"ኧረ ምልምሎ ነው" (አዲስ የወሪሳ አባል ነው)

"ተቅሟል?" ጠየቀች (ተቀፍሏል?)

"ናሙና ናሙናው ነው" (በደንብ አልተቀፈለም)

"ይገረብ?" (በደንብ ሊቀፍለው?)

"ይመችሽ" (ትችያለሽ)

"ተንፍቶበታልንዴ" (ፈዛዛ ነው?)

"ኧረ መሬ ነው"

እዚህ ላይ አባባ ጀቢራ "መሬኛው" ያሉኝ ትዝ አለኝ። ከመተርጎሜ በፊት ገባኝ። ነቃ አልኩ።

"ጀለሴ (ጎደኛዬ) ተጫወት" አለችኝ።

"እሺ" አልኳት። ቆንጆ ወንድ ትመስላለች። ለመልኩ ግድ የሌለው።

"ሟቹ ሰሀኑን አጠብለታ" አለች፡፡

ሟቹ ቀን የጠመመበት ወሬሳዊ ነው፡፡ የሌብነት ዛር የሞተበት፡፡ ስለዚህ በጉልበቱ እያገለገለ እራሱንና ሱሱን ይችላል፡፡ ቅርም ሳይለው ተነስቶ ሰሀኑን ቋ ውጣ፡፡

"ትምሮ ኔፓ ነው?" አሁንም ጠያቂዋ እሷ ናት፡፡ ከመልሳቸው ምን እንደጠየቀች ገባኝ፡፡

"ኧረ አስተማሪ ነው"

"ምንድነው የምታስተምረው?"

"አማርኛ" አልኳት፡፡

"የሚከይፍህ ምንድነው?"

"እ?"

"ዝንባሌህ፡ ተሰጦህ ማለቴ ነው" አለችኝ፡፡ ስታወራ እንደራፐሮች ያደርጋታል፡፡ ፊቷ ወዝ አልባ ይሁን እንጂ አይኖቿ ስትስቅ እየተጨፈኑ የደስ ደስ አላብሰዋታል፡፡

"ማለት?" አልኳት

"የሚከይፍህ ፊልም ነው? ማንበብ ነው? ሙዚቃ ነው? ምንድ ነው?"

ሌሎቹ ፀጥ ብለው የፌቱት ሜት ላይ ተጥደዋል፡፡ "ተረት" አልኳት ሳላስብበት፡፡ ጅል መሰዬ እታያት ይሆን?

ሁሉም ሳቁ፡፡ ፈላስፋው ብቻ የሊለ ያህል በራሱ ተመሰጧል

"አይገርምም? እኔም ተረት ይከይፈኛል፡፡"

ተበረታታሁ "ወደፊት የተረት መፅሀፍ ማሳተም እፈልጋለሁ" አልኳት፡፡

"ግሬ" አለችኝ እጇን ጨብጣ፡፡ ገጨሁ፡፡ ለዚህ አልሰነፍኩም፡፡ "እኔ ጋ ያለውንም አንድ ላይ አድርገሽ ታሳትሚዋለሽ፡፡ ይመችሽ" አለችኝ፡፡





"እሺ፡ አመሰግናለሁ"

"ብቻ አሁን እናፋፍመው"

"ምኑን?"

"አረንጓዴ ሽብሩን ነዋ"

ግራ ተጋባሁ፡፡ ካስተረጎምኩ በኋላ ነው ሜት እንቃም መሆኑን ያወኩት፡፡

"ፍሙም ይላክ"

ያለችው ስላልገባኝ ወደ ሽኩኩ ዞሬ አየሁ፡፡

"ሜትና ሲጋራ ላክና ተረቱን ትነግርሃለች" አለኝ፡፡

ሟች ሰሀኑን አጥቦ ሲመለስ ሃምሳ ብር አውጥቼ ሰጠሁት፡፡

"እንደቻለ" አለችው፡፡ (በሁሉም ግዛበት ማለት እንደሆነ ያወኩት በኋላ ነው)

## 25 - የተረት እናት

ሜቱ ተገዝቶ ጥቂት ቃም-ቃም እስኪታደርግ ጠብቄ፡-

"በይ ተረቱን" አልኳት፡፡ ሁሉም ሳቁ፡፡ አሁንም ፈላስፋው ከኛ ጋር አይመስልም፡፡ የተጃጃልኩ መሰለኝ፡፡ እሷ ግን ፈገግም ሳትል፡-

"ደብተር ላክ፤" አለችኝ፡፡ "ሁሌ ቲቸር አይደብርህም? አንዳንዴ እንኳን" አጉረመረመች፡፡

ልጆቹ መሳቃቸውን ቀጥለዋል፡፡

"በመልሱ ይምጣ" አልኩ፡፡

"ችሏል፡ ሌላ ብር ስጠው፡ ሟች ና ግዛለት" አለች፡፡

አስር ብር አውጥቼ ሰጠሁ፡

"በተረፈው ሲሽ ሽምትበት" አለችው፡፡

ደብተሩ መጣ፡ 16 ሉክ፡፡ አሁንም መልስ የለም፡፡

"እስክሪፕቶ ምናምን ይገዛልሀ ጀለሴ?" አለችኝ፡፡

"አለኝ" አልኳት፡፡



@BOOKALEM

ሳቁ አልተቋረጠም፡፡

"ሄፍ" አለችና ቀጠለች፡፡

"አንድ ወሪሳዊና አንድ የእሪ በር (እሪ በከንቱ) ልጅ ጀለሳሞች ነበሩ..."

"ጀለስ?" አልኳት አቋርጬ

"አዎ፣ ጓደኛሞች" አለች፡፡

"ጀለስኮ በእንግሊዘኛ ምቶኛ ማለት ነው"

"እኛ እያወራን ያለነው በወሪሳኛ ነው"

አሁንም ቤቱ አውካካ

"እነዚህ ጀለሳሞች ከእለታት አንድ ቀን ገበያ አብረው ወጡ፡፡"

"እሺ"

"ወሪሳዊዋ በዚያውም ቢዝነስ ልታፋፍም (ልትሰርቅ) ነው የወጣችው፡፡ እሪ በሯ አልባንንችም (አላወቀችም)"

"እሺ"

"እሪ በሯ ገዛዝታ ልትሄድ ስትል ወሪሳዊቷ ትገግምና ያየችው እቃ ላይ ሁሉ ሙጎት ትገጥማለች፡፡ ሰንት ነው? ምናምን? እስኪ ለኪው እያለች ሻጩንም እሪ በሯንም እያደናገረች ትሸምቃለች (ትሰርቃለች)"

"እሺ"

"ከዚያ ከገበያ ሲመለሱ እሪ በሯ ምርር ብሏት 'ሁሉ እማረሽን ገበያ አታውጪት' የሚለውን ተረት ለመጀመሪያ ጊዜ ፈበረከችው፡፡"

"እ?" አልኳት ተገርሚአለሁ፡፡

"ሁሉ እማረሽን ገበያ አታውጪት ሲባል ሰምተህ አታውቅም?"

"ኧረ አውቃለሁ፡፡"

"ብቃእ ያቺ እሪ በሯ ናት የፈበረከችው፡፡"





"ለዚህ ነው እንዴ?"

"አዎ፣ ጻፈው እንዳትረሳው"

"የሚገርም ነው፡፡" ጻፍኩት፡፡

"የወሪሳዋ ምን ብትላት ጥሩ ነው?" ጠየቀችኝ

"ምን አለቻት?"

"የእሪ በሯ ተጠቂራ የለ?"

"ምን?"

"የወሪሳዋ በሸመቀችው የእሪ በሯ ሌባ ተብላለች አይደል? ሌላ ቀን መጥታ ገበያ እንሂድ ስትላት፡፡"

"እ?"

"ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ" ስትል ተረት ፈበረከችባት፡፡"

"ለካ ለዚህ ነው?"

"አዎ፣ ጻፈው፡፡ ባይዘቄይ (በነጋራችን ላይ) የወሪሳዋ የእኔ እናት ናት፡፡"

"እውነት?"

"ገብርኤል ቆማጣ ያድርገኝ"

"ኧረ ጠላትሽ" ጻፍኩት፡፡ አሁን እኔ የአማርኛ አስተማሪ ነኝ? ይቺ ልጅ የምታውቀውን ከላወኩ ምኑን አስተማርኩ? በዚህ ላይ ለዛዋ፤

"እዚህ ከላም የምታደርገን (የምታየን)..."

"እ?"

"የተረታሞች ልጆች ነን፡፡ "አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ" ይባላል አይደል? ሰምተሃል?"

"አዎ"

"የድቄስ አያት በበሉት ነው በአይጥ የተሳበበው"

"ይገርማል"

"ጻፈው" ጥቂት በሲጋራ ጭስ መካከል ዋኘታ ስታበቃም "ይሄን ተረት ሰምተኸው ነበር?"

"የቱን?"

"አንድ ሰውዬ የበግ ቅልጥም ግጦ"

"እሺ?"

"የውስጡን..."

"መቅኔውን?"

"አዎ፣ እሱን ለመብላት ብዙ ለፋ።"

"እሺ" ቋንቋዋ ለእኔ እንዲመጥን እያቀለለችው እንደሆነ ገብቶኝ ተገረምኩ።

"ከዛ የቅልጥሙን ጫፍ ቢጎረጉር፣ ቢጎረጉር የውስጡ አልወጣ አለው። ይሄን ተረት አልሰማህም?"

"ኧረ ሰምቻለሁ፣ በተሰበረበት በኩል ወደ አፉ አስገብቶ ወደ ውስጥ በጣም ሲስበው መቅኔው ሳያጣጥመው ዘሎ ወደ ሆዱ ገባ።"

"ከዛ ምን አለ?" ጠየቀችኝ

"ለእኔ ባይልሽ ነው አለ።"

"ይሄ ፌክ (ሀሰተኛው) ነው። እውነቱ ግን ሰውየው አይኑን ጨፍኖ ወደ ውስጥ ሲስበው መቅኔው ከአጥሉ ላይ የጠለፉት አባባ ጆቢራ ናቸው። ከዛ አሳቸው ጥጥ ሲያደርጉት 'ሰውየው ለእኔ ባይልሽ ነው' አለ።"

"ይገርማል። መዘገብኩ።"

"ሽኩኮ አያት ደግሞ" አለችኝ

"እ?"

"ሊሞቱ ሲያጣጥሩ ነፍስ አባት ተጠራላቸው። እየተናዘዙ እንዳለ ቺካቸው (ሚስታቸው) መጥተው በጆሮአቸው "ምኑን ሞቱት" አሏቸው።

"እንዴት?" አሉ

"የከፈን እንኳን የለ"

"እንቺኮ..." አሉ

"ሙቱ ስሎት"

"ጉድ ሆንኩ በይኛ" አሉና ወዲያው ድምፃቸውን አጥፍተው መናዘዝ ቀጠሉ። የነፍስ አባትየውም ሰላልተሰማቸው ጆሮአቸውን





አፋቸው ላይ ሲለጥፉ ከቄሱ ግራ ኪስ ገንዘብ አጨናግፉ (ሰረቁ) ቺካቸውን ጥሩልኝ ብለው በሽሉ (ደብቀው) ሰጧቸው። ቄሱ ጻዊታቸውን ሲያወጡ ሲሉ ግራ ኪሳቸው ውስጥ የነበረው ብር የለም። ቢደነግጡም ተጠራጥረው ዝም አሉ።

"ትንሽ ቆይቶ የሽኩኮ አያት ቺክ (ሚስት) መጡና "ምኑን ሞቱት" አሏቸው

"አሁን ደሞ ምን መጣ?"

"ብሩ አይበቃም"

"እንቺኮ..." አሉ

"ሙቱ ስሎት"

"አሁንም የሽኩኩ አያት ድምፃቸውን አሰለመሰሙ። ኑዛዜው አልሰማቸው ያለው ቄስ ሲጠጉ ቀኝ ኪሳቸው ውስጥ ሰተት አሉ። ሌላ አጡ። እጃቸው መስተል ይዞ ወጣ። ቺካቸውን ፖሽሬው (ሽጪው) አሏቸው።

"ቄሱ ከኑዛዜ በኋላ አሁንም ቀኝ ኪሳቸውን ሲፈትሹ መስቀላቸውን ተቀጥተቀዋል (ተሰርቀዋል) ምን ቢሉ ጥሩ ነው?

"እ?"

"የግራው ሲገርመኝ ቀኙን ደገመኝ"

"እሃ- እሃ- እሃ" አልኩ

"በዛው የቄሱ ንግግር ተረት ሆና ቀረ"

"ይገርማል"

ቤቱ ሁሉ በመሳቅ ላይ ነው። በዚህ መካከል በየት እንደወጣ ያላየሁት ሽኩኩ የያ ብር ፊቴ ላይ ደንቅሮ፣

"ሃያ አምስት ብር ተድሯል(ተሸጧል)። አምስት ብር የደላላ ተቆርጧል" አለኝ

"ምኑ?"

"ሰሀኑ ነዋ"



@BOOKALEM

በደብተሩ ፊቴን ሸፍኜ ቀረሁ፡፡ እምጳረጵር፣ የእምጳረጵር፣ ይጳረጷር ዘንድ... አባቴ የተሸፈነ ፊቴ ላይ ጭራውን ወንጨፍ አደረገ፡፡

## 26 - ትውልድ

በጠዋት ወደ ሥራ ለመሄድ ሳከበኩብ እማማ ጉደ አፋፊም ፊት ይዘው ድቅን አሉብኝ፡፡ ያኔ በቆንጨራ እሳቸውና የልጅ ልጅ...ልጃቸው ላይ ከዛትኩ ወዲህ ቀርበውኝ አያውቁም፡፡

"ደህና አደርክ?"

"እግዚሀር ይመስገን" አይኔን ወጠርኩባቸው

"እንደው ላስቸግርህ..." እያሉ የይስሙላ ከተሽኮረመሙ በኋላ "የልጅ ልጅ.. ልጄ ቄስ ትምህርት ሊጀምር ነበር"

"እና?"

"የምከፍለው አጣሁ..."

"እና?"

"ያኔ ለእርጥቡ ሱሪ ማስመለሻ አስር ብር አበድሬህ ማለቴ ለሽኮኮ ከፍዬ..." ዝም አሉ፡፡

እሳቸው ብቻ ያጃጃሉኝ ይመስል እንዲህ ማምረሬ ተገቢ እንዳልሆነ ገባኝ የተወጠረ አይኔን እርግቤ..

"እውነት ማሙሽ ትምህርት ሊገባ?" አልኳቸው፡፡

"አዎ" አሉኝ እንኳን ደስ ያለህ በሚል ቃና

"ገና ልጅ አይደለም እንዴ?"

"ቢሆንም ፊተኛ በስኋል?" ዘና ማለት እየከጀላቸው መለሱ፡፡

"እሱስ ልክ ነው፡፡ ለመሆኑ የት ትምህርት ቤት ሊያስገቡት ነው?"

"እዚሁ ወሪሳ ቄስ ተማሪ ቤት"





"ወሪሳ ቄስ ትምህርት ቤት አለ እንዴ?"

"እንዴ፣ ያውም የኖረ ነዋ፡፡ አልገፋንበትም እንጂ እኛ ሁሉ እዚያው ፊደል መቁጠር ጀምረን ነበር፡፡"

"እውነት?" ትምህርት ቤት ሲባል ልቤ ይቆማል፣ የመምህር ነገር ለማየት ጓጓሁ፡፡ "ለመሆኑ ምኑ ጋ ነው?"

"እዚህ እላይ ወይራው የለም?"

"አዎ"

"ከሱ ጥቂት ሄደት እንዳልክ ከቦኖ ውሃው ወደ ውስጥ ገባ ብሎ፡፡"

አስር ብር አውጥቼ ለእማማ ጉደ ሰጠሁና ወደዚያው አቀናሁ፡፡ ትምህርት ቤትና ተረት ሲሉኝ ለምን ልቤ እንደሚቆም እንጃ፡፡ ከዚህ ቀደም እንዴት እንዳልሰማሁ አልገባኝም እንጂ ገና ቦኖ ውሃው ጋ ስደርስ የልጆቹ ጫጫታ ተሰማኝ፡፡ ሰበአ-ሰገሎች ኮከቡን እየተከተሉ እንደሄዱ እኔም የውሪዎቹን ድምፅ እያዳመጥኩ ደረስኩ፡፡

ትምህርት ቤቱ ዙሪያውን በሳጠራ ግድግዳ ተከብቦ ሲታይ ትልቅ ቅርጫት ይመስላል፡፡ ዞር-ዞር ስል ፊት ለፊት "የወሀዴድ ጽ/ቤት" የሚል ፅሁፍ አነበብኩ፡፡ በሩ ዝግ ነው፡፡ ወደ ቄስ ትምህርት ቤቱ፤ መምህሩ ልጆቹ ፊት ቆመው "ማነው ጭራዬን የሰረቀ?" እያሉ ይጠይቃሉ፡፡ ብዙ ጭቂም ልጆች ቁሱን እያዩ ዝም ብለዋል፡፡

"ማነው ኀበዝ ልጅ የሰረቀኝን የሚነግረኝ?"

ዝም

"የሰረቀኝን ይሄን እሸልመዋለሁ" ብለው ከኮት ኪሳቸው ውስጥ ጥቂት የተንካለት ሽልጦ አወጡ፡፡

ሲባው ሀፃን አሳዘነኝ፡፡ እኔ ልጅ ሳለሁ እንኳን የሰረቀ ትምህርት ቤት አልሄድም ያለ እንዴት በአለንጋ ይገሳቆል እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡

አንድ አይኑ ፈጣጣ ትንሽ ልጅ "ይኸው እኔ ነኝ" ብሎ ጭራውን ከፍ አደረገ፡፡



@BOOKALEM

"ና ውጣ እዚህ" አሉት፡፡

ልጁ ወጣ፡፡ ቄሱ እናቱ ላይ እጃቸውን አስቀምጠው

"አይ ልጅ፡ አይ ልጅ" አሉ "አንዴ አጤብጭቦለት... ድገሙ... ሰልሱ... ይበቃል፡ ይበቃል፡፡ አያችሁ ይሄ አንድ ፍሬ ማቲ ከእኔ ካዛውንቱ በልጦ ከዚህ ቀደም ዘጠኝ ጊዜ ጭራዬን አንድ ጊዜ ዳዊቴን፡ ሁለት ጊዜ ጥምጥሜን ሰርቆኛል፡፡ ይኸው ዛሬ ደሞ ተንከርፍፎ በማየቱ ዝንብ እያባረርኩ ከእጄ ላይ ሲሰርቀኝ አላወኩም፡፡ መቼም ግሩም ጥበብ ነው፡፡ ያዝልቅለት፡፡ እናንተም ከእሱ ብዙ ትማራላችሁ፡፡"

ተምታታብኝ፡፡ ቄሱ ለልጁ ቃል የገቡትን ገማጣ ሽልጦ ሰጥተው ወደመቀመጫው ከሰደዱ በኋላ መፌክር እንደሚያወጣ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፡-

"የተንከረፈፈ" አሉ

ልጆቹ በአንድ ድምፅ "ተዘረፈ" አሉ፡፡

"እያያዙን አይተው" ቀጠሉ ቄሱ

"ጭብጠውን ቀሙት" ተማሪዎቹ

"የዘንጋ" ቄሱ

"ተወጋ!" ተማሪዎቹ

"ቤታቸውን ሳይዘጉ"

"ሰውን ሌባ ይላሉ!"

"አባቱ ዳኛ" ቄሱ

"ልጁ ቀማኛ!"

"የማንከሪያ ልጅ"

"መላፊያ"

ቀስ ብዬ በመጣሁበት አኳኋን ተመለስኩ፡፡ የቄሱና የህፃናቱ ድምፅ ረጅም መንገድ ድረስ ተከተለኝ፡፡

"የሮጠ!"

"አመለጠ!"

"የቆመ!"





"ቀሰጠ!"

እማማ ጉዱ የልጅ ልጅ--- ልጃቸውን ፊደል አስይዘው በአጠገቤ አለፉ፡፡

"ወዮልሽ ወሪሳ" ማለት አሰኘኝ... "ይህን በማድረግሽ እጅግ በድያለሁ አሁን ግን ታላቅ ስንፍና አድርጌያሁና የባሪያህ ሐጢአት ታስወግድ ዘንድ እለምናለሁ የምትይበት ቀን እነሆ ቀርቧል..."

የነቢያት ቁጣ በላዬ ላይ ነደደ፡፡ ኃይል ቢኖረኝ ኖሮ ቤተ እግዚአብሄር አፀድ ውስጥ እንደተገኙት እርግብ ነጋዴዎች ወሪሳዎችን ስለልጆቻቸው ፈንታ ከነቤታቸው በመነቃቀርኳቸው ነበር፡፡

"ወዮልሽ ወሪሳ"

ወሪሳን እንደለቀቅሁ ከየት መጣች ያላልኳት ጭፍን ፊቴ ላይ ገጭ አለች፡፡ ደነገጥኩ፡፡ ፀጉሯን እንደማከክ እያለች ጭንቅላቷን ግራ ቀኝ በቀስታ አማታች፡፡

"ጠርሮብኛል" አለችኝ፡፡

የወሪሳ ቃላት አበሳ ሆነውብኛል፡፡ በየቀኑ ከሽኮኮ ሃምሳ ሃምሳ ቃላት እገዛለሁ፤ አዳዲስ ቃላት መፈልፈሉ አልቆመም፡፡

"ምን?"

"ቸስቻለሁ(ቸገሮኛል)"

"እና?"

"ሰው እርገኝ"

"እ?"

"ሊቀቅብኝ"

"ምንድነው የምትይው?" ገንዘብ ስጠኝ እያለች እንደሆን ገብቶኛል፡፡ እንዳልገባኝ ሆኜ የማረም ፍላጎት ደግሞ አድሮብኛል፡፡

"ትንሽ ፍሊስ (ፍራንክ) ግፋልኝ(ስጠኝ)"

በቅፈላ ጊዜ አይኖቿ መሬት መሬት እያዩ ይቅለሰለሳሉ፡፡ የትምህርት ቤት ሰዓት ስለደረሰብኝ ለመገላገል ድፍን አስር ብር



@BOOKALEM

እውጥቼ ሰጠኋት፡፡ ከፊቱ ዘወር አላለችም፡፡ በአባቷ ላይ እንደምትሞላቀቅ አይነት እያረጋት...

"ይሄን ምን አደርገዋለሁ? ባይሆን እንደ እዳ ይያዝብኝና አስር ብር ጨምርበት"

ምን እንደሆን አላውቅም ደስ ብላኛለች፡፡ እንደሚያጥረኝ እያወኩ እውጥቼ ሰጠኋት

"ግጭ" አለችኝ ነቃ ብላ

ገጨኋት

"ዛሬ ከዘነበልኝ እንቺ ላይ አካፋብሻለሁ" አለችኝ፡፡

"ይመችሽ" አልኳት፡፡

በጽንጽዬ ደስ የሚል ሳቅ ሳቀች፡፡ አይናፗ ተጨፈኑ፤ ደስ የሚል ስሜት ለአፍታ ጎብኝቶኝ ሄደ፡፡

"ግጨው"

ገጨሁ "ተረቱንስ?" አልኳት

"ከዘነበልኝ ማታ እየተሜሜስን..."

"ግዴለም ለኔ ይዘንብልኛል"

"ቢዝነስ(ሌብነት) ጀመርሽ?" አለችኝ

"አይ ሞዴል?..."

"ምንድነው እሱ?"

"የመስሪያ ቤት ብድር ..."

ደስ ያላላት መሰለኝ፡፡ የሰጠኋትን ሃይ ብር እየዘረጋች "እኔ ከሌላ ቦታ እፈልጣለሁ አንተ ያዘው፤ ጨምዴ(እቃ ማስያዝ) ከምትገባ" አለችኝ፡፡

"አራዳ ገገማ አይደለም፡፡ በይሉኝታቢስነት አይተዋልም" ሲባል እሰማ ነበር፡፡ አሁን አረጋገጥኩ፡፡

"ግዴለም፤ እሱንም ብወስድም መበደሬ አይቀርም፤ ያዥው" ብያት ተለየኋት፡፡" ከበስተኋላዬ እንደምታየኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡ የአምጸርጽር ልጅ ስታየኝ የተሰማኝ ሽግግር ያለ ስሜት በጭፍን ላይ የለም፡፡ ለምን?





ስለትምህርት ቤት ህይወት

* * *

ሞዴሉን ጠዋት መጨረስ አልቻልኩም፡፡ ዘወትር ደሞዝ መዳረሻ ላይ እንደማደርገው የተረት ቋጠሮዬን ፈትቼ እንደጥሬ መቆርጠም ጀመርኩ፡፡

በምሳ ሰዓት ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ውዬ ካልበላሁ ጭፍን እንዳለችው "እንዴጠረረብኝ (እንዳጣሁ) ይባንናል(ይታወቃል)፡፡" ስለዚህ ወከ እያደረኩ(በእግሬ) ወረሳ ደርሼ ለመመለስ ወሰንኩ፡፡

ወረሳ በዚህ ሰዓት ጭር ትላለች፡፡ ወረሳውያን ከተማዋን ካስተናገዱ በኋላ ነው ለምሳ የሚሰባሰቡት፡፡ እማማ ጉዶ ብቻ በር ላይ ቁጭ ብለው ድፍን ምስር ይለቅማሉ፡፡

አቤት ምላ ያለኝ ይመስል ተጣድፌ ገባሁ፡፡ ዛሬ ገና ወና ወና ሸተተኝ፡፡ ስለራበኝና የምግብ ሽታ ስላነፈነፍኩ ይሆን? እንዲነፍስበት በሩን ከፍቼን ትቼው አሲጋ ላይ ተቀመጥኩ፡፡

"እሺ፤ ተረት አምጣ" አልኩ እራሴን "ምላ የለም፤ ተረት አምጣ እንደ እሸት ያለ ተረት፤ ታዛ ስር ቁጭ ተብሎ ተረተር እየማተሩ ቃም፤ ቃም የሚደረግ ተረት..."

ይቺን ሰሞን ተረት ሳስብ ጭፍን ድቅን ብላ እልላቶች ትለኝ ጀምራለች፡፡

"ያሁኑ ይባስ ሲባል ሰምተሃል?" ትለኛለች፡፡

"አልሰማሁም" እላታለሁ ተረቱን አውቀዋለሁ እዚ ስትተርከው መስማት ግን የተለየ ጣዕም አለው፡፡

"አንድ ወረሳዊ ነው"

"እሺ"

"በቸርኬው ሲፈጨው (በእግሩ ሲሄድ) ውሎ ድከሞው ከች አለበት (ደከመው) በዚህ ላይ ጠርሮበታል (ቸስቷል) ማላ(ዘዴ) ሲፈልግ አንድ ቤት ፊት ለፊት ይከስትለታል (ይታየዋል) ይመርሽና (ይሄድና) ባሉካዋን (የቤቱን ባለቤት)

"ድክሞነው (ደክሞኛል) ታይሙም መርጂል (መሽቷል) እዚሀ ልክሸሽና (ልተኛና) በጠዋት እፋታሻለሁ (እሄድልሻለሁ)" ይላታል፡፡

"እብሽር፡ ባሉኳው (ባሌ) እስኪከሰት (እስኪመጣ) ቤት መግባት ቶግር (ክልክል) ነው" ትለዋለች፡፡

"ምን ጣጣ (ምንም ችግር የለውም) ይልና በር ላይ ዱቶ (ቁጭ) ይላል፡፡ ቺኳ ሉቆ (ቆሎ) ሲሉ (ጠላ) ይዛ ከች አለች (መጣች)፡፡ ሉቆውን እያሜወተ (እየበላ) ቀዳዳ (ወሬ) ይጀምራል፡፡

በቀዳዳ መካከል "ከየት ነው ከች ያሉት (የመጡት)?" ትለዋለች፡፡

ከላም ሲያደርጋት (ሲያያት) ያልባነነች (ምንም የማታውቅ) እንደሆነች ይበላታል (ያውቃል) ሙድ ልያዝባት (ላሹፍባት) በሚል "ከሙታን ሰፈር" ይላታል፡፡

"እፈር በበላሁ፣ የእኔን እናትና አባት ታርፋቸዋለህ? (ታውቃቸዋለህ?)" ትለዋለች

"እስከቀግ (በደንብ)"

"ታርፋቸዋለህ?" (ታውቃቸዋለህ?)

"እስከቀግ ስልሽ" (በደንብ)

"ቀመቻችተዋል?" (ለምደዋል?)

"በመጠኑ" ወሪሳዊው ቀዳዳውን ወደ ቢዝነስ (ሌብነት) ለመቀየር አሰበ

"እንዴት?"

"ብሮክ (ችስታ) ናቸው"

ባለካዋ በፋራ ሙድ "እፈር በበላሁ ምናምን እያለች ትቀዋውጠውና (ትረብሽና) "ምን ይላክላቸው? ትላለች...

‹‹ቡላ (ምግብ) ልባብ (ልብስ)፣ ፍሉስ (ገንዘብ)..."

ወደ ጓዳ ገብታ የተባለውን ታሳቅፈዋለች እዚህ ከምደቅስ (ከምተኛ) ባፋጣኝ ይድረስላቸው ይልና ይነካዋል (ይሄዳል)

ባለካዋ (ባሏ) ከች ሲል የሆነውን ትቀድሰታለች (ትነግረዋለች)





"ወይኔ እናፍዞሻል (እታለሻል)" ብሎ ፈረሱን እጥሚው (እምጨው)" ወሪሳዊው ወደ ሄደበት እይነካውም፡

ወሪሳዊው ደሞ ትንሽ እንደነካው አሁን ሰላም ብሎ ዛፍ ሥር ቁጭ አለ፡፡ ትንሽ እንደደቀሰ (እንደተኛ) የፈረስ ኮቴ ሰማ "ወይኔ ባሉካው ነው" ብሎ የያዘውን ልብስ አርቆ ይወረውርና ባላየ፡ ባልሰማ ቁጭ ይላል፡፡

ባሉካው መጥቶ

"ልባብ (ልብስ) ያነገበ (የተሸከመ) ከዚህ አልፏል?" ይለዋል፡፡

"አሁን በዚህ በኩል ነክቶታል (ሮጧል)" ብሎ ወደ ቁልቁለት ያስከልመዋል (ያሳየዋል)

"ወይኔ፡ መንገዱ ለፈረሴ አይደላውም (አይመቸውም)" ይላል፡፡

"ምን ጣጣ ከች እድርገው (አምጣው) እኔ እመነጥርልሃለሁ (እያየሁ እጠብቅልሀለሁ)" ይለዋል፡፡

"ይመችህ" ብሎ ፈረሱን ይገጨውና (ይሰጠውና) ሲመርሽ ሲል

"ለመሆኑ ሥምህ ማነው?" ይለዋል፡፡

"ያሁኑ ይባስ"

"የሚደላ ስም ነው" ብሎ ይመርሻል፡፡ ወሪሳዊው ልባቡን (ልብሱን) ጭኖ በፈረሱ መርሸሰታ

ባሉካው ከሄደበት ሲመለስ ተቀይሶታል (ጠፍቶበታል) "ያሁኑ ይባስ፡ ያሁኑ ይባስ፡" እያለ ተጣራእ... ወሪሳዊው አይደላም? (ደስ አይልም)

"የመቤ (የመጨረሻ)" ነልኳት፡፡ በኔ ምላሽ የበለጠ ፍንቅት ብላ ሳቀች እይኗ ጥፍት ሲል ዓይን ይሰባል፤ እንዴት? የተጨፈነ ነገር አይን ሊሰብ ይችላል? ለመሆኑ ማነው ጭፍን ያላት?...

በዚህ መካከል የቤቱ ብርሃን ተጋረደ፡፡ እንደ ጭፍን ቤቱም አይኗን ጨፍና የሳቀች መስሎኝ ነበር፡፡ ወደ በር ስመለከት አንድ



@BOOKALEM

የተንጠለጠለ ፊት ወደ ውስጥ አስገሳ ይመለከታል፡፡ የአምጳርጵር ልጅ፡፡

"ወይኔ ሰሀኑ" ሽክክ ትዝ አለኝ፡፡ "ደነገጥኩ፤ እምጳርጵር እዝነው ምግብ ቢልኩ ከነ ሰሀኑ?"

"ግቢ-ግቢ" አልኩ፡፡ ገባች፡፡ ቤቴን ሞላችው፤ ጠባብ ቤት ውስጥ የቆመ ትልቅ ቋም ሳጥን መሰለችኝ፡፡ ካለፈው እነስ ያለ ጉድጓዳ ሰሀን በጡቶች አስጠልላ ሆዷን አስደግፋ ይዛለች፡፡

ሆዷ እንደ ለማጅ ማሲንቆ ገዘገዘ - ጡሩሩሩሩሩ…

"ሰሀኑን ልወስድ ስመጣ አባዬ እንዴት ባዶ እጅሽን ትሄዳለሽ? ሲለኝ ይሄን…" እንደ ልጅ ተንተባተበች፡፡

"ቁጭ በይ" አልጋውን ለቀቅኩላት

"አልጋ ላይ ነውር ነው፡፡ አባዬ ይቆጣኛል፡፡" የያዘችውን ሰሀን እየሰጠችኝ "ያኛውን ሰሀን ስጠኝና ልሂድ" አለች፡፡

የምለው ሳጣ "እረ ቁጭ በይ" አልጋውን አሳየኋት

"አባዬ ይገድለኛል" ተሽከረመመች፡፡ አስር ልጆች የሚያስተኛ ሆድ አላት፡፡ እንደ ልጅ ስትሆን እውነታን ታሳክራለች፡፡ እጇ የኩይሳውን ሳይበልጥ አይቀርም፡፡ "ሰሀኑ ጠፋ" ስላት ይሄን እጇን ብትከድንብኝስ?

"ሰሀኑን ስጠኝና…"

የሰጠችኝን ሰሀን ከመሞቅ፣ አልፎ ወደማቃጠል ያዘነበለ ነው፡፡ የምላት ግራ ገብቶኝ ስታይ፡-

"ጠፋብህ?" አለችኝ

እራሴን በእምንታ ነቀነኩ..

"እነዚህ ብስብሶች፣ ባለጌዎች ሰረቁህ?"

እራሴን ነቀንቅኩላት

"እነዚህ… ለምን ይሄን ሰፈር አትለቅም? ሌቦች ናቸው፡፡ አባዬ ቢሰማ ይገድለኛል፡፡ እንዳትነግረው መልሷል እለዋለሁ.. እሺ?" ቅልል አለኝ፡፡

"እሺ"





"በቃ ብላ…"

"አንቺ አትበይም?"

"አባዬ ይገድለኛል ከወንድ ጋር በላሽ ብሎ"

ፈጠርጫራው ሽማግሌ እንዴት ይቺን ተራራ እንደሚገድሉ አልከሰትልህ አለኝ፡፡ ዶማ ይዘው እሳይዋ ላይ ቢወጡ እንኳን ያለጥርጥር አንድ ወር ሙሉ ይቆፍራሉ፡፡

እግሯ ከቤት ሲወጣ፣ እጄን ወደ ሰሀኑ ከተትኩ፡፡

## 28 - ፍቅሮ እስከ ቅብሮ

"ቁንጣንን ያላወቀ ረሃብን ያማርራል" አሉ፡፡

ብዙ ጊዜ እየራበኝ አስተምሬአለሁ ዛሬ ግን ቁንጣን ይዞኝ አልቻልኩም፡፡ ሁሉም ነገር ሰለቸኝ - "እጥኑ" ብዬ ወጣሁ፡፡ የትምህርት ቤቱ ግቢ ጭር እንዳለ ነው፡፡ የክፍል ሥራ እንደሰጠሁ እስመስዬ የበረንዳውን ተራዳ ተደገፍኩ፡፡ ጥጋብ መጥፎ ነው ሲጃራ እጭስ-እጭስ እሰኘኝ፡፡ የሰባት ቁስ ዘር አባቴ ምን ይል?

"አንት ትምንባኋም!!"

ልጆቼ ሲንጫጩ ክፍል ገብተህ በጠገበ ሆድህ እርገጥ እርገጣቸው አሰኘኝ፡፡

"ከተራብ ለጠገበ አዝናለሁ" አሉ እንደምንም ሰዓት ደርሶ ከግቢው ስወጣ ጭፍን ፊት ለፊት ቆማለች፣ ደነገጥኩ፡፡

"ምናባቷ ልታደርግ መጣች?" ጭፍን ከወረሳ ውጭ ሲያይዋት ታሳፍራለች ልበል? እዎ ከወረሳዎች ጋር ስትነፃፀር ነው እምራ የምትታየው ወደእ ስትመጣ የሥራ ባልደረቦቼን ገልመጥ ገልመጥ ብዬ ቃኘሁ፡፡ ቀድሜ ነው የወጣሁት፡፡ እንደቀረበችኝ እጄን ይገፎ እውራውን መንገድ ተሻገርኩ፡፡

"ልለቅብህ ነው የመጣሁት" አለችኝ፡፡

"ምንድነው የምትለቂብኝ?"



@BOOKALEM

"ካፌያ" ሳቀች፡፡ "ዘንቦልኛል"

ከይ ያልጠበኩት ለስላሳ እጅ እጄ ውስጥ... ዘወር ብዬ አየኋት፡፡ እንደ ኅበዝ ተዋናይ አንድ የዱርዬ ገፀ ባህሪ እየተጫወተች መሰለኝ፡፡ ሲያበቃ ግሩም ሴት የምትሆን...

"ከንትር ግሮሰሪ" ይዛኝ ገባች፡፡ ቤቱን ወራሳዎች ይወዱታል፡፡ ይሁንና የሥራ መውጫ ሰዓት ላይ "ሥራ" ስለሚበዛባቸው አልተሰየሙም፡፡

"ጅን ደብል" አለች ጭፍን፡፡ የኒያላ ፓኬት አውጥታ ሲጋራውን ወገብ ይዛ እሽት እሽት አደረገች፡፡ ለኮሰች፡፡ የክብሪቱ ብርሃን ፊቷ ላይ ብርቱኳናማ መብረቅ መስሎ ተብለጨለጨ፡፡

"ለእሱም ጅን ደብል" አለች፡፡ በሴት ስጋበዝ የመጀመሪያዩ ነው፡፡ ቅሉ ጭፍን ሴት ባትሆንም ጅኑ ከሎሚ ጋር ቀረበ፡ ተጎነጨሁለት፡፡ ለጥጋቤ መድኃኒት ያገኘሁ መሰለኝ፡፡ ሰውነቱ ሁሉ ሆድ ሆኖ ከበደኝ ነበር፡፡

ጭፍን ደጋግማ ሲጋራዋን ትለብጣለች፡፡ ስትስት ብቻ ሳይሆን ሲጋራ ስትለብጥም አይኖቿ ይጠፋሉ፡፡

ዝም እንደተባባልን የሁለት ደብል ጅን ዘመን ከነፈ፡፡ አልፎ አልፎ "ተጫወት" ትለኛለች፡፡ "ተረት ንገረኝ" እንዳልል እየተጋበዝኩ በመሆኑ ትክክል አልመሰልህ አለኝ፡፡

ጭፍን ሦስተኛ ሲጋራዋን አጋምሳ ከረገጠች በኋላ፣ "የተረቱን መፅሀፍ ጀመርከው?" አለችኝ

"አዎ" አልኩ እራሷ በማንሳቷ ደስታ እያቁነጠነጠኝ፡፡

"እኔም ትናንት ጀመርኩ"

"ምን?"

"መጽሀፍ መጻፍ ነዋ፣ የእኔ ግን ተረት አይደለም፡፡"

"ምን?"

"ልቦለድ፡፡ ፍቅሮ እስከ ቅብሮ የሚል ርዕስ አለው፡፡"





ቋንቋዋም ተስተካከሉብኝ፡፡ ትወናዋ አበቃ ይሆን? "ርእሱ አልገባኝም" አልኳት፡፡

"ፍቅሮ' ፍቅር ማለት ነው"

"እሺ."

"እስከ ያው እስከ ነው"

"እሺ."

"ቅብሮ' ደሞ መቃብር ነው"

"እንዴ? ፍቅር እስከ መቃብር?"

"አዎ" ጅኑን እንስታ ተጎነጨች፡፡

"ይሂማ የጥበብ ስርቆሽ ነው፡፡"

ዘወር ብላ ገረመመችኝ፡፡ የመታዘብም፣ የመናደድም አይደለም፡፡ ታዲያ የምን? "ታሪኩ ምን ላይ ነው? ማለቴ በርዕሱ ብቻ..."

"ታሪኩ ወራሳና አረብር ላይ ነው፡፡ አንድ ወራሳዊ ሀይለኛ የአረብር ልጅ አፍትሮ የቺኳ (የሴቷ) አባት መሬ (ሀይለኛ) ናቸው፡፡ እና ወራሳዊውን እመርሸዋለሁ (እገድለዋለሁ) ሲሉ ተሸብልሎባቸው ወራሳ ይመጣል፡፡ ልጃቸውን ያስፎታል፡፡ ወራሳዊው ቢጠብት ቢጠብት ቺኳ አልከሰት(አልመጣ) ስትለው ወደ አረብር ለመሄድ ይቆርጣል፡፡ መጀመሪያ ግን በሞባይል ሚሴጅ ልኮላት ነበር፡፡ ቺኳ ትጨንትና ወደ ወራሳ ስትመጣ አሪ በከንቱ ወንዝ ማጁካዎች (ማጅራት መቺዎች) ሀንግ ሰርተውት(ማጅራት መትተውት) ወድቆ ታገኘዋለች፡፡ እዛው እጇ ላይ ይሞታል፡፡ ከዛ በኋላ ቺኳ ወደ አረብ አገር ትሄዳለች እዛ ሞታ አስከሬኗ ሲመጣ በተናዘዘችው መሠረት ከፎንቃዋ (ከፍቅረኛዋ) ጋር አንድ መቃብር ትቀበራለች፡፡ ቢቃ"

የምለው ጠፋኝ

"ሚሴጅ ምን ብሎ ቢልከላት ጥሩ ነው?"

"እ?"

"ስሟ ቤቲ ነው"

"እሺ.

"በግጥም ነው ሚሴጁ"



@BOOKALEM

"ቀጥይ"

"ቤቴ፣ ቤቴ፣ ቤቴ ጀለሴ እመቤቴ፣
ከሚጨሰው ሜሽ ነሽ ከቃሚው ቀማቴ፣
ፋክት ከሆነማ እኔ እንቺን ማጣቴ
ምን ዋጋ ሊኖረው ያ-አራድነቴ፣
መንጩ ሰሩኝ ወይኔ - ወረላ በመሆኔ፡፡"

"ፍቅር እስከመቃብር' የተሰኘውን ልቦለድ አንብበሽዋል?" ስል ጠየኳት፡፡

"አዎ፣ ምነው?"

"ምንም፣ ጨርሰሽዋል?"

"አዎ፣ ምነው?"

"ምንም"

ከዚህ በላይ ምን ይወራል? ዝም ብዬ ትኩረቴን ጅኑ ላይ አደረኩ፡፡ ጭፍን ሲጋብዟት እንጂ ስትጋብዝ ደስ አትልም፡፡ ወደ ቤቴ መሄድ አሰኘኝ፡፡ "ልሂድ" አልኳት

"አልተመቸኽም?" አለችኝ ሌላ ሲጋራ ወገቡን ይዛ እያሸች፡፡

"አይ"

"አይዞህ አሁን ቤቱ ይደራል፡፡ ቃሚውም፣ ተቃሚውም መምጫው ደርሷል" አለችኝ፡፡ ንግግሯ ውስጥ እንዳልሄድ ፍላጎት አሳየችኝ፡፡ ከእሷ ጋር በመሆኔ የደበረኝ ስለመሰላት ተቁነጠነጠች፡፡ አልተጨነኩም፡፡

"አሁን ጨዋታው ይደራል" አለች፡፡ "ድቁሱም፣ ፈላስፋውም፣ ልባሙም... ይመጣሉ፡፡"

"ልባሙ ደግሞ ማነው?"

"አታውቀውም?"

እራሴን ግራ ቀኝ አማታሁላት፡፡

"አንተ ቤት አጠገብ ያለው፡፡"

"ኩይሳው?"





"አይ - በወዲያ በኩል..."

ያ ከአይን የፈጠነ ከምናምን የቀጠነ ጎረቤቴ፡፡ ዝናውን እንጂ አካሉን በቅጡ አላውቀውም፡፡

"በወረላ ታሪክ..."

"እ?" ቸኮልኩ?

"ሁለት ሰዎች ጠላታቸውን በስርቆት አሳብደዋል፡፡ አንደኛው አባ ንጠቃቸው ናቸው፡፡"

"እሺ" ቋንቋዋ ሲስተካከል ታወቀኝ፡፡

"ሁለተኛው ልባሙ ነው"

"እንዴት አድርጎ አሳበደ?"

"ሰውየው 'ፉግር' (ሰላይ) ነው፡፡ ባስ ላይ ወረላዊ ሲወጣ ሰውየው 'ኪሳችሁን ጠንቀቅ ኪሳችሁን ጠብቁ፣ ኪስ መርማሪዎች ገብተዋል' ይላል፡፡

"ልባሙ ይሄንን ሲሰማ ለመጀመሪያ ጊዜ ባስ ላይ ይወጣል፡፡ ሰውየውን ፈልጎ አጠገቡ ይቆማል፡፡ ሊሎቹን ወረላዎች ሲመለከት "ኪሳችሁን ጠንቀቅ፣ ኪስ መርማሪዎች ገብተዋል" ይላል፡፡ ሰው ሁሉ አዲስ የገቡት ሰዎች ላይ ያተኩራል፡፡

ይሄን ጊዜ ሰውዬውን ጠጋ ያለው ልባሙ ኪሱ ገብቶ ቦርሳውን ይሰርቀዋል፡፡ ብዙም ሳይቆይ ሰውየው፡፡

"እንዴ? እንዴ? ሾፌር እንዳታቆም፣ ትኬት ቆራጯም በር እንዳትከፍቺ ወደ ፖሊስ ጣቢያ፡፡ ቦርሳዬን ከነገንዘቡ ተሰርቄአለሁ፡፡"

ሲመክር የሰሙት ግራ ተጋብተው ዝም ይላሉ፡፡

"ሾፌር፣ ትኬት ቆራጭ... ቀጥታ ወደ ፖሊስ ጣቢያ!"

በዚህን ጊዜ ተሳፋሪ ሳቀ፡፡ ልባሙ ቦርሳውን ሌላ ኪሱ ውስጥ ይከትለታል፡፡

"እንዴ? እንዴ? ሾፌር ማቆም ትችላለህ፣ ትኬት ቆራጯም በር መክፈት ትችያለሽ፡፡ ቦርሳውን ከነገንዘቡ አግኝቼዋለሁ፡፡"

አሁንም ተሳፋሪው ይስቃል፡፡



@BOOKALEM

ልባሙ ጥቂት ቆይቶ አሁንም በርሳውን ይሰርቀዋል፡፡

"እንዴ? እንዴ? ሾፌር፡ ትኬት ቆራጭ ቀጥታ ወደ ፖሊስ ጣቢያ..." ይመልስለታል

"እንዴ? እንዴ? ሾፌር ማቆም ትችላለህ፡ ትኬት ቆራጭ..."

ተሳፋሪው ነገሩ ቀልድ አልሆን እያለው መነጋገር ይጀምራል፡፡ "እብድ ነው፡ እብድ ነው...."

ልባሙ በዚሁ ቀጠለ፡ ሲሰርቀው፡ ሲመልስለት፡ ሲመልስለት... ሰውየውም ሲዘላብድ ቆይቶ ከባሱ ሲወርድ በመጨረሻ ሰረቀው፡፡ ሰውየው ባሱን እየተከተለ "ሾፌር፡ ትኬት ቆራጭ..." አለ፡፡ እስካሁንም ባስ እየተከተለ "ሾፌር ትኬት ቆራጭ..." ይላል፡፡ አበደ፡፡"

ከታሪኩ ይልቅ የጭፍን ጥርት ያለ አማርኛ ትኩረቴን ሳበው፡፡ ትክ ብዬ አየኋት፡፡ ምን መሆኑ ነው ብላ አየችኝ፡፡ ከዚህ በኋላ በቅጡ ሳንተያይ እንደተፋፈርን የተባሉት ድቂሱ፡ ፈላስፋው፡ ልባሙ፡ ሸኮኮ... መጡ፡፡ በመጨረሻ አባባ ጆቢራ መጥተው ቤቱን ሞሉት፡፡ ግሩም ሆነ፡ ወሪሳ ተከር ጭውውት ተካሄደ፡፡ ሳላስበው ብዙ ጠጣሁ፡፡

## 29 - የሥጋ ግድግዳ

ጠዋት የነቃሁት አልጋዬ ጠቦኝ ነው፡፡ አለወትሮው ግድግዳው ቅርብ ሆነብኝ፡፡ ወደ ግድግዳው የተጠጋሁ መሰለኝ በተቃራኒው ሽሽት ስል ጫፍ ላይ በመሆኔ ተምዘግዝጌ መሬት ወደቅሁ፡፡ ተምዘግዝጌ ያልኩት ካልጋ ሳይሆን ከቆጥ የወደቅሁ ያህል መሬት ስለራቀኝ ነበር፡፡

"እኔን" የሚል የሴት ድምፅ ሰማሁ፡፡ ከጎረቤት እማማ ጉዶ መሰሉኝ፡፡ በቀዳዳ ሲያዩኝ ነበር ማለት ነው? አይደሉም፡፡ ድምፁ የመጣው ከወደ አልጋዬ አቅጣጫ ነው፡፡

"እኔን ድፍት ያድርገኝ - ለእኔ ያድርገው"

ድምፁ ተደገመ፡፡ ከወደ አልጋዬ አቅጣጫ... ማታ ሰክሬ ጭፍንን ይገርት መጥቻለሁ ማለት ነው? ምንም ትዝ ያለኝ ነገር





የለም፡፡ ወዳልጋው መመለስ ፈራሁ፡፡ ጭፍን እንኳን እራቁቷን ከነልብሷ፡ ወንድ መስላም ታርበደብዳለች፡፡

ወደ አልጋው እንዳንጋጠጥኩ እንደ ደመና የከበደ ፊት እላዬ ላይ ተንጠረበበ፡፡ ድርብርብ ጉም የመሰለ ፊት፡ ሥጋ፡ ደነገጥኩ፡፡ ድንጋጤዬ ውሃ አደረገኝ፡፡ የእምጳርጳር ልጅ፡ እንዴት ከእኔ ጋር አደረች? በሥካር ፈረስ ሄጄ ከቤቷ አመጣኋት? ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ነው የሚባለው፡፡ እኔ ግን የእምጳርጳርን ልጅ በሆዴ ከጅያት አላውቅ፡፡ ታዲያ እንዴት ይዣት መጣሁ?

"እእን፡ እእን..." አለችኝ፡፡

"እኔን ድፍት ያድርገኝ"

ለመደፋት ሰበብ የምትፈልግ መሰለኝ፡፡ ምነው ደጋገመችው? የማደርገውን የማላውቅ እኔን ይድፋኝ እንጂ...

"መነሳት አቃተህ?" ብላ እጇን ለእርዳታ ሰደደች፡፡ እጇን መዳፏ ላይ ሳስቀምጠው የእስክሪፕቶ ቀፎ ያህል አነሰ ታየኝ፡፡ ሰባ ሳይሆን እንጠልጥላ አነሳችኝ፡፡ የምለው ግራ ገብቶኝ ዝም እንዳልኩ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጥኩ፡፡ ከደርባዬ ተከምራለች፡፡ የሰውነቷ ወላፈን ይጋረፋል፡፡

"እንዴት መጣሽ?" አልኳት፡፡

"አባዬ የሰሀኑን ጉዳይ ሲሰማ ተቆጣኝ፡፡ እኔም አንተን ዘመድ ብዬ መጣሁ፡፡ አንተም አይዞሽ እዚህ እኔ ጋ ትኖሪያለሽ አልከኝ፡፡"

"ምን? እንደሱ አልኩ?"

"አዎ"

"ሰክሬ ነው"

"እኔ ደሞ የዛሬን ልደርና ነገ እሄዳለሁ አልኩህ"

"ጥሩ ብለሻል"

"አንተም ነገ እንነጋገራለን አሁን ተኚ አልከኝ፡፡ እኔ ከወንድ ጋር አልተኛም ስልህ አግባባኸኝ፡ አይሆንልኝም እንኳን



@BOOKALEM

ወንድ ተጠግቶኝ ገና ሱሪ ሲያነጥፉብኝ ነው ቅሬት የምይዘው አልኩህ፡፡ አንተ ደሞ ይሁና ለአንድ ልጅ እንሳለሁ ወይ? አልከኝ..."

"እንደሱ አልኩ?"

"አዎ"

"ሰክሬ ነው"

"እኔም ተወኝ አይሆንልኝም አልኩህ 'እንቢ ካልሽ' ብለህ ስታፈጥብኝ ፈራሁ..."

"አንቺ?"

"አዎ"

"መፍራት አልነበረብሽም፣ ከዚያስ?"

"ከዚያማ ለህይወቴ ስፈራ..."

"ኡ...ሁ!" በረጅሙ ተነፈስኩ፡፡ ይቺን የሥጋ ጉብታ፡፡ ምን ሳደርግ እንዳደርኩ የማስታውሰው ነገር የለም፡፡ እንኳንም ማስታወስ አልቻልኩ፡፡ እድሜ ልኬን የሚዘገንን ትዕይንት ለአእምሮዬ ከማስቀር መዘንጋቴ በጅቶኛል፡፡

አልጋው ራስጌ ላይ ሱሪዬን አስጥቼዋለሁ፡፡ ለካ እራቁቴን ኖሪያለሁ፡፡ ብድግ ብዬ ልብሴን ማንሳት አሳፈረኝ፡፡ ቅድም እርቃኔን አይታኝ አልነበር? ማታስ? ይሄን አልተኛ ስትለኝ እርቃኔን ተነስቼ ፎክሬ ይሆናል፡፡ ያንን የአባቷን ቆንጨራ ከአልጋ ስር ለማውጣት ሳፈነድድ... እንኳንም ቤቱ ውስጥ ካሜራ አልተገጠመ፡፡

አልጋው ላይ በቂጤ እየተንፏቀቅኩ ግርጌውን ቀርቤ ሱሪዬን አነሳሁ፡፡ ሳልቆም ታጥቄ አጠናቀቅኩ፡፡ የጓሮ አትክልት ማብቂያ መደብ የሚያክል ጫማዋን አቀርቅሬ እያየሁ...

"አሁን ታዲያ አትሄጂም?" አልኳት

"እሄዳለሁ 'ንጂ፡፡ እንደ ማታው ካላስፈራራኸኝና ከፈቀድክልኝ እሄዳለሁ።"

"ማታ ሰክሬ ነው"

"ግን..." ብላ ዝም አለች





ቀና ብዬ የተንጠረበበ ፊቷን አየሁት፡፡ ግንባሯ፣ ትንድቧ፣ የአይኗ ቆብ፣ ጉንጮቿ፣ ሎከሎኪዋ፣ ከንፈሯ...ሁሉም ተትረፍርፎ የተንጠረበበ ሥጋ ነው፡፡ ማታ ይሄን ከንፈር ስሜው ይሆን?

"ግን ምን?" አልኳት

"ሴት አይደለሁ..."

"እና?"

"የተኛሁበትን አጥቤ፣ ያደርኩበትን ጠራርጌ፣ እቃዎቹን በወግ በወግ አሰናድቼ እሄዳለሁ፡፡"

"እንደፈለግሽ ብቻ ሂጂ" ብዬ እየተካለፍኩ ወጣሁ፡፡ ፊቴንኳን ለመታጠብ ያልፈለኩት የሚወስደውን ጊዜ እሷ ያለችበት መቆየት ስላስጠላኝ ነው፡፡ በስህተት ወደ ስራ ልሄድ ነበር፡፡ ለካ ቅዳሜ ነው፡፡ ከንትር ግሮሰሪ ፊቴን ለመታጠብ ገባሁ፡፡ በጠዋቱ የተሰየሙ ጠጪዎች ነበሩ፡፡ "ኖር ኖር" አሉኝ፡፡

"በእግዜር፣ በእግዜር" እያልኩ ወደ ጓሮ ስዞር መንገዱ በሥጋ ግድግድ ተዘግቷል፡፡ ዛሬ የሥጋ ግድግዳ ቀን ነው እንዴ? ብዬ ቀና ስል ያአባባ ጀቢራ ፊት ፊቴ ላይ ተደቅኗል፡፡ ማታ እዚሁ አብረን ነበርን፡፡ ሲጠጡ አድረው ነው? ፊታቸው እንደገነተረ ነው፡፡

መተላለፍ ስላልቻልን እኔ እንደ መኪና የኋላ ማርሽ አስገብቼ አፈገፈኩ፡፡ አጥቂና ተጠቂ ጦር ይመስል አባባ ጀቢራ ወደፊት እየገፉ፣ እኔም ስልታዊ ማፈግፈግ እያደረኩ ሰላምታ ተለዋወጥን "ልጋብዝህ" በሚል ኩራት "ጋብዘኝ" አሉኝ፡፡ በተጋባዥ መሽቆጥቆጥ "እሺ" አልኳቸው፡፡

* * *

ጀቢራ መሬት ለቅቀው ቢሰክሩም ወሬአቸው እንኳን ሊንገዳገድ ሳቅም አይልም፡፡

"እግዚሀር ባንክ የለው
አምጣ አብላን ይባላል፣
አንዱን ጣይ አንዱን አንሺ እርጎ ያቻችላል፡፡



@BOOKALEM

ሲባል አልሰማችሁም? ይኸው ነው የእግዚሀር ጥበብ፡፡ አንዱን ሀብት ሰጥቶ ልብ ይነሳዋል፤ ሌላውን ሀብት ነስቶ ልባም ያደርገዋል፡፡ "ሀብት ስጠኝ" ብሎ መፀለይ "ልቡና ንሳኝ" ከማለት አንድ ነውና ከንቱ መታከት ነው፡፡"

ጀቢራ እራሳቸውን የወሪሳ ሰባኪ አድርገው ሾሙዋል ፡ እንዲሁም የታሪክ ሰው፡፡

"በመንግስቱ ኃይለማርያም ጊዜ ተደራጁ፣ ተደራጁ.. ሲባል እኛም ሰብሰብ ብለን የኢትዮጵያ ሰርቶ አደሩ ፓርቲን አቋቋምን፡፡ መፈክር ያስፈልጋችኋል ሲባል ደግሞ "የዓለም ሰርቶ አደሮች ተባበሩ" አልን፡፡ ምልክታችሁ የታል? ሲባል ደሞ ሌባ ጣትና ተከታይዋን ጣት ቁልቁል ቀስረን ሌሎቹን ጣቶች አጥፈን አቀረብን፡፡ ምልክቱንቱ ኪስ የሚገባ ጣት ነው አልን፡፡ አሁን አሁን የኛን ምልክት ወደ ላይ ገልብጠው የድል ምልክት ነው ይሉታል፡፡ ያኔ እኛ ስንፈጥረው ትርጉም ነበረው፡፡"

የጅን ብርጭቋቸውን ለስንትና ስንት ጊዜ አነሱና ቀመሱ፡፡ እኔ ያልሰከረው ጆሮዬ ብቻ ነው፡፡ በአግባቡ ስራውን ያከናውናል፡፡ እፌ እንኳን መጠየቅ የምፈልገውን እንቢ ብሎ ሳልወድ በግድ ዝም ብያለሁ፡፡ በእዚህ መካከል አንድ ቅር የሚለኝ ነገር አለ፡፡ ጭፍንን አላየኋትም፡፡ ናፍቃኛለች ልበል? ጀቢራ ቀጠሉ

"መካከላችን ሁካታ ተነሳ፡፡ ጉም፣ ጉም፣ ጉም ይላል ሁሉም፡፡ ምን ሆናችኋል ምን ተፈጠረ? ሲባልስ ከአባሎች የሰርቶ አደሩ ፓርቲ ውስጥ ጭቆና፣ መድልኦ፣ ምዝበራ፣ ማግለል... አለ የሚል ቅሬታ ቀረበ፡፡

"እንዴት ሁኖ? ስንልስ የኪስ አውላቂ የበላይነት ሰፍኗል፡፡ ማጅራት መቺው፣ ቤት ሰርሳሪው፣ ወንዝ ለወንዙ" (የተሰጣ ልብስ ሰራቂው)... አልተወከለም፡፡

"እንዴት? ስንልስ ነፍሱን ይማረውና አባ ላፊው ብድግ አለ፡፡ ማጅራት መቺ አይደል? እንሱን ወክሎ ነው፡፡ ምልክቱን ማየት ብቻ በሰርቶ አደሩ ፓርቲ ውስጥ ጭቆና፣ አድልኦ፣ ምዝበራና ማግለል እንዳለ ያስታውቃል፡፡ በፓርቲው ምልክት ውስጥ የታለ እኛ የተወከልነው? አይልም?





"ሃይ፣ ሃይ፣ ሃይ.. ተባለና በመጨረሻ አንድ ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ ከተዘቀዘቀው የኪስ አውላቂዎች ጣት ጎን በፍርግር የማድግዳ ማገር አሎሉቶ የሚያይ ዓይን ጨመርን፡፡ ይሄ ምልክት በኋላ የቱጥጥር ኮሚቴ አርማ ሆኗል፡፡ ይሄኔ ሁሉም መወከሉ ተረጋገጠ፡፡ አባ ላፊው ጓድ ላፊው ተብሎ ፓርቲውን እንዲያፀድቅ ተወከለ፡፡

"ጓድ ላፊው አንድ ሁለት ሳምንት ላይ ታች ካለ በኋላ ከመንግሥት መልዕክት ይዞ መጣ፡፡ የፓርቲው አባላት በግንባር እየመጡ ፎርማቸውን በፎርማ ያረጋግጡ ተብሏል አለ፡፡ መቼም ታሪክ ማወቅ ጥሩ ነው የአጤ ቴዎድሮስ መላ ስርውጥ አለኝ፡፡

"እንዴ? እንዴ? እንዴ? ይሄማ አይሆንም፡፡ አንድ ጋ ተንጋጦ መሄድ አይበጅም፡፡ ባይሆን አንድ አንድ እያልን ነገሩን እናጥና አልኩ፡፡

"ጓድ ላፊው ቱግ አለ፡፡ እንዳውም ጠርጣሪ የጠርጣሪ ልጅ ብሎ ከእኔ አባቱ ጭምር ሰደበ፡፡ በዚህ ቂም ይዤ ጊዜ ስጠብቅለት መንግስት ቀደመኝ፡፡ ተሰብስበው የሄዱለትን የሰርቶ አደሩ ፓርቲ አባላት ሲረሽን ጓድ ላፊውም አብሮ ቀይ ሽብር ተፋፋመበት፡፡ መቼም ጀግና አይደል? ሲገደል መፈክራችንን ከፍ ባለ ድምፅ እየፈከረ ነበር አሉ፡፡ የአለም ሰርቶ አደሮች ተባበሩ! ፋሺስቶች የሰርቶ አደሩን ትግል አያደናቅፉም! ሌባ ይሞታል ሌብነት አይሞትም! በእርግጥ ጓድ ላፊው እንዳለው ነው፡፡ ሌባ ሞተ እንጂ ሌብነት አብሮት አልሞተም፡፡ ይኸው እስከ ዛሬ ለመብታችን እየታገልን አይደል?"

## 30 - ዱብ ዕዳ

ወፍ ሲንጫጫ ከእንቅልፌና ከስካሬ ባነንኩ፡፡ ዛሬም አልጋዬ ጠቦኝ ነው የነቃሁት፡፡ ያ የሥጋ ግድግዳ የአልጋዬን ሩብ ብቻ ትቶ ተገድግዷል፡፡ ንዴትና ድንጋጤ ተቀላቅለው ይህ ነው የማይባል ሰካራም ስሜት አስተናገድኩ፡፡

"ዛሬ ደሞ ምን?" ንውዘት ተጠናወተኝ፡፡ የተኛሁበት ሆኜ ገላዋን ላለመንካት ተጠንቀቅኩ፡፡ ትንፋሽ የሌለበት እንቅልፍ፣



@BOOKALEM

የማስመስል ማድፈጥ እንደሆነ አውቃለሁ:: በጥልቀት እንቅልፍ ውስጥ ያለች በማስመሰል ላይ ነች:: ምን አባቱ እንደምላት ግራ ተጋባሁ:: እንግዲህ በዚህ መካከል ነው በር የተንኳኳው:: ማንኳኳቱ የኩይሳው አይነት እጅ ያለው ሰው መሆን አለበት:: ደጃፉ በማንኳኳቱ እንደ መከፈትና መዘጋት ያህል ተርበደበደች::

"ማነው?" አልኩ ድምጼን አጀግኜ:: የአልጋው ግርጌ ላይ ያሰጣሁትን ሱሪ ታጥቄ በካናቴራ እንዳለሁ በሩን ከፈትኩ:: እምጳርጵር ሶስት ሰዎች አስከትለው ቆመዋል:: በእጃቸው ሳይሆን በጠንካራው በመንፈሳቸው ያንኳኩ መሰለኝ:: የተቆጣ ድምፅ መሰለው በጉሮሮዋቸው አጉረመረሙ::

"ሺ-ትርገጥ አለች?"

"ማናት ሺ-ትርገጥ?" አልኳቸው መንፈሳቸው ከስጋቸው በላይ ነው::

"ምን ያላወቀ ትመስላለህ? የእኔ ልጅ ናታ"

ሳልመልስላቸው ገልመጥ ብዬ አየኋት:: ተነስታ አልጋው ላይ ተከምራለች:: የተራቆተ ገላዋ እንዳይታይ አንሶላውን ሰብሰብ አድርጋ ጋርዳለች:: ሥጋ የበዛው ፊቷ ስጋት ይኑር አይኑር አያሳብቅም::

እምጳርጵር ባለው ክፍተት ሾልከው ወደ ውስጥ ገቡ:: ያዩትን ካለማመን ክው ብለው የድመት ሀውልት መሰሉ:: ከቆይታ በኋላ አስከትለዋቸው ወደመጡት ሰዎች ዞር ብለው...

"ኑ ጉዴን እዩ" አሉ::

ሺ-ትርገጥ አባቷን ለምን እንደምትፈራ አሁን ገባኝ:: የተዘጋ ቤት ውስጥ በአልሞትባይ ተጋዳይነት የገጠመ ድመት ምን ምኑ ይመታል (ይያዛል) ተርበተበተች:: እንደማልቀስ ከጀላት::

የተጠሩት ሰዎች ገብተው ከእምጳርጵር ጀርባ ተሰለፉ:: እምጳርጵር ማብራሪያቸውን ጀመሩ::

"ልብ ብላችሁ እዩ:: ልጄን እዚህ ቤት ስታገኙዋት እንዴት ተኮራምታ እያለቀሰች እንደነበር ለክራችሁ ትመሰክራላችሁ::"

ሦስቱም በአንድ ቃል "እሺ" አሉ::





"ሁግ እያለ እንደሌለ ጨለማን ተገን አድርጎ የልጄን ሰብአዊ ክብር ገፍፎ እንደ በሬ በመጥለፍና አስገድዶ በመድፈር ፍርድ ቤት አገትረዋለሁ:: በድርብ ድር-ብርብ ወንጀል አንቀፅ ጠቅሼ አስራ አምስት ዓመት አከናንበዋለሁ:: ሌላው ቀርቶ አስራ አራት ዓመት ቢሆን እንኳን ይግባኝ እላለሁ:: እንኳን ለራሴ ለሰው ይዘፍናል እንግቴ" አሉ::

ነገራቸው አልገባኝም:: የጠለፍኩና የደፈርኩ መሰሏቸው እንደተሳሳቱ ገባኝ::

"እምጳርጵር..." ብዬ ስጀምር

"እስኪ መጀመሪያ የገባህበትን ወንጀል ተወጣ:: በወንጀል ላይ ወንጀል አትደራርብ:: ስሜ አምበርብር እንጂ እምጳርጵር አይደለም::" ተሽቆጠቆጥኩ::

"ሺ-ትርገጥ'ኮ የመጣችው እርሶ የላኩልኝን ምግብ ልትሰጠኝ..."

"የማይመስል ማመኻኛህን ተወው:: እኔ ምግብ ግገር እንጂ ላንተ ሰጪ አልወጣኝም:: ምግቡን ይዛ በትመጣ ጨለማን ተገን አድርገህ መንግሥት እያለ..."

"ለምን እሷን አትጠይቁም?" አልኳቸው::

"ትጠየቅ፣ ትጠየቅ" ተባለ::

ይቺ የሥጋ ክምር ለካ ማልቀስ ጀምራ ኖሮ ፊቷ ተዝረክርኳል:: በአንሰላዬ ጫፍ ተናፍጣ

"እንዳልከው ነው" አለች

"እንዴት እንዳልከው?" አሉ እምጳርጵር እየደነፉ::

"ምግቡን ገዝቼ ስመለስ የሚካኤልን ሰይፍ የመሰለ ገጀራ ይዞ ትገቢያለሽ አትገቢም? አለኝ... "

"ወይኔ አምበርብር! 'ትፈጭ ነበረች ማንንስል ተሳናት' አሉ:: ነገር እንፍንፈ እሂድ የነበረ ቤቱ ድረስ፣ ያውም ልጄን... "

"እስኪ ረጋ በሉ" አሉ ከሦስቱ አንዱ:: ሰውየው ያከፈከፈ ፊት አላቸው:: "ለኛም ለምስክርነቱ እንዲበጀን እናድምጥ..."

"ጨረሰችው'ኮ ከዚህ በላይ እንዲህ አድርጎ ተጫወተብኝ እስክትል ነው?"

"ምን ሆንኩል እንበር..." ያኮፈኮፋት ለምስክርነት ቋምጠዋል:: አምጳርጵር ተፍጨርጭሯው ዝም አሉ::

"ለዘዴዬ ምግቡን አድርሺ ልምጣና እገባለሁ:: -ለባቴ በረሃብ ይሞትብኛል አልኩት:: ለምን ድብን አይልም አለኝ::"

"ድብን እል-እልል እንደሆን እናያለን" አምጳርጵር ወደ ላይ እያዩ፡- ዛቱብኝ:: የሺ-ትርገጥ አኳኋን እኔንም አሳመነኝ:: እንባዬ ንፍጢ...

"በኋላ እሺ እገባለሁ ግን ቶሎ ልቀቀኝ አልኩት አለቅሼ እንደውም ስመኘሽ ስለኖርኩ መድፈሩን ወደ ጠለፋ አስተላልፌዋለሁ:: ወንድ የሆነ ይጠይቀኛል ብሎ እስገባኝ:: ምግቡን በላ..."

"ዝርዝሩን ተይው፡ ምኑ ያምርና ታወጊዋለሽ? ከእንግዲህ በስምሽ አትጠሪም:: የግል ተበዳይ ነሽ እናንተም ከእንግዲህ በስማችሁ አትጠሩም:: የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ትባላላችሁ:: የአቃቢ ሕግ ምስክሮች፡ የምታጣሩት ነገር ካለ ጠይቁ:: ካለበለዚያ...."

እስካሁን ያልተናገረ አንድ ግሽርጥ አይን ሰካራም ጣልቃ ገባ:: ሊያስማማን መስሎኝ ነበር::

"በእሪ በከንቱዎች ባህል የበደለንን ስናገኝ እዚያው የበደለበት ቦታ ከታትፈን በፌስታል ነው ወደ ፍርድ ምንወስደው አሁንም..."

"ተው እንጂ መጣባቸው" አሉ ሌላኛው "ይቺ ልጅ አርግዛ ቢሆንስ? የቅዘ ሥጋችንን አባት? ባይሆን..."

"የአቃቤ ህግ ምስክሮች..." አሉ አምጳርጵር:: "እኔ ጠላቴን ስበቀል ደስ የሚለኝ መጀመሪያ በመንግሥት አስፈርጄበት ነው:: ፍርዱን ጨርሶ ሲወጣ ያኔ እንዳላችሁት ከታትፈን በፌስታል ወደ ቤቱ እናስገባዋለን:: ለመሆኑ ያስፈራራበት ቆንጨራ እዚህ ቤት ውስጥ አለ?" ልጃቸውን ጠየቁ





"አለ፡ አልጋ ሥር..."

"የአቃቤ ህግ ምስክሮች፡ አባካችሁ ቆንጨራውን ከአልጋ ስር አውጡ::"

እንደ ትንሽ ልጅ ተሽቀዳደሙ:: ግሽርጥ አይኑ መዝዞ አወጣው:: ፈራሁት:: ቆንጨራውን ሲይዝማ ቋመጠልኝ::

የማስበው ሁሉ ተምበረበረብኝ:: የምለው ጠፋኝ...

"ልብ በል" አሉኝ አምጳርጵር "እኔ ክርክሬ ምስጢር የለበትም:: ወንጀለኛ መቅጫ ህግ 587- እጠቅስብሃለሁ:: ጉዳዩ የመንግስትን ህልውና የሚመለከት ሲሆን በእርቅ የሚያልቅ አይደለም:: ጠልፈሃል፡ ደፍረሃል:: እነስ ቢባል 15 ዓመት፤ ለዚያውም ክስ ማቅለያ ብልሃት ካገኘህ:: ይሄው ነው::"

ጋዜጦች ሲያጋንኑ "የአማርኛው መምህር አስገድዶ በመድፈር ተከሶ 15 ዓመት ተፈረደበት" ሲሉ ታየኝ:: እልቅስ፡ እልቅስ አለኝ:: አምጳርጵር እግር ላይ ዘፍ ብዬ እንዳይወጡ ተማፀንኳቸው::

"ልከትክተው?" ሲል ያ ግሽርጥ አይን ይሰማኛል:: ብከተከት ይሻለኛል:: የተዋረደ፡ ክሰው ተራ የማያቆም ወንጀል:: የእኔን ንፅህና ማን ያውቃል? እግዚአብሔር ለአምጳርጵር አድልቶ ሁሉንም አመቻችቶ አስቀምጦልኛል:: "ደስ ይበልህ እግዚሀር..." በፊጣሪዬ ላይ ትንቢት መናገር ከጀለኝ::

አምጳርጵር እየተፍጨረጨሩ "ለእኔም ቢሆን ጠላቴ ቆፍጠን ሲል ነው ደስ የሚለኝ:: ላይሞት ይፈራል፡ ላይድን ይሸሻል ሲባል አልሰማህም? ይልቅ በርታ በልና እኔንም አበርታኝ"

"እንዴት? እንዴት አድርጌ?"

"ተነሽ አንቺ ደሞ፡ ምን ይወዝፍሻል? የክስ ማመልከቻሽን ግጥም አድርጌ እረቅልሻለሁ ነገ ፎሊስ ፊት ቀርበሽ ቃልሽን መስጠት:: ተነገ በስቲያ ተቤቱ ሆነ ተመስሪያቤቱ እየተዳፋ ዘብጥያ ይወርዳታል:: ለእኔም ቢሆን የመንፈቅ ሥራ አገኘሁ:: ለነገሩ እጅ-ተፍንጅ ስለሆነ ወርም አይሟገት::"

በተስፋ መቁረጥ እዚያው ወለሉ ላይ ዝርፍጥ አልኩ::



@BOOKALEM

ያ ግሽርጥ አይን "ለእግዝቢት ቆንጨራውን እንያዘውና" አለ፡፡

"የለም አንዱ ገድሎብን መና ከምንቀር እራሴን ይከላከልበት፣ እዚሁ ተውለት፡፡"

ሙቀት እንዳገኘው የበረዶ ክምር ዕለት ዕለት እየሟሟሁ የሄድኩ መሰለኝ፣ ላቤ፡፡

"የአቃቤ ህግ ምስክሮች፣ እንዲሁም የግል ተበዳይ ቀጥታ ወደ ቤታችን፡፡" እምጳርጵር ቀደሙ፣ ልጃቸው ግንድስ፣ ግንድስ እያለች ተከተለች፡፡ ግሽርጥ አይኑ ተከተለ፣ ያኮፈኮፈ ፊት ያለው ቀጠለ፡፡ ሦስተኛው የአቃቤ ህግ ምስክር እንደማመንታት እያሉ ወደ ኋላ ቀርተው፦

"አማላጅ ላከባቸው" አሉኝ፡፡

"ማንን? ምን ብዬ?፣ ለማን?..."

"ኤዲያ! ለእምጳርጵር ነዋ፡፡ እከላለሁ፣ እንዳሉኝ እሆናለሁ ብለህ አማላጅ ላክ፡፡"

"ሶስተኛ የአቃቤ ህግ ምስክር!" እምጳርጵር ውዬ ቆመው ይጣራሉ፡፡ ሰውየው እየተቻኮሉ ወጡ፡፡ "ከተከሳሽ ጋር አፍ ለአፍ ገጥሞ ማውራት ወንጀል እንደሆነ አጥተኸው ነው?" እየተንጫነጩ ሲሄዱ በድምፃቸው መራቅ አወቅሁ፡፡

"ምነው ፈረድክብኝ እለተ ሰንበት" ብዬ ወለሉ ላይ ተሰጣሁ፡፡ መሬት ላይ የተውት የገጀራ እጀታ ጭንቅላቴን አገኘኝ፡፡ እንደ መርፌ የቀጠነች ጠንካራ ህመም ተሰማኝ፡፡





# ምዕራፍ አራት

## 31 - ሀሰሳ አማላጅ

'ልፋ ያለው ቆዳ መጫኛ ይሆናል' አሉ፡፡ በዓይን-ህሊናዬ መላ ወረሳን አሰስኩ፡፡ አባባ ጀቢራ፣ እማማ ጉዶ፣ ኩይሳ፣ መምሬ፣ ጭፍን፣ ሽኩ፣ ድቡሴ፣ ልባሙ...

... ወረሳ ሽማግሌ የሌለባት መንደር መሆኗ ዛሬ ተሰማኝ፡፡ ቢሆንም ያሉትን አማላጅነት እጠይቃለሁ፡፡

አባባ ጀቢራ ዝም ብለው ሲያዳምጡኝ ቆይተው "አሁን ምን አድርግ ትለኛለህ?" አሉኝ፡፡

"አማላጅ ይሁኑኝ"

"እኔ?"

"አዎ"

"አይዋስ ቢዋሰኝ ከባለ ዕዳ ባሰኝ" ሲባል አልሰማህም? አሆሆሆሆ እምጳርጵርን እያወከው?..."

"ታዲያ ምን በጄኝ?"

"ግመል ምን ተጭኖሃል ሽመል፣ ምን ያወዛውዝሃል እመል አሉ፡፡ እምጳርጵርኮ ነገሬን ቀሙኝ ነው፡፡ የሚሆንልህ ከሆነ ሌላ አማላጅ ፈልግ"

እማማ ጉዶ'ጋ ሄድኩ፡፡ አፋቸውን ከፍተው አዳመጡኝና...

"እምጳርጵር ላይምረው አማፀነው፣ ላይበላው አበላሸው ነው፡፡ ትርፍህ አማላጅ ልክ ነበር ስለሆነ ዝም ብለህ መጥሪያው እስኪመጣ ጠብቅ"

"ከዚያስ?"

"ፍርድ ቤት እንዳደረገህ መሆን ነዋ፡፡ ወይ ታገባታለህ፣ ወይ አርባ ብር ትቀጣለህ፡፡"

እሳቸው የዘመናቸውን ደንብ ነው የሚያወሩት፡፡ የደጉን ዘመን፤

"እኔም ገና አንድ ፍሬ ሳለሁ ተጠልፌ ነው የተዳርኩት፡፡ አባ አደናግሬ ቤት ተነስቶ ለካ አድፍጦ ኖሯል፡፡ ታዲያ እኔ..."

ተረት እና ታሪክ እንዳላነፈንፍኩ ለጆሮዬ ተጠየፍኩ፡፡

ኩይሳ ፊቱ ድንገት ስንተርበት ተርበተበተ፡-

"ምነው? ደሞ ምን አሉህ? ምንድን?..." የተራራ መንቀጥቀጥ ያስከተለው ርዳት...

"እምጳርጵር..."

"እ? ምን አሉ? ደሞ ምን ነገሩዋቸው?..."

"አማላጅ እንድትሆነኝ ነው"

"አማላጅ ልሁንልህ ማለትህ ነው?"

"አ-ይ አንተ ለእኔ አማላጅ..."

"በዘዴ ላከውና ልግደለው አሉህ እንዴ? ነቂ ነኝ..." እየተገላመጠ ከአጠገቤ ተሰወረ፡፡

እንግዲህ ምን ቀረኝ?

ልፉ ያለው አንድ እንጨት ያስራል አለ፡፡ እንግዲህ ፀጉሬን ተላጭቼ፣ ከርቸሌ ወርጄ፣ ተረቴን መከምከም ነው፡፡

የወሬሳ እንኳሮች ለእሪ በከንቱ ኮልኮሊዎች ናቸው፡፡ ማን አክብሯቸው? ለጠላቴ እንኳን ያልተመኘሁት ጭንቀት ወረደብኝ፡፡ ተዋኝቶ በማይዘለቅ የጭንቀት ባህር መካከል ለእግር ማቆሚያ ብቻ





የምትበቃ የተስፋ ደረት መሬት ታየችኝ፡፡ በትምህርት ቤታችን ዳይሬክተርና አስተዳደር በኩል፡፡ መቼም ሥጋ ለሚመዝን ሰው ሁለቱም ክኪሎ በላይ ናቸው፡፡ በሌላ በሌላ ይመዘኑ የተባለ እንደ ሆን ነው ጉዱ፡፡ በተለይ አስተዳደሩ የስራኝን መቼም አልረሳውም፡፡ ያንን ታሪክ ሳስታውስ ለአማላጅነት እሺ እንደማይለኝ ገመትኩ፡፡

ገና ወደትምህርት ቤቱ ተመድቤ ስመጣ ያናገረኝ እሱ ነው

"ልጅ አለህ?" ሲል ነበር የጠየቀኝ፡፡

ድንግርግር እያለኝ እራሴን በአሉታ ወዘወዝኩ፡፡

"ዘግይተሃል፣ መዘግየትህ ታውቆሀል?"

የማይታውቅ ሰው እንዲህ የሚያናግር ጅል መሆን አለበት እያልኩ እራሴን ነተነኩለት፡፡

"ውለድ እንጂ - ውለድ"

በሌላ ቀን፣ በተናጥ ልዩነት "ወለድክ?" ይለኛል፡፡

እራሴን በአሉታ እነቀንቅለታለሁ፡፡

"ውለድ እንጂ፣ መዘግየትህ ታውቆሃል?"

ዝም እላለሁ፡፡

"ልጅ ማሳደግ በራሱ ፈጣሪን በእግባቡ ማገልገል ነው፡፡"

እንዴት? እስከለው ጠብቆ ሲያጣ ቀጠለ

"አየህ፣ የሰው ልጅ አስርቱ ትዕዛዛትን ማክበር የሚጀምረው ከወለደ በኋላ ነው፡፡ ልጁን ጥሎ እንዳይታሰር አይገድልም፣ አይሰር ቅም፣ በጊዜ ገብቶ ልጁን መንከባከብ ስላለበት አያመነዝርም፣ አይሰክርም፣ በተለይ ደግሞ ለልጁ አርአያ ለመሆን አይዋሽም፡፡ ይሄን ስታይ እግዚአብሄርን ማገልገል ነው አትልም?"

የአስር ልጆች አባት የሆነው አባቴ ቢያገኘው 'አዲስ አረኛ ከብት አያስተኛ' ይለው ነበር፡፡ እንግዲህ በቅርቡ የወለደ መሆን አለበት ስል አሰብኩ፡፡

አንድ ቀን ከስራ በኋላ ልጄን ካላሳየሁህ ብሎ ችክ አለ፡፡ የግዴን ተከተልኩት፡፡ መንገድ ላይ ስለ ልጅ አስተዳደግ ይነዘንዘኝ ነበር፡፡



@BOOKALEM

"ልጅን ምንም ሳትዋሽና ሳትደብቅ ማሳደግ ይጠበቅብሃል፡፡ እንደ ልጅ..."

ቤቱ ደረስን፡፡ ልጁ አራስ መስሎኝ ነበር፡፡ አምስት አመት ይሆነዋል፡፡ ቆቅ ቅልቅል ነው፡፡ እንደ አባቱ ትክሻው የጻበረ እንገት የሌለው ፍጥረት፡፡ ስንተዋወቅ ስሜን ስነግረው ከእንቅልፉ እንደባነነ ሆኖ አባቱን አየ፡፡

"ስለዚህ ሰው ነግረኸኛል?" አባቱን

"አዎ" ልጄን

"አዲስ ተቀይሮ መጣ..."

"አዎ" አባት

"ጅል ቢጤ ነው ብለኸኝ ነበር" ሲል ጠየቀ፡፡

እኔ ደነገጥኩ፡፡

"አዎ" አለ አባት ለልጁ ወደኔ ዞር ብሎ ደሞ "እንደነገርኩህ ነው፡፡ ልጅ ስታሳድግ መዋሸት አያስፈልግም"

"ግዴለም" አልኩ የሞት ሞቴን፡፡

"እውነቱን ስለነገርከኝ አመሰግናለሁ አባቴ" አለ፡፡

አባትየው "ምንም አይደለም" አለውና ወደ ማብራሪያ ገባ "እንደምታየው ነው፡፡ ጅል ሰው ገፅታው ይመሰክራል፡፡ ንቃት የለውም፡፡" አለ፡፡

"እውነቱን ስለነገርከኝ አመሰግናለሁ አባቴ" ልጁ

"ልጅን መዋሸት አይገባም ብዬህ ነበር" አለኝ፡፡

"እርግጥ ነው" አልኩ ቃሉ እንደ ሬት እየመረረኝ፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ገበታ ቀርቦ ተሰየምን፡፡ ልጁ ከኛ ጋር አንድ ላይ ይመገባል፡፡ አሁንም የትውስታ ማህደሩን በመበዝበዝ ላይ እንዳለ ያስታውቃል፡፡ በዝብዞ፣ በዝብዞ አዲስ የነገር ፋይል አገኘ፡፡

"ሆዳም ብጤ ነው አላልከኝም?

"ጉዴ ፈላ" አልኩና በጣቶቼ አክርሬ የያዝኩትን ጉርሻ አሳላሁ፡፡





"የእኔ ልጅ" አለ አባት፡፡ "ብዙ ጅሎች ሆዳሞች ናቸው፡፡ እንደነገርኩህ የእሱንም ሆዳምነት ለማረጋገጥ ፊቱ ላይ ትሪውን ምን ያህል እንዳራቆተ ማስተዋል ይበቃል፡፡"

"እውነቱን ስለነገርከኝ አመሰግናለሁ አባዬ"

አባት ወደ እኔ ዞር ብሎ "ልጅን መዋሸት ደግ አይደለም፡፡ አይመስልህም?"

ዝም አልኩት፡፡ እራሴን ጅልም፣ ሆዳምም አድርጌ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡ እነዚህ ትክሻቸው የዳበረ ነገሮች ሰድበውኛል ወይም እውነቱን ነግረውኛል፡፡ የአባቱ "ዋሌት ሳይዝ" ፎቶ የመሰለው ልጅ አእምሮው አሁንም እንዳላረፈ ያስታውቃል፡፡

"አባዬ?" አለ

"ወይዬ" አለ አባት እጁን ጉርሻው ላይ እንደብሎን ማጥበቅ እያሽከረከረ፡፡

"ሙሉ ደሞዝ ተቀብሎ አያውቅም በብድር ግቢውን"

"እርግጥ ነው" አባት...

"እውነቱን ስለነገርከኝ አመሰግናለሁ አባቴ"

"ዝም በሉ!" አልኩ ወፈፍ አድርጎኝ፡፡ "ዝም በሉ፣ አለባልተኞች!" ልጁ ላይ አፈጠጥኩ "አንተም አባትህም ወሬኞች"

ልጁ ከመደንገጥ ይልቅ "እውነቱን ስለነገርከን እናመሰግናለን፣ የአባዬ ጓደኛ" አለኝ፡፡

ከቤቱ እንዴት እንደወጣሁና እንደሄድኩ አላስታውሰውም፡፡ እጄን አለመታጠቤን እንኳን ያወኩት እቤቴ ስደርስ ነበር፡፡

እናስ? ይሄ ትክሻው የዳበረ አስተዳዳሪ ለአማላጅነት እሺ ይለኛል?

## 32 - አባሪነት

እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር ነጋ፡፡ ሰኞ ወፍ ሳይንጫጫ ተነሳሁ፡፡ ለባብሼ ሰዓቱን እንደ ፍቅረኛ መጠበቅ ጀመርኩ፡፡ ከሰዓት በፊት በሬ ተንኳኳ



@BOOKALEM

"ማነው?"

አምጳርጵር ከቤት ሳልወጣ መጥሪያውን ይዘው የመጡ መሰለኝ፡፡

"ከፈት እኔ ነኝ" ጀቢራ ነበሩ

"ምነው በደህና?" ከፈትኩ "እንቅልፍ ሳይወስደኝ አደርኩ፡፡ አሁን ሲነጋጋ አንድ ዘዴ መጣልኝ"

"ም-ምን? ምን ዘዴ?"

"ለፓርቲያችን አመልክትና የትብብር ደብዳቤ እጽፍ"

"የምን ፓርቲ? የምን የትብብር ደብዳቤ?..."

"እውነት ሳትሰማ ቀርተህ ነው?" ሄደው አልጋዬ ላይ ተቀመጡ

"እኔ'ቴ"

"ፓርቲ'ኮ አለን፡፡ የወራሳ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ወ.ህ.ዴ.ድ) ይባላል፡፡ ደርግ በግፍ ጓድ ላፊውን ቀይ ሽብር አላፋፈመበትም?

"አዎ"

"ደርግ ከወደቀ በኋላ የጓድ ላፊውን አርማ አነሳን፡፡ የኢትዮጵያ ሰርቆ አደሩ ፓርቲን ለማስመዝገብ ስንሄድ ይሄማ ሲያሳጥሩት ኢሰፓ ነው አሉን፡፡ እውነትም ምህፃረ ቃሉ ኢሰፓ ነው ለካ፡፡ ተጨንቅን፣ ተጠበብን፤ በኋላ ሁነኛ ሰው አፈላልገን ብናማክር ለምን አባር ድርጅት አትሆኑም? አለን፡፡

"ምንድነው አባር? ብንል

"ታብራላችሁ፣ ያብሯችኋል ቀላል ነው፡፡ አዎ በሉ ስትባሉ አዎ፣ አይ በሉ ስትባሉ አይ ይሄው ነው" ተባልን፡፡

"ጥሩ፣ ምን ገዶን ብለን ስማችንም ከዚያው ተሠጠን፡፡ ያኔ ነው ወራሳ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት የተባልነው፡፡

"ይሄንን የተመለከቱ እረ በከንቱዎች የተበለጡ መስሏቸው በወሩ እኛም አባር ድርጅት ነን አሉ ወዲያውኑ የእረበከንቱ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅትን (ኢ.ብ.ህዴ.ድ) አቋቋሙ፡፡"





"እ-ና...?" የምለው ጠፋኝ፡፡

"እናማ አባሮች ነን፡፡ የህብረት ስምምነታችን ላይ በአባርነት የምንሰራቸው ተጠቁመዋል፡፡ እኛ የሚደበድብ ሲኖር በአባርነት የምንሰራቸው... ባለፈው ምርጫ እረ በከንቱ ላይ አንድ አባርነታችንን ይጠይቃሉ፡፡ ባለፈው ምርጫ እረ በከንቱ ላይ አንድ ብሄራዊ ድርጅት እ.በ.ህ.ዴ.ድን ሊያሸንፈው ሲቃረብ የሙያ እገዛ ጠየቁን፡፡ ድምፅ ሳይሰማ ላፍ-ላፍ አድርገን ከጉድ አወጣናቸው፡፡ እረ እኛም ጋ ከምርጫ በኋላ ጥቂት ጉምጉምታ ተነስቶ ነበር፡፡ እረ በከንቱዎችን የሙያ እገዛ ጠየቅን፡፡ ያጉረመረመውን ጠርገው ጠርገው ጣሉት፡፡ 18 ሞቶ 26 ቆሰለ፡፡ በዚሁ ተደመደመ፡፡"

"እ-ና..."

"እናማ እ.በ.ህ.ዴ.ድ አምጳርጵርን እንዳያማልድህ ው.ህ.ዴድ የትብብር ደብዳቤ ይጻፍልህ፡፡"

## 33 - ውጥንቅጥ

መፍትሄ አምጳርጵር ከሆነ የአውራሪስም ወተት ቢሉኝ ለማለብ ከመነሳት ወደኋላ አልልም፡፡

ለካ የወ.ህ.ዴ.ድ. ፀሀፊ ፈላስፋው ኖሯል፡፡ በድፍን እጅግም ዝርዝር ሳልገባ ነገርኩት፡፡

"ደብዳቤ እንድንፅፍልህ አባል ሁን" አለኝ፡፡

"ምን ገዶኝ?" አልኩ፡፡

"ከስድስት ወር ፊት የተመዘገብክ እንዲመስል የሰባት ወር መዋጮ ክፈል" አለኝ፡፡

ባምስት ብር ተሰልቶ ከፈልኩ፡፡ ነገ ተመለስ ስባል "አሁኑኑ" ብዬ ፈትሬ ያዝኩ፡፡ ግሩም የትብብር ደብዳቤ ተፃፈልኝ፡፡

*"ለእረ በከንቱ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት አዲስ አበባ*

*ጉዳዩ፡- ትብብር ስለመጠየቅ*

*... ስማቸው ከላይ የተጠቀሰው ጠንካራ አባላችን ከድርጅታችሁ ሰው ጋር በገቡት አምባጓሮ የተነሳ የድርጅታችን*



@BOOKALEM

*ስራ መስተንገል አጋጥሞታል። በመሆኑም በእናንተ በኩል አምባገሮው ዲሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ እንዲቀረፍ ትብብር ታደርጉ ዘንድ አባርነታችሁን በመተማመን እንጠይቃለን።*

*የሕብር ድርጅት አባርነት ለዘላለም ይኑር!*

*ፊርማ*

እንጃ፣ ብቻ ደስ አለኝ። አምጳርጵር የሰው አማላጅነት የሚያጠረቃቸው ሰው አይደሉም። ይሁንና ዳይሬክተሩንና አስተዳደሩን መላኬን አልዘነጋም። በዚህና በዚያ እንደቆዳ መወጠር ክፋት የለውም። ይሳሳባል። የያዘለት እንደያዘ ይቀራል፣ የከሸፈውም...

* * *

የዳይሬክተሩ እና የአስተዳደሩ አማላጅነት ከሸፈ።

"እንዴት ነገር ተው ይባላል?" አሉ አለ አምጳርጵር። "እርስትህን ተው፣ ሚስትህን ተው፣ አገርህን ተው... ቢባል የወግ ነው። እንዴት ነገር ተው ይባላል? አሉ አለ "

አለ ጥርስ ሊላ የሌላቸው ጉንዳን ሰውዬ፣ ነክሰው ይዘውኛልና አይለቁኝም። እንግዲህ ለአስራ አምስት ዓመት ዘብጥያ የሚያገለግሉኝን የፀሎት መፅሀፍና የተረት መፅሀፍ... ልግዛ እንጂ። ለአምላኬ እየፀለይኩ፣ በእኔ እየተረትኩ ያን ሁሉ የአመታት አቀበት ታስሬ መገስገስ ነው።

ሆድ ባሰኝ። ቢሆንም የኢ.ቢ.ህ.ዴ.ድ.ን ምላሽ ተስፋ አድርጌ መጠባበቅ ያዝኩ። በመካከሉ የአምጳርጵር መጥሪያ ቢመጣስ? ጉዳዩ መንግሥት እጅ ገባ። ስለዚህ እኛ ብንስማማም ክሱ ይቀጥላል ማለት ነው።

ኡ-ሁሁሁሁ!

ጭጭ፣ ጭልፊት እንደዞረው ጫጩት አለ። አምጳርጵር እንደ ክፉ መንፈስ እጅ እግሬን አስረው ያለክልካይ ሊወቁኝ ነው። ጉንዳን የሆኑ ሰውዬ!

ጭንቀት እብደት ሊሆን ሲቃጣው ቢታገስልኝ በሚል ወደ ከንትር ገርሰሪ ሄድኩ። መጠጥ ቤት ጉዳዬን ሳይመዝኑ የማታለያ





ቦታ ነው። ነገ ከእሩሃቸው ሲሆኑ ሳይገኙ "አለን" ባዮች ጊዜአዊ ተስፋ ይሰጣሉ። በሰው ነገር ተነስቶ ተደፈርኩ ባይ ፎካሪም አይጠፋ። በመጠጥ ልቡና ሲያዳምጡት መፍትሄ የሚመስል ሀሳብ ሰጪም አለ። ሀሳቡ ግን ከመጠጥ እንክብል የተፈጠረ ጤዛ ነውና ነገ ወደ ልቡና በመመለስ ሳቢያ በንኖ ይጠፋል።

ከስካር በፊት፣ የአምጳርጵር ሥም ሲነሳ ያልራደ ወሪሳዊ አልነበረም። "ማንን ከሰሱ? ከማን ጋር ተጣሉ?" ጆሮ ይቆማል። ከዚያ ተሟግተው ከርቸሌ ያወረዱትና አድፍጠው የገደሉት... ወሪሳዊ ታሪክ ይከተላል።

ከሁሉም ባለታሪክ የእኔን የመሰለኝ የጨሌልጨሌ ነው። ጨሌልጨሌ ጠጥቶ ፎከረባቸው አሉ።

"አንድ እግር በርበሬ መንቀል አትቋችሁ፣ አምጳርጵር፣ ለብልቦ አቃጥሎ ፈጃችሁ" ይችን ነው የተናገረው። በነጋታው ጠዋት አምጳርጵር በሩ ላይ ቆመዋል። ሲወጣ መጥሪያ ዘረጉለት።

ጨሌልጨሌ የማታውን ዘንግቶ "ምን አደረኩ?" አላቸው አሉ።

"ያረከውን ከፎሊስ አፍ ትሰማዋለህ። እኔ አልደግመውም። ይደገምልኝ ካልክ ከፍተኛው ፍርድ ቤት መሀል ዳኛው ይደግም ልሃል" አሉት።

እግራቸው ላይ ወደቀ (እንደኔ)

እግራቸውን ነጥቀው ሄዱ (እንደኔ)

መሬት ላይ ዘጭ ብሎ ቀረ (እንደኔ)

በጀርባው ተንጋለለ (እንደኔ)

አማላጅ ላከባቸው (እንደኔ)

"እንዴት ነገር ተው ይባላል?" አሉት አሉ (እንደኔ)

ጭንቀት እብደት ሊሆንበት ቃጣው አሉ (እንደኔ)

እሱ የተጠቀሰበት ወንጀለኛ መቅጫ-አንቀፅ የስድስት ወር ዘብጥያ ጌታ ነበር አሉ። አንጳርጵር ያንሰዋል በሚል አውጠነጠኑና ሽኩኩን ላኩበት።

"ዛሬ ማታ ና እና እንነጋገር"

የቀጠሩት ቤታቸው ነው:: ፌቴልፌቴሊ ነገር ሊቀልልኝ መስሎት ማታ ጭለማ ለብሶ እምጸርጽር ቤት ሄደ:: ለነ ስለከሰሰኩት ሊገድለኝ ዝቶብኛል ብለው ሦስት ሽማግሌ ምስክሮች አዘጋጅተው ጠብቀውት ኖሯል:: ቤታቸውን ሲቆረቁር እጅ ከፍንጅ ተያዘ፡ ተመሰከረበት፡ መከላከያ ምስክር ያቀረበው ሽኩኩ ፌርቶ አላውቅም አለ::

ፌቴልፌቴሊ፡ መንግስት እያለ እንደሌለ በመቁጠር፡ በህግ የተያዘን ነገር በመናቅ፡ ጨለማን ተገን አድርጎ፡ ባላጋራው ቤት ድረስ ሄዶ...ብዙ ማጠናከሪያ አንቀፅ ተጠቅሶበት አምስት ዓመት ተፈረደበት::

"ያንሰዋል" ይላሉ እሉ እምጸርጽር:: "ሲወጣ ደሞ አዘጋጅቼለታለሁ"

ቶሎ፡ ቶሎ ፌለጥኩ:: 'መጠጥ ትራሱ መጠጥ ልብሱ የመጣው ቢመጣ አለመመለሱ' ብዬ ፎከርኩ "እገድላቸዋለሁ!" አልኩ:: ደግነቱ ስም አልጠራሁም አሉ::

"ተው" ያለችኝ ጭፍን ብቻ ናት:: ያንን ምሽት ፍፁም ሴት ሆና አመሸች፤ እኔን ስትለማመጥ ቤቴ ከመድረሴ በፊት ግን ከስካሬ ባንኜ ነበር:: ስላበዛሁት ጭፍን በጥፊ ብላኝ ነው ስካሬ የበነነው:: እንዳፈጠጥኩ ነጋ::

## 34 - የጫፉ-ጫፍ

ጠዋት ስራ ልሂድ አልሂድ እያልኩ በመንገዋለል ላይ ሳለሁ በሬን ሽኩኩ ቆረቆረ:: ስከፍትለት፡-

"ዛሬ ማታ ና እና እንነጋገር" አለኝ::

"ማን? ምን?" አላልኩትም:: የፌቴልፌቴሊ ጠስ:: አሁን እስራ አምስት ዓመት እንሰኝ ነው ሊያስጨምሩብኝ ደፋ ቀና የሚሉት?

"እሺ" አልኩት





'የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም' በደንብ ይፈረድብኝ:: እንዳውም ቆንጨራ ይገዩ እሄድላቸዋለሁ - ይምሽ ብቻ...

ከእኔ ይልቅ ጭፍን ተሻለች:: "ለምን ትፈነዳለሀ?" አለችኝ:: "ከቆንጨራ ይልቅ ለሦስት ምስክሮች ተናግረህ ሂድ"

"እምጸርጽር ላይ ማን ሲመሰክር?"

"እኔ፡ ልባሙና ፈላስፋው እለን"

* * *

ለአይን ያዝ እንዳደረገ እምጸርጽር ቤት ደረስኩ:: በፌራ ተባ በሩን ቆረቆርኩ:: ይሄኔ ምስክሮቹ ያቆበቁባሉ:: እምጸርጽርም ወጥመድ የገባች ቆቅ አድርገው ያስቡኝ ይሆናል:: የልጆች ድምፅ ከፍ ብሎ ይሰማኛል:: ዳግም ቆረቆርኩ:: በሩ ሲከፈት የልጆቹ ድምፅ እንደቀስት ተወርውሮ ጆሮዬ ውስጥ ተቀበቀበ::

በሩን የከፈተችው ሺ-ትርገጥ ነበረች:: ስለ ፍቅር እንደሚዘፍን ድምፅዋ ልቧን ይዛ ቀረች::

'ምን መሆኗ ነው?' ለመገላመጥም ወኔ አነሰኝ:: "እሉ?" አልኳት በደፈናው::

እንደመባነን ብላ "አለ፡ አባዬ!" እንደ ልጅ ቦረቀች::

ገባሁ:: እምጸርጽር ከአንድ ከሌላ ሰው ጋር ቁጭ ብለው አራት የልጅ ልጆቻቸውን እፊታቸው ደርድረው ትርኢት የሚያይ መስለዋል:: እኔን ከጉዳዩ ሳይጥፉኝ ቀጠሉ::

"በሉ ደግሞ ከእኔ ጀምሩ:: መሀከል ላይ የሳታችሁት ስም አለ" አሉ::

ልጆቹ ተነቃቁ

"እምበርብርን ማን ወለደ?" ልጆቹን ጠየቁ

"ከትከቴ" ልጆቹ መለሱ

"ከትከቴን ማን ወለደ?"

"ማን እይቶት"



@BOOKALEM

"ማን አይቶትንስ?"

"ማን ነክቶት"

"ማን ነክቶትን ማን ወለደ?"

"መጣባቸው" እና "አብጤ" ተደባለቀ…

"ተዉ እናንተ ልጆች ዛሬ፣ ጉድ ይፈላል"

"መጣባቸው"

"መጣባቸውን ማን ወለደው?"

"አብጤ"

"አብጤን ማን ወለደው?"

"አርዴ"

"አርዴንስ?"

"ደምለው"

"ደምለውንስ?"

"ሰው አይተርፈው"

ከአምጳርጵር ጋር ያለው ተጋባዥ ትርኢቱ ቢቸከውም እራሱን ላይ ታች እያወዛወዘ ስሜቱን ለመደበቅ ይጥራል።

"የሰው አይተርፈው አባት?"

"ያየህ ይሩጥ"

"ያየህ ይሩጥ አባት?"

"ያየህይራድ"

"ይበቃል ለዛሬ። ድሮ እኛ እስተ ሰባባ ትውልድ እናውቅ ነበር። አይ ዘንድሮ! ሁሉ ብላሽ። በሉ ግቡ ወደ ጓዳ፣ እራታችሁን ስጪያቸው፣ ከንቱ ቢሆኑም ቅሉ"

እኔ እንደ ፍርደኛ ተፈታቸው ቆሜያለሁ። ሁለቱም ምስክሮች እስከአሁን አልተከሰቱም። አምጳርጵር እራሳቸውንና ልጃቸውን ካልጨመሩ ምስክሩ አይሟላላቸውም። ጉሮሮዬን በአስታውሱኝ አፀዳሁ። በኋላ ግን ትክክል አለመሆኔ ገባኝ።





አምጳርጵር ገላምጠውኝ አጠገባቸው ወደ ተቀመጠው ዞሩ. "የ ማመልከቻ የሄፈው ከንቱ እሱ ነው" አሉ።

ሰውየው እንደ አዲስ አጨንቁሮ አየኝ "እስቲ ቱጭ በል" አለኝ።

አምጳርጵር እስኪያዙኝ ዝም ብዬ ቆምኩ

"አትቀመጥም እንዴ?" አምጳርጵር ተቱነጠነጡ። ቢሆንም የእሳቸውን ፈቃድ መጠበቁ አስደስቷቸዋል።

"ሲርበኝ ታንቅሁ፣ ሲጨንቀኝ ታረቅሁ መሆን አልጠፋኝም" አሉኝ። ዝም አልኩ። "ጥሩ አማካሪ አለህ። በእናት ድርጅቱ መጣህብኝ እንጂ እኔና አንተ እጥፈና ጠፊ ነበርን። የድርጅቶች አባርነት እንዲጠናከር በማሰብ ነገሩን በእንጥልጥል ትቼዋለሁ።"

ከእኔ ቀድሞ ሰውየው አመሰገናቸው።

"ጉልበት ሳም እንጂ" አሉ አምጳርጵር። ጉልበቷን እንድትሳም ይመስባል ይሄኔ ሺ-ትርገጥ መጥታ ተሰየመች። ከአምጳርጵር፣ ቀጥሎ የእንግዳውን ጉልበት ሳምኩ። ሳንገራግር …

"የእሷንም ሳም" አሉኝ። ከምር ጉልበቷን ስስም፣ ቁንቅላቷን ዳሰስ አደረገችኝ። መላ ሰውነቴን ሸገገኝ።

"እሱ የድርጅታችን አ.ቢ.ህ.ዴ..ድ ፀሀፊ ነው" አሉኝ። ከአንገቴ ቅንጥስ ብዬ አመሰገንኩ። "እኔ ደሞ የድርጅቱ ገንዘብ ያዥ ነኝ።"

"ድርጅታችን ለዚህ አስተዋፅኦ ወረታውን ይከፍላል" አለ ሰውየው።

ወረታው ክፍያ እኔን በማረድም ቢከናወን ተገቢ ነው እላለሁ። የተሸከምኩት ጭንቀት ሲራገፍ ትከሻዬንም አብረው ያወረዱት ያህል ቀለለኝ።

"ሲያዝሉት ነካሽ - ሲያወርዱት አልቃሽ፣ ነው ይሄ" አሉ አምጳርጵር።

የካድኳቸው የጦር ቃል ኪዳን ትዝ አለኝ። እንግዲህ እንቀጥል ማለታቸው አይቀርም። ከእስገድዶ መድፈሩ ወንጀል



@BOOKALEM

እስር ጊዜ ይሻለኛል፡፡ እስትንያዝ እንቀጥላለን፡፡ ስንያዝም እኔ አባሪ ተባባሪ ስለሆንኩ ፍርዴ ከእሳቸው ዝቅ ይላል፡፡ ይሄን አውቀው ይግቡበት፡፡

ሰውየው ብዙም ሳይቆይ እኔን መካከሮኝ ሄደ፡፡

አምጾርጵር እንደ አዲስ እየጎፈሉ ማንብነብ ጀመሩ፡፡

"የእሪ-በከንቱ ህዝቦች ዴሞክራሲዊ ድርጅት ቢባል እውነት መስሎሃል፡፡ አንዱም የእሪ በከንቱ መንፈስ የለበትም፡፡ አሁን ብፈልግ እንደ ዝንጅሮ መንጋ በሽመል ገብቼ እበትነው ነበር፡፡ ታዲያ ምን ይሆናል በገንዘብ ያዥነቴ ጥቂት የጎደለብኝ ስለለ እሱን በህግ እንዳይጠይቁኝ ማለሳለሻ ያልኩት ነው አማላጅነታቸውን የተቀበልኩት፡፡ አፈር ሳልገባ አንተ ዋጋህን ሳላሰጥህ አልቀርም፡፡ እትየኝ አይንህ ይፍሰስና"

እንኳን አይንህ ይፍሰስ ማለት ቢያፈሱትም ነጻ ከመውጣቴ ጋር አይነፃፀርም፡፡ ዝም አልኩ፡፡

"በል እስተዚያው ልጅን የምትከስበትን እኔንም የምትዛመድበትን ሀሳብ ከሽማግሌዎች መክረህ በዚህ ሁለት ቀን ተመለስ" አሉኝ፡፡

"እሺ" አልኩ ከቤት እስክወጣ ቸኩዬ

"ወሪሳ ሽማግሌ የለም፡፡ አማክራለሁ ብለህ ጭርሱን ገደል እንዳይሰዱህ" አሉኝ "ደሞ አስብበት ትፀድቅ ትኮነን ቢለው ቆይ መክሬ አስታውቃለሁ እንዳለው እንዳትሆን"

"እሺ"

"እሺ፣ እሺ፣ እሺ አይደለም፡፡ ተልብህ፣ ተቀልብህ ሁን፡፡ ባለፈው ተመጡት ያቃቢ ህግ ምስክሮች..."

"እ?"

"ወደ ኋላ ቀረት ብሎ አፍ ለአፍ ገጥሞ ያናገረህ?"

"እ?"

"እሱን አማክረኝ በለው"

"እሺ"





## 35 - ሌላ ጫፍ

እራሴን ቤቴ አገኘው ይመስል እዛ ደርሼ የምስራቹን ለራሴ ለመንገር ተቻኮልኩ፡፡ እዚያ በጭንቀት ተቆርጦ የቀረ ምንነቴ ሳይኖር አይቀርም፡፡ ደስታው አልሟላልህ፣ አለኝ፡፡

የእሪ በከንቱን ወንዝ በፍርሃት ሳልገላመጥ ተሻገርኩ፡፡ ወንዟ በእንቅልፍ ልቧ የምታልጎመጉም ትመስላለች፡፡ እሷም እንደኔ ያልተቋጨ ጉዳይ አሆዷ አድሮባት ይሆናል፡፡

ወደ ወሪሳ ለመግባት አቀበቷን እንደጀመርኩ አንዳች ነገር ከወደ ሰንሰሉ ብቅ አለ፡፡ ከድንጋጤ ብዛት መፎከርም፣ መሮጥም ተስኖኝ ደርቄ ቀረሁ፡፡ ጭለማው ላይ እንዳፈጠጥኩ

"እንዴት ሆንክ?" የሚል የሴት ድምፅ መጣ፡፡ ጭፍን ነበረች፡፡ ለካ በጭንቀት ሰንሰል ውስጥ ቆማ ትጠብቀኝ ኖሯል፡፡

"በስምምነት ፈታነው" አልኳት ምህረቱ በልመና፣ በውርደት በነፍስ ግቢ ነፍስ ውጪ እንዳልተገኘ እያስመሰልኩ፡፡

"አትለኝም"

እራሴን ላይ ታች ወዘወዝኩላት

ተወርውራ አተፈችኝ "ደስ ሲል"

ለካ ደስታዬ ያልተሟላው የምስራቹን ጭፍን ስላልሰማችው ኖሯል፡፡ እንዳቀፈችኝ ብዙ ቆየን፡፡ እቅፏን ሳታላላ አንገቴ ላይ ሳም አደረገችኝ፡፡ ለቃኝ ጎን ለጎን ወደ ወሪሳ ሄድን፡፡ መጨለሙ ለእኔም ለፀም ሳይበጀን አልቀረም፡፡ ሀፍረታችንን ቀንሶልናል፡፡

የወሪሳ ጭል-ጭል ያለ ብርሃን እንኳን አልተስማማንም፡፡ እኔ እጧን በግራዬ አድርጌ ወደ ቀኝ ፊቴን መልሼ ነበር፡፡ አንዳንዴ ሰርቆ ሳያት እጧ እኔን በቀኝዋ አድርጋ ወደ ግራዋ መለስ ብላ ነበር፡፡ እንደሄድን ከንትር ግሮሰሪ ደርሰን ገባን፡፡

ህዝበ-ወሪሳ ተሰይሟል፡፡ ቀድሞ የጀመረው በግማሽ ያህል አርቆን በስካር ነጉዷል፡፡ የወሬው ክፍፍል በስካር መጠን የተዳረሰ ይመስላል፡፡ ብዙ የሰከረ ብዙ ያወራል፡፡ ገና ሞቅም ያላለው ሲጠየቅ ብቻ ይመልሳል፡፡



@BOOKALEM

ልባሙ የቤቱ ማዕከል ሆኗል፡፡ አንዱን ይነቁራል (ነገር ይፈልጋል) አንዱን ይተርባል፣ አንዱን ያደንቃል፡፡ በመጨረሻ ወደ እኔና ሜፍን አይቶ፦

"ይሂ መርከብ (ጋባዥ) አልሰመጠም? (አልቸሰተም)" አላት

"አስታሬ (ኧረ ዝም በል)" አለችው፡፡

"ግን አረፍ ካፒቴን ነሽ፡፡ እስካሁን ባህሩን አላቋረጥሽም (ገንዘብን ጨርሰሽ ዕቃ ማሸጥ አልጀመርሽም)"

ሜፍን ፊቴን አይታ እንደገባኝ አውቃለች "ለምን ላሽ (ዝም) ብለህ አትመጥም? (አትጠጣም)" አለችው፡፡

ወደ ሌሎቹ ጠጪዎች ዞሮ "ባህር አቋራጭ ካፒቴን ምንድነው የሚባለው? አህጉር አቋራጭ?"

ሜፍን ቱግ አለች "አንተ እንዲህ አይነት ከእናትህ ጋር ትቀልዳለህ" ተነሳች "ከእኔ ጋ ተሰፋፍጠናል (ተደፋፍረናል) ወይ ትመርሸኛለህ፣ ወይ እመርሽሃለሁ (በምላጭ ትቆርጠኛለህ ወይ እቆርጥልሃለሁ)" ነብር ሆነች፡፡ እንኳን ተነታራኪዋን እኔን አራደችኝ፡፡

የልባሙ አይን ከእሷ ላይ ሲሸሽ አየሁት፡፡ የፍርሃት ጥቆማ ነው፡፡ ከአይን ቀጥሎ ልብ ይሸሻል፣ ከዚያ እግር ይከተላል፡፡ ልባሙ እግሩ ከመሸሹ አስቀድሞ ሰዎች መካከል እንዲገቡ በአይኑ ጋበዘ፡፡

"አይደብራችሁም እንዴ?" ነው የወረሳ ግልግል፡፡

በዚሁ አበቃ፣

ሜፍን ቱጭ ብላ የተቀዳላትን መለኪያ ጅን ወደ ውጭ ረጨች፡፡ በቅዱልኝ እንኳኳች፡፡ ሆን ብዬ ልባሙን አየዋለሁ፡፡ ስካሩ ከድንጋጤው ጋር አጋትሮት ፈርጥጧል፡፡ እኔን እንኳን በሙሉ አይኖቹ ማየት አልቻለም፡፡

እኔ ሂሳቤን ጀምሬአለሁ፡፡ ልባሙ እምጻርጵርን አይፈራም፣ ሜፍን ደግሞ ልባሙን አስፈራርታለች፡፡ እናስ?...

...እምጻርጵር ሊጣቸውን አእምሮዬ ላይ ቀሩ፡፡ ልጄን ካስ ብለውኛል፡፡ ተበድሬም ቢሆን ብር እሰጣታለሁ፣ እኔን





የምትዛመድበትን አስብ ብለዋል፣ የጦር ቃልኪዳናችንን አድሳለሁ፡፡ በቃ! ደስ የሚል ነፃነት ተሰማኝ፡፡ የቀረበልኝን መጠጥ እንስቼ ተጎነጨሁ፡፡

ሜፍን ግራ በመጋባት ታየኛለች፡፡ የፊቴ መፍገግ ከእሷ ፀብ ጋር የተያያዘ ሳይመስላት አልቀረም፡፡

"በቃ እርሺው" አልኳት

"ኧረ እናቱን አበዛው፤ ዛሬ ብቻኮ አይደለም" ድምጿ ጎላ ቢልም ልባሙ ያልሰማ ለመምሰል ሲሞክር አየሁት፡፡ ሜፍን ምን አይነት የፀብ ታሪክ ቢኖራት ነው ልባሙ የፈራት? አጓጓኝ፡፡

"ከፍንዳታ ጋር..."

"እሱ ነው ፍንዳታ? አንተን ይበልጣል - እሺ፡፡ ቢያንስ በአስር አመት ይልፍሃል፡፡"

"ኧረ ዝም በይ"

"ሚካኤል ቆማጣ ያድርገኝ"

"አይመስልም"

"መንግሥቱ ኃይለማርያምን ያኳተነ(የሰረቀ) እኮ ነው"

"ያኳተነ?"

"አዎ፣ ሰዓቱን ሰርቆታል"

"የት?" እንዲህ ያሉ ጨዋታዎች በእራሳቸው የሚያዝናኑ ይመስለኝ ነበር፡፡ ግን ባለፉት ሁኔታዎች እየተዝናናሁ የነበረው በነፃነቴ እንደሆን ገብቶኛል፡፡ ይኸው ዛሬ ሜንቀት ሲቀርልኝ አፈልጋቸው ጀመር፡፡

"ፍል ውሃ፣ ማስፋፊያ ተደርጎለት ሲመረቅ መንግሥቱ እየተዘዋወረ ሲጎበኝ ልባሙ እስኪቀርበው ጠብቆ፦ "የአምባ ልጅ ነኝ" ይለዋል"

"የአምባ ልጅ ነው እንዴ?"

"አይደለም የአምባ ልጅ ጓደኛ አለው፡፡ ከሱ የሰማውን ይዞ 'አባታችን' ይለዋል፡፡ መንግሥቱ ደስ ብሎት ጠጋ ብሎ ያነጋግረዋል፡፡ ለካ መንግስቱ ፍል ውሃውን ሲጎበኝ ሲገባ ገላውን

ታጥቦ ሰዓቱን ኮት ኪሱ ውስጥ አድርጎት ነበር፡፡ ልባሙ ሆዬ እያናገረ አኳተነው፡፡"

"ከዚያስ?"

"ከዚያማ መንግሥቱ የቤተ መንግሥት መግቢያ ወረቀት ሰጥቶት በቅርቡ መጥተህ እንነጋገራለን' አለው፡፡"

"ልባሙ ተቀብለ ሸል' አለ፡፡ በነጋታው ምድረ አኳታኛ ይታፌስ ጀመረ፡፡ ስውር (ነጭ ለባሽ) ወሪሳን ባዶ አደረገው፡፡ ምንድነው ሲባል የመንግስቱ ሰዓት ጠፍቷል፡፡

"ልባሙ ይሄን ሲሰማ መንግሥቱ በሰጠው ወረቀት ተጥታ ወደ ቤተመንግሥት ሄዶ ገባ፡፡ መንግስቱ ጋ ሲያቀርቡት 'አባታችን' አለው፡፡

"'ልጄ' አለ መንግሥቱ፡፡ ልባሙ አቅፎት ከኋላ የተንጠለጠለ ኮት ኪሱ ውስጥ ሰዓቱን ከተተለት፡፡"

"እሺ?"

"ምሳ ሰዓት ደርሶ ስለነበር መንግሥቱ ኮቱን ሲለብስ ከበደው እጁን ሲከት ሰዓቱ አለ፡፡ ስልክ አንሳና ወደ ህዝብ ደህንነት ደወለ፡፡

"'ሃሎ ጓድ መንግሥቱ ነኝ' አለውና ሰዓቱን ስላገኙሁት ፍለጋውን አቁሙ አላቸው፡፡ ልባሙ ስልኩ ውስጥ ምን እንደተባለ አልሰማም ግን መንግሥቱ እየተገረመ

"'ምን? አራት መቶ አርባ ሰባት ሰዎች ይዘን አራት መቶ አርባ አንዱ አምነዋል ነው የምትለኝ? በሉ ልቀቋቸው እናንተ ልጆች' ብሎ ስልኩን ዘጋው፡፡"

ከልቤ ሳቅሁ፡፡ ሳቁ ከልቤ ሲወጣ ደስ የሚል ስሜት እንደተካው ገብቶኛል፡፡ ምን እንደሆን ግን አላወኩም፡፡

## 36 - ሌላኛው የሥጋ ግድግዳ

በደስታ የተጠጣ ጤና ነው፡፡ ጠዋት ስነቃ ግድግዳው ቀረበብኝ፡፡ እጄን ወደ አሊጋው ጫፍ ስሰድ መውደቂያዬ ቅርብ ሆኖ ነበር፡፡ ወደ ግድግዳው እጄን ስሰድ ያ የሥጋ ግድግዳ አለ፡፡





ደነገጥኩ፡፡ ሺ-ትርገጥ ከነ ስጋ ቀልሷ እላዬ ላይ ያንሻበበች መሰለኝ፡፡ ተንዳ ልትተብረኝ? ብድግ አልኩ፡፡ መብራት አበራሁ፡፡ ማመን አልቻልኩም ጭፍን አጠገቤ ተኝታለች፡፡

"ምነው?" አለችኝ

"ኡይ" የምለው ጠፋ፡፡

"ምን ሆንክ?" ድምጿ ውስጥ ከለላነት አለ፡፡

"አብረን ያደርን አልመሰለኝም ነበር፡፡ እንዴት...?" መምጣቷን ስላልጠላሁት ወሬዬን ገታሁት፡፡

"ማታ ሰክረህ ስለነበር ልባሙ በኔ ደንቶ ቢወጋህስ ብዬ አብሬህ መጣሁ፡፡ አስገብቼህ ልመለስ አልኩና የቤትህ በር አይሆኑ ስለሆነ ገንጥሎ ቢወጋህስ ብዬ አብሬህ አደርኩ፡፡"

ልቤ አቀፋት፣ እጄ ፈራት፡፡

"ገና ነው፣ አትተኛም?"

መብራቱን አጥፍቼ ጎኗ ጋደም አልኩኝ፡፡ የማታው መጠጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ገላዋ በጣም ይሞቃል፡፡ ሱሪዋን ብታወልቅም ከላይ ቲሸርቷ እንዳለ ነበር፡፡

ልቤ ከእኔ ላይ ነስቶ እሷ ላይ ቢያርፍም እጄ ግን አልቻለም፡፡ ምነው ልቤን ባደረገኝ የሚል ሃሳብ መጣብኝ፡፡ ሁለታችንም ነቅተናል፡፡ ነገር ግን ትንፋሽ ጨምረን የተኛን መስለናል፡፡ በዚህ እንመሳሰላለን፡፡ በየልባችን ያለው ግን ላይመሳሰል ይችላል፡፡ እጄን ሰደድ ሳደርግ ወንድ ወንድን እንደነካው ሁሉ ቅፍፍ ብሏት ተፈናጥራ ብትነሳስ? ሺ-ትርገጥ እንዳለችው አፈንድጂ ገጀራ አወጣለሁ? ጭፍን ገጀራ የያዘስ ትፈራለች? እንዴ ተመችታም ቢሆን እንዴ ለመምታት ትናጠቃለች እንጂ፡፡

በእራሴ ተናደድኩ፡፡ ደስ የሚል ስሜቱን ገጀራ፣ ገጀራ እያልኩ አደበዘዝኩ፡፡ በረጅሙ ተነፈስኩ፡፡

"ምነው?" አለችኝ ጭፍን

"ምንም"

"ፈራህ?" ጥያቄዋ ውስጥ ያ የከለላነት ድምፀት አለ፡፡ ብታቅፈኝ ብዬ፡-

"እ" አልኳት፡፡

ለአጭር ጊዜ ዝም ብላ ተኛች፡፡ ተናደድኩ፡፡ ላልታቀዩ ነገር በፈሪነት መመዝገቤ ቆጨኝ፡፡

"እይዞህ፣ ነገም እዚህ አንተ ጋ መጥቼ አድራለሁ" ድምጿ ክርር፣ ግርር ያለ አልነበረም፡፡ ልስልስ፣ ቅዝቅዝ ብሎ ለሰካራም ልብ መድህን የሚሆን፡፡

እጇ መጥቶ እጄን ሲፈልግ ታወቀኝ፡፡ በጀርባችን እንደተንጋለልን እጇ ከክርኔ ጀምሮ ቁልቁል ወረደ፡፡ እንጓዬን አልፎ መዳፏ መዳፌን አገኘው፡፡ ጣቶቿ ጣቶቼን መጋጠሚያ ውስጥ ውሽቅ አሉ፡፡ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ልክ ሺ-ትርጥ ስትመጣ እንደምንቀረቀበው፡፡ ይሄኛው ግን ይጥማል፡፡

አሁን ልቤ ፈራ፣ ገላዬ ደግሞ በተራው ደፈረ፡፡ ሳላዘው ዞሮ እጇን እጄ ሳይለቅ ሊላኛው እጄ አልፏት ወደ ግድግዳው ሄደ፡፡ እፏም ዞራ ኖሮ መዳፌ ጀርባዋ ላይ አረፈ፡፡ ጭምቅ አድርጌ አቀፍኳት፡፡ አስጠጋኋት፡፡ ከሙቀቷ ውጭ ነፍስ ያለባት አልሆነችም፡፡ ማን ሳሚ፣ ማን ተሳሚ እንደሆን ሳይታወቅ መሳሳም ሥራ ላይ ውሎ አገኘሁት፡፡ ጭፍን ሲያቅፏት ፍፁም ሴት ናት፡፡ ያውም ተሸናፊ፣ ተንበርካኪ፣ ተረቺ ሴት... ከለላ የምትሻ ደካማ ሴት፡፡ ጥለኸኝ አትሂድ እፈራለሁ የምትል፣ ለሳር ቅጠሉ ተንበርካኪ፡፡

በመተቃቀፍ መካከል "እወድሃለሁ" የሚል የተጨቆነ ቃል ያፈተልካል፡፡ "እወድሃለሁ፣ ታሳዝነኛለህ"

"ለምን?"

"እኔንጃ" ጭፍን እኔ የማደርገውን ጠባቂ እንጂ ይሄ ይሁን፣ ይሄ ይቅር የምትል ባለመብት አልነበረችም፡፡ ከላይ የለበሰችውን ሳወልቅ ከጀርባዋ ቀና አለችልኝ፡፡ ትንሽ ጡት ሙትት ያለ ገላ፡፡ እንደ አቦ ሸማኔ ሽንጥ ብቻ ናት፡፡ በእያንዳንዱ የነርቬ ቅንጣት አጣጥማት ገባሁ፡፡ ሰው እንዲህ ይጣፍጣል?





ያን መሰል ተፈጥሮሽ ያን መሰል ቁመና
ያን መሰል ወረርሽኝ ያን መሰል ወዘና
ያን መሰል መከወን ያን መሰል ፍፅምና
ከወዴት ዘረፍሽው የትስ ይገኝና፡፡

ልቤ እንደ አዝማሪ ከባለቅኔው እንደበት እየተቀበለ ተወጣው!

በየፊናችን ደስታ ማጣጣሚያ ፋታ ወሰድን፡፡ ብዙ ጊዜ ወሲብን የሚከተለው ፀፀት ነው፡፡ ዛሬ ያ ፀፀት የታለ? ልቤን፣ መንፈሴን፣ አእምሮዬን... ፈተሽኩ፡፡ ፀፀት ያልተፈጠረ ያህል አልነበረም፡፡ እንኳን ፀፀት ሐፍረትም ድራሽ አባቱ የለም፡፡ ለምን?

ዞር ብዬ ተንጋላ ያቀረችውን ጭፍንን አየኋት፡፡ መንጋጋት በመጀመሩ በየስንጥቁና በየሽንቁሩ እምልጦ የሚፈስሰው የላመ ብርሃን ፊቷ ላይ ከፅልመት ጋር ትንቅንቅ ገጥሟል፡፡ ውስጧ ውስጥ እንደሆነች ያስታውቃል፡፡

"ፈራሁ" አለችኝ

"አይዞሽ፣ እኔ አለሁ" አልኳት፡፡ ፍርሃቴን አስመለስኩ፡፡

ዘወር ብዬ አቀፍኳት፡፡ ዘወር ብላ ተወሸቀችብኝ፡፡ "ምን አስፈራሽ?"

"ሁኔታዬ"

ቀና አድርጌ አፏን ሳምኳት፡፡

"ሁኔታሽ ደስ ይላል፣ ምን ያስፈራል?"

"በምን አወቅህ?"

"የእኔም ሁኔታ እንደዚያው አይደል? አውቀዋለሁ፡፡"

"ታድለህ" አለችኝ፡፡ "እኔ! የሚሰማኝ ከተሰማህ ታድለሃል፡፡"

ዝም አልኳት

"ምን ይሰማሃል?"

አሁንም ዝም አልኳት

"ንገረኝ ምን ይሰማሃል?"



@BOOKALEM

"ፍቅሮ እስከ ቅብሮ" አልኳት፡፡ በሀፍረት አንገቴ ውስጥ ገብታ ተቀበረች፡፡ ሁኔታዋን ለማየት ከአንገቴ ላላቅቃት ሞከርኩ፡፡ ክርር ብላ እቃተችኝ፡፡ ተውኳት፡፡ ሲወጣላት ንግግር ጀመረች፡፡

"መብለጥ የለም" አለችኝ

"እንዴት?" አልኳት

"ከተንቀዠቀዠ አራዳ የተረጋጋ ፋራ ይሻላል..."

ከት ብዬ ሳቅሁኝ፡፡፡

"እውነቴን ነው፡፡ ብዙ አራዶች ሊበልጡኝ ሲሞክሩ ጃስ ብያቸዋለሁ፡፡"

"እኔ ፋራ ነኝ?"

"በደንብ ነዋ!"

"ፈሪ ነኝ እንጂ ፋራ አይደለሁም"

"አንዳንዴ ምን እንደምትመስለኝ ታውቃለህ?"

"ምን?"

"በሽወዳችን እየተላተክ(እያሾፍክ) ዝም የምትለን"

"እንደሱ እንኳን አይደለም፡፡ ለመውደድ ስታመቻቺኝ ነው"

"አሁንማ እንዴ ወድጄሀለሁ"

"እውነት?" ብዬ አይኗን ለማየት ስሞክር እዚያው ጉድጓዷ ውስጥ ገባችብኝ፡፡ በግድ ፈልቅቄ አውጥቼ አፏን ሳምኳት፡፡ ያ ሙትት የምትለው አገልጋይነቷ መጣ፡፡ ስስማት እንኳን አፀፋ የላትም፡፡ ዝም ብላ መቀበል፡፡ መላ ሰውነቷ የሚመጣውን ለመቀበል ያለ ምንም መቋቋም ይጠብቃል፡፡ እንግድነቱን ሳላውቅበት አልቀረሁም፡፡

## 37 - እውን እልም

በፍቅር ተሞሽረን የተጫጉላ ቀናችንን በር ዘግተን ዋልን፡፡ ወደ ስራ አልሄድኩም፡፡ ሰው መዋያ ማደሪያን የሚያሰፋው ፍቅር ሲያጣ እንደሆን ገባኝ፡፡ ከሚጠላው ለመራቅ፡፡ ፍቅርማ ሲሆን





ይኸው አንዲት አልጋ ለመዋያ ማደሪያ በቂታ የለም? አልጋዋም በዝታ ተርፋ የአንድ ጣውላ ስፋት ተቃቅፈን ተኝተን የለም? የተቀረው የአልጋ ሥፋት በሌሎች ቢወሰድ ምን ተጎዳችን? የሚበቃንን ጥቂት ይዘናል፡፡

ሰው ፍቅር ሲያጣ በአካል ብቻ ሳይሆን በአእምሮም ይናውዛል፡፡ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ሳይንስ፣ ተረት፣ ድርሰት፣ እንቆቅልሽ... የፍቅር ማጣት ንውዞቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሁሉ የሚበልጥ ደስታ ከዝምታችንና ከተራ ወሬዎቻችን ውስጥ አግኝተናል፡፡ የእኔም ተረት፣ የእፀም ድርሰት ተረስተዋል፡፡

ሰው ፍቅር ሲያጣ መንፈሱ ብቻ ሳይሆን አካሉም ልክ ያጣል፡፡ (ምን ለማለት ፈልጌ ይሆን?) ካልሆነ ስለምን እኛን አልራበንም? ይሄንን የማስበው ፍቅር ላይ ተጥጄ አይደለም፡፡ ብቻዬን ተንጋልዬ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሎሚን ጋር ከተጠልኩ ፈላስፋ መሆኔ ነው፡፡ ተረቱ ቀረ፡፡

ወደ አንድ ሰዓት ገደማ ምናምን ለመቀማመስ ከቤት ወጣሁ፡፡ ከበላሁ ሃያ አራት ሰዓት አልፎኛል፡፡ ለፍቅር፣ ውስጤ የርሃብ ንዝንዝ ቀርቶልኛል፡፡ ከንትር ግሮሰሪ የምስር ሳንዱች ከበላሁ ከበቂ በላይ እንደሚሆን ገምቼ ወደዚያው አመራሁ፡፡ ለግሮሰሪዋ ጥቂት እንደቀረኝ ስሜን ከበስተኋላ ሰማሁ፡፡

ጠሪዬ ማን እንደሆን በቅጡ አልተገለጠልኝም፡፡ ፊታቸው ግን አዲስ አልሆነብኝም፡፡

"አቤት" አልኩ እንደ አስተናጋጅ በመሽቆጥቆጥ፡፡

"አረሳኸኝ? ቤትህ መጥቼ ነበር፡፡"

"እኔ'ጋ?"

"አዎ፣ ከአምጳርጵር ጋር..."

"አዎ ልጄ፣ አዎ--- አዎ ታዲያ..."

"ያ--ው እንደምታውቀው ነው፡፡ አምጳርጵር እንደሆኑ ልባቸው ከቂም በቀል፣ ቃላቸው ከበደል፣ እጃቸው ከመግደል በዝና አያውቅም"

"እ...ና..."



@BOOKALEM

"ቃል እስገብተውሃል መሰል"

"እዎ፤ ለነገ ቀጥረውኛል..."

"ታዲያ የሚሆነውን ከወዲሁ አትፈጣጥምም፡፡ እሳቸው እንደሆን ሰበብ ፈላጊ ናቸውና በጊዜ ገደብ አመሃኝተው ኋላ..."

"እንግዲህ የተጣለብኝን ለማድረግ ነው የቆረጥኩት፡፡"

"የተጣለብህ ምንድነው?"

"በግልፅ አላሉትም እንጂ ልጃቸው ገንዘብ እንድትካስ የሚፈልጉ መሰለኝ፡፡ ከእኔም ጋ ዝምድና ፈልገዋል፡፡ ባይሆን የልጅ ልጃቸው ሲገረዝ ዓይን አይዝና... "

"ቃል በቃል ያሉህ ምንድነው?"

"ያሉትማ ልጄን የምትከሰበትን፡ እኔንም የምትዛመድበትን ከሽማግሎች ምክር ነው፡፡"

ሰውየው ጥቂት የሳቅ ፍንጣቂ አመለጣቸው፡፡ በጨለማው ትከ ብዬ ተመለከትኳቸው "ምነው?"

"እይ፡ ወዲህ ነው"

"እንዴት ወዲህ? ግራ አጋቡኝ እኮ..."

"አሁን ነገሩ ሳይገለጥልህ ቀርቶ ነው?"

"ምን?"

"የአምጳርጽር ፍላጎት"

"እኔ እቴ..."

አሁንም ያቺ ቁራጭ ሳቅ እንደምራቅ ተፈናጥራ ካፋቸው ውጭ ዋለች፡፡

"ምንድነው?" ትዕግሥቴ አለቀ፡፡፡

"አምጳርጽር የጠየቁህ ሁለት አይደለም አንድ ነው፡፡"

"እንዴት? ልጃቸውን መካስ እሳቸውን መዛመድ..."

"ገባኝ - ገባኝ፡፡ ልጃቸውን እንድታገባ ይፈልጋሉ፡፡ ይኸው ነው፡፡"

"ምን?"





"እዎ"

* * *

ያን ቀን ማታ በህልሜ ልበለው በትዝብቴ እንጃ ሺ-ትርገጥ እላዩ ላይ ያኮፈኮፈ ጉብታ መስላ ስትንጠረበብብኝ አደረች፡፡ ሰውነቷ በጓል፡ በቋጥኝ፡ በቁጥቋጦ... የተሞላ ይመስለኛል፡፡ እንደ መካድ የሚቃጣው የሰውነቷ አፈር ቋጥኞችን መፈቢሱ እያሳጣ፡ ሊናድብኝ ሲንሸራተት፡ እኔም ሰባትት አደርኩ፡፡

"ብ-ስ-ሙ-አ-ብ-ው-ው-ል-ድ-ው-ሙ-ን-ፈ-ሱ-ቅ-ዱ-ስ-"

አጠገቤ ጭፍን የለችም፡፡ ሺህ አመት አብራኝ እንዳደረች ሁሉ ሺህ ጊዜ ቅር አለኝ፡፡ ትናንት ከንትር ግሮሰሪ ስጠጣ ባመሸም ሳትመጣ ቀርታለች፡፡

"የት ሄደች? የት አመሸች? የት አደረች?" እንደ ሲጋትም እንደ ቅናትም አደርገኝ፡፡

ማታ ከሰውየው ጋር ከንትር ግሮሰሪ ቁጭ ብለን ተወያየን፡፡ በቅድሚያ ሊሆን እንደማይችል ተናግሬ ነበር፡፡ ሰውየው በተረጋጋ መንፈስ መከሩኝ፡፡

"ናዳ መጣልህ ቢሉት ተከናንቤአለሁ አለ አሉ?"

ተረት እንደምወድ ስለሚያውቁ እንደሆን አልገባኝም ሰው ሁሉ በተረት ሊረታኝ ይጣጣራል፡፡ እኚህም ሰው እንደ ሺ-ትርገጥ ገላ ባኮፈኮፈ ተረት ሊቀብሩኝ ይጣጣራሉ፡፡

"የት ትሄዳለህ ቢሉት እሁዳዳቸው፡ ምን ያሮጥሃል? ቢሉት ውቃቢያቸው' እና አምጳርጽር በህይወታቸው ላንተ ሲለሳለሱ ማየቴ ነው፡፡ የጠየቁትን ቢያጡ እጥፍ ድርብ ጠላትህ ሆነው የሆነ ያልሆነውን ጨማምረው ከወህኒ የሚወጣው እራሳህ ነው፡፡"

ጭፍን ትዝ አለችኝ፡፡

"'ይጣልህ፡ መገልበጥ እያለልህ' ይባላል፡፡ አሁን እሺ፡ እሺ ባላቸው ከዚያስ በተረጋጋ መንፈስ ስር ስሩን የታሰረብህን ትፈታለህ፡፡"

አምጳርጽር ከሺ-ትርገጥ ጋር የሚኖሩት ዝምድና እግር ብረት ሆኖባቸው ሳይሆን አይቀርም፡፡ እነዚያ በእሳቸው ሽምቀቆ

እንድገባ ወጥመድ አበጁብኝ። የኩነኔ ኑሯቸውን በሙሏ አስተላለፉብኝ።

ዙሪያዬ አደጋ ባረገዘ ካብ ታጥሮአል። ልዝለልህ ብሎ ተንዶ ይገድለኛል። ያለኝ መውጫ አንድ ነው። ያ መውጫም ፒ. ትርጉጥን ማግባት።

"እግዜር ይይልዎት አምጸርጽር"
ከዚህ ሌላ ትዝብት ውረሱ፣
ሳይነጋ እንዳስመሸብኝ፣
ጊዜና ትውልድ ይፍረደን
ሳልነቃ እንዳስረፈዱብኝ።

የባለቅኔን እንደበት ተዋስኩ።

## 38 - *ሥጋትና ቅናት*

የኢሪበከንቱውን ሰው ከዳይሬክተሩና ከአስተዳደሩ ጋር አያይዤ ወደ አምጸርጽር በአማጭነት ላኩዋቸው። አምጸርጽር የማሰቢያ ጊዜ ይሰጠኝ አሉ አሉ። ለሳምንት ቀጠሮ ተያዘ።

በድንጋይ ከተካበው ወህኒ በስጋ ወደተገነባው ዘብጥያ ለመውረድ አንድ ሳምንት ቀረኝ። ህልሜ ሁሉ በሺ-ትርጉጥ ተሞላ። መሬት ስቆም ተራራ፣ አላይዋ ላይ ሰወጣ ገደል ሆና ትታየኛለች። የሰላም እንቅልፍ ጠፋ።

አንዳንዴ ደሞ እንደ ደብረ ዳሞ ተራራ በመጫኛ ገላዋ ላይ ስጉተትባት ይታየኛል። ቀና ስል ጎታቼ አምጸርጽር ናቸው። ወደ ላይ መውጣቴም፣ ወደ ታች መውረዱም ጭንቅ የሆነበት አጋጣሚ ላይ እንዳለሁ እነቃለሁ።

እንኳን ከእንቅልፌ ከአፍላ ፍቅሬ ተናጠብኩ።

ጭፍንን ካየኋት ሁለት ቀን አለፈ። በጭንቀት መካከል እንደ ክረምት ፀሀይ ትውስታዬ ላይ ብልጭ ብላ ትጠፋለች። ስጋትና ቅናት ልክ ድሪያ ላይ እንዳሉ አባቦች ተጎናንነው ይጎበኙኛል። ስጋትና ቅናት ኃይለቃል ብቻ ይለያቸዋል እንጂ ጎረቤታሞች እንደሆኑ እነሆ አየሁ!





"የት ሄደች?" ስጋት

"የት አባቷ ሄደች?" ቅናት።

በሦስተኛው ቀን ከስራ ተመልሼ ቤቴ ስደርስ በሯ ገርበብ ብላለች። ውሻ ወይ ድመት የከፈታት መሰለኝ ነበር። ስገባ ጭፍን ፊቷን ወደ ግድግዳ መልሳ ተኝታለች። አልጋው ላይ ከእሷ ሌላ የተቋጠረ ፌስታል ይታየኛል።

ተርበተበትኩ። ያደፈጠ ናፍቆት ሆ! ብሎ ወረረኝ። ትልበት አጣሁ። የጠረራው አፍላነት ጋብ እስኪል ቆሜ ጠበኩ። ጫፉ ወዳልጋው ተጠግቼ ባያትም ጭፍን የምትነቃ አልሆነችም። የተቋጠረው ላይ ቁጭ ብዬ ፌስታሉን ወደ መሬት አወረድኩ። ልብስ እንደሆን ገብቶኛል።

"አብሬ ልኑር ልትል ይሆን አምላኬ?" ቀልድ የተጣባው ህይወቴ በሺ-ትርጉጥ ጣጣ ላይ ይሄንን አክሎ መሳቂያነቴ ሊቀጥል መቻሉ አያጠራጥርም።

አልጋው እየተንዘፈዘፈ ነበር። ዞር ብዬ አየሁት። የጭፍን ሆድ እየተንቀጠቀጠ ነው። እያለቀሰች መሆን ገባኝ። ምንም ሳልላት ደጃፉን መለስ አድርጌ መጣሁ። ከጀርባዋ ተኛሁ። እጄን በብብቷ ውስጥ አስገብቼ አቀፍኳት። ለቅሶዋ ለረጅም ሰዓት ቀጠለ። በእንባዎቿ ቅናቴ፣ ምክንያቴ፣ ንዴቴ... ሟሙቶ አዘኔታዬ ደረጀ።

ጭፍን ወንዳወንድ ብቻ አይደለችም። ፍፁም ወንድ ናት። ስታለቅስ የምትደበቀው ለዚህ እንደሆን ገብቶኛል።

"ከወዳጅ ዘመድ ርቆ
እንጀቱን በእንጀቱ ታጥቆ
ተሸሽጎ ተገልሎ፣ ተሸማቆ ተሸማቆ
ከቤተ ሰው ተደብቆ
መሽቶ የማታ ማታ ነው፣
ሌት ነው የወንድ ልጅ እንባው
ብቻውን ነው የሚፈታው።...
ብቻውን ነው የሚረታው።.."

የባለቅኔው ቅኔ የሎፍን ሲቃ ማባሪያ፣ መጠለያ አደረኩት፡፡ እኔ ያየሁትን ገጣሚው ቢያይ ምን ብሎ ያርመው ኖሯል? "ወንድ" አጠገብ በቅንፍ "ወንዳ ወንድ" ይጨምርበት ኖሯል?

ሎፍን ገልመጥ ብላ "መጥተሃል እንዴ?" አለችኝ አሁን እንደነቃ አስመስላ፡፡

"እ" ብዬ እንገቷን ሳምኳት፡፡

የመለየያ ገና ብዙ እስማታለሁ፡፡ ያቀፋት እጄን አሸት አሸት አደረገችው፡፡

"የት ጠፋሽ?"

ዝም

"የት ጠፋሽ?"

"ታስሬ"

"እ--- ለምን?"

እንዲት የሳቅ ፈንዲሻ ከነፈረ ሆዷ ተፈናጥራ ደረሰችኝ፡፡

"እውነቴን እኮ ነው፣ ለምን..."

"በመንግሥት ግልበጣ"

"እ? ለ--- ለምን አንቺ እዛ ውስጥ..."

"እስኪ ዝም በል! ሌላ ምን አድርጌ የምታሰር ሆኖ ነው የምትጠይቀኝ?"

እውነትም ጅል ነኝ፡፡ አስተዳደሩና ልጁ ትዝ አሉኝ፡፡ ሲስቁብኝ ታየኝ፡፡

"እ...ና..."

"አሁን ጥያቄ አያስፈልግም ዝም ብለህ እቀፈኝ፡፡" ፊቷን ወደ እኔ መለሰችው፡፡

ጊዜአችንን ለዝምታ አስረከብን፡፡

ሎፍን የቀድሞዋን አልሆነችም፡፡ ከአገልጋይነት እራሷን ወደ ተገልጋይነት ቀይራ ነበር፡፡ አሳሳሟ፣ ዳበሳዋ፣ አስተቃቀፏ ሁሉ ኃይል ወዳለው ድርጊት ተቀይሯል፡፡ እኔ ተቃራኒዋን ሆኜ





ተቀበልኳት፡፡ እንደ እሷ፣ እንደበፊቷ ሙትት ያለ ተንከላዋሽ ሆንኩላት፡፡

* * *

ከሁሉም በኋላ...

... በጀርባችን ተንጋለን የየፊና ጉዞ ቀጠልን፡፡

ለእኔ የሰባት ቀን የእግር ጉዞ የማያጠናቅቃት ሺ-ትርገጥ ከፊቴ ተንጥፋለች፡፡ እንደ ተባይ የመጫሚያዋን አቀበት በመጫኛ ታስሬ ወጥቼ አውራ ጣቷ ላይ ቆሜ አሻግሬ የማይ ይመስለኛል፡፡ ቀለጥሟን ደትድቴ ገና ጉልበቷ ጋ ሳልደርስ ጀንበር ታዘቀዝቅ ይሆናል፡፡ ማልጄ ብገሰግስ ሎፍን አልፌ ሆዷ መጋጠሚያ ስርጥ ውስጥ አዳር አረጋለሁ፡፡ በቀጣዩ ቀን የተሳሰረ ጡንቻዬን አፍታትቼ ጉዞ ብቀጥል ረባዳውን ጨርሼ እንብርቷ አካባቢ ድንኳኔን እጥል ይሆናል፡፡

የአራተኛው ቀን ጉዞ በሁለት ተራሮች መካከል የሚከናወን ነው፡፡ ተራሮቹ ሎላዳ ዝንጅሮ ዋሊያ ሳይኖርባቸውም አይቀር፡፡ የተራሮቹ መጋጠሚያ ከፍተኛ ሙቀት ስለማይቻል የጊግራ ተራራውን በመጠኑ ወጥቶ መጓዝ ይሻላል፡፡ ከደረት እስከ አንገት ያለው ጉዞ ሌላ አንድ ቀን ጠያቂ ነው፡፡ የመንገጭላዋን ዳገት ማልዶ ለመጀመር በጊዜ መተኛት ግድ ነው...

"ሰማሁ" አለች ሎፍን

"ምን?"

"የአምጸርጽርን ልጅ ልታገባ..."

ፊቷን ወደ ግድግዳ መለሰች፡፡ የምለው ጠፋኝ፤ ማልቀስ እንደ ጀመረች ገባኝ፡፡ ቅጡ ጠፋኝ፡፡ ሎፍን ሰበብ ፈልጋ በእኔ ምታለቅስ መሰለኝ፡፡ ወደሷ ዞሬ የሚንቀጠቀጥ ሆዷ ላይ እጄን ጣል አደረኩ፡፡

ሲበቃት ዞራ ትክ ብላ አየችኝ፡፡ ደግነቱ የቤቱ ብርሃን መደናገዝ ጀምሯል እንጂ አይኖቿ ይገድሉኝ ነበር፡፡

"ግን ምን መሆኔ ነው?" እራሷን ጠየቀች፡፡

እራሷ ለራሷ ምላሹን ትስጥ ብዬ ዝም አልኩ፡፡

"እንዲህ መሆኔን ጀለሶቼ ቢያውቁ ምን ይላሉ? እኔ ላንተ እንዲህ መሆን ነበረብኝ?..."

ዝም አልኳት

"ኧረ እንዴ... ይሄ ሺም (ውርደት) ነው፡፡"

የኩቱ እራድነቷን አወጣችው፡፡

"ይመችህ" ብላኝ ካልጋው ላይ ተፈናጠረች፡፡ ሱሪዋን ታጠቀች፡፡ ምንጭርጭር እያለች ፌስታሏን አነሳች፡፡

"የት ልትሄጂ..." እጇን ለመያዝ ሞከርኩ፡፡

"እንዳትነካኝ!!" አለችኝ፡፡ የልባሙ ጠስ፡ ጥንቡሳስ...

"መደፋፈራችን እዚህ ላይ ይብቃን፡፡ አይመስልህም?" በሩን ከፍታ ወጣች፡፡

ወናዬን ቀረሁ፡፡

* * *

ለምንም ነገር ፍላጎትና ስሜት አጣሁ፡፡ በሬን ዘግቼ አልጋ ላይ ተንጋለልኩ፡፡ ለካ አለኝ ብዬ ያልቆጠርኩት ብዙ ነገር ነበረኝ፡፡ አሁን ሳጣው ታወቀኝ፡፡ የመብላት ፍላጎት ሀብት ነው፡፡ አሁን እርሱ የለኝም፡፡ የመጠጣት አምሮት ነበረኝ - አሁን እሱን ፀጋ ተገፍፌአለሁ፡፡ የማፍቀር፡ የመፈቀር ጉጉት ነበረኝ - አሁን እሱ ህልም መሆኑን አረጋገጥኩ፡፡ የሥጋም ሆነ የመንፈስ ጥያቄዎቼ በንነው ጠፍተዋል፡፡ በድን ሆኜ የመንጋለል ግዴታዬን እየተወጣሁ እገኛለሁ፡፡ ዘልአለማዊ መንጋለል፡፡

እጅ፡ እግር፡ አይን፡ ጆሮ፡ ምላስ፡ አፍንጫ፡ ልብ፡ ሳንባ፡ ኩላሊት... ለበድን ምን ያደርግለታል? መንጋለል የሚጠይቀው ጀርባ ብቻ ነው፡፡ ጀርባ ደግሞ አለኝ፡ በቃ፡፡

ለምን ያህል ጊዜ እንደተንጋለልኩ አላውቅም፡፡ ብቻ ከሞት አፍ ተመንጭቆ እንደመላቀቅ ያለ ነገር ተከሰተ፡፡ በሬ ተበርግዶ እየተልመጠመጠች ከግድግዳ ጋር ተላተመች፡፡ ትንሳኤ ሙሙታኔ





በድንግጿ ታወጀ፡፡ ወደበር ስመለከት ጭፍን ይዛ ከወጣችው ፌስታል ጋር ገባች፡፡

"እንግ ፍቅር እሲዘህ ተኝተሃል አይደል?" አለች፡፡ በጣም መስከሯ ያስታውቃል፡፡ ፍቅር የያዛት ሳይሆን የተቀማችውን ማስመለስ ተስኗት በቁጭት የቆመች ትመስላለች፡፡ ፌስታሏን እንደቆመች ጣለችው፡፡

"እናትህ አፈር ትብላ" አለች፡፡ ስድቧ በወኔ የተደገፈ አልነበረም፡፡ አሁንም በተስፋ መቁረጥና ምንም ማድረግ ባለመቻል ስሜት ውስጥ ያለች ትመስላለች፡፡

ቀጭ አልኩ፡፡

"ወጠምጠጫም!" (ድግምታም!)

ዝም አልኩ አልፈራኋትም፡ አልተናደድኩባትም ግን አሳዘነችኝ፡፡ ስለእሷ ሞቼ መነሳቴን ማን በነገራት? አልጋውን እየተመተምኩ ተቀመጭ አልኳት፡፡

"ካንተ ጋር? ብሞት! አይገርምህም፡ አላደርገውም" የቆመችበት ትወዛወዛለች፡፡ በተከፈተው በር በኩል ወሪሳዎች ብቅ ጥልቅ ይላሉ፡፡

"አንተ ፍቅር አሲዘኸኝ ከተረሁማ ሞቻታለሁ፡፡"

በሩን ለመዝጋት ስሄድ ሳለመያዝ በማሰብ ሽሽት አለችኝ፡፡ አልፌያት በሩን ስዘጋ ጀርባዬን ላላ አድርጋ ደለቀችኝ፡፡ ዞር ስል ለሌላ ዱላ ተዘጋጅታለች፡፡ ሁለት እጆቿን ያዝኳት፡፡ የውሽት ተፍጨረጨረች፡ ለመናከስ ሞከረች፡፡ ይሄ ሁሉ ያልቻለች መስላ ለመሸነፍ እንደሆን ገብቶኛል፡፡ ሁለት እጇን እንደያዝኩ አልጋ ላይ ጣልኳት፡፡ እንዳትመታኝ የሰጋሁ መስዬ እላይዋ ላይ ሆንኩ፡፡

"ቢቃ ይቅርታ፡ ይቅርታ አድርጊልኝ" አልኳት፡፡

ምንም ማድረግ ባልቻለ ሙድ (የእሷ ንግግር ተጋብቶብኛል?) ማልቀስ ጀመረች፡፡ እኔም በማባባል ሙድ አቅፌ ለመሳም ሞከርኩ፡፡ ግራና ቀኝ ፊቷን እያዟዟረች ሳለመሳም ተጣጣረች፡፡ በመጨረሻ ግን ተወችውና ምላሽ ሳትሰጠኝ መሳሜን ቀጠለች፡፡ ነገሩ በዚሁ አልቀረም ለመሳሚ ምላሽ ትሰጥ ጀመር፡፡

ወደ መሬት የተንጠለጠለ እግሯን እንስቼ አልጋ ላይ አወጣሁት፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ሚማዋን ያወለቅሁላት፡፡ የጠፋው ረሃቤ ተገኘ፡ ያጣሁት ጥማቴ ተመለሰ፡ የማፍቀርና የመፈቀር ጉጉቴ እጥፍ ድርብ ሆኖ ገባልኝ…

## 39 - ፍቅር እስከ ትዳር

"እንኳን ደስ ያለህ" አስተዳደሩ ሲያቅፈኝ ተንደረደረ፡፡

"እንኳን አብሮ ደስ ያለን" ለመታቀፍ ተዘጋጀሁ፡፡ አቅፎኝ፡ ተንፍሶ

"ይሄን ምሥራች ለመንገር ጓጉቼ በጠዋት መጣሁ፡፡ በር በሩን ላይ ነው የረፈደው፡፡"

ነፃነቴን ፍፁም ሊሆን እንደሆን ይሰማኛል፡፡ እምጰርጵር ጋ ከተላኩት ሦስት እማሬዎች አንዱ አስተዳደሩ ነው፡፡ እምጰርጵር ለእሱማ አልደርግም ብለዋል ማለት ነው፡፡ በትዳር ፋንታ እሪ በከንቱን ተሸከመህ ዓለምን ዙር ቢሉኝ ይሻለኛል፡፡ ደግሞም አደርገዋለሁ፡፡ እሪበከንቱ ከሺ-ትርጓጥ አይከብድም፡፡

"ይኸውልህ" አለ አስተዳደሩ "ይኸውልህ ከሦስት ሰዓት ድርድር በኋላ አባትየው እሺታቸውን ሰጥተውናል"

ሞት ተፈርዶብሃል ቢሉኝ እንዲህ አልደነግጥም ነበር፡፡ ጠላሁት፡፡ ይኼን አንገት የሌለው የአንድ ልጅ አባት በለው በለው አሰኘኝ፡፡

'ጠመንጃ ያለ ጥይት ዱላ፡ ወንድ ያለ ሴት ነሁላላ ይባላል' አለ፡፡ አስተዳደሩም ተራች ነው? ተረት የሌለበት የታባቱ ልድረስ?

'ከእንግዲህ ልጅህን ወልደህ የእግዚአብሄርን ትዕዛዛት መፈፀም ነው፡፡ ልጅህን ሳትዋሽው ቃል ግባልኝ፡፡'

ሺ-ትርጓቶን ማግባት ገደል፡ ከእፎይ መውለድ ደግሞ መቀመቅ መሆኑን አስተዳደሩ አልተረዳም፡፡ አስኮንኖኝ እንጨፍር ይለኛል፡፡

'ልጅ ከአንጉል፡ እህል ከገራንጉር' ይባላል፡፡ መቼም ዞሬ ዞሬ ከተረት ቂጥ ሥር አልጠፋ፡፡





* * *

መርዶ ሀንሼ ወደ ቤቱ፡፡ ቀፍን ጠዋት እንደተኛች ጥያት ወጥቻለሁ፡፡ ምሳ አብረን እንደምንበላ ተቀጣጥረን ነበር፡፡

ወደ ቤት ስዘልቅ ነባሩን የአፈር ሽታ አጣሁት፡፡ በምትኩ የትኩስ ወጥ ሽታ ቤቱን አውዶታል፡፡ አላመንኩም፡፡ ያቺ እንደ ዱካ በእሷ ደፍቼ የምቀመጥባት ብረት ድስት ተጥዳ ትንተከተከለች፡፡ ቀፍን ወደ ግድግዳ ዞራ ተኝታለች፡፡

"ኧረረረረረረ…" ስል ቀፍን በሀረፍት እግሯን ሰብስባ አደፈጠች ወጥ ስለሰራች መሆኑ ነው፡፡

"ግና ወሪሳ ስገባ ነው የሸተተኝ፡፡ የማነው ወጥ? የትኛዋ ባለሙያ ናት የሰራችው? የእሷ ባል ማን ይሆን? እንዴት ብትወደው ነው እንዲህ ተጨንቃ የጠበቀችው? እያልኩ…"

ሀፍረቷን አባባስኩባት፡፡ ከኋላዋ ትከሻዋን ያዝ ሳደርጋት በሌቀቀኝ መንጨትጨት ብላ የበለጠ አደፈጠች፡፡ እንገቷ ላይ ሳምኳት፡፡ ወዲያው በወር ብላ በማተፍ ፊቷን ከእይታዬ ለመሸሸግ ሞከረች፡፡ ሲታፍር የበለጠ ታምራለች ልበል?

ቀፍን ከሀፍረቷ እንድታገግም ብዙ ልምምጦችን መቀለብ ነበረብኝ፡፡ ባልፀና የሐፍረት አቅሟ ተነስታ ተንጎዳጎደች፡፡ እንጀራው በፌስታል ተገዝቶ ተቀምጦ ኖሯል፡፡ ትሪ ስላልነበረ እዚያው ፌስታሉ ላይ ተዘረጋ፡፡ ለካ ሞልፋም አልነበረም፡፡ ድስቱን በእሮጌ ጨርቅ ይዛ እንጀራው ላይ ወጡን አፈሰሰችው፡፡ እየተጎራረስን መብላት ጀመርን፡፡ ቀፍን ታጎርሰኛለች እንጂ ወዳፏ አትልም ነበር፡፡ ሳጎርሳትም ጉርሻው አፍዋ ውስጥ ይንከራተታል፡፡

ለምን? በሚል አልተብከነከንኩም፡፡ አውቄዋለሁ፡ ገብቶ ኛል፡፡ ስለጉዳዩ እንስቼ መወያየት ግን ከሞት ገዝፎ ያስፈራራ ኛል፡፡ በነገር እንዠብቤ የሚፈለገው ላይ ለማረፍ አሰብኩ፡፡

"ፍቅር እስከ ቅብሮ ከምን ደረሰ?" አልኳት፡፡

ፊቷ ቅጭም ብሎ "ተቀይሯል" አለችኝ፡፡

"ለምን? እንዴት? ወዴት?" በነገር ስላከር እንደማደርገው ንግግሬን ተርበተበተብኝ፡፡



@BOOKALEM

"ፍቅሮ እስከ ትዳሮ ብዬዋለሁ፡፡ ጥሩ አይደለም?"

የነገር ጧያራዬን በአንድ ምት አወረደችው፡፡ ማንገቧ ከሸፈ፡፡

"ምን እናድርግ?"

"ምንም! ምን እናድርግ አልኩ? በቃ! ወድጄህ ነበር፣ በጣም! ለምን እንደሆነ ለኔም አልገባኝም..." እንባዋ ሲመጣ ፊቷን መለሰች፡፡

"... ንፁህ ነህ፣ ደግ ነህ፣ ሰው ታምናለህ፣ታዝናለህ..."

የእሷ ንግግር አይደለም ጭፍን ይቺ አይደለችም፡፡ የተካቻት ሌላ ሴት ናት፡፡

"እኔ ንጹህም፣ ደግም፣ አዛኝም አይደለሁ፡፡ ፈሪነቴና ጅልነቴ ነው እንደዚያ እንድታስቢ ያደረገሽ፡፡"

መለስ ብላ በማይተረጎም እይታ አተኮረችብኝ፡፡

"አዛኝ እራሱን ከጣጣ ለመገላገል የሊሳውን ስሜት አይጎዳም፡፡ እኔ እራስ ወዳድ፣ የማልረባ መሞት ያለብኝ ሰው ነኝ፡፡" ከቷ በላይ ብሶት አጥለቀለቀኝ፡፡ ይሄን ጊዜ ጭፍን ወደ አባባይነት ተቀየረች፡፡

"ደግነትህ ከፋት ይመጣል ብለህ እንድታስብ አላደረገህም፡፡ ንፁህነትህ ወጥመድ መኖሩን እንዳትጠራጠር አደረገህ፡፡"

"ምን እናድርግ?"

"ምንም ቢቃ የሞተ ነገር ነው፡፡ እምአርጽር ከዚህ በፊትም እንዲህ አድርገው ልጃቸውን የዳሩለት ነበር፡፡ በኋላም መሮት ነው (ጠፋ) ግን ቆይተው አስያዙት፡፡ ስምንት ዓመት ሴት በመድፈር ሸቤ አስገቡት (አስፈረዱበት) ይግባኝ ብለዋል ይባላል፡፡"

ሀይወቴ ዘልአለም መውደቅ የሚመዘገብበት የእንጦሮጦስ ማሽቆልቆል ሆኖ ታየኝ፡፡ ምን ባደርግ ይሻለኛል? ነፃ ለመውጣት፣ ጭፍንን አግብቼ ለመኖር...





40 - መጪው ጊዜ

እምአርጽር በአሸናፊነት እንዳንድ የትዳር መመሪያዎችን ሰጡኝ፡፡ መጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ ወሪሳን ጥዬ እሪበከንቱ እንድገባ የሚያሳስብ ነበር፡፡

"ወሪሳዎች ሌት ከጅብ፣ ቀን ከሀዝብ የሚኖሩ ወሸከንዳዎች ናቸው፡፡ ልጄ ከእነሱ አትደባለቅም" አሉ፡፡

በጠብ ወኪልነት ይሄንኑ ለጆቢራ አደረስኳቸው፡፡ ጭንቅላታቸውን በመገረም ነቅንቀው

"ሥምህ ማነው ቢሉት ነገርህ አይመች፣ ማን አወጣልህ ቢሉት ጎረቤቶች አለ አሉ፡፡ የእሱ ነገር የቸገረ ነው፡፡ ይልቅዬ..." አሉ

"ን"

"ይልቅዬ እዚሁ ከወሪሳ ሳትወጣ ብትኖር ደግ ነበር፡፡ የወ.ህ.ዴ.ድ ምዝጉብ አባል ነህና ከጥቅሙም ልትጋራ ይገባል፡፡"

"የምን ጥቅም?"

"የፖርቲው ጽ/ቤት በር ላይ የተፃፈውን አላየህም?"

"አላየሁም"

"መጪው ኑሮ ከወ.ህ.ዴ.ድ ጋር ፍሰሃ ነው ይላል፡፡ እንዳው ፈሊጥ እንዳይመስልህ፡፡ ሳይንሳዊ ሃቅ ነው፡፡"

የሚሉኝ እንዱም አልተፈጠበጠልኝም፡፡ ግራ በመጋባት አየኋቸው፡፡

"ይኸውልህ ልጆቻችን ደረሱልን፡፡ የወሪሳን ውሃ ጠጥተው፣ በአፈሯ ተጫውተው፣ በትምህርት ቤቷ ሀሁ ቆጥረው ያደጉት አሁን በዚህ መንግስት ቄልፍ ቄልፍ ቦታ ይዘዋል፡፡ የወ.ህ.ዴ.ድ ምዝጉብ አባልም ናቸው፡፡ ሰማኒያ ሚሊዮን፣ ሰባ ሚሊዮን መዘበሩ የሚባሉት የኛ ልጆች ናቸው፡፡ ወሪሳ እመድ አፋሽ አልሆነችም፡፡"

ግር አለኝ፡፡ "እውነትዎን ነው?"

"ዛዲያ እየዋሸሁ መሰሎሃል? ብር ሚኒስቴር...."

"ገንዘብ ሚኒስቴር ማለትም ነው?"

"ያው ነው፤ እ- ወርቅ ሚኒስቴር፣ ባንክ ሚኒስቴር፣ ነዳጅ ሚኒስቴር፤ ሲሚንቶ ሚኒስቴር… ይሄ ሁሉ በኛ ልጆች የሚተዳደር ነው፡፡ የዚች የጉዶ የልጅ ልጅ፣ ትንሽ…"

"እ?"

"የእሱም አባት ሚኒስትር ነው፡፡ የወሪሳን ባህል ይወቅ ብሎ ነው እዚህ የተወው እንጂ እንደሳቶ ያሳድገው ነበር፡፡"

"ጉድ! ጉድ!" ካልኩ በኋላ፣ ጉድ ከእማማ ጉዶ ስም ጋ ገጠመብኝ፡፡ "ጉድ ጉዶ"

"ይኸውልህ ይሄ ሁሉ ተሰልቶ የዘንድሮው ወቅታዊ መፈክራችን ከወ.ዘ.ዴ..ድ ጋር መጪው ዘበን ፍሰሃ ነው የሚለው እንዲሆን ምልአተ ጉባኤው በሙሉ ድምፅ አፀደቀው፡፡ እንግዲህ ወሪሳ እለፈላት፡፡ ፎቅ በፎቅ መሆኗ ነው፡፡ እንደሚባለውማ ቤተመንግስቱም ወደ ወሪሳ ይዛወራል ነው፡፡ እዚህ ከፍ ብሎ ወደ ፓርቲው ጽህፈት ቤት መግቢያ ጋ ወይራ የለም?"

"አዎ"

"እዚጋ ቤተመንግስቱ ይቆርቆር በሚል ተስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ፊት ለፊት ደሞ የሰማዕታት ሐውልት ይቆማል፡፡"

"የምን ሰማዕት?"

"የኛ፣ የወሪሳ፣ ጓድ ላፊውስ? ሰማዕት አይደለምን? ስንቶቹ በዱር በገደሉ ባይሆንም በየጣሪያውና በየባሱ ላይ አልተገደሉም?"

"አዎ ልጄ" አልኩ

"ከእንግዲህ ወሪሳን የነካ መንግስትን የነካ ነው፡፡ ፍርዱን በህዝብ ተወካዮቹ ጠድቆ እፍታም ሳይቆይ ይገደላል፡፡"

"እምርጸርጵ አለቀላቸዋ" አልኩ፡፡

"እሱ ማሟሻ ይሆናል፡፡"

ተስፋ እንደጠዋት ፀሀይ ፊቴ ላይ ተሟወተች፡፡

"በአምስት አመቱ መርሃ ግብራችን ላይ መካላከያንም ወደ ወሪሳ የማዞር ግብ አለን፡፡ ያኔ ለችግር በጀት ካንዱ ወዳንዱ በፍጥነት እየተዟዟርን… " ጠተስ አደረጉኝ፡፡





"ብእውነት?"

"ባዲያ በውሸት ነው? ሲነቃብንም በእግር መሮጥ ቀረ፡፡ ሄሊኮፕተራችንን አስነስተን እ-ብ-ስ፡፡ ግፋ ያለ ከመጣም ዘለን ታንካችን ውስጥ ጥልቅ፣ ወይም በአድማ መበተኛ ውሃ እንረፈርፈዋለን፡፡ እና ልጄ፣ መጪው ጊዜ ከወሪሳ ጋ ፍሰሃ ነው፡፡ አይደለም እንዴ?"

"ነው እንጂ"

"ከዚሁ ከወሪሳ ሳትወጣ ብትኖር ደግ ነበር፡፡"

"ቢቻልማ…" እንባዬ አይኔ ላይ ተንቆረዘዘ፡፡ የአየር መንገድ ቫንጣ ማመላለሻ ላይ የተቀመጥኩ ይመስል ወሪሳዎች በአይኔ ላይ አለፉ፡፡ እማማ ጉዶ፣ የልጃቸውን ልጅ—ልጅ፣ ኩይሳው፣ ልባሙ፣ ሽኮኮ፣ ፈላስፋው፣ ድብሱ፣ ሞፍን… ሞፍን ፎቶ መስላ አይኔ ላይ ተገትራ ቀረች፡፡

"ምናባቴ ላድርግሽ?"

ክፍል ሁለት

# የእራ በከንቱ ውድቅቶች

@BOOKALEM

# ምዕራፍ አምስት

## 1 - ወይ እሪ በከንቱ

እሪ በከንቱን አራት ዋነኛ ሠፈሮች ያዋስኑዋታል፡፡ አሮጌው ቄራ፥ ዶሮ ማነቂያ፥ ወሪሳና ወሮበሊ፡፡ እሪ በከንቱ ለዐብ አምላኪዎቹ ሠፈሮች አድባር መስላ መኻከል ተጐልታለች፡፡ አንዳንዴ ሠፈሮቹ በሰው አምሣል ዱላ ይዘው አይነ-ህሊናዬ ላይ ይጣዳሉ፡፡ በእሪ በከንቱ እግር ሥር ሾልኮ ያመለጠውን ትርፍራፊ ፀበኛ ያለእርህራሄ ለመቀጥቀጥ ዘወትር ንቁ ሆነው የሚጠብቁ፡፡

ሐሳቤ ወደ ህልም ተቀይሮ ያ ትርፍራፊው ፀበኛ እኔ ሆኜ እያየሁ እቃዣለሁ፡፡ እንደፈረጠጠ በሬ በዱላ ቀንድ ቀንዴን እያሉ ወደእሪ በከንቱ ይመልሱኛል፡፡ እሪ በከንቱ ደግሞ በንዴት የተንደረከች ፍም መስላ ትጠብቀኛለች፡፡ ብዙ የፍም ሰቀላዎች፥ የነበልባል ሰዎች በራቸው ላይ ተኮልኩለው ይታዩኛል፡፡ አጋፋሪው እምቧርቧር እየተንበለበሉ ከላይ ታች ይቁነጠነጣሉ፡፡ ወደ እያንዳንዱ ቤት የተዘረጋው ብረት የእግር መንገድ የጋመ ፌሮ መስሎ ተወሳስቧል፡፡ የእሪ በከንቱ ወንዝ የቀለጠ ብረት ይንጨለጨልበታል፡፡ የእሣት እርጎ ይመስል ደርበብ ብሎ የሚወርደውን ወንዝ አንድ እሳተ-መለኮት የነበልባል ገጀራ ይዞ ሻገር ያለው መሰለኝ፡፡ መጣባቸው ከስተጓላዩ ሊመጣብኝ እንደሆን ጠረጠርኩ፡፡ እኔን ከትክቶ በእሳት ፈፅታል ለመቋጠር መሆን አለበት፡-

እሪ በከንቱ ከገባሁ ጀምሮ የረባ እንቅልፍ በአይኔ አልዞረም፡፡ ያቺ የሥጋ ጉብታ ሚስቱ ታንኮራፋለች፡፡ አንዳንዴ

ሌሊትም ቢሆን ተነስቼ በር ላይ እቀመጣለሁ፡፡ ቅዠት የእሬ በከንቱዎች ሁሉ እጣ-ፈንታ ይመስለኛል፡፡ ብዙ ሰዎች ደጃፋቸው ላይ ቁጭ ብለው ማዶ-ማዶውን ሲማትሩ ያጋጥመኛል፡፡

በእሬ በከንቱ ቀኑም ሌላ ቅዠት ነው፡፡ ትናንት ይሁን ከትናንት በስቲያ እምስት አመት የሚሆነው የመጣባቸው ልጅ አንድ ዘግናኝ ትርኢት ሲያከናውን አጋጠመኝ፡፡ ድመት አንገት ላይ ሽምቀቆ አስገብቶ በቤት ማገር ውስጥ ገመዱን በማሳለፍ በሰንደቅ አላማ ሥነ ሥርዓት ያንጠለጥላታል፡፡ ትፈራገጣለች፡፡ የመጣባቸው ልጅ ብሔራዊ መዝሙር ያሰማል፡፡

‹‹የ-ዜግነት ክብር
በኢትዮጵያችን ሰፍኖ…››

ድመቷ በማዕር ላይ ነች፡፡ መላ ሰውነቷ ስለከበደው አንገቷ እየቀጠነና እየረዘመ ሲሄድ ያስታውቅ ነበር፡፡ ይሄንን ዘግናኝ ትርኢት ትልልቆቹ እሬ በከንቱዎች በፈገግታ ያስተውላሉ፡፡

የመጣባቸው ልጅ ብሔራዊ መዝሙሩን እስኪያጠናቅቅ የድመቷ ማዕር ተራዘመ፡፡ በመጨረሻ የገመዱ መዳረሻ ማገሩ እንደተቃረበ እይኗ ፈጦ እግሯ ተንጨፈረረ፡፡ የመጣባቸው ልጅ ብሔራዊ መዝሙሩን አጠናቀቀ፡፡

‹‹ኢትዮጵያችን ኩሪ፤
እኛም ባንቺ እንኩራ፡፡››

ይሄ ትንሽ ሲጣን አቅም እጣ እንጂ ሰውም እንዲሁ እንጠልጥሎ ብሔራዊ መዝሙር ቢያሰማ ደስታው ይመስላል፡፡ እሬ በከንቱዎችም እንደ አዲስ ነገር የሚያዩት አይመስልም፡፡

## 2 - የማወክ ስልጠና

በእሬዊቱ እሬ በከንቱዋዊ መካከል ንጉሡ የሚሰቱ አባት እምጳርጵር እንደሆኑ ለመረዳት ጊዜ አልወሰደብኝም፡፡ እንደ አንበሳ ድንገት ተነስተው ያገሳሉ፡፡ እጥንት ለመስበር እንደቃበዙ ሁሉ ሳይመርጡ ይደነፋሉ፡፡

‹‹ደባ ይሸተኛል፡፡ ጠብ ከላይ የተሰጠኝ ፅጣ-ክፍሌ ነው፡፡ በእናንተ ቤት እርጅቷል መሰሏችኋል፡፡ ከመካከላችሁ ሁለቱን ሸኘ





ባልይዝ አልሞትም፡፡ የዘር ነው! እንደታቦት ሳንታጀብ ምን ቢያገድ…››

እምጳርጵር ሲደነፉ ከሪበከንቱዎች መካከል ብቅ የሚለው የመጣባቸው ልጅ ብቻ ነው፡፡ ጠብ እንደከጀለ አውራ ዶሮ ይንጠረበባል፡፡ እሳቸውም አይንቁትም፡፡

‹‹ሚጨት ብትሆንም ለነገሩ ጀግና ነህ፡፡››

‹‹እራስት ኖት ሚጨት›› ይላል፡፡

ገና ዛሬ እምጳርጵር እኩያ ያገኙ ይመስለኛና ፈገግ እላለሁ፡፡

‹‹እክክክክ… ታዲያ እንቱታውን ተወዋ! እንደ አፋር በክል ማጣጣም ይቻል ነበር፡፡››

‹‹ወንድ ኖት››

እምጳርጵርን እንደድመቱ እንጠልጥሎ የህዝብ መዝሙር…

‹‹ወንድነቱን አንተ እስትደርስ በአባትህ አሳይሃለሁ…››

በዚህ መካከል አባቱ ከቤት ቱር ብሎ ይወጣና የድመት ግልገል ይመስል አንገቱን አንቆ በማንጠልጠል ይዞት ይገባል፡፡

እምጳርጵር ወደእኔ ዞረው ‹‹የልጅ ባላጋራ ጥሩ ነው፡፡ ሲያድግ ጠብ አያሳጣህም፡፡ ቂሙ እንዲበረታ አባቱን ደህና አድርጉ መኰርኰም ነው፡፡ ዛሬ ማታ በቃልኪዳናችን መሠረት ከሆነልን መጣባችውን…››

የታደለ የቁንት መኪና ረዳት ይሆናል እኔ ለጠብ አባሪ ተባባሪነት ታጭቻለሁ፡፡ ጨነቀኝ፡፡ ባለቤቱን ገብቼ፡-

‹‹ሺ-ትርገም›› አልኳት

‹‹ፍቅሬ›› አለችኝ፡፡

‹‹ፍቅሩን ተይው›› ለማለት ቃትቶኝ ተውኩት፡፡ "እኒህ አባትሽን ብትመከሪያቸው…››

‹‹ምን አደረገ?››

‹‹አባውንት ናቸው፡ ጠብ እያሸተቱ…›› ንግግሬን ሳልጨርስ በግምት ሦስት ሜትር ስፋት ያለው እካሏን ፊቴ ላይ ደንቅራ ቀኔን አጨለመችብኝ፡፡



@BOOKALEM

‹‹መመከርስ ያለብህ አንተ፡፡ ምን አይነት አይነተኛ ነው ጠብ የሚያስጠላ? እንኳን አንተ እኔ ቤቷ ስለጠብ ሲነሳ እንዴት እንደሚያቁነጠንጠኝ አላየኸም?››

ዝም አልኳት፡፡ ገለል ብላልኝ ቀኑ እስኪበራ፡፡

‹‹ብል የጫጉላ ጊዜአችን ዛሬ አልቋል የጠብ ልብስና ጌላ ገዝቼልሃለሁ፡፡ ቀጥታ...››

አይ እዳዬ! እኔ ዞር አልኩ፡፡ እምጳርቋር እግር ተእግር ተከትለውኝ ኖሮ ከጓላዬ አገኘኋቸው፡፡ መቼም ሁለመናቸው ድመት ነው፤ ኮቴ የላቸውም፡፡ እእን አልፈው ልጃቸውን አነጋገሯት፦

‹‹ዱላው ለምኔ ነው አልሺኝ? ትድም ሳልጠይቅሽ››

"ለእሱ ነዋ! ለባል ተብዬው"

እምጳርቋር መለስ ብለው አይተውኝ ‹‹ሁከት እንደዚህ በቀላል ይጀመር መሰለሽል፡፡ ብቻ አይዞህ እኔ አባትህ እያለሁ የወንድ ወግ ላይ ሳላደርስህ ከንዴን አልንተራስም፡፡››

‹‹የወንዱ ቀርቶ እኛ ሴቶቹ የደረስንበት በደረሰ›› ወደ ጓዳ ገባች፡፡

‹‹ተይ አንቺ ሽል አፍ፤ ሁከት ቀስ እየተባለ ነው የሚለመደው፡፡ ከጠበኛ አልተወለደ እንደ እኛ...›› ኩራት ኩራት አላቸው፡፡ ‹‹ለመሆኑ አባትህ ጠበኛ ነበሩ?››

‹‹አይ፤ ቄስ ነው››

‹‹ያንተ ነገር፤ ቄስነት ጠብን ያስተራል መሰለሃል? ስንት ሁከተኛ ቄስ አለ ‹ጠበኛ ቄስ እየደበደበ ይቀድስ› ሲባል አልሰማህም? እንደው አባትህ እንዴት ነበሩ?››

‹‹ሽረ ሰላማዊ ነበር››

‹‹አ-ዬ፤ ተበላሽተው አበላሹህ፡፡ ጠብን ከቤትህ ወጥተህ ካልፈለከው ቤትህ ድረስ ፈልጎህ ይመጣል፡፡ እዚች አለም ላይ ሠላማዊ የሚባል የለም፡፡ ፈሪ እንጂ፡፡ ጠብን ችሎ ማሳለፍ ሠላማዊ አያሰኝም፡፡››





ዝም አልኳቸው፡፡ የአባቴ መወረፍ ቢኮሰኩሰኝ ምን ላመጣ?

‹‹የእኔ አባት የወጣላቸው ሁከተኛ ነበሩ፡፡ አገር የሰገደላቸው፡፡ ስመጥር ሆነው ሰው ሁሉ እየሸሻቸውና እየተለማመ ጣቸው ለሦስት ቀን ጠብ አጥተው ቆዩ! አሉ፡፡ በኋላ በመቁነጥነጥ ላይ ሳሉ አንድ ወዳጃቸው እወዲያ-ሰንሰል ውስጥ ሲፀዳዳ ያዩታል፡፡ በአጠገቡ እንደማለፍ ብለው...››

‹‹እያ እርገጡ...›› አሉት

‹‹ጌታዬ›› አለ ከጠብ የሚያመልጥ መስሎት፡፡

‹‹ጌታዬ ምን ያሻል? ባጠገብህ ሳልፍ ምነው እኔን ምሰል አላልከኝ፡፡ ቂም ቋጥረህብኝ ኖሯል እንዴ?›› አሉት፡፡

‹‹እንብላ እንጂ እንራ አይባል ጌቶች?››

‹‹ካበላ ያሳራ ይፀድቃል ሲባል አልሰማህም?››

‹‹እሱስ ነው››

‹‹አንተ ተወው፤ እኔ ግን እንተን አግርቼ መፅደቅ እፈልጋለሁ፡፡ በል ቂምጣህን ታጠቅ ብለው አሣሩት፡፡ አ-ሃ-ሃ-ሃ-ሃ... እንዲህ ያሉ ጀግና ነበሩ፡፡››

አብሬአቸው አልሳቅኩም፡፡ በአባቴ ተታከኮ የተሰካብኝ የስድብ ስንኩፍ ገና እየቆጠቆጠኝ ነው፡፡

‹‹ምነው?›› አሉኝ ሸቅብ እያዩኝ፡፡

‹‹እንዴት?››

‹‹አልሳቅህም፤ ነገሬን ተጉዳይ ባትጥፈው ነው?››

ለፀብ የከጀሉኝ መሰለኝ፡፡ የዱር ድመት ጠባያቸው ኩፍ አደረጋቸው፡፡

‹‹ነገር ሆዴ ገብቶ ነው››

‹‹የምን ነገር?›› ባጥን ላይ ቂጭ አሉ፡፡

‹‹አባቴ ስትለ... ጆቢራው ያጫወቱኝ ትዝ አለኝ፡፡›› የአባት ሀመሜን እንዲቀምሱት መከጀሊ ገፋፋኝ››

‹‹ደሄ ወሻካች ምን አለ?››



@BOOKALEM

‹‹እይ- ከጀቢራው አባት ጋር አባትዎ ጃንሆይ ፊት ቀርበው…››

ባልጠበኩት አኳኋን የአምጻርጵር ሳቅ ግድቡን ጥሶ ተክለበሰብኝ፡፡ ሺ-ትርጉዋም ከጓዳ ወጥታ ሆዷ ላይ ታች እያለ እምጻርጵር በሳቅ መካከል፡-

‹‹ቁርበት ምን ያንቋቋሃል ቢሉት ባያድለኝ ነው እንጂ የነጋሪት ወንድም ነበርኩ አለ አሉ፡፡›› ሳቃቸው ቀጠለ፤ የሺ-ትርጉዋ እጃቢነትም…

ማብሸቁ ቀርቶ በሽቅኩ…

‹‹እየሁ፡ ጥንብ እንሳም ጦር ሜዳ ይውላል፡ ግን አይዋጋም፡፡ ሙያው ለየቅል ነው፡፡ እንደውም አባቴ ሲነግሩኝ እንዲህ እየተባለ ይለቀስ ነበር አሉ፡-

‹‹የጀግናው እናት ታጠቂ በገመድ፤
ልጅሽን ወሬሳንጂ አይቀብረውም በመድ››

ሳቃቸው ቀጠለ፡፡

‹‹የቅኔ መምህር ልጅ ነህና? ይህን ሳንተ አልፈታም››

ደገሙኝ፡፡ ሁለተኛው ስድብ የበለጠ አመመኝ፡፡ ይሁንና እምጻርጵር ሁኔታ ውስጥም የተረዳሁት ነገር አለ፡፡ ለምን ሳያደምጡ ተከሳከሉ?

‹‹ጀቢራ'ኮ ዘመትን አላሉም፡፡ እሳቸው ያሉት…››

‹‹ተወው አልኩህ…››

‹‹እሪ በከንቱ ሰውን እንዴት እንዳገኘ…››

‹‹ያመዋል እንዴ? ተወው እያልኩህ?…››

‹‹አባትዎ…››

እምጻርጵር ወፍ እንዳየ ድመት ተፈናጥረው በመነሣት ወደ ልጃቸው እንጋጠው ‹‹ባልሽን ጠበል ውሰጂው፤ ያመዋል›› ብለው ቤቱን ለቀውልን ሄዱ፡፡





እንጀቴ ትቤ ጠጣ፡፡

ይቺን ሳብሰለሰል ደስ ብሎኝ አመሸሁ፡፡ ማታ ሺ-ትርጉዋ ከእባቷ ጋ እንድ ደብዳቤ ይዛልኝ መጣች፡፡ በለቀት የሚያወሳ መስ ሎኝ ለዳግሚያ ደስታ ተዘጋጀሁ፡፡ አጭር ማስታወሻ ቢጤ ነው፡፡

‹‹ዛሬ ማታ የዚያን የጫሬውት አባት እንደበድብዎለን፡፡ እኔ እበሬ ላይ ቁጭ ብዬ እጠብቃለሁ፡፡ እንተም በእናንተ ደጅ በሰላም ለንዲያልፍ ተጠንቀቀህ ዱላህን ይዘህ እንድትጠብቀው ይሁን፡፡››

ስም፡- ፊርማ

ደስታዬን የሥጋት እግ-ነባሪ ዋጠብኝ፡፡ ያሉት ሰዓት ደርሷል፡፡ ምንም እንዳልተፈጠረ በማስመሰል እያፏጨሁ ወደ መኝታዬ ሳቀና ሺ-ትርጉዋ እፊቴ ተደቅና ሁለመናዬ እጿ ብቻ ሆነችብኝ፡፡ የድብድቧ ልብሴንና እህል ውሃ የማያሰኝ ዱላ ይዛ ነበር፡፡ እንደልጅ እያመነጫጨቀች ለዐብ እስታጠቀችኝ፡፡ ዋርድያ በታዬ ላይ ጐልታኝ ወደ ቤት ገባች፡፡

ዱላዬን እንደሀፃን ልጅ ታቅፌ ተጐለትኩ፡፡ ሁለመናዬ በሱት ላይ ነው፡፡ መጣባቸው ቢመጣ ምን እለዋለሁ ጌታዬ? ከጨለማ እመር ብዬ እከመርበታለሁ? ለምን? ከመጣባቸው ይልቅ የመደብደብ ምክንያት ያለኝ እምጻርጵር ላይ ነው፡፡ ይሄን ሰውዬ እለቀርተህ ከጉድ አውጣኝ፡፡

እኔ ያለሁበት ቦታ ከአፍንጫ አልፎ የሚታይ ነገር የለም፡፡ ወፍራም የጨለማ ምሸጊት ያለጭላንጭል እየኑ ላይ ተለጥፏል፡፡

ባልመጣ፡ ባልመጣ፡ ባልመጣ…

መጣባቸው ከመምጣቱ በፊት አንዳች ነገር ከወደትከሻዬ ውልብ ያለ መሰለኝ፡፡ እከታትሎም ጭንቅላቴ ላይ ከቋጥኝ የከበደ ነገር አረፈ፡፡ ፀሎቱ እና ሥጋቱ አንድ ላይ ድርግም ብለው ወና ሆንኩ፡፡ ወዲያው በእፍጢሜ ድፍት ብዬ ቀረሁ፡፡

የነቃሁት አልጋ ላይ ተጋድሜ ነበር፡፡ ነገሮቹን ለማቀናበርና የሆነውንና ያለሁበትን ለመረዳት ጊዜ ወሰደብኝ፡፡ ይሁንና ሺ-ትርጉዋና እምጻርጵር በመሐሉ ቁልቁል እያዩኝ መደነቅ ጀመሩ፡፡ የእምጻርጵር ንግግርም ተከተለ፡-

‹‹ተመስጌን! ሁከት አስለጥንሃለሁ ብዬ በዱላ ገድዬህ ነበር››



@BOOKALEM

## 3 - እሪ በከንቱዎች

ሦስት ቀን ተኛሁ፡፡ ጭንቅላቱ ሲመታ ባዶ የነበረውን ያህል አሁን ከእጥፍ በላይ ከብዶ አስጨነቀኝ፡፡

እምጷርጷርና ሺ-ትርንጥ ቤቱን ማሰማመር የጀመሩት እለቱን ነበር፡፡ ወለሉን ሳጠራ አለበሱ፡፡ ግድግዳውን ለጠፉበት፡፡ ጋዜጣው የመጣው ከእምጷርጷር ጋ ነበር፡፡ ሙቅ ተሞቆ ጉን ሙቅ ይለቀልቁና ለሺ-ትርንጥ ያቀብላሉ፡፡ ሺትርንጥ ብዙም ሳትቸገር ከጣሪያው እንስቶ እስከ ግድግዳው ወገብ ትለጥፋለች፡፡ ከወገቡ በታች እምጷርጷር እየተንጠራሩ ይለጥፋሉ፡፡ እኚህ ድመት የሆኑ ሰውዬ፡፡

ቤቱ አምሮ ሲያበቃ እምጷርጷር እሪ በከንቱዎችን ማስጨነቅ ያዙ…

‹‹ምራቴን ጠየቃችሁ?… አሁን ወሬ ሳይሰማ ቀርቶ?… ጉድ ነው! ለነገር ያላችሁት ነው’ጂ…››

እሪ በከንቱዎች ተግተለተሉ፡፡

ሺ-ትርንጥ ‹‹የመጣውን መዝግቢ፡ ከነአመጣው ነገር ጭምር›› አለችኝ ወረቀትና እስክሪፕቶ ይገፍ ጠበኩ፡፡

- እዳፍኔ ሁነኛው ማንጉ ጁስ
- መርጌ ቢሻው ኪሎ ሙዝ
- ሽኮኮ (ደላላው) ኪሎ ብርቱካን
- መጣባቸው ሳሁን እንጀራ
- የእምባጓሮ ጠጅ ቤት ጠጅ ቀጂ አንድ ጠርሙስ ጠጅ
- ወ/ሮ ይታጠቂ ፍትፍት
- ደምስሰው ኪሎ ሙዝ

ሺ-ትርንጥ የመጣውን በእጇ መዘን መዘን እድርጋ ወደጓዳ ታሸሻለች፡፡ እንዳንዱም፡ ‹‹ኪሎ አይሞላም›› እያለች እንደሸማች ትከራከራለች፡፡

እምጷርጷር ማታ ይመጡና የጠብ ግብራቸውን ይቆጥራሉ፡፡





‹‹እልኸኛው ምን ሆኖ ቀረ? ምን ይመጣብኛል ነው? ጠንክሮ ኪያዘኝ እስቲ እናየዋለና፡ ሽንቅሬስ? አልፈራሁም ነው? ዋሩ፡ ለመሆኑ ሃምሳ አለቃ መርጌ ምን ይዞ መጣ አላችሁኝ? ኪሎ ሙዝ? አልቀረሁም ለማለት ነው? ተመጣም አልቆጥረው!…››

በሁለተኛውም ቀን ጥየቃው እንዲሁ ቀጠለ፡፡ በመካከሉ የመጣባቸው ልጅ ሽምቀቆ ገመዱን እንደያዘ መጣ፡፡ ፈራሁት አበል? አይኑ ይንቀዠቀዠል፡፡ እንዴ ወደእሌጋ ስር፣ እንዴ ወደ ጓዳ አይኑ ይማትራል፡፡ ድመት ይሁን እምጷርጷርን እንጃ ይፈልጋል፡፡ የተሰጠኝን አንድ ብርቱካን ሰጠሁት፡፡

በጥርሱ መላጥ ጀመረ፡፡ የብርቱካኑን ልጣጭ የሚነክሰው ለመብላት በጓጓ ሁኔታ ሳይሆን ቂም በያዘ ሀበኛ እኳኋን ነው፡፡ አበላሉም ውስጥ የታባክ! አለበት፡፡ እጣጥሞ ጣቱን ሲልስ ‹ሰራቀሌሁ› የሚል ይመስላል፡፡ ተሎ ጠይቆኝ ቢወጣ ተመኘሁ፡፡ ያለወትሮው ብቻችንን ነን፡፡ ድመትና እምጷርጷርን ሲያጣ ሽምቀቆውን እንገቴ አስገብቶ ቢንጠለጠልብኝስ? እንደተንጠለጠለ ‹የጴግነት ክብር…› ቢልስ? እኔ እንደሆን በሁኔታዬ ተከላካይ የምተርፍም አይደለሁ፡፡ ምናልባት ነፍስ ሲይዘኝ…

…እራሴን ታዘብኩት፡፡ የአምስት አመት ልጅ ይፈራል? ምክ ቢሆን… ደፈር ብዬ አናገርኩት

‹‹ማሙሽ ትምህርት ቤት አልገባህም?››

በንቀት ገልመጥ አድርጐኝ ‹‹እምባጓሮ ያስተምራሉ እንዴ?›› አለኝ

‹‹ሉ-ይ፡ ፊደል፡ ቁጥር…››

‹‹ምን ያደርግልኛል?››

‹‹እንድታነብ… እንድትቆጥር…››

‹‹አንብቤስ? ቆጥሬስ? ምን ያደርግልኛል?…››

ማስረጃው አጠረኝ፡፡ አሁን እኔ መምህር ነኝ?

‹‹እኔ የምፈልገው እየርወለድ መሆን ነው፡፡ እንዲህ እያረኩ አንቄ እንድገድል ያስለጥኑኛል›› አለ ሽምቀቆውን ከፍ አድርጐ እየሸመቀቀ፡፡



@BOOKALEM

ቀዳዳው እሱው ስለከፈተልኝ በዚያ ሾለኩ፡፡ «ታዲያ አየርወለድ ለመሆን ቢያንስ እስከ ስምንተኛ ክፍል መማር አለብኝ»

«አለበለዚያ አይሆንም?»

«አይሆንም»

«እንዲያ ከሆነስ እማራለሁ፡፡» ንግግሩ የአምስት አመት ልጅ አይመስልም፡፡

«ለመሆኑ ስንት አመትህ ነው?»

«ስምንት»

«ኸከከከከከ...» አልኩ፡፡ እንደ አምጿርጿር ከራሱ ሁከተኛ ኖረል፡፡

«አስራ ስድስት ሲሆነኝ መጀመሪያ የምገለው አምጿርጿርን ነው፡፡»

«ጎሽ» ልለው ከጀለኝ፡፡ ያኔ እኔም ነፃ እወጣለኋ! ጨቅላው ነፃ አውጪ፡፡ መቼም ከዚያ ወዲህ የእኔ ነፃነት አይታሰብም፡፡

* * *

አምጿርጿር የጠየቀኝን ካዱ፡፡ ያልጠየቀኝ ላይ ዛቱ፡፡

«ነገር ሲፈልጉኝ ገና ከጥንስሱ አውቄዋለሁ፡፡ ነገር የዘር ማንዘሬ ውርስ ነው፡፡ መቼስ ርስቱ እንደሆን እንዲ ተወርሷል። ነገሬን ግን አላስነካም፡፡ ውርሴ ነው፡፡ እንተያያለን» አሉ፡፡

ማታ አምጿርጿር ከጠጅ ቤት መልስ እኛ ጋ ሲመጡ ቤታችን በጠያቂ ግጥም ብሎ ሞላ፡፡ የተካዱት ጠያቂዎቼ በድጋሚ ያልጠየቁኝ ስለተዛተባቸው ፈርተው መጡ፡፡ ከአዳዲሶቹ ውስጥ ግንፍሊ የተባለ ፍልጥልጥ ግንባርና ሳጂን መርጌ የተባለ የእሪ በከንቱ ፖሊሲ ጣቢያ አዛዥ ነበሩ፡፡ አንድ የእኔን ሚስት የምታህል ሊላም ሴት ነበረች፡፡ ሺ-ትርንዋ ቀስ ብላ የአምጿርጿር ትምህርት እንደሆነች በኩራት ነገረችኝ፡፡ ለካ እሳቸውም እንደ እኔ ሁሉ የሥጋ እስረኛ ነበሩና? ወዶገብ ቢሆኑም ያው ዘብጥያ ወርደዋል በሚል ተፅናናሁ፡፡





ሺ-ትርንዋ በጆሮዬ ስትንግረኝ የፍትር ምስጢር የመሰላቸው እሪ በከንቱዎች «እሰይ፥ እሰይ ትዳር እንዲህ ነው» እያሉ አጓጉቱ፡፡

ሺ-ትርንዋ ለእኔ የድንጋይ ዘብጥያ ሽሽቼ የታገትኩባት ገዟአዊ የሥጋ እስር ቤቱ ናት፡፡ ብችል ገርስሼአት ነፃ ብወጣ ደስታዬ ነበር፡፡ መገርሰስ ቢሳነኝ እንኳን ይሄን የሥጋ ካብ ዘልዬ ማምለጥ የማይታበል ህልሜ ነው፡፡

በዚህ መካከል አምጿርጿር ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማውራት ጀመሩ፡፡

«እኔ ነኝ የመታሁት፡፡ ሌላ ማን ደፍሮ ሊሞክረው? እሱ እንደሁ ቅብዝብዝ ደም የጠማው»

ምን ማለታቸው ነው? በሚል ጆሮዬ ቆመ፡፡ መላው እሪ በከንቱዎቹ እንደእኔው ጆሮውን ቀሰረ፡፡

«ምን ከፉ ቀን ከሱ ጋር እንዳዛመደኝ እንጃ፡፡ አሁን ሳጣራ እንሩ ሦስት ሰው ገድሎ ነው ወዲዲሳባ የሸሸው»

ስለማን እንደሚያወሩ ጠረጠርኩ፡፡ ይሁንና እሪ በከንቱዎች ፊሪው ስለእኔ እንደሆነ የገባኝ በአይናቸው መላልሰው ሲያዩኝ ነው፡፡ አምጿርጿር ያበዱ መሰለኝ፡፡ ይሄ የስካር መዘላበድ ብቻ አይደለም፡፡

«የጠባችን መነሻ፥ እዚህ እናንተ መካከል ባለሰው ተዛላቂዎቹ ጠጉሬን ስንጭ ያያል፡፡ ‹ምነው? ምን ሆኑ?› ሲለኝ ጠንኛ መሰሎኝ የሆዴን መንገር፡፡ ከእኔ ብሶ ቱጭ! አሁን ካላገደልኩ ሞቼ እገኛለሁ አይልም፡፡ ‹ጠብ አይነት አለው፡፡ ቅር ያለንን ሁሉ ገድለን እንችላለን? እግዚአብሔርም በፍርድ ማዛባት ይወይቀናል› ብለው ኧረ ወዲት! እሱ ያየው እኔ የልጁ አያት መሆኔን ነው፡፡ ተው ስለው....

«እንዴ የነገር ጭራ አስይዞ ምንድነው ተው? አይለኝም፡፡

«በጉዴ ወጣሁ፡፡

«እንግዲህ የልጄን ነገር አደራ፡፡ ለእኔ እንደሁ ስደት ቀለቤ ነው አይደለም?



@BOOKALEM

‹‹መስደዱም፣ መግደሉም ወግ አለው፡፡ ሲያስፈልግ ይሆናል፡፡ በተነካሁ ተከለፍላፊ መሆን ደግ አይደለም እያልኩ መከርኩት፡፡

‹‹እንግዲህ አንዴ ልቤ ተነስቷል፡፡ የልቤን ሳላደርስ ወይ ፍንክች አይልም

‹‹ኡ-ይ እንግዲህ ጠብህ ከኔ ነው፡፡ ገና ለገና ጥቂት ተማተው ብዬ የሰው-ሰው አላስገድልም፡፡ ተዚህ እንዳሽረሳለን አልኩታ፡፡

‹‹እርስዎ እንዳሻዎ አባቴ ነዎት፡፡ እሱን ግን እገድለዋለሁ፣ አልምርም ሲለኝ ደሜ ተኒኒኒኒኒ... ብሎ አናቱ ላይ ወጣ፡፡ ተዚያ ባላይ ያደረኩትም ተሰቶኛል፡፡ እንጃ! እኔ የምታሳዝነኝ አንድ ፍሬ ልጂ ናት›› አለ፡፡

ሺ-ትርገጥን ዞር ብዬ ሳያት የኀዳውን ጉብን ተደግፋ ማን ባት ጀምራለች፡፡ እሪ በከንቱዎች ሃይ-ሃይ-ሃይ ደሏት ጀምረዋል፡፡

አባትና ልጅ በጋራ ያበዱ መሰለኝ፡፡ ወደ እሪ በከንቱ ፖሊስ አዛዥ ዞር ስል ማስታወሻ ቢጤ ይይዛል፡፡ የፈራሁት የድንጋይ ዘብጥያ በሎጋ እስር ቤት ስርቆሽ በር በኩል መምጣቱ ታወቀኝ፡፡

እንግዶች ሲወጡ ጠብቄ አምጳርጵርን ‹‹ምነው ጉድ ሰሩኝ?›› አልኳቸው፡፡

‹‹ዝም በል፣ ከንቱ›› አሉኝ፡፡ ‹‹እሪ በከንቱዎችን አታውቃቸውም፡፡ ከግድቅ ሀጢአትን የሚያመልኩ ህዝቦች ናቸው፡፡ ነፍስ ገዳይ መሆንህን ስናገር አንተን ይፈሩሃል፣ እኔንም ለመናቅ አይከጅሉም›› አሉኝ፡፡

‹‹ይሁን›› ብዬ ዝም አልኩ፡፡

## 4 - ተቅበዝባዡ

በሁለተኛው ይሁን በሦስተኛው ቀን ተነስቼ ሥራ ገባሁ፡፡ እራሴን ያዞረኛል፡፡ እንደተጐዳሁ ባስብም አስተዳደሩ ‹‹አምሮብሃል፣ የታሰረች ሴት መስለህ የለም እንዴ?›› አለኝ፡፡





ዝም ብዬው አለፍኩ

‹‹እንግዲህ መውለድና የአስርቱ ትዕዛዛትን መፈፀም ነው››

ወደ ክፍል ገባሁ፡፡ ተማሪዎቹን ገና ስመለከት በመደዳ-ጨፍጭፋቸው ጨፍጭፋቸው አሰኘኝ፡፡ ስሜቴን ገሰፅኩት፡፡

‹‹ባለፈው ክፍለ ጊዜ ምን ላይ ነበር ያቆምነው?›› አልኳቸው፡፡

‹‹ስለተረት አስፈላጊነት››

‹‹ዛሬ ደሞ ስለእውነት አስፈላጊነት እንማራለን›› ብዬ የብዕቱን ዘከዘኩ፡፡ አምጳርጵር የዋሽትን፣ ሚስቴ በለቅሶ ያጀበቻቸውን... ተማሪዎቹ ሳይታዘቡኝም አልቀሩ፡፡

ወደቤቴ በጊዜ አዘገምኩ፡፡ እንደማንኛውም አማርኛ መምህር የቀድሞ መዳረሻዬ ተረት መሆኑ ቀርቷል፡፡ ተረት በሚመስል እውነት ተተክቷል፡፡ እውነቴን እንደ ጥሬ ስቆረጣጥም ሦስት ሽማግሌዎች በር አንኳኩተው ገቡ፡፡ እየተያዩ ፊቴ ተደርድረው ቆሙ፡፡

‹‹ምነው! ቁጭ በሉ እንጂ›› አልኩ፡፡ ከሦስቱ አንዱ አምጳርጵር በአቃቤ ሕግ ምስክርነት ቤቱ አምጥተውት የነበረው ደባደቦ ፊት ነው፡፡

‹‹አንቀመጥም›› አለ ደባደቦው ሌሎቹንም ወክሎ ‹‹እሺ ሳትለን አንቀመጥም›› ሦስቱም የተቀዳደደ ነጠላቸውን አደገደጉ፡፡

‹‹ምንድነው እሺ የምላችሁ?›› ከብዶኝ እኔም ቆምኩ፡፡

‹‹መጀመሪያ እሺ በለን››

‹‹ሳልሰማ?››

‹‹ላንተ አይከብድህም፡፡ እኛ የማትችለውን አንጠይቅህም››

‹‹ምንድነው?››

‹‹እሺ በለን››

‹‹እሺ ንገሩኝ››

‹‹አመብርሃን እሺ ትበልህ›› ብለው ቁጭ አሉና ነገሩኝ፡፡

‹‹አማላጅነት የላኩን አምጳርጵር ናቸው››



@BOOKALEM

‹‹ምን ብለው?››

‹‹ልንነግርህ አይደል? በልጁ ጉዳይ ከመጣባቸው ጋ ስለተጋጨን እገድለዋለሁ ብሎኛልና አይግደለው ነው ያሉት›

‹‹እላቸው ደሞ—›› ግልፍ አለኝ፡፡

‹‹እንዴ ቃልህን ሰጥተኸን የለም እንዴ? ተው እንጂ...››

ይሄን ጊዜ ሺ-ትርንጥ ከወደጓዳ ብቅ ብላ ተከላተረችብኝ፡፡ ሽማግሌዎቹ ሲመለከቷት እንደማልቀስ ብላ፡-

‹‹ለእኔም አስብ እንጂ፡፡ አንተን ተማምኜ መስሎኝ እድሌን የሰበርኩት›› አለች፡፡

‹‹ሃይ-ሃይ-ሃይ›› ሽማግሌዎቹ

‹‹እሺ ይሁን›› አልኩ፡፡

‹‹ቅዱስ ጊዮርጊስ መላእኩ እሺ ይበልህ›› በሚል ጀምረው ምክር አዥጎደጎዱ፡፡ ‹‹ተከለፍላፊና ተቅበዝባዥ ባህርይ የህጻያት ውርስ ነው፡፡ ለጊዜው ለምድራዊ ህይወት አስደሳችነት እያማም፡፡ ይሁንና ሦስት ነፍስ ከበቂ በላይ ነው፡፡ አንድ ያልገደልን እኛን ማየት ደግ ነው፡፡ ከእንግዲህ ግድ ካልሆነ ነፍስ ማጥፋቱ ይቅርብህና እርፈህ እዚቹ ተቀመጥ፡፡ እረበከንቱ የመጨረሺያ መኖሪያህ/ትሁን፡፡››

‹‹እሺ››

ሽማግሌዎቹ እያመሰገኑ ተደስተው ሄዱ፡፡

ሺ-ትርንጥ ያ ሁሉ የማስመሰል እንባዋን ፊቷ መጥጠት ‹‹እኔ ሺ-ትርንጥ ከአምስት ወንድ እበልጣለሁ፡፡ ታዲያ ምን ይሆናል እሪ በከንቱዎች ከጉን የሚያዩት ወንድ ልጅ ሆኖ እባቱ ተቸገረ፡፡ የሚንጠረበብበት በዛ፡፡ እና ይቺን ስለዋልክለት ከትልቅ እንዳትቆጥረው›› አለችኝ፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ፈራኋት፡፡ ብትወድቅብኝም ብወድቅባትም ሟቹ እኔ እንደሆንኩ አሰቤ ሥጋት ገባኝ፡፡

‹‹ኧረ ግዴለም፣ የምን ሙሰታ ነው?››





* * *

በተጣዩ ቀን በጠዋት ወደ ሥራ ልሄድ በር ስከፍት ሁለት ፖሊሶች አስከትሎ ሳጅን መርጊ ደጃፍ ላይ ቆሟል፡፡ ደነገጥኩ፡፡ እምአርጽር ከፖሊሶቹ ኋላ ዱላቸውን ተደግፈው በብልጣ-ብልጥ አይናቸው አጨንቁረውብኛል፡፡

ሳጅን መርጊ በጥፊ ሊመርግብኝ እየዳዳው ፖሊስ ጣቢያ እንደምፈለግ ነገረኝ፡፡ ቀደምኩ፡፡ እምአርጽር ፈጠን፣ ፈጠን እያሉ ከጉኔ መጎዝ ጀመሩ፡፡

‹‹እኔ ነኝ›› አሉኝ ‹‹እኔ ነኝ ሦስቱን ሽማግሌዎች ምስክር አድርጌ የከሰስኩህ፡፡ ሰው መግደልህን እመን፡፡ ፖሊሶቹ ሟቾቹን ፈልገው ሲያጡ ይለቁሃል፡፡ እኔ ግን የእሪ በከንቱ እልጉምጓሚ ቃቹን አደብ እስገዛለሁ ማለት ነው፡፡ በአንተ ወደ መታፈሪ እና መዘበሪ እመለሳለሁ፡፡››

ወይ እዳዬ!

5 - ምርመራ

በሦስት ነፍሶች ማጥፋት ተከስሼ አሥራ አራት ቀን ተመረመርኩ፡፡ መርማሪዬ እራሱ ሳጂን መርጊ ነው፡፡ አሁን ታሁን መረገብኝ ስል፡-

‹‹ጀግና እወዳለሁ›› አለኝ፡፡ ‹‹ጀግና ስመረምር ደስ ይለኛል፡፡ እኔም ጀግና ነበርኩ፡፡ ፈፋ ለፈፋ የማዳፋ፡፡ ገርማይነታቸው አማላጅ ልከውብኝ ነው የተውኩት፡፡ አስራ ስድስት ነፍስ እጄ ላይ አልፏል፡፡ ታዲያ አንዳንድ ቀን ወደዚያው ልመለስ ይሆን እላለሁ፡፡ አሁንም ይንሸጠኛል፡፡››

በወዳጅነት ትከሻዬን ቸብ ቸብ አድርጎ ቀጠለ፡፡

‹‹እኔ የማልወደው ፈሪ እና ሌባ ነው፡፡ ከቻልኩ ሞት እስፈርባቸዋለሁ፡፡ ለነገሩ እዚህም የምቀጠቅጣቸው ከሞት በላይ ነው፡፡››

ፈሪነቴን ቢያውቅ አለቀልኛ... ጀግንነትን ለመተወን ተዘጋጀሁ፡፡



@BOOKALEM

‹‹ሟቾች የታወቁ ናቸው ወይስ ከዚያም ያልፋል?›› ቢል ጠየቀኝ፡፡

‹‹ኧረ ነገሩስ…›› ብዬ ዝም አልኩ፡፡ አጣብቂኝ ገባሁ፡፡ ገደልኩ ብል አፍን የከፈተ ዘብጥያ ውስጥ እራሴን መወርወር ነው፡፡ ውሸት ነው ብል የመርጌ የሞት እኩያ ዱላ አለ፡፡

‹‹እ?››

‹‹እርስዎ ፈልገው ቢደርሱበት አይሻልም ጌታው››

‹‹አንተስ ብትነግረኝ ምን ክፋት አለው?››

‹‹እ-ይ፡ ይሄ የጀግና ወጉ አይደለም››

‹‹እሱስ እኔም የወደድኩልህ ሙያ በልቡ መሆንህ ነው፡፡ እንግዲህ ቃል እንገባባ፡፡ እኔ ተዚህ መንቅዬ አወጣሃለሁ፡፡ አንተ ደሞ ደመኞቼ ብዙ ናቸው፡፡ ተዚህ ተወጣህ ላትተወኝ ቃል ግባልኝ››

የአምጳርጵር የጠብ ቃልኪዳን ትዝ አለኝ፡፡ በግንባሬ ላይ ተፅፎ ይከታተለኛል፡፡ ሌላ ምን አማራጭ አለኝ?

‹‹ይሁን›› አልኩ፡፡

ተጨባበጥን፡፡ ከዚያች ዕለት በኋላ የነበረውን አስር ቀን በአስረኛ ደንብ አላላለፍኩም፡፡ መርጌ ማታ መጥቶ ‹ለምርመራ ይዞኝ ይወጣል፡፡ ይሄን ጠጅ ስንመረምር አምሽተን ፖሊስ ጣቢያችን እንገባለን፡፡

ሁለት ነፍሰ-ገዳይ ግንባር በመፍጠሩ እሪ በከንቱዎች ተርበተበተ፡፡ አምጳርጵር ብቻ ተንጠረበበ፡፡

‹‹አላልኳችሁም? እንግዲህ ሰው ሁሉ ደመ-ከልብ ሆነ›› አለ፡፡

## 6 - ጠበለተኛው

ሳጂን መርጌ ለትምህርት ቤቱ የሣፈልኝ ደብዳቤ አስፈሪ እንዲሆን ሀሳብ አቀረበ፤ ይሁን አልኩ፡፡





‹‹በምስት ነፍስ ማጥፋት ተጠርጥሮ ቢታሰርም ማረጋገጥ ስላልቻለ ብቻ ምርመራው በእንጥልጥል ተይዞ…›› የሚል አስፃፍኩ፡፡

ዳይሬክተሩ ደብዳቤውን ካነበበ በኋላ የጥንት ወዳጅነቱ ጠፋች፡-

‹‹ካስፈለገ በቦታህ ሰው ተክተን ያሰኘህን እረፍት መውሰድ ትችላለህ›› አለኝ፡፡

‹‹ግዴለም ለእኔም ስሰራ ይሻለኛል›› አልኩት፡፡

‹‹ድንቅ›› ተቁለጨለጨ፡፡

ይሁንና ሳምንት ማስተማሬንም እንጃ፡፡ እንደገና ለሰባት ቀን የምቀርበት ከእትም በላይ የሆነ ነገር ገጠመኝ፡፡ እንዲህ ነው፡-

አምጳርጵር እንደተፈታሁ ሊላ ወሬ ጀመሩ ‹‹የተለቀቀው እንኮሉ የተቃወሰ መሆኑ ተረጋግጦ እንጂ መግደሉስ ገድሏል››

‹‹አሁንስ አበዙት!›› ስል ሺ-ትርንጥ ፊቴ ላይ ትጋረጣለች፡፡

‹‹ብስተርጅና ዘመኑ ታፍሮና ተከብሮ ቢሞት ምን ትጉዳለህ?››

ልትወድቅብኝ ይሆን? ልትጨፈልቀኝ? ‹‹ይሁን›› አልኳት፡፡

እሪ በከንቱዎች አንዳንዴ ባለቤቱን ደጃፍ ላይ ጠርተው አናግረዋት ይሄዳሉ፡፡ ነገሩ ልምምጥ መሆኑ ነው፡፡

‹‹ባለቤትሽ እንዴት ነው? አሁን ከሰሞኑ?››

‹‹ብሶበታል›› ትላቸዋለች፡፡ ‹‹እኔስ እድሌ ነው፡፡ ሌት ቁጭ አድርጐ ያሳድረኛል፡፡ አባዬን ማን እንዳንንጠጠው እንጃ አሁን ሄጄ ካልገደልኩ ሲል አደረ፡፡››

‹‹ሥራው ቢሄድ ጤነኛ ይመስላል››

‹‹እዎ፡ ቀን ሲያብሰለስል ይውልና ሌት ነው የሚነሣበት፡፡››

‹‹ይሄን የመሠለ ልጅ ምን አገኘው?›› ይሉና የፍርሃት መርፌ ተወግተው ይሄዳሉ፡፡

አምጳርጵር ተፍነከንከዋል፡፡ ሠፈሩን በማን አህሎኝነት ያስሱታል፡፡ እሪበከንቱዎች፡-

‹‹ለምን ትንሽ ትልቁን ይነግሩታል?›› ሲላቸው፣

‹‹ኋላ የልጅ ባል ሥጋው አይበላ›› ይላሉ፡፡ ‹‹ለተቃኑ ነውኛ...››

እኔን ደግሞ፡-

‹‹እንዳንዴ ብቻህን ብትነጋገር፣ ያየኸው ላይ ብታፈጥ ይነበር›› ይሉኛል፡፡

አንድ ሌሊት ባለቤቴ ያለውትሮዋ ተነሲታ በሩን ከፍታው ተመልሳ ተኛች፡፡ ምን ማድረጓ እንደሆን በማብሰልሰል ላይ ሳለ በተከፈተው በር ድንገት ሦስት ጠብደሎች ገቡና የተኛሁበት ተረባረቡብኝ፡፡ እንዱ ግንፍሌ እንደሆን በፍልጥልጥ ፀበኛ ግንባሩ አውቄዋለሁ፡፡ የፈጥኝ አስረውኝ ሲጨርሱ አምጳርቋር መጡ፡፡

‹‹በሉ እንዲሁ ይደርና ሲነጋጋ ሲል ጠበል እንወስደዋለን፡፡ እናንተ ሂዱና ሰዓቱ ሲደርስ እቀሰቅሳችኋለሁ፡፡ እንዲህ ነው ጉረምሳ›› ብለው ከሸኙ በኋላ ወደ እኔ ዞሩ፡-

‹‹እየህ የአሪበከንቱን ሰዎች አታውቃቸውም፡፡ ከጤናኛ ሰው ማመዛዘን የጐደለውን፣ የተቃወሰውን ይፈራሉ፡፡ እንተ ጠበል እንድትሄድላቸው ብር እዋጥተዋል፡፡ ነገ ጠበል ትሄዳለህ፡፡ ወዲያውም ላንተ ጥሩ ነው፡፡ የተደበቀ በሽታ ካለብህ ይወጣልሃል፡፡ ለእኔም ጥሩ ነው እንደ አማትነቴ የመፈራትህና የመከበርህ ተካፋይ እሆናለሁ፡፡››

አንድ ሰባት ተጠምቄ ሁለቱን ሰባት አቋርጬ መጣሁ፡፡

## 7 - ማስታወሻ

የመጣው ይምጣ ወደማለት አዘንበልኩ፡፡ ይሄንን አምጳርቋር ተረድተውት ኖሮ አንድ ዘዴ ተጠቀሙ፡፡

ትዳሜ ጠዋት የልጅ ልጆቻቸውን እግተልትለው መጡ፡፡ እኔ አምጳርቋር እንደሆኑ ሳውቅ የኩርፊያ ተከናነብኩ፡፡

‹‹አባዬ ምነው በጠዋት?›› ትላቸዋለች ሺ-ትርገዋ ልጆቿን መለሰ ብላ አለማየቷን ገና ዛሬ ልብ አልኩ፡፡





‹‹ጋዜጣውን ሁሉ እዚህ አምጥተን ለጥፈነዋል፡፡ ልጆቹን በምን ላስጠናቸው?›› አሉ፡፡

ሆን ብለው ሊያስፈሙሁብኝ እንደ ዶለቱ ገመትኩ፡፡

‹‹ብሉ ልጆች፣ እንቺ ትልቋ ይሄን በትላልቅ የተፃፈውን አንብቢ... እም እሱን፣ በያ ምን ያርበተብትሻል?››

ልጅቷ በግድታም ቢሆን አነበበች ‹‹ታዳጊዋን የደፈረው በ15 ዓመት ፅኑ እስራት ተቀጣ››

ጆሮዬ ቆሟል

‹‹ጥሩ፣ እንቺ ደሞ ይሄንን አንብቢ-- እም እሱን--በያ››

በሆዷ ስትቆጥር ዝምታ ሰፈነ፡፡ ‹‹የልጆች እናት የጠለፈው አስራ ሁለት አመት ተፈረደበት››

‹‹ጉድ ፈላ›› አልኩ በሆዴ፡፡ ይሄ ሁሉ እኔ ግድግዳ ላይ ነበር? ለምን ለጠፉት?

‹‹አንቺስ? ይሄ ምን ይላል? እ? በይ ፊደሉን ስጠቁምልሽ እንቺ ጥሪ ይሄ?--ይሄ? ይሄ--ይሄ--- አንድ ላይ››

‹‹ከፍተኛው ፍርድ ቤት በደፋሪው ላይ የእስራ አራት አመት ቅጣት ወሰነ››

‹‹ያንሰዋል›› አሉ አምጳርቋር ‹‹እኔ ብሆን ይግባኝ እላለሁ፡፡››

የተከናነብኩበት የተኛሁ መስዬ ትንፋሼን አበረከትኩ፡፡

‹‹እንቺ ትንሿ ይሄን አንብቢ፣ አልቻልም? እ? እስተዛሬ ምን ሲደረግ? በይ ሞክሪ... ይሄ? ይሄ? ይሄ?-- ለነገሩ ዘር ዘሩን ይዘሽዋል፡፡ ቅጥሉ ነው የሚቀርሽ፡፡ እኔ ላንብብ...››

‹‹ልጁ የተደፈረችበት አባት ደፋሪውን ገደለ፡፡ ፍርድ ቤቱ የአራት አመት ፅኑ እስራት ፈርዶበታል፡፡››

የእኔ መግደል ካንተ መድፈር ጋር አይነፃፀርም ማለታቸው እንደሆነ ገብቶኛል፡፡ እንዳልሰማ ዝም፣ ጭጭ፡፡ ዝምታና ጭጭታዬ የማድፈጤ ብቻ ሳይሆን በፍራቻዬ ዳግመኛ የመወረሬ ምልክት ነበር፡፡

## 8 - ተማፅኖ

‹‹ብቅሎ ማሰሪያዋን በጠሰች፣ ሰገዛ እራሷ አሳጠረች›› ነው:: እንግዲህ ማሰሪያዬን በገዛ እራሴ አሳጥሬአለሁ:: እምጸርጽር ተደጥ ይጠባል... በተቀናነሰ ቀለብ፣ በተጣበበ ቅጥር ባርነት ቀመሰ ህይወት መምራት::

ወደነበርኩበት ለመመለስ የሚጠቅመኝ የእምጸርጽርን ልብ ማለዘብ ብቻ ነው:: ነጭ እረቂ ገዝቼ ወደ ቤታቸው ሄድኩ::

ወደውስጥ ስዘልቅ የልጅ ልጆቻቸውን እስከ ምንጃሳቱ እያስቆጠሩ ነበር::

‹‹ዋ-እናንተ ልጆች!›› ይላሉ:: እኔን ሲያዩ ችላ እንደማለት ብለው በቁመት እጅግም ወደማይበልጧቸው ልጆች አተኮሩ::

‹‹እንደምን አደራችሁ?›› እንደአዲስ ገቢ ድምጼን ከፍ አድርጌ::

‹‹እንደምን አደርክ?›› ብለው በኩርፈያ ፊታቸውን አዙረው ‹‹መቼ ከንብንብህ ተገለጠ?››

‹‹የምን ክንብንብ?››

‹‹ቤትህ ስመጣ ተከናንበህ ሳየህ ለአመትም የምትገለጥ አይመስልም ነበር:: ‹ናዳ መጣብህ ቢሉት ተከናንቤአለሁ› እንዳለው ሰው መሆኑ ነው:: መቼም ናዳን ከንብንብ እንደማይገታው የቂስ ልጅ ነህና ላንተ አልገለጥም፤››

አሁንም ሰደቡኝ:: ምን ይሆናል? ፈገግ አልኩ የግዴታ ፈገግታ::

‹‹ምን እግር ጣለህ?››

‹‹ይቺን መርቀው ቢከፍቱና እየቀመስን ብንጨዋወት ብዬ ነው::›› በብብቴ የያዝኩትን በጋዜጣ የተጠቀለለ እረቂ ጠረጴዛ ላይ ጉለትኩት:: እረቂውን በማየት ብቻ ዘና አሉ:: ምልክትነቱ ይቅርታ ያድርጉልኝ የሚል መሸንፍ እንደሆነ አላጡትምና::

‹‹በደህና ጊዜ ቢሆን ጥሩ ነበር:: አንተ ግን ሲያዝሉት ነካሽ፣ ሲያወርዱት አልቃሽ ሆነህብኛል›› ብለው የጨው እምድ





የመሰሉ የልጅ ልጆቻቸው ላይ አፈጠጡ ‹‹ወደጓዳ አትገቡም ወይ? እዋቂ ሲያወራ...›› እየተደነቃቀፉ ገቡ::

እረቂውን አንስተው ጋዜጣውን እንደ መጋረጃ ገለጥ አድርገው አዩ::

‹‹ጅ-ኪ-ኪ-ኪ የፈረንጁ ነውና:: እንደጥፋትህ ቢሆን ሰንጋ መጣል ይገባህ ነበር:: ግን ምን ይሆናል እራስህ ቆርቁሮህ ስትመጣ ቢደ እጅህንም ቢሆን ሁለተኛ ነገር ነው::››

ተቅለሰለስኩ::

እረቂውን ይዘው ቆሙ:: እኔም ቆምኩ:: መክደኛውን በቀኝ እጃቸው እየጠመዘዙ፦

‹‹የአብርሃምና የሳራን ነጭ እረቂ የባረከ የእኛንም ይባርክ›› አሉ::

ሳቁ መጣ:: እራሴን ተቆጣሁት::

‹‹ስዚህም እማቻችን ልብ ሰጠው የሚደባደብበት ቀልብ ስጠው እማቱን የሚፈራበት፣ ዘር ስጠው፣ ትዳሩን አጥብቆ የሚይዝበት::›› ጨረሱና በክዳኑ ቀመሱ::

* * *

ቁርስ ሳንበላ ስለተያያዝነው ገና ሁለት ሁለት መለኪያ እንደቀነደብን ሞቅ አለን:: ሞቅታ ደጉ በክብር እሳቸው ዝቅ እኔ ከፍ ያለን ያህል እኩያነት ተሰማን:: እንዲሁ በቁመት እኔ ዝቅ እሳቸው ከፍ ያሉ ይመስል ትክክልነት ሰፈነብን::

'እንዲረሳሳ የምፈልገውን ጉዳይ አነሳሁ::

በሞቅታ ‹‹ያንዬ ስለጆቢራ እና ስለርስዎ እባት ያነሳሁት እንዳ ብዬ ሳይሆን ለወግ መነሻ እንዲሆነን ነበር::››

ሞያ በሚገፍ ሞቅ ያለ እይታ ቆዩብኝና ‹‹መች አጣሁት›› አሉ::

ሞቅታዬ ልትበር ካቆበቆበች በኋላ እየተረጋጋች ‹‹እውነት?›› አልኳቸው::



@BOOKALEM

‹‹ኋላ ውሸት ነው? ሰማህ ወይ፣ ከንተረቱት የእርበኛ ልጅ ይወጋል፣ የእሮጌ ልጅ ያወጋል'ም አይደል?

በንገር ወጋኝ፡፡ ግልፍ ሲለኝ ካለ በኋላ እስታውሼ ተውኩት፡፡

‹‹መቼም አባቴ ፈሪ፣ ከሃዲ ነበሩ የሚል ምድ አይገኝም፡፡ እንደውም የፈረሰውን የአባቴን ታሪክ የሚያበጃጀው ይበዛል፡፡ ጀቢራም አባቴን ተኔው አቆራኝቶ የሚያወጋው የዛው ቢጤ ነው፡፡ ሐረግ ሬ ያድጋል?››

ገና ዛሬ እዛውንት ሆነው ታዩኝ፡፡ ወጊ ተመቻችቼ ተቀመጥኩ፡፡

‹‹ጀቢራ እንደሚለው ሳይሆን እረበከንቱ ስሟን ያገኘችው ከእምዬ ምኒልክ ነው፡፡ ገና አዲስ አበባ መቆርቆሯም አይደል? ዛዲያ እንዲያና እንዲህ ሲባል እረበከንቱ ያኔም ነባር ሠፈር ናት፡፡ እጤ ምኒልክ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያንን ሲያሰሩ ሆነ ጣይቱ ሆቴልን ሲቆረቁሩ በዚችው እየተሳበቱ ነው፡፡ እረበከንቱዎች የእጤውን እጀቢ ተኳላ-ተኳላ ሦስት አራቱን እያፈኑ ያስቀራሉ። ጠበንጃ ለመግፈፍ፡፡ እጤ ምኒልክ ጣይቱ ሆቴል ደርሰው፦

‹‹ባላንባራስ?›› ሲሉ

የለም

‹‹ባልደራስሳ?››

የለም

‹‹ያያቸው የለም ወይ?››

ዝም፡፡ ‹‹ብቻ እስከ ዘብጡ ድረስ አጭር ምንሽር ይዘው ተኳላ-ኋላ ሲያፈደፍዱ ነበር›› የሚል ይገኛል፡፡

‹‹ዛሬም ያው፣ ነገም ያው ሆነ፡፡ በዚህ መካከል አጤ ምኒልክ ተሰልደቶ የማረኩት ጠበንጃ እያሽቆለቆለ ሄደ፡፡ ከግለቱ በፊት አሉና እረ በከንቱ አፋፍ ላይ ማስታወቂያ አስለጠፉ፡፡››

‹‹በዚህ አትተሳለፉ፡፡ ለእንጉስ ያልተመለሰ ሽፍታ አለበትና ወደ አራዳ የምትሄድ ሳይ-ሳዩን አዲስ መንገድ ተከፍቶልሃል፡፡





ይሆን እያልንህ በዚህ የተሳለፍክ እረበከንቱ ነው፡፡ ተዚያን ጊዜ አንስቶ ስሟ ፀናላት፡፡ እረ በከንቱ ተባለች፡፡››

‹‹ለካ ለዚህ ኑሯል?››

‹‹ነው መቼም ባትኖርበትም ታውቀዋለህ፡፡ ወንድነትና ጠበንጃ ተገጠሙ ያቅበጠብጣል፡፡››

ምን ማለታቸው ነው? ሳይወርፉ ማውጋት አያውቁም ይሆን? አልኩ በልቤ፡፡ በአፌ ‹‹እ-ሺ›› አልኳቸው፡፡

‹‹እረበከንቱም ተቅበጠበጠች፡፡ ጠበንጃው በንፍስ ወከፍ ተዳርሷል፡፡ ሴቶች ተጠርተው በሉ በሶውን፣ ድርቆሹን አበጃጁ ተባሉ፡፡

‹‹የት ትሄዱ?›› አሉ ሴቶች

‹‹ዘመቻ››

‹‹ማንን ትወጉ?››

‹‹ወሪሳን-እናስገብራለን››

‹‹ተሆነላችሁ ምን ከፍቶን››

ሁሉ ተዘጋጀ፡ የዘመቻ ወጉ እንዲሟላ እንጂ ወሪሳ ስንቅ የሚያስፈልገው እርቀት ላይ አልነበረችም፡፡ ሴቶቻችንም የዘማች ሚስትነት ወጉን መሻታቸው ግድ ነው፡፡ የሚወቀጠውን ወቃቀጡ፣ የሚጨበጠውን ጨባበጡ የሚደርቀውን አደራረቁና ‹‹በሉ'ንሱ ሂዱ ዝመቱ›› አሉ፡፡

ዘመቻው በበነጋው ማለዳ እንዲሆን ተቆረጠ፡፡ የእረበከንቱ የጉበዝ አለቃ የእኔ አባት ከትከቱ ማንአይቶት ናቸው፡፡ ነጋሪት አስጐሸሙ ይባላል፡፡

‹‹እንዲህ ያለ የጉን ውጋት ተነስቶብኛልና አቅም ያለህ በንልበትህ፣ አቅም የሌለህ በፀሎትህ እርዳኝ፡፡ ወስልተህ የቀረህ ግሪያምን ትጣላኛለህ፡፡ ለዚህ አማላጅ የለኝም›› አሉ፡፡ እንደው ለወጉ ነው'ጂ ከእረበከንቱ ጦር አይቶ የሚቀር የለም፡፡

እናቴም ጀግና ነበረችና በበኩሏ አዋጅ አስነገረች፡፡

‹ጀግና እወዳለሁ:: ወደኋላ የምትልበት አንዳችም የለህም:: ኸጦር ሜዳ ብትሞት ልጅህን ተማሪ ቤት አስገብቼ እንደ ልጄ ከባክቤ አይዛለሁ፣ ይሄ ቃሌ ነው› አለች::

እባቱ እለቱን ደብዳቤ ወደ ወረሳዎች ላኩ::

‹‹...ደረሰንባቸው ሳይታጠቁ ማለት ላላታተንም፡፡ ይሁንና የጀግና ወጉ ባለመሆኑ እሽምቀን መውረፍን ትተነዋል:: ታጠቁና ጠብቁን:: ከቻላችሁ ወደእረበከንቱ ወንዝ ዝቅ ብትሉና ብትገጥሙን እንወዳለን::››

‹‹ጦርነቱ ሦስት ጊዜ ተካሄደ:: እረበከንቱዎች በንቂስ ወጥተው ሲያጠቁ፣ ወረሳዎች በንቂስ ወጥተው ይሸሻሉ:: ቢደገም ያው፣ ቢደገም ያው... እሪ በከንቱዎች ታከቱ:: ወና ሠፈር ይቶጣጡና እፁን-ታሁን ይመጣሉ በሚል ይጠብቃሉ:: እመሻሽ ላይ ‹እንግዲህ ምን በጀን?› ይላሉ:: እንደሰባራ ቤት ጠባቂያቸው አደረጉን:: እኛ እዚህ ብናድር እነሱም እዚያ ያድራሉ:: እግዚአር ለኛ አላላቸውምና የማንኳኳን አደረገን:: እንግዲህ ወደየምሽቶቻችን እንሂድ›

‹‹እሪ በከንቱዎች ሲሄዱ ወረሳዎች ይተካሉ:: የተሰጣው ደርቆ፣ የተጣደው በስሎ ይጠብቃቸዋል:: እቧን በልተው ያድራሉ:: እረበከንቱዎች በጀግንነት ማስገበር እንጂ ዘረፋ ነውራቸው ነው:: እንግዲህ ከዚያን ጊዜ አንስቶ እረበከንቱ የወረሳ ደመኛ ሆኖ ቀረ:: የጃቢራም አባት የወረሳ የፊሪ አለቃ ነበሩና ቂማቸውን ለልጃቸው አውርሰው ሞቱ:: ይሄው ነው::››

## 9 - የድል በዓል

የነጭ አረቄ ስካር ነጭ ነው:: ሁለመናው ጉም ይወርሰውና እውኑ ህልም ህልም ይመስላል:: ቤቴ የደረስኩት በህልም ጢያሪ እየተንሳፈፍኩ ነው:: ጊዜ ቢሆንም አልጋዬን ከፉኛ ናፈቅኩ:: ይሁንና እቤት ስደርስ ሺ-ትርጉተ ጉብታ መሰላ ተከፍላ ጠበቀችኝ:: ቅዱስ ላሊበላ ቢያገኛት ኖሮ አስፈልፍሎ ሌላ ቤተ-እግዜር ያሰራባት ነበር:: ከግዝፈቷ፣ መጠጠሯ::

‹‹አትነሽም ወይ ዝም ብለሽ ታይኛለሽ?›› አልኩ ነገር-ነገር እያለኝ::





‹‹እስይ-እስይ ዛሬስ ወንድ ወጣህ›› አለችኝ::
‹‹ልትደበድበኝ ነው፣ የቤት ወግ ልታሳየኝ››

‹‹ከዚያ በፊት አለኝ ጉዳይ›› አልኳት::

እየተሽከረመመች በሩን ዘጋች:: አልጋ ላይ ተቀመጥኩ:: ወደጓዳ ገባ ብላ እፍታም ሳትቆይ መጣች:: ስትገባ ልብስ ነበራት፣ ጓዳ ሽፍታ ያለ ይመስል ልብሷን ተገፍፋ እርቃኗን መጣች:: እንዲህ ሆና ለመጀመሪያ ጊዜ ሳያት ነበርና ደነገጥኩ:: ብዙ እጥፋት፣ ብዙ ንብርብር ያለው ገላ:: በዚህ ላይ ጉርብርብ ነው:: ከረት የተሞላ ትልቅ የጨርቅ ቀረጢት::

ከዚያ በኋላ የሆነው ነገር ደብዛዛ ቢሆንም አልተረሳኝም:: ግን ልክደው እገደዳለሁና ከእውንታ መዝገቤ ፍቄዋለሁ::

* * *

ለመጀመሪያ ጊዜ ግድግዳዬን አወቅኋት:: ማለቴ... ግድግዳው ላይ የተለጠፈው ጋዜጣ ምን ምን እንደሚል:: ‹‹ፖሊስና እርምጃው›› ብዙ የእኔን የመሰለ መአት ይዟል:: መጨረሻቸው ያጣፈ ደፋሪዎች፣ ጠላፊዎች፣ ገዳዮች፣ ዘራፊዎች... ሞት፣ ዕድሜ ልክ፣ ሃያ አመት፣ አስራ አምስት አመት ተፈረደባቸው ይላል:: እምልርጽር ሆን ብለው በፍርሃት አጥረውኛል::

‹‹ኡ-ሁ-ሁ-ሁ-ሁ----›› በረጅሙ ተነፈስኩ::

‹‹ምነው? ፍቅርዬ፣ ተንሰተሃል? እፉር በሆንኩ፣ እምትበላው ተዘጋጅቷል፣ ልብህን ቅዝቃዝ የሚያደርግ መጠጥም አለ...›› ሺ-ትርጉተ ጠብ እርግፍ አለችልኝ:: የልቧን አድርሼላታለሁ ማለት ነው? ኩራት ኩራት አለኝ:: ከዚህ በላይ ለወንድ ድል የታለውና? የጦር ሜዳው፣ የችሎቱና የድብድቡ ሁሉ መርታት ለወንድ ቅዕሉ ነው:: ዋናው እሸናፊነትና ተሸናፊነት ያለው ከቤት ጋር በአልጋ ጦርነት ላይ ነው::

‹‹እስቲ ተይኝ፣ እረፍ ልበልበት›› ከድል ፀኋላ ያለ ፋክራ መሆኑ ነው::

‹‹እሺ ጌታዬ - ይሁን›› ሺ-ትርጉተ የመሸነፍ ማንቀላበጥ አሳየች::



@BOOKALEM

ሺ-ትርጉተ ሲያይዋት ለዚህ ተሸናፊ አትመስልም፡፡ እስ
ማሽንፍ የሚፈትን ከባድ የትልበት ሥራ ስለሚመስለኝ ሌላ ትዕ
ዕዳ አድርጌ እቆጥረው ነበር፡፡ ድንጋይ ሲፈልጡ ውሎ ሲፈል
እንደማደር የከባድ ወንጀለኛ ቅጣት ነው ብዬ ደምድሜ ነበር፡፡
ነገር ግን ትጥቁን ፈትቶ እንደተኛ ተዋጊ ድንገት ተማረከችልኝ፡፡
የጐመን ቅንጥስ ይመስል ሲያይዋት ከባዷ ሲቀቅሏት ምን
ሆንችብኝ፡፡ ድሂኔ እክ የእሷ ተቃራኒ ደግሞ አለች፡፡ ሲያይዋት
ቀላል፡ ሲቀቅሏት ከባድ---እ?-እ?-እ?-----እ?-እ?-እ?- ሦፍን
ሦፍን፡ ከሀዲ ነኝ፡፡ እስታውሺያት እንኳ አለማወቴ፡ በእኔ ችግር
ተጠምጄ የዕለት-ተዕለት እርምጃዬ ቀልቤን ወስዶብኝ እኔ
ከነሥራሽ ዘነጋሁ፡፡ እንባዋ፣ ሦንቀቷ፣ ፍቅሯ--- አሁን እኔ ምኑ
ነኝ? የቂስ ልጅ ነኝ? የአማርኛ አስተማሪ ነኝ?....

## 10 - የሽንፈት በዓል

ሦፍንን ለተከታታይ ሦስት ቀን ከሐሳቤ፡ ከሀሊናዬ፡
ከልቦናዬ.... ሳልንጥላት ቆየሁ፡፡ እስካሁን የዘነጋሁበት የጁ
በመሆን ስቃዩን በፀጋ ተቀበልኩ፡፡ ካንዴም ሁለቴ ወደ ወሪ
ለመሄድ ዳድቶኝ ትቼዋለሁ፡፡ ሦፍንን ብቻ ሣይሆን የአክስቴን
ልጅና ቤቱንም ሦምር ዘንግቼ ከርሚያለሁ፡፡ ለዚህ ደግሞ በእነዚህ
ቀናት የደረሰብኝ መብከንከን ሲያንሰኝ ነው፡፡

ወደቤት ሳመራ ሺ-ትርጓሞን ከሩቅ አየኋት፡፡ በር ላይ
ተኮፍሳለች፡፡ ሰሞኑን ያመጣችው እንዱ ጠባይ ነው፡፡ ግቢውን
ሞልታ ቁልቁል ወደመጣባቸው ቤት ታያለች፡፡

እንደደረስኩ ‹‹ምነው?›› እልኳት

‹‹ምነው?›› አለችኝ፡፡

‹‹በር ላይ መጐለትሽ...››

‹‹ለብልሃቴ ነው››

‹‹የምን ብልሃት?››

‹‹እይ የመጣባቸውን ልጅ ደጋግሜ በማየት እሱን የመሰ
ለመውለድ፡፡››





‹‹እንዴት ማለት?››

‹‹ላይገባህ ቀርቶ ነው? ዕንስ ይገባሃል›› የተነሳ መንቀጥቀጥ መሬት የመሬት
የትልበቱ ሚስጥ በከባዱ ተከናወኑ፡፡

‹‹ሕ-ሕ-እንዴት? እንቺ? ከማን?....››

‹‹ከማን ይሆናል? ከአንተው ነዋ! እኔ እንደሆን ጥብቅ

ነኝ ገና ከትናንት በስተያም አይደል እንዴ እንትን....
››

‹‹ሕ-ዎ››

‹‹ሕ-ና?›› ነፃ መውጪያ ቀዳዳ ያገኘሁ መሰለኝ፡፡

‹‹ከባለቤቱ ያወቀ--- እሉ፡፡ እራሴን የማውቅ እኔ ነኝ፡፡ እን
ኳን ወንድ ደርሶብኝ ሱሪም ቢያንጥፉብኝ ተብ! ነው፡፡ ወሩ መጥቶ
ነድ ታይቶ እሉ፡፡ እኔ እስተዚያም አልቆይ፡፡ እውቀዋለሁ፡፡››

በረጅሙ ተንፈስኩ፡፡ ደሜ ከቀረ መቼም ቀሊጨ ቀረሁ
እንደማለት ያለ መርዶዬ ነው፡፡ የእሷ ዘብጥያነት ሳያንስ ሌላ እሷን
የመሰለ ዘብጥያ? እድሜ ልክ ፍርድ! እለም በቃኝ!

‹‹ፍቅርዬ ምን ቢወለድህ ትመርጣለህ?››

‹‹ሚኖ የለሽም? የልጅ ዝርዝር›› ብልሎ እለብኝ፡፡

‹‹እኔ ወንድ! የመጣባቸውን ልጅ የመሰለ ነው
የምፈልገው...››

‹‹ድመት ሲያጣ እባትሽንም ያንጠለጥላቸዋል›› የምለውንም
የማውቅ አይመስለኝም፡፡ ወደ ቤት እልፎእት ገባሁ፡፡ ቤቱ
ጨለመ፡ ሺ-ትርጉተ ገባች ማለት ነው፡፡

‹‹ምን ለማለት ፈልገህ ነው? ይቺን ሰሞን ከፉኛ
ተቸናጥተሃል›› አለች፡፡

ያስመዘገብኩት ድል በጊዜ እርገሙት እየደበዘዘ መጥቷል
ማለት ነው፡፡ ሌላ ድል ለማስመዝገብ በመሞከር ያልተረጋገጠውን
የልጅ ነገር አላረጋግጥም፡፡ አፈጠጥኩባት፡፡

‹‹ምንስ ብል?››

‹‹ዋ!››

‹‹ምናባትሽ ትሆኚ?››

‹‹እባቴን? አንተ? ዘረቢስ...››

‹‹ዋ!›› አልኳት፡፡ እየገባሁበት ያለው ፀብ እንደመንዝ ተረት መሣቂያ እንደሚያደርገኝ አላጣሁትም፡፡ በሰፈድ ተራ እየገፉ ‹‹ግፉ ተንጣጣ›› እንዳሉት አይነት፡፡ ይሁን እንጂ እራሴን መገሰጥ ተሳነኝ፡፡

‹‹ዋ-ዋ-ዛሬ!›› አልኳት፡፡

‹‹ወንድ! ወንድ!›› አለችኝ፡፡

ለወንድ ከዚህ የተሻለ ምን ድንበር አለው? እንግዲህ የቀረኝ አይኔን ጨፍኜ ወደ ድብድቡ ማምራት ነው፡፡ ምኗን መምታት እንዳለብኝ እንኳ በቅጡ ሳላገናዝብ ዘለይ ተንጠላጠልኩባት፡፡ ተንገዳግዳ ከመውደቅ መትረፏ ትዝ ይለኛል፡፡ እጄ ምኗ ላይ እንዳረፈ አላውቅም፡፡ አይኔ እንደተጨፈነ እጄን ሰሰድ ቆየሁ፡፡ አይኔን ስገልጥ የሺ-ትርንጦ ፊት እና ቤት ተዝረክርኳል፡፡ ጆሮዬን ስከፍት የሚሰቱ ጩኸትና የጐረቤት ሃይ ሃይታ ቤቱን አፍኖታል፡፡ እጄን ሰድጄ ፊቴን ሰዳብስ እኔም ደምቻለሁ፡፡

ነገሩ እንዳይሆን ሆኖ መደምደሙ ከደሚ መፍሰስ በላይ አስከሮ አሆረብኝ፡፡ እንግዲህ እምጷርጵር በተደፈርኩ ይጕፈላሉ፡፡ ልጃቸውን አፋትተው ይወስዳሉ፡፡ ለእኔ መጥሪያ ያመጣሉ፡፡ የሞተ የመሰለው የመድፈር ፋይል ከጭንቅላቱ ቀና ይላል፡፡ የገዛ ፊርሜዬ እንደከሣሽ ልጅ በገዛ እራሴ ላይ ይመሰክርብኛል፡፡ እርግጊደን ይሆናል፡፡





# ምዕራፍ ስድስት

## 11 - የሚስት ዓይነት

እምጷርጵር እንድ ግራ አጋቢ ብሒል አላቸው፤ እንዲህ

የሚል፡-

‹‹ሲጠሩህ ዝም በል፣
ሳይጠሩህ አቤት በል፣
ነገሩ እንዲዘናበል፡፡››

በልጃቸው በኩል ለፀብ ስጠራቸው ዝም አሉ፡፡ እንግዲህ እንድ ቀን ሳልጠራቸው ‹‹አቤት›› ይሉና ነገሬን ያዘናብሉብኛል፡፡ በሁለተኛው ቀን እራሷ ሺ-ትርንጦ በኩርፊያ አባቷጋ ሄደች፡፡ ዝም ብል የተደፈሩ ለመሄድ ወይም እማላጅ ለመላክ ወሰንኩ፡፡ ይመስላቸው ይሆናል፡፡

ብዙ ሰዎች ‹‹አማልዱኝ›› ስል እኛ ከእምጷርጵር ጋር እንነካካም በሚል እምቢ አሉኝ፡፡ እራሴ ሄድኩ፡፡

እንደፈራሁት መሆኑ ቀርቶ እንደውም እምጷርጵር ከእኔ ጎን ቆሙ፡፡

‹‹ዝም በይ! እንደውም እሱ ሆኖ ነው፡፡ እኔ ብሆን እግልሽ ነበር፡፡ አይ ጊዜ! አይ ጊዜ! ወንድ ሲቆጣ ወደውጭ?...››

‹‹እ-ህ! ሲመታኝ ታዲያ...››

‹‹ቢገድልሽስ? ወደውጭ ይታያል? በይ አሁን ቤትሽ ግቢና ጠብቂው››



@BOOKALEM

ኢየሱስ ያንን ተራራ ብታዙት ተነቅሎ ወደናንት ይመጣል እንዳለው እንዲሁ ከተአምር በሚቆጠር አኳኋን ሺ-ትርንዋ ተራራ እምጳርጽር ኢምንቱን ታዘዘች፡፡

የንዳውን መጋረጃ ገለጥ አድርገው የሚያሥሉቱትን ነጫጭ ህፃናትም እምጳርጽር ተቆጡና ሾክክ ብለው ባለፈው ጊዜ ያስተረፍናትን ነጭ አረቄ አመጡ፡፡ እየጠጣን ወግ ጀመርን፡፡

‹‹በእነ አባቴ ዘመን የነፍስ አባታችን እናቴን ሲመክሯት የሰማሁት ነው›› አሉ፡፡

‹‹ምን አሏቸው?››

‹‹ነገር ላይ ክልብ-ክልብ አትበል፡፡ ልነግርህ አይደል? ለዛ ቢሉህ ይሄኔ…››

ስለልጃቸው በሌላ አቅጣጫ ነገር ሲፈልጉኝ መሰለኝ፡፡ ሳልጠራቸው አቤት ሊሉኝ…ዝም!

‹‹አባ ምን አሉ፤ መጥፎ የምትባለው ሚስት ባሏ ዱላ ሲያነሳ የምትሸሸው ናት፡፡ መጥፎም ጥሩም ያልሆነችው ሚስት ደግሞ ዝም ብላ የምትደበደበው ነች፡፡ መልካም የምትባለውን ሚስት እግዚሐር ሲመርቅ የምትገኝ ናት፡፡ እሷም ገና ለገና ባሌ ተቆጥቶ ሊመጣ ይችላል በሚል መደብደቢያዋን ዱላ ቆርጣ የምትጠብቅ ናት፡፡ እዬ! ጥሩ ጊዜ አለፈ፡፡ በማሚጠሚው ላይ መልካሟ ሚስት የት ተገኝታ?›› አረቄያቸውን በአንድ ትንፋሽ ጨለጡ፡፡

እኔም አሳቸውን ለመምሰል ንዴታቸውንና አጠጣጣቸውን ኮረጅኩ፡፡

‹‹መልካሟን ሚስት ባገኟት በልጃገረድ ደንብ ባገባኋት ነበር›› አሉ ቀልድ በማይመስል አኳኋን፡፡

## 12 - ግብረ-መልስ

የእምጳርጽር የግል ጠባቂ እስከመሰል ድረስ ዱላ እስይዘው ያስከትሉኝ ጀመር፡፡ እረበከንቱ ውስጥ ያሉትን ጠጅ ቤቶች በሙሉ አንድ በአንድ እያልን እናስሳለን፡፡





- ጠብ እርግፍ ጠጅ ቤት አንድ - አንድ
- እምባገሮ ጠጅ ቤት አንድ - አንድ
- ይታጠቁ ጠጅ ቤት አንድ - አንድ
- እርማጌዶን ጠጅ ቤት አንድ - አንድ
- ጠብ ያሌ ጠጅ ቤት አንድ - አንድ
- ሰንጌ ጠጅ ቤት አንድ - አንድ

በመጠጣት ሳይሆን በመዞር ይዞርብኛል፡፡ በየገባንበት ጠጅ ቤት እምጳርጽር ጠብ ለመለኮስ ያጀበጅባሉ፡፡ ማንም ደፍሮ እሳቸው ያስያዙትን ጠብ የሚገፋበት የለም፡፡ በዚህ አኩራኸኝ ይሉኛል ብዬ ሳስብ፦

‹‹ንቀት ነው›› አሉ፡፡

‹‹እንዴት?››

‹‹መከበር፣ መፈራት ሌላ ነዋ፡፡ ስትከበር፣ ስትፈራ የመታኸው ነው ዝም የሚልህ፡፡ የተናገርከው ዝም ካለህ ንቀት ነው፡፡››

‹‹እንዴት አረጋገጡ?››

‹‹ይኸውልህ እዛ ማዶ ያለው የቀይ ዳማ ፈንክቼ ክሼዋለሁ፣ ቢፈራኝ ኖሮ ይካስ ነበር? እዚህ በኛ መደዳ ጠይሙ በግ ነጋዴ ነው፡፡ በግ ገፍፎልኝ ሒሳብ ተቀብሎኛል፡፡ ይሄ ሳያንስ ደግሞ ቢፈራኝ ቆዳውን ምናምኒት ሳይጨምር በአገር ዋጋ ገዝቶኛል፡፡ ቢፈራኝ ኖሮ በግ ገፎልኝ ያስከፍለኛል? ቆዳ ባገር ዋጋ ይገዛኛል? እንደተራው ሰው ከተዳደርኩ ምኑን ሁከተኛ ሆንኩ? ምኑን ተፈራሁ? አሁን፣ እድሜ ላንተ ነገሩን ሁሉ አስተካክለዋለሁ፡፡››

ግራ ተጋባሁ፡፡ ‹‹እንዴ ደብድቦ መካስ፣ በአገር ዋጋ መሸጥ መደፈር ነው?››

‹‹አይ አንተ ከንቱ፤ መቼ ይሆን ነገር የሚገባህ? ‹ለአንበሳ እያበድሩም፣ ካበደሩም አይጠይቁም› ሲባል አልሰማህም? ምኑን ያሮጌ ልጅ ሆንክ ይሄን ካላወቅህ?››

በአባቴ በኩል የሚያጠቁኝ ብዙ ቦታ እንዳያዳርሰን እየሰጋሁ ነው፡፡ ስጋቴን ግን አልነገርኳቸውም እንጂ፡፡

* * *

በቀጣዩ ቀን ጠዋት እምጰርጵር ሰው ላኩብኝ፡፡

‹‹ሰው ላይ ያለኝን ዕዳ ሁሉ ስለምሰበስብ በስሌት እንድትረዳኝ አሁኑኑ ና›› መልእክቱ ውስጥ ግራ ያጋባኝ ‹‹ዱላዬን እንዳትረሳ›› የሚለው መደምደሚያ ነበር፡፡

‹‹በዱላ ሂሳብ ይሰላል?›› ለማንኛውም ዱላዬን እንደያዝኩ ደረስኩ፡፡

እምጰርጵር እንደሰባኪ ጋቢያቸውን አደግድገው ዱላ ይዘው ቆመዋል፡፡ እንደምዕመን እጃቸውን ጥንን ያጣመሩ ሁለት ሰዎች ፊት ለፊታቸው አሉ፡፡ ሰዎቹን አጠኳቸው ማታ ያሳዩኝ በግ ነጋዴና ተደብድቦ የተካሰው ነበሩ፡፡

እምጰርጵር የእኔን መግባት እንዳረጋገጡ ዱላቸውን ግድግዳ አስደግፈው ስብከታቸውን ጀመሩ፡-

‹‹ዕዳ ጥላ ነው፤ አይለቅም ይከተላል፡፡ ጠጅ ቤት ሄዱ፣ ሰማይ ቤት ገቡ አይለቅም፡፡ ይከተላል፡፡ ዛሬ ዕዳችሁን ስትከፍሉኝ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለእናንተም እረፍት ነው፡፡ እና…››

በግ ነጋዴው አቋረጣቸው ‹‹የምን ዕዳ ነው የሚያወሩት? እኔ በበኩሌ ከእርስዎ ጋር በገንዘብ ተዋውዬ አላውቅም፡፡››

‹‹ተው'ጂ›› አሉ እምጰርጵር ‹‹ምነው ሃች እምና ለዘመን መለወጫ የበግ ቆዳ አልሸጥኩልህም?››

‹‹ሸጠውልኛል››

‹‹አንተ ብትረሳ እኔ አልረሳም፡፡ ቆዳውን የገዛኸኝ 12 ብር ነበር፡፡ ወዲያው ብዙም ሳልርቅ ሌሎች ቆዳ ነጋዴዎች 14 ብር ሲሉ ጆሮዬ ጥልቅ አለ፡፡›› እምጰርጵር ወደኔ ዞረው እንዳሰላላቸው በምልክት ነገሩኝ፡-

‹‹ሁለት ብር አትልም፡፡ ብዙም ሳይቆይ ለመስቀል በዓል ቆዳ ሃያ ብር ገባ፡ ስምንት ብር አትልም፡፡ ብዙ ሳልቆይ ለጥምቀት ለፋሲካ ጭራሽ ናረና 32 ብር ገባ፤ ሃያ ብር አትልም፡፡ እሁን በቅርቡ ባለፈው ዘመን መለወጫ 38 ብር ሆነ 26 ብር አትልም?››





በግ ነጋዴው ነገሩ ሁሉ ተዘናብሎበት ፈገግ ቀረ፡፡ እምጰርጵር ወደኔ ዞረው ‹‹ዕዳውን አስላና ንገረው!›› አሉኝ፡፡ ‹‹ወለድ አልበላበትም፡፡ የተጭበረበርኩትን ብቻ በተሰላው መሠረት በረድፍ በረድፉ ቁጭ!››

‹‹ለእኔ ደግሞ ምን ሸጡልኝ?›› ሲል የተካሰው ጠየቀ፡፡

‹‹አንተስ ምንም አልሸጥኩልህ፡፡ ብቻ ትዝ ይልህ እንደሆን ላንተስ ፊንክቼ ካሣ በልተኸኝ ነበር፡፡ ሽማግሌዎች 50 ብር እምና ፊንክቼ ካሣ ብለው ብር አልካስም ብለህ ትርፍ 50 ብር ዕዳ ይበቃሃል ሲሉህ ያለ ሙቶ ብር አልካስም ብለህ ትርፍ 50 ብር ዕዳ አስቀመጥከልኝ፡፡ ይሁን ብዬ ስኖር በዚያ ሰሞን እዚህ ጎረቤቶቻችን ተፈናክተው 25 ብር ሲካካሱ ሳይ ጥቃቱ ገነፈለ፡፡ ስለዚህ ተገቢውን ዋጋ ወስደህ 75 ብር እንድትመልስ፤ ካልሆነም በብሩ ፋንታ በ25 ብር ሒሳብ ሦስት ቦታ እንድፈነክትህና እዳህን እንድታወራርድ ነው ያስጠራሁህ፡፡›› ዱላቸውን ግድግዳ ከተደገፈበት አንስተው ለፀብ አመቻችተው ያዙ፡፡

መካከል ለመግባት ቃጣሁ፡፡ እምጰርጵር በአይን ጥቅሻ ተቆጡኝ፡፡ በግ ነጋዴው እንበላቸው ያሉ መስሎት እየተርበተበተ፡-

‹‹የእኔን አስላልኝ - እዳዬን ከፍዬ ልሂድ›› አለኝ፡፡

ሁለተኛው ግን እፍጥጦ ሦስቴ ከመፈንከትና 75 ብር ከመክፈል የትኛው እንደሚሻል የሚያሰላ መሰለ፡፡ እሳዘነኝ፡፡ የመጣ ይምጣ በሚል ጣልቃ ገባሁ፡፡ እገባቤ ላይ ነገር ገደፍኩ ‹‹እምጰርጵር›› አልኩ፡፡

‹‹እምበርብር በል - ከንቱ!›› አሉኝ

‹‹የእርስዎ ዕዳ አመዳደብ ከህግ ውጪ ነው››

‹‹ዝምበል - አብድ! ገና ያንተም አለ፡፡ ልጄን ስታገባ ጥሎሽ ደንብ ነበር፡፡ አምስት ግራም ወርቅ፣ ሁለት ጫማ፣ ልብስ፣ ጃንጥላ፣ ሽቶ፣ እምባርና ድሪ ሲሰላ የትናየት፡፡ ይሄ ሁሉ ተሰልቶ ለእኔ ባባቷ ጋቢ ሲጨመርበት መቶ ጊዜ ብፈንክትህ ከእዳህ አትወጣም፡፡ ስለዚህ ፈንክት ስልህ መፈንከት ብቻ!!›› ሦስታችንም የእምጰርጵር ምርኮ ሆንን፡፡



@BOOKALEM

## 13 - የከሸፈው ተልዕኮ

በዚያው ሰሞን አመሻሽ ላይ ከሥራ ስመለስ እሪበከንቱ ተተራምሶ ደረስኩ፡፡ ግማሹ ወደላይ ግማሹ ወደታች ይሮጣል፡፡ ‹‹ጉድ፣ ጉድ፣ ጉድ›› ይላል፡፡

ከተማው ቢቃጠል እሪ በከንቱዎች እንደ ቁሳር እሮ ከሚቀ ጋራ ይሞቁታል እንጂ ይደነግጣሉ የሚል ሀሳብ የለኝም፡፡ ከከተማ መቃጠል በላይ ምን ደረሰ?

የጠብ እርግፍ ጠጅ ቤት ጠጪዎች ብርሌያቸውን ይዘው በር ላይ ተኮልኩለዋል፡፡ ጠጅ ቀጂው ማንቆርቆሪያውን እንጠልጥሎ ያስግጋል፡፡ በጅምላ ጠየኩ፡፡

‹‹ምን መጣ?››

ሁሉም ዝም ሲሉ አንድ ንዴት ቅልቅል ድምፅ ምላሽ ሰጠኝ፡፡

‹‹አምጸርጵር የእጃቸውን ሊያገኙ ነበር››

ሰውየውን እየሁት በአምጸርጵር ፊንክተው የካሱት ነበር፡፡ ዕዳውን መክፈሉ ያስከተለው ምን መአት ደረሰ?

‹‹የመጣባቸው ልጅ የልጅ ልጃቸውን በገመድ ሊያንጠለጥላት ሞክሮ ከብደቷን በምን ይቻለው? በልብ ብቻ አይሆን፡፡ ያሰበውን ሳይከውን ተደረሰበት አሉ፡፡ የእሳቸው ግፍ እንኳን ለሥጋ ዘመዶቻቸው ለጋብቻውም ይተርፋል፡፡››

የነገር መድፊያውን እንዳልሰማሁ አለፍኩት፡፡ ተስፋ እንዳጣ ረሀብተኛ እውሬ ተንደርድሮ ሊመሰግብኝ እንዳቆበቆበ ታውቆኛል፡፡

አምጸርጵር ቤት ሲደርስ ጋቢያቸውን እንደለበሱ ነጭ ድመት መስለው በሰዎች ተከበዋል፡፡

‹‹ከእንግዲህ ቁርጡ ደረሰ፣ እሱን ከሰሶ ምንም አይፈይድም፡፡ እንጠለጥለዋለሁ፡፡ ከዚያ እባቴን በገመድ እሸመቅቀዋለሁ፡፡››

የአምጸርጵር ቶክራ ውሃ አላነሳ አለኝ፡፡ በተለይ መጣባቸውን ለማንጠልጠል ቢሞክሩ እንደመጣባቸው ልጅ





ሳይሳካላቸው እንደሚያዙ እሙን ነው፡፡ ገመዱን እየጐተቱ ቀርቶ እየተንጠለጠሉም መጣባቸውን አይሸመቅቁትም፡፡ ይሄንን እያወቁም ጐረቤቶች ይለምኗቸዋል፡፡

ሺ-ትርገጥ ከጓዳ ወጣች፡፡ ትንፋረቃለች ብዬ ገምቼ ነበር፡፡ ቆምጨጭ እንዳለች እባቷን ተቆጣች፡-

‹‹ሙያ በልብ ነው፣ እስቲ ዝም በሉ››

ነገሩ ያለው ሺ-ትርገጥ ጋ ነው፡፡ ከፈለገች የመጣባቸውን ልጅ እንደ ሳንቲም በመሀረብ ቋጥራ ጡቶቿ ውስጥ ልትከትተው ትችላለች፡፡ ከዚያ በኋላ እንደፍርዷ መላላትና መጥበቅ የእስር ጊዜው ይወሰናል፡፡ እነዚያ የጡቶቿ ሐሩር ውስጥ እንድ ቀንም በህይወት መቆየት አዳጋች ነው፡፡

‹‹የትኛዋን ነው የመጣባቸው ልጅ...›› ስል ሺ-ትርገጥ በጥፊ የመደርገም ያህል እስደንጋጭ እይታ ለጠፈችብኝ፡፡ እኔም በመሀረብ ቋጥራ ጡቷ ውስጥ ልትከተኝ?

‹‹ትንሿን ነዋ›› አሉ አምጸርጵር ‹‹መቼም ለመጣባቸው ልጅ ክተት አላውጅም፡፡ አንተ ሌላ ሥራ አለህ፣ ለመጣባቸው ልጅ ከአባቱ እኔ እበቃለሁ፡፡››

‹‹እሺይ›› አልኩ፡፡ እኔ ለመጣባቸው ልጅ ጦርነት ተጠባባቂ ጦር መሆኔ እረፍት ሰጠኝ፡፡

## 14 - ሥረ መሠረት

የመጣባቸው ልጅ ከእሪበከንቱ ከጠፋ ሁለት ቀን ሆኖታል፡፡ አምጸርጵር ዱላቸውን ይዘው በእላቻ ሰዓት መጣባቸው ቤት ዘው ቢሉም አላገኙትም፡፡ አምጸርጵር ገና አሁን እኩያቸውን አገኙ ስል አሰብኩ፡፡

ተጠባባቂ ጦርነቱን ባለበት ለማቆየት እና እጥቂ ሆኜ እንዳልመደብ እረቂ ድርጉ ይገፍ እሂዳለሁ፡፡ እሳቸው ወደ እናዳጅ ዕለታዊ ጉዳይ ሲጐተቱ እኔ ወደ ታሪክ እሰባቸዋለሁ፡፡

‹‹እዚህ ነው የተወለዱት?››



@BOOKALEM

‹‹ዘር ማንዘሬ እንጂ፡፡ አባቴ፡ አያቴ፡ ቅድም አያቴ፡ ሁሉም እዚሁ ነው፡፡›› አረቄአቸውን ተጐንጭተው ፊታቸውን አኮፉተሩ፡፡

‹‹ቅም ይሁኑ ቅምቅም አያቴ ከተጉለት ነው የመጡት፡ አመጣጣቸው እዚችው ቦታ ላይ የነበረ አንድ የአካባቢው ሌባ ስህተት በመፈፀሙ ነበር፡፡››

‹‹እንዴት? ምን ፈፀመ?››

‹‹ክልብ-ክልብ አትበል›› ገሰጡኝ፡ አረቄዋን ደገሙና ቀጠሉ፡፡

‹‹ያኔ የጦጋበኛ ዘበን ነበር፡፡ አንዱ ድንገት ተነስቶ ‹ሌባ ነኝ› ይላል፡፡ ‹እጤ› በሉኝ፡፡ ‹እጤ ያላለኝን ጭንቅላቱን እቆርጣለሁ› ይላል፡፡ የፈራው ከበዛ እሱ እስኪደክምና ሌላ ጦጋበኛ እስቲነሣ አስገባሪ ነው፡፡

‹‹በቅምቅም አያቴ ዘበን እዚህ ነግሶ እራሱን አጤ ያሰኘ ጦጋበኛ ‹ጦር እምጪ› እያለ በየቀኑ መሬትን እርባ እርባ ጅራፍ ያስገርፍ ጀመር አሉ፡፡

‹‹ይሄንን ጉዳይ ቅምቅም አያቴ ሰሙ፡፡ ‹እንዴህ ያለ ጦጋበኛ ጦር እምጪ እያለ መሬትን በግርፊያ አስጨንቆ ያለት› ሲባል እንቀጠቀጣቸው፡፡ ‹እረ ይሄ ፈሳም፡ ጦር ተተፈለገ ታጥቶ ነው መሬትን መግረፉ? መሬት ባበላች ባጠጣች ምን አጥፍታ ነው? ንሱ በቅሎዬን ጫኑ› አሉ ይባላል፡፡ ዕለቱን ተተጉለት እዚህ፡፡

‹‹ያለሽሙል ምንም አልያዙም ነበር፡፡ ጀምበር ተጠለቀች በላይ ነገር ደግ አይደለም ብለው አደሩ፡፡ ማለዳ እዚህ ቢመጡ ገበያ ሙሉ ሰው ከብቦ ምድር በጅራፍ ፍዳዋን ትበላለች፡፡ መካከል ገቡ፡፡

‹‹እንኳ መሬት ሰጪዋ፡ ወጪትስ ማብሰያዋ ክብር አይደለችም ወይ?›› አሉ፡፡

አጤው መከዳው ላይ እንደተኮፈሰ ‹‹ምን ይላል ይሄ፡ እኛስ ምን አልን? ጦር ስጪን ተማለት በላይ? ቀጥል መግረፍህን››

‹‹እናትና መሬት የዘሩባቸውን ሰጪ ናቸው፡፡››





‹‹ጦር ዘርተን አልበቅል አለን›› አይልም አጤው፡፡ አድርባይ ሁሉ እንዲ አሙካኘ፡፡

‹‹የዘራችሁትማ ይኸው አፍርቶ አታዩትም? ሳታጭዱት ሲያጭዳችሁ ነው›› በሽሙል ገባባቸው፡፡ ገበያ ሙሉ ሰው እንደዝንጀሮ ብትን አይልም፡፡ አጤው ከመከዳ ወረዱ፡፡ ጋሻ ጃግሬዎቹ የያዙትን ጦር እየሰበቁ ወረወሩ፡፡ ቅምቅም አያቴ ላመል ሸተት ብሎ ጦሩን ካሳለፈ በኋላ ቀልጥፎ ያሰፈው ጦር እየተጥመዘመዘ ሳለ እጀታው ላይ በሽሙሉ ይመታዋል፡፡ ጦሩ የተወረወረበትን አቅጣጫ ትቶ በመዞር ወርዋሪዎቹን እያሳደደ መውጋት፡፡ ‹‹ጉድ›› ተባለ፡፡ ቀስት ቢወንጭፉ እንደዚያው ‹‹መሬት የወለደችው መቀጣጫ መጣ›› ተባለ፡፡

‹‹ጦጋበኛው አጤ ቢፈራም ምንተፍረቱን ሽሙል ገጥሞ ሁለቱ ሲዠብዱት እየበረረ ቂልቂል ወደ እሪበከንቱ ወንዝ ተፈተለከ፡፡ ቅምቅም አያቴ ሲከተሉ፡ አጤው ሲበር እለቱን ጅማ ገብተው አደሩ፡፡ እንግዲህ ከጅማ መልስ ነው ቅምቅም አያቴ እዚህ ገብተው የቀሩት፡፡››

እምጵርጵር በወሬአቸውና በአረቄው ሰውነታቸው ተዝናንቶ የመጣባቸውን ልጅ ድርጊት ለጊዜው የዘነጉት መሰሉ፡፡

‹‹እንግዲህ አያ ትድመ አያቶቼ ደማቸውን አፍስሰው፡ አጥንታቸውን ከስክሰው ያቆዩትን እርስት በእኔ ጊዜ አሳወረስኩ፡፡ ግዴለም እድሜ ላንተ እሱንም አስመልሳለሁ፡፡››

ሌላ ቀጮትና ሌላ ቀልዕኮ፡፡ ያሁኑ ይባስ አሉ፡፡ ብዬ ብዬ የእምጵርጵርን ርስት ለማስመለስ መንግሥትን ጦርንት ለገጥም ነው?

‹‹እንዴት?›› አልኳቸው

‹‹ያሮጌ ልጅ ሆነህ ይሄ ጠፋህ? ‹ርስት በሺ እመት፡ ይመለሳል ለባለቤቱ› ሲባል አልሰማህ ሆኖ ነው?››

በእባቱ በኩል የሚያጠቁኝ ብዙ ቦታ ላያዳርሰን ይቀራል ብላችሁ? አልነገርኳቸውምንጂ

## 15 - ዳግማዊ ወረሳ

ክብት ይመስል የፊት የፊቴን ስግጥ ግጨው ያለፍኩትን ምድር ለእፍታም ዞር ብዬ አለማየቴ ገረመኝ፡፡ ይሄን ያሰብኩት ጀቢራ ትምህርት ቤት ድረስ መጥተው ሲያስጠሩኝ ነው፡፡ ዳይሬክተሩ እራሱ እየተሽቆጠቆጠ ትፈለጋለህ አለኝ፡፡ ከሦስት ሳምንት በፊት ግን እየጠራ ሲጋራ ግዛ ብሎ ይልከኝ ነበር፡፡ ሳጂን እስከበረኝ፡፡

«መጣሁ በላቸው» ብዬ መልሼ ላኩት፡፡ ሆን ብዬ ነው፡፡ አለበለዚያ ምኑን ሁከተኛ ሆንኩት? ነኝ እንዴ?

ዳይሬክተሩ ሦስት ጊዜ «እሺ» አለ፡፡ «እሺ-እሺ-እሺ» አንድ አይበቃኝም ኖሯል? የመታዘዙን ፍፅምና በሦስት እሺ ማረጋገጡ የፍርሃቱን መጠን የሚገልፅ ነበር፡፡ ለመሆኑ ማነው የፈለገኝ? ወጣሁ፡፡

ኩይሳ? በረገግኩ፡ ሳላስብበት ከሆነ አሁንም ኩይሳን እፈራዋለሁ፡፡ መንበርከኩን፡ ማልቀሱን፡ መለመኑን.... ሳስታውስ ነው መበርገጌ የሚታገሥልኝ፡፡

ሎፍን? ተፀፀትኩ፡ እሷን ማሰብ ልቤን ይከብደዋል፡፡ ስትመጣ ሆን ብዬ መንገድ እንዳገጣጠመኝ አብዳ በእዝነ ህሊናዬ እሸሽጋታለሁ፡፡

የትምህርት ቤቱ በር ላይ የቆሙት ፈላጊዬ ጀቢራ ነበሩ፡፡ ወተት የመሰለ ጋቢ አጣፍተዋል፡፡ አዛውንትነታቸው እርትን፡ ይቅርን፡ ታጋሽነትን፡ የሰው አለመፈለግን... ይሰብካል፡፡

«ምነው ልጄ ዝም ብለህ ተውከን?» አሉኝ፡፡

ምላሽ አጣሁ፡፡ «ክብት ስለሆንኩ የፊት የፊቴን ስግጥ» ልበላቸው?

«የእኛ ይቅር በፓርቲህ ላይ እንዴት አስችሎህ ጠፋህ? በወ.ህ.ዴ.ድ ይጨክናል?»

ምን ማለታቸው ነው? ወደ ጉያቸው ሥር እጃቸውን ሰድደው የታሰረ የጥሪ ካርድ አወጡ፡፡ መርጠው አንዱን ዘረጉልኝ፡፡ ተቀበልኩ፡፡ «የወረሳ ህዝቦች የባህል እና የታሪክ





ሲምፖዚየም» የሚል ርዕስ አለው፡፡ በጥያቄ መልክ እየኳቸው እራሳቸውን በእዎንታ ነቀነቁልኝ፡፡

«ባለፈው ስርዓት ባህላችንን እንዳናንፀባርቅ ተደርገን ማንነታችን ተቀብሮ በጭቆና እንኖር ነበር፡፡»

ጀቢራ የጥንቱን አልመሰሉ አሉኝ፡፡

«አሁን ህገ-መንግስታችን ባጎናጠፈን መብት ተጠቅመን ባህላችንን ማዳበር፡ ማስፋፋት፡ ማስተዋወቅ ችለናል፡፡ ማንነታችንን ሳንፈራ፡ ሳንሸማቀቅ በዘፈን፡ በፅሁፍ፡ በፎቶግራፍ እናስተዋውቃለን፡፡ ይሄም የባህል እና የታሪክ ሲምፖዚየም የዚህ ህገ-መንግስታዊ መብታችን አንዱ አካል ነው፡፡»

ያ ሁሉ ለዛቸውን ምን ዋጠውና እንዲህ ገረሩ? ደረቁ? ፖለቲካ ለዛ ማድረቂያ የባህርይ ስጦ ይሆን?

«አንተም ምዝጉብ አባል በመሆንህ ቀደም ብለህ በማደራጀት ብታግዘን ድርጅታዊ ትስስርህ ይጠናከራል፡፡»

በፖለቲካ እየተራቀቁብኝ መሰለኝ፡፡ በመጨረሻም «ከወሀ ዴድ ጋር መጪው ኑሮ ፍሰህ ነው!» ሲሉ መፈክር አሰሙኝ፡፡ የግዴን «ነው!» አልኩ፡፡

«እናሸንፋለን!»

«ማንን?» ሳላስበው

«እሚሸንፈውን፡ ለማንኛውም መፈክር አይመረመርም፡፡ ዝም ብሎ እንጠራጠርም ማለት ነው፡፡»

* * *

እምድርድር ስለ ሲምፖዚየሙ ሲሰሙ ከእረቂው እኩል ነገሩ ልባቸውን ላፋቸው «ጉድ እኮ ነው፡ በየዘመድህ ቢሉት እከንባሉ ጋዋ ገባ አሉ፡፡ ወረሳዎች ተየት ያመጡት ባህልና ታሪክ?»

እንጃ እንደማለት ትከሻዬን ሰበቅሁት

«ጭልፊት ባህል አለው? የጥንብ እንሳ ታሪክ ያው የሰው ግዳይ ላይ ሰፍሮ መዘንጠሉ ነው፡፡ ነግቶ ልናይ! ዓሣ ሲጐረጉሩ ዘንዶ እንዳያወጡ»



@BOOKALEM

«እንዴት?»

«እኔ እማውቀው ብዙ ነገር አለ፡፡ አይ ታሪኩንቱ! እንዲህም አድርጎ ባህል የለም፡፡» እንደመቋነጥነጥ ብለው ቀጠሉ፡፡

«በጠላት ጊዜ ከጥሊያን ጋር ተመሣጥረው የአክሱምን ሐውልት ተከፋፍለው ነበር፡፡ ጥሊያን አቅም አለውና አንዱን ነቅሎ ወደሮም ወሰደው፡፡ ወረሳዎች ግን ሐውልቱን እንደበሬ በገመድ አስረው ሊያመጡ ሲጐትቱ ወድቆ ተሰበረ፡፡ ይሄንን ይሆናል ታሪክ የሚሉት፡፡»

እረቄውን ተጐንጩና ፊታቸውን አከፋተሩ፡፡

«እ-ሺ» አልኩ እኔም፡-

«ምን እሺ አለው?» ብለው አፈጠጡብኝና «በዚያው ዘበን ጥሊያን የእጤ ምኒልክን ሐውልት ተጐርጊስ ቢያነሣው ወረሳዎች ለኛ ይገባናል በምኒልክ ተበድለናል አሉ።

«እንዴት? ቢባሉስ ቀድሞውኑ ሐውልቱን ያሰራነው እኛ ነን፡፡ ወረሳ ውስጥ ለማስተከል ነበር፡፡ አባ-ሞጭልፍ የተሰኘው የወረሳ ሰው ለእኛ ያደረገውን ከውለታ በመቁጠር ነበር፡፡ እጤ ምኒልክ ሐውልቱን እንዲመርቁ ብንጠራቸው «ወግዱ አላማረባችሁም ሐውልቱን እጤ ምኒልክ በሉት፡፡ ጊዮርጊስ ፊት ለፊትም ይተከል አሉን አሉ፡፡»

«ጉድ! ጉድ! ጉ!»

«ጥሊያንም ሰው የሚያውቀው በአባ ሞጭልፍ ሳይሆን በአባ ዳኘው ነውና ሐውልቱ መቀበር አለበት ሲል ወሰነ፡፡

«እሺ ሐውልቱ በሥነ ሥርዓት ወረሳ ተወስዶ ይቀበር አሉ፡፡»

«ሥነ ሥርዓቱ ለአባ ዳኘው ስለሚመስል በሚስጥር ይቀበር አለ ሶላቶ፡፡ ይሄ ነው እንግዲህ የወረሳ ታሪክ፡፡»

«ታዲያ ታሪካቸው ያሳፍራል እንጂ ምኑን ያኮራል?» አልኩ ወገንተኝነትን ተገን አድርጌ ወሬአቸውን ለመኮምኮም፡፡





«የባለጌ ልጅ ቢቀመጥ ቂጡን ገልቦ ነው ይባል የለም? ያርጌ ልጅ ሆነህ ነገር ታጠፋለህ» በነገር ወጉኝ፡፡ ተሸማቅቄ ዝም አልኩ

«በአብዮቱም ጊዜ የእጤ ኃይለሥላሴን የይሁዳ ኮከብ ሐውልት ከቢያሳ የሰረቁት ወረሳዎች ናቸው፡፡ መንግሥት ከሌብነት ሳይሆን ከአብዮታዊ ተግባር ቆጥሮ ሸለማቸው፡፡»

«ጭራሽ?»

«እዎ ጓድ ላፊው የተባለ ነገር አዋቂ ነበራቸው፡፡ በዚህ መንግሥት ደግሞ ከፓርላማ ግቢ ውስጥ ሁለት የጥንት መድፍ ሮቀዋል፡፡»

«እዎ-እዎ ልጄ በፓርላማው ፊት ለፊት በር ውጭ የቆመ መድፍ ነበር»

«ይኸውልህ፡ የመንግሥት አጋር ነን በሚል ላይ ታች ሲሉ የሸማግር መንግሥቱ፡ አጋር ነን ካላችሁ አጋርነታችሁን መድፉን በመስረቅ አሳዩ አላቸው፡፡ ዕለቱን ሰረቁት፡፡»

## ፲፮ - የሚበቁ ሁለተኛ ገፅታ

እባቷ ‹በአባቴ› እሷ ደግሞ በሆዴ ያጠቁኝ ጀመር፡፡ በደበሎች የደሞዝ ሰሞን የሺ-ትርጉም በሆድ የማጥቃት እርምጃዋ ነፍስ የማያዋድቅ አመፅ ይቀሰቅስብኛል፡፡ እሷ እንደሆን ለሆዷ ግድ የላትም፡፡ በልታ ሳይሆን ፍርጃዋ ሆኖ ነው የወፈረችው፡፡ በተለይ እንደፈለገችው ሆኜ ያላደርኩ ቀን ምግብ ስጠይቃት መከላከያ የተረት ጋሻ ታነግባለች፡፡

«የሆድ ብዛት ሥም አያስጠራም» ትለኛለች፡፡

እኔም እንደአማርኛ መምህርነቴ መጠን የተረት ጋሻዋን በስቶ የሚያልፍ የተረት ሾተል እሰብቅባታለሁ፡፡

«ሆድን በጎመን ቢደልሉት፣ ጉልበት በዳገት ይለግማል» እላታለሁ፡፡

«እውቀህ ሞተሃል» መቼም ንቀቷ አይነሳ «ያንተ ሆድ በጀርባህ ቢሆን ገፍትሮ ገደል ይጨምርሃል»



@BOOKALEM

እኔም አልሸንፍ «ጆንያ የሚቆመው እህል ሲሞላ ነው»

«እንደ አዲስ መሬት እህል እህል ቢሉት ምን ይፈይዳል?»

«ልጅ ከጠረው ሆ የጠረው ሲባል አልሰማሽም መሰል»

የተረት ግጥሚያችን የሚደመደመው በእሷ ተሸናፊነት ነው፡፡ እያጉተመተመች ድስት ትጥዳለች፡፡

በእንዲህ ያለ ቀን የምትከተለው ሙያ አይነሳ፡፡ ውሃ ተጥዶና ሲፍለቀለቅ ሽሮውን፣ ሽንኩርቱን፣ ዘይቱን፣ ጨዉን አንዷ ጨምራ ሲድበከበክ የበቆሎ ገለፈት ሸፍና ትከድንና ክዳኑ ላይ ድንጋይ ትጭንበታለች፡፡

«የበቆሎ ገለፈቱ ደሞ ምንድነው?» እላታለሁ፡፡

«ጅሎ፣ ቶሎ እንዲበስልልህ ነዋ፡፡ አንተ እንደሆን የሆድህ ነገር ጊዜ አይሰጥህ፡፡ እንደሌሊቱ ቀንም ብትታገሥ ምናል ነበር?»

ውጥ አሰራሩ የዚያ መዘዘኛ ሌሊት ትዕግሥቱ ቅጣት መሆኑ ነው፡፡

«ሲበስል እውጥተህ ብላ» ብላኝ ቡና ለመጠጣት ወደ ጐረቤት ትሄዳለች፡፡

ከቆይታ በኋላ ስከፍተው ለድስቱ ባዕድ የሆነ ነገር በብዙ አይኖች ያፈጥብኛል፡፡ ለመብላት ባልደፍረውም፡፡ ባለቤቱ ስትመጣ ማቷን ከክንዷ ጀምሮ እየላሰች ታጣጥመዋለች፡፡ ለእንደዚህ አይነትም ምግብ ፍላጐቷ ሲቀሰቀስ ለጉድ ነው፡፡

ዳግት እንደወጣች ሁሉ ቁና ሙሉ ተንፍሳ «ስለማፈጠኝ ነው መሰል ብዙ በላሁ» ትላለች፡፡

## 17 - የወረሳ መዘዝ

ቀዳሚ ሰንበትን አሊጋ ላይ ማረፋፈድ ልምዴ ነው፡፡ ነገር ግን በጠዋት እምጳርጵር መጥተው በዱላቸው በር ቆረቆሩ፡፡ ሺ-ትርጎዋ ተነስታ ከፈተች፡፡

«የመዘዘኛ ሰው ፈስ - አይን ያፌስ አሉ፡፡ ጉድ እኮ ነው»





«ምነው?» ሺ-ትርጎዋ፡፡ እኔ አድፍጫለሁ፡፡

«ወረላዎች ጉድ አፈሉ»

«እንዴት? ጦርነት አነሱ?»

«እሱን ማን ያደርሳቸዋል፣ ይሄማ የወንድ ተግባር ነበር»

«ታዲያ?»

«የባህልና የታሪክ ሲምፖዚየም ብለው እረበከንቱዎችን አስሰብኝ እንጂ፡፡ እንግዲህ ሒሳብ ይመርመር፣ ብር ይመንዘር ለሱ ነው፡፡ ወይኔ እምበርብር እንዲህ ያለድፍረት ከሚደርስብኝ ምቼ በቀረሁ ነበር፡፡ በፊት ቢሆን ‹ለእንበላ አያበድሩም፣ ከዘደሩም አይጠይቁም› ነበር፡፡ አሁን ጉልበቱ ደከመ፣ አይኔ ላመ ብለው... ግዴለም ቀስቅሺው ባልሽን ዱላ ይያዝና ባርቴው ሰብሰባ እንሂዳለን፡፡»

ደነገጥኩ፡፡ ከአንድ ሥፈር ጦር ጋር እኔና እምጳርጵር ስንገጥም ታየኝ፡፡

«ተንስ-ተንስ-ተንስ»

ታጠቅ! ዝመትን እኔ ጨመርኩበት፡፡ የግዴን ተነሣሁ፣ የግዴን ታጠቅሁ፣ የግዴን ዘመትኩ፡፡ ሙትና ቀስለኛ ሆነን ወደምንመለስበት ጦር ሜዳ መሄዳችን እርግጥ ነው፡፡

«እረበከንቱ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት» የሚል ለሁፍ የተለጠፈበት አዳራሽ ውስጥ ገባን፡፡ የአዳራሹን ዙሪያ ገባ ስመለከት ሰውነቱን ሁሉ ቀፈፈኝ፡፡ ጦር፣ ጋሻ፣ ገጀራ፣ ጠበንጃ፣ ጐራዴ... ተሰቅሎበታል፡፡ እንግዲህ በዱላ ያጣደፍነው ጐራዴውን እንስቶ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት... ዘገነነኝ፡፡

ከእረበከንቱ ሰው የቀረው የመጣባቸው ልጅ ብቻ ነው፡፡ እንደልቡ ከሆነ የእህዴድ ምዝጉብ አባል ሳይሆን አይቀርም፡፡ የት ገብቶ መጣባቸው እንኳን ጋቢ ተከናንቦ መካከል ተጐልቷል፡፡ ይሆን? እዚያ ወዲያ ደግሞ የእምጳርጵር ወዳጅ ሺ-ትርጎዋን መስላ ተቀልላለች፡፡ ጠቡ ሲጀመር ከማን ወገን ትሰለፍ ይሆን? ይሄ የሚወሰነው እምጳርጵር ባስመዘገቡት የሌት ውጤት መሰረት ነው።



@BOOKALEM

ፊት ለፊት፡ ፊታችንን ወደ እረበከንቱዎች ፊት መልሰን ቁጭ አልን፡፡ በግ ነጋዴው፡ ተበዳሪው፡ ጠጅ ቀጂ፡ ሳጂን... ሁሉም አለ፡፡ የእኔ ከእምጰርጵር ጋር መቀመጥ አብዛኛውን ግር አሰኝቷል፡፡ ያም ሆን ይህ ስብሰባው ቀጠለ፡፡ ንግግር ከሚያደርግና ጥያቄ ከሚጠይቀው የሚፎክረው ይበዛል፡፡ አብዲሳ እጋ የፉከራ ትርኢት ሳሳይ ብሎ ሶልዳቶዎቹን ጉድ እንደሰራቸው እኔና እምጰርጵር ጉድ እንዳንሆን ስጋት ገባኝ፡፡

እምጰርጵር ቤት እንዲ ያየሁት የአበህዲድ ፀሐፊ ዘግይቶ ገባ፡፡ ዝናር ታጥቆ ነበር፡፡ እልልታው ቀለጠ፡፡

እምጰርጵር ወደጆሮዬ ተለግተው ‹‹ፊሳምኮ ነው፡፡ አሁን በሽመል ብገባበት እንደዝንጀሮ አውራ መንጋውን ትቶ ይፈረጥጣል›› አሉኝ፡፡

ቀናቸው ደርሶ፡ ቀናቸው እንዳያልፍ ፀብ ፀብ የሚላቸው መሰለኝ፡፡ እኔም ቀኔ ባይደርስም በእጃቢነት አብሬአቸው መሞቴ ነው፡፡ ወይኔ! ፀሐፊው ዝናሩን እያስተካከለ አጠገባችን ተቀመጠ፡፡ ፉከራው ቀለጠ፡፡

‹‹ይበቃል! ይበቃል›› አለ ፀሐፊው ‹‹አሁን ደሞ ወደ ቁም ነገሩ እንግባ፡፡ ገንዘብ ያዥው ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ እምጰርጵርን ወደ መድረክ፡፡››

‹‹ልቤ ስንጥቅ አለች፡፡ እምጰርጵር ሲባሉ የፀሐፊውን አናት ይተረክካሉ ብዬ ነበር፡፡ እሳቸው ግን ወደሌላ ጉዳይ አተኩሩ፡፡

‹‹የተንኮል ያልከው ነው'ጂ የኔ ራቦል መቅደም ነበረበት? ግዴለም እበቀልሃለሁ›› ብለው ዛቱብትና ቆሙ፡፡

ድፍን እረበከንቱ ለሒሳብ ሪፖርቱ ቀልቡን እንደሰጠ ያስታውቃል፡፡ ይሁን እንጂ እምጰርጵር ሒሳቡን ትተው ስለጥንቷ እረበከንቱ ማውራት ቀጠሉ፡፡

‹‹የጥንቷ እረበከንቱ ሁለመናዋ ጠብ ነበር፡፡ አይ ደጉ ጊዜ! እንኳን እንደአሁኑ ፎክራችሁ ቀርቶ ወደላይ ብታዩ 'አሳቀለኝ' የሚል ጠበኛ ይመጣላችሁ ነበር፡፡ ወደታች ብታዩ 'አፈር ግባ አለኝ' የሚለው ዱላውን አመቻችቶ ይመጣል፡፡ ወደጐን መልከት ብትሉ 'ከአገር ያብርህ አለኝ' ይልና ካቤቱታ በኋላ ትግል





ይጥማል፡፡ እረበከንቱ በደጉ ጊዜ እደናችሁ ማረፊያ ያጣ ነበር፡፡ አሁን እንዴህ በነፃ ፎክሮ ያለ ጠብ ወደቤት፡፡ ያሳዝናል›› አሉ፡፡

ፀሐፊው ብድግ ብሎ ‹‹እሺ ሪፖርቱን አዳምጠናል ጥያቄ ያለው›› አለ፡፡ ሁሉም እጁን አወጣ፡፡

‹‹እንደወረሳዎች የባህልና የታሪክ ሲምፖዚየም ለማሳየት ዕድሜያ ሂሳብ ይመርመር›› አሉ ግማሾቹ፡፡ ከእነዚህ ወገኖች ጋር እኔና እምጰርጵር ደም ልንታባ ቀጠሮ ያዝን፡፡

‹‹ደሄን እንደበድብዋለን›› ይላሉ እምጰርጵር

ግማሾቹ ደሞ ‹‹ሒሳብ ውስጥ ምን ከተተን? ወጪው እየተመዘገበ ሲምፖዚየሙን እንጀምር››

‹‹ደሄንን እንጋብዘዋለን፡፡››

ለግማሹ ጠጅ ለግማሹ ጠብ ልንደግስ ነው፡፡ ግራ ገባኝ፡፡ ግራ የገባኝ እኔ ብቻ አልነበርኩም፡፡ ፀሐፊውም ግራ ተጋብቷል፡፡ እኩል ለእኩል የተሰነጠቁት እረበከንቱዎች ለውሳኔ አልመቹ አሉ፡፡ ግራ መጋባቱን ለማስታገስ ከሁለቱም ወገኖች ሁለት ሁለት ሰው አስተያየት ይሰጥ አለ፡፡

እምጰርጵር ‹‹አይመርመር›› ያሉት አስተያየት ሲሰጡ በፈገግታ ተቀበሏቸው፡፡ ‹‹ይመርመር›› ያሉት ላይ ደግሞ ጉፈሉ፡፡

የመጀመሪያው አስተያየት ሰጪ በእምጰርጵር ተደብድቦ የተካሰው ነበር፡፡

‹‹እኔ በበኩሌ ይመርመር ነው የምለው፡፡ ምክንያቱም ለእሳቸውም ቢሆን ዕዳ ስለማይሆንባቸው...››

ድንገት እምጰርጵር አቋረጡት፡፡ ‹‹አፍህን በማር ሳብሰውና ዕዳ ብትል አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ ባለፈው ሳምንት ሰባ አምስት ብር ዕዳ አስቀጥሬህ ለሳምንት ልትከፍለኝ ካልሆነ ሞቴቱ ልፈንክትህ ፎርመህልኝ ነበር፡፡ ስትወጣ እንነጋገራለን፡፡ ለማንኛውም ቀጥል›› አሉት፡፡ ደነገጠ፡ ተርበተበተ፡፡

‹‹እና እንዳልኳችሁ ዕዳው እሳቸው ላይ ስለማይሆን አይመርመርብኝ ካሉ መቼስ ምን ይደረጋል፤ አይመርመር ነው የምለው›› ቁጭ አለ፡፡

ቀጣይዋ ሴት ተነሱ፡፡



@BOOKALEM

‹‹መቼስ ፓርቲያችን ሲቋቋም መብታችንን እንድናስጠ ብትና እራሳችንን እንድናስተዋውቅበት ነው፡፡ ስለዚህ ቤ ይመርመር ማለት ወንጀል አይደለም፡፡ ስለዚህ…››

እምጳርጵር አሁንም አቋረጡ፡-

‹‹እፍኝን በማር ላብሰውና ወንጀል ብትይ አንድ ነገ ታውሰኝ ነው፡፡ ልጅሽ ልጁን የማነት ወንጀል ፈፅሞ ሲሰወር እንኳ ልጅና ያሳደግሽው ውሻ እንኳ ሲሳውን ቢነክስ በሽምቅቆው እንደት ገቢ ህግ ደንግጓል፡፡ ስለዚህ የእምስት አመት ህፃን ሸምቀቀኝ… ለማንኛውም ስትወጪ እንነጋገራለን፡፡ አሁን ቀጥይ…››

ሴትየዋ ብርክ ያዛቸው፡፡ መቀጠል አቅቷቸው እንደቆሙ ቀሩ፤ አሳዘኑኝ፡፡ ወደ እምጳርጵር ጆሮ ተጠጋቼ፡-

‹‹ሲሳውን ነገር ሲላ ቀን ቢጠይቁ አይሻልም፡፡ የሒሳቡን ሪፖርት እየጠለፉ…›› ስላቸው፡፡

‹‹እፍህን በማር ላብሰውና እየጠለፉ ብትል አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ አንተም ብትሆን መንግሥት እያለ እንደሌለ በማስመሰል ልጁን ያለውዴታዋ ጠልፈህ ማግባትህን አትዘንጋ፡፡ ለማንኛውም ስንወጣ እናወራለን አሁን ቀጥል›› አሉኝ፡፡

እንደሴትዮዋ ባይሆንም ብርክ ያዘኝ፤ መቀጠሉም ተሳነኝ፡፡

## 18 - እስግንጣዩ

ሲምፖዚየሙ ከተጀመረ ወረሳ ደረስኩ፡፡ እማማ ጉዶ ሙሉ ያበሻ ልብስ ለብሰው ከቄስ ትምህርት ቤቱ መምሬ ጋር ያወራሉ፡፡ የልጃቸው ልጅ እንደ ተሳታፊ ታቅፎት እየሁ፡፡ ድቄሱ፣ ከይሳው፣ ልባሙ፣ ሽኩኩ፣ ፈላስፋው…ሁሉም ዘንጠዋል፡፡ ዋናው ኢጋፋሪ ጆቢራ ናቸው፡፡ ውተት የመሰለ ጋቢ ደርበው ዋራ የተቀባ ግድግዳ መስለዋል፡፡

እንግዶቹን ወደ ባህል እና ታሪክ ሲምፖዚየሙ አመራን፡፡ በትልቅ ዳስ ውስጥ የተለያዩ ቁሣቁሶች፣ ፎቶዎች፣ አልባሳቶች ይታያሉ፡፡





ልቤን መንፈሴ፣ ነፍሴ… ባዶ፣ ወና ሆኖ ተሰማኝ፡፡ ቅር ቅር የሚያሰኝ ነገር አለ፡፡ የማነው፣ የምሰማው፣ የማሸተው፣ የማቀምሰው፣ የምዳስሰው… አላጠግብ ብሎኛል፡፡ ለምን?

ጆቢራ የኤግዚቢሽን መግለጫ ጀምረዋል፡፡ ሰቃዎቹና ፎቶዎቹ ላይ በረጅም ዘንግ እየደነቀሉ ያብራራሉ፡፡

‹‹ይሄ›› አሉ ጆቢራ አንድ እፍኝ ሙሉ ድንጋይ ላይ ጠቁመው፡፡

‹‹ይሄ በወረሳዎች የድንጋይ ዘመን የነበረ መሣሪያ ነው፡፡ ብረት ባልተሰለጠነው ጊዜ ወረሳዎች ይሄንን ድንጋይ በመጠቀም እንስሳ ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡ ማለቴ የሚዘረፈውን በዚህ ድንጋይ ከኋላ በመምታት (የራሱ አመታት እስው) ኪሱን ይበረብሩ ነበር፡፡ ፎ…››

አንድ እህል ውሃ የማያሰኝ ዱላ ጠቆሙ

‹‹ከድንጋይ ዘመን ጥቂት ተሻሽሎ ብቅ ያለው የዱላ ዘመን ነበር…››

እኔ ከውስጤ የሚጉተጉተኝ ስሜት የጆቢራን እንዳላዳምጥ እየተከላከለኝ ይገኛል፡፡ እፍ እንዳልፈታ ልጅ ውስጤ የሚፈልገውን ከመናገር ይልቅ ይንቀጫቀጭብኛል፡፡ ምን?

‹‹ይሄ አባ ላፊው ከአጤ ቴዎድሮስ ያጭበረበረው የሹመት ልብስ ነው፡፡ አብረውት ያሉት በየደረጃው ላሉ የዘመኑ ወረሳዎች የተጭበረበሩ የሹመት ቀሚሶች ናቸው…›› የዘረፋን በረቀቀ ?

ምን? ውስጤን እጠይቃለሁ እንጂ ያለኝ ይመስለኛል፡፡

‹‹ይሄ የአባ መንትፍ ልጅ አባ ንጠቀው ጠላቱን ያሳበደበት እር መስረቂያው ነው…››

ከውስጤ ጋር ድብብቆሽ ያዝኩ እንጂ የሚጠይቀኝን አውቀዋለሁ፡፡ ጭፍን… ጭፍን… ጭፍን የለችም፡፡ የት ሄደች?

‹‹ይሄ ዘመናዊውን የወረሳ ጊዜ የሚያንፀባርቅ የቦርሳ ማስገሪያ መንጠቆ ነው፡፡ ይገርማችኋል…››

ጭፍን… አላማዩ በሰበብ እሷን ማየት ነበር፡፡ ግን የለችም፡፡ ከሳቋ ይልቅ ለቅሶዋ በርከቶ ትታየኛለች፡፡ የት?



@BOOKALEM

‹‹እነዚህ ፎቶዎች የሚያሳዩት ከወረሳ ህዝብ በግፍ የተዘረፉ ሐውልቶች፣ ምልክቶችና የመገልገያ መሣሪያዎችን ነው፡፡››

ጭፍን…ጭፍን… ጭፍን

‹‹አሁን ደግሞ ወደ ወረሳ ራዕይ እንሸጋገራለን፡፡ በሐቀኛ ልጆቿ ጭቆናን፣ የበታችነትን፣ መናቅን እስወግዳ ወረሳ ደርሳለች፡፡ እነኝድ ላፈው ደማቸውን አፍስሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው ለዚህ ራዕይ አብቅተዋታል፡፡››

አይኔን ከርተት ከርተት አደረኩ፡፡ እማማ ጉዶ እንደ አዘጋጅ ሳይሆን እንደ እንግዳ በአንክሮ ጀቢራ የሚሉትን ያደምጣሉ፡፡

‹‹እዚህ ጋ የምትመለከቱት የአምስት አመቱን የወረሳ የልማት ራዕይ ነው፡፡ በአዲሱ የልማት ስትራቴጂ መሰረት ባህላችንንና ታሪካችንን ያገናዘበ ወረሳ በቀል ማሰልጠኛ ማዕከል፣ ሰርቶ ማሳያና ዩኒቨርስቲ እንገነባለን፡፡ እነዚህ ሦስቱ ፕላኖች የህዝ ግንባታውን የሚያሳዩ ናቸው፡፡››

‹‹ተቃውሞ››

ሁሉም መለስ መለስ እያለ ተቃውሞ ባይዋን ተመለከተ፣ እማማ ጉዶ ነበሩ፡፡ ‹‹ተቃውሞ አለኝ›› አሉ፡፡

‹‹ተቃውሞኝን በአጠቃላዩ የወሀዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ እንድታቀርቢ ተነጋግረን የለም?››

‹‹አይሆንም፣ የሲምፖዚየሙ ተሳታፊ ሁሉ እንዲሰማኝ እፈልጋለሁ፡፡ እዚህ የምታዩት የወረሳ የልማት ራዕይ ሁሉንም ወረሳዊ ያማከለ አይደለም፡፡ በተለይ የደቡቡን ወረሳ ህዝብ ከተጠቃሚነት ያገለለ ነው፡፡ ስለዚህ እኛ ደቡብ ወረሳዎች የራሳችንን እድል በራሳችን ወስነን ከሰሜኑ ጨቋኝ አገዛዝ እንገነጠላለን፡፡ በቅርቡም የራሳችንን የባህል፣ የታሪክ የልማት ራዕይ ሲምፖዚየም እናዘጋጃለን፡፡ የደቡብ ወረሳ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሲምፖዚየሙ ላይ በይፋ ይመሰረታል እናሸንፋለን! ጨረስኩ›› ነጠላቸውን ከፍ ከፍ እያደረጉ ሄዱ፡፡ ወረሳ የእርስ በእርስ ጦርነት እንደሚያሰጋት ሆኖ ተሰማኝ፡፡ ለመሆኑ





የአክስቴ ቤት ሰሜን ነው ደቡብ? ጥቅሜን የሚያስጠብቀው ወገን የጀቢራ ነው የእማማ ጉዶ?

ከዚህ በኋላ ያለው የሲምፖዚየሙ መንፈስ የቀዘቀዘ ነበር፡፡ ከደብሙ፣ ልባሙና የእማማ ጉዶ የልጅ ልጅ ባልቴቷን ተከትለው ሄዱ፡፡ እኔም ከራሴ ጋር መደባበቴን ትቼ የአክስቴን ቤት ለመመልከት አመራሁ፡፡ ከበስተኋላዬ ጀቢራ ጠሩኝ፡፡ ዞር አልኩ፡፡

‹‹ከገንጣይ ወንበዴ ጋር ማበርህ ነው?›› አሉኝ፡፡

‹‹ኧረ እኔ…››

‹‹ሁሉንም አውቀናል፡፡ የእሪበከንቱ አስገንጣዮች ተላላኪ መሆንህን ደርሰንበታል፡፡ ለገንጣይና ለአስገንጣይ ሴራ ወረሳ አትበገርም›› አሉኝ፡፡

ገንጣይ? አስገንጣይ? ምነው እግሬን በሰበረው፡፡

* * *

አክስቴ ቤት ገባሁ፡፡ ሁለመናው በአቧራ እንደተዋጠ ነው፡፡ እዚህ ቤት ከመግባትና ከመውጣት ውጭ አደርግ የነበረው ነገር ገራ አጋባኝ፡፡ ቁርጡ ሆነ አስተካክዬ አላውቅም፡፡ እና ስገባና ስወጣ አቧራዎቹ ካረፉበት እንደዝንብ ተነስተው ይበሩ ነበር?

በአቧራ የጭጋግ መልክ የያዘው ፍራሽ ላይ ተቀመጥኩ፡፡ ለመቀመጫነት ከአቧራው ውጭ ቤቱ ትቼው እንደሄድኩት ነበር፡፡ በአፉ የደፋሁት ድስት እንኳን እንዳለ ጠብቆኛል፡፡

‹‹እንዴ? እንዴ? እንዴ? ድስቱን ጭፍን ወጥ ሰርታበት አልነበር? እና? ማን በአፉ ደፋው? ድስቱን በአፉ ለመድፋትብቻ እዚህ ቤት የገባ ሰው ነበር ማለት ነው? ማን? ለምን? እንዴት?

ጥያቄዎች እንደፉርጥ ተቀጣጥለው እኔን በማሳፈር ወደ እንቅልፍ ሰፈር ወሰዱኝ፡፡ ሳላውቀው ሺ-ትርጉም እየረገጠች እንቅልፍ ነሰታኝ ኖሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘና ያለ ደልቃቃ እንቅልፍ በእቅፉ እንደላቀቀኝ፡፡

የነቃሁት በእንቅልፍ መዕደቁ በቅቶኝ በእውነታዬ የኩነኔ ኑሮ መኖር አስኝቶኝ አልነበረም፡፡ አንዳች ነገር ተጫጭኖኝ



@BOOKALEM

እንጂ፡፡ በእንቅልፍና በንቃት መካከል እንደሆንኩ አይኔን ላኩ፡፡ የቤቱ ውስጥ ብርሃን ተደናግዞ እንዳች የሰው ቅርፅ አጠገቤ ተቀምጦ አየሁ፡፡ በግራጫ ሸራ ላይ በጥቁር ቀለም የተሣለ የሰው ቅርፅ፡፡ በፍጥነት መብራቱን ሞከርኩ፡፡ የለም፡፡ ሳልከፍል በመቅረቴ ተቆርጧል ማለት ነው፡፡

‹‹ማ-ነው? ማነው?›› አልኩ

‹‹እኔ›› የሴት ድምፅ፡፡ የሴት ከመሆኑ በላይ በቅርብ የማውቀው ድምፅ፡፡ መብራቱ በመቆረጡ ተደሰትኩ፡፡ ዝም እንደተባባልን ቆየን፡፡

‹‹ጠፋህ››

ነገር መፈለጊያ ተኩስ መሆኑን አላጣሁትም፡፡

‹‹አለሁ›› አልኩ ጦርነቱ ዴሞክራሲ በሆነ የዲፕሎማሲ ንግግር እንዲለወጥልኝ በማመልከት አይነት አሳዛኝና ተፀፃች ቅላፄ፡፡

‹‹ፍሬንዴ ሊላው ይቅር፡ ቤቱን እንኳን መለስ ብለህ አታየውም? እንዴት ቢደላህ ነው? እንዴት ቢስማማህ ነው?››

በሰለጠን አኳኋን ያቀረብኩት የድርድር ጥያቄ ውድቅ ሆኖ የማጥቃት እርምጃ ተከፈተብኝ ማለት ነው? ቢሆንም ዝም አልኩ፡፡ የተሰፋ ጭላንጭሉ እስኪዳፈን በዝምታ መጠበቅ።

‹‹ዝም አልክ››

‹‹ምን ልበል?››

‹‹ለነገሩ በተግባር እየነገርከኝ ነው፡፡ ያልገባኝ እኔ ነኝ እንጂ›› የለቅሶ ዳርዳርታ

ቀዝቃዛው ጦርነት ወደለየለት ውጊያ ተሸጋገረ፡፡ ልቤ በከባድ የእንባ መሣሪያ ይደበደብ ጀመር፡፡ ተንቀጠቀጠ፡ ተርበደበደ፡ ራደ… እያንዳንዱ የእንባ ጠብታ ልቤን እየበረበረ ትላልቅ ሸለቆ ይፈጥራል፡፡ የልብ ላይ ምሽጌ ሲፈርስ ነው፡፡ ‹‹የዓለም መንግሥታት›› ተብሎ አይሮጥህ ነገር፡፡ ኡፍፍፍፍ…..

‹‹ትምህርት ቤትም መጥቼ አጣሁህ፡፡ የማገኛ ሽርሽር ሄደህ ነበር መሰለኝ››





‹‹ሽሙጥ ባፈሙዝ›› መሆኑ ነው፡፡ ከእንባዋ ይሻለኛል፡፡ ትስደበኝ፡ ትምታኝ ግን አታልቅስብኝ፡፡

‹‹ፈንድተህ ታስረህ ነበር ሲሉ ሰማሁ›› እንባ ቅልቅል ሳቅ፡፡

እዩ በሽሙጥ ‹‹ተቀላቀል›› ስትል እኔ ደግሞ በልፊያ ‹‹ተቀላቀል›› አልኩ፡፡ የጨበጣ ውጊያችን ለየቅል አላማ ቢኖረውም የኔ አይሎ ስለተገኘ አጠገቤ እስተኝቼ ምርኮነቷን አረጋገጥኩ፡፡ የድል በዓል ቀን ሆኖ ድፍን ኢትዮጵያ ሊያከብረው የሚገባ፡፡ ቢያንስ ወሪሳና አረበከንቱ….

## 19 - ሞትን ፍለጋ

‹‹እንዲህ ሆንኩላችሁ›› ጭፍን እንዳረገዘች ነገረችኝ፡፡ እንደ ክላስተር በንብ ማስማር የተሞላ ፈንጂ፡፡ ያልተመታና ያልቆሰለ ሰውነት የለኝም፡፡ ‹‹የበላችው ያገሳታል፡ በላይ በላዩ ያጕርሳታል›› አሉ፡፡ እግዚአብሔር ያለእኔም አላየ? ከአንድ ምስኪን የአማርኛ መምህር ጋር እንዲህ ያለ ባላንጣነት ለእሱስ ቢሆን ጥሩ ነው?

ሰዓቱን በሙሉ ባላውቀውም እኩለ ሌሊት ይሆናል፡፡ ሞቱን ለማቋረጥ ተመኘሁ፡፡ ከአከስቱ ቤት ወጥቼ በአረበከንቱ ወንዝ ወሰንኩ፡፡ ድንገተኛ ሞት እዚያ አይጠፋም፡፡ ትዛዜ የሌለበት ፈጣን ሞት!

‹‹(አረበከንቱ ወንዝ) አንድ ሞት ብቻ አይደለም ብዙ ሞት ተሰብስቦ የሰፈረበት ብዙ ስቃይ ብዙ ጣር ተሰብስቦ የሰፈረበት ቦታ ነበር፡፡

‹‹ባንድ አመት ውስጥ (የአረበከንቱ) ውሃ የሚሰደውን፡ አሞ የሚበላውን፡ ሽፍታ የሚገድለውን፡ አባብ ነድፎት ወይም ወባ አሞት የሚሞተውን ተደብድቦ ወድቆ አሙሬ የሚቀራመተውን፡ ልብሱ የሚገፈፈውን ሀብቱ የሚዘረፈውን ይህን ሁሉ ሞት ይህን ሁሉ ጣር መከራው የደረሰበት ቤት መከራው የደረሰበት ቤተሰብ ይቆጥረዋል እንጂ ቆጥሮ ይህን ያህል ነው ሊል የሚችል የለም፡፡››



@BOOKALEM

(ምንጊዜ ጥቀስ አትበለኝ፡፡ ተስፋ የቆረጠ ጊኝ ከዚ ቀድም ያነበበውን ለንባራዊ ሁኔታው ማላያ ለማድረግ ስላሊጉመጉመ ምንጊዜ ለመጥቀስ አይገደድም፡፡ ለትንግሊ ሙያ የመጨረሻ ፍርድ የኮፒ ራይት ጥሰት አንዱ መስፈርት ከመ ንገሩኝ፡፡ እስከዚያ እቀጥላለሁ....)

‹‹(እሪበከንቱ ወንዝ) ውስጥ ተሰብስበ ከሰፈረው ጥቅ ስቃይ የበለጠ ደግሞ ወሬው ያስፈራ ነበር፡፡ መከራ የደረሰባት የደረሰበትን መከራ በመቶ አብዝቶ ያልደረሰበትን በጉልበ በብልሃቱ ወይም በጊዜው ታምራት ባያመልጥ ኖሮ ሊደርስበት የነበረውን ራሱ ፈጥሮ ወዲያው የፈጠረውን በሸህ አብዝቶ ሲያወራ እንዲህ ያለው ወሬ እየተሰፋፋ (እሪበከንቱን) ልክ እንደ ዝነኛ የማያውቁት ሁሉ በወሬው ብቻ ይፈሩት ነበር፡፡››

እሪበከንቱ ወንዝ ወቅት የካደው ጉልበቱን ወቅት በከዳው ድምፅ አጅቦ ይንጨላጨላል፡፡ ደካማዋ የጨረቃ ብርሃን የሰለጠነች በት የወንዙ ውሃ አልፎ አልፎ ሲታይ መስመር ይዞ የሚደህ ብራማ የትል ሰራዊት ይመስላል፡፡ ወንዟን ሻገር እንዳልኩ ወንዙ በአየር ላይ ተንስቶ ወደ ጭንቅላቴ ሲወንጨፍ አየሁ፡፡ የቃጀሁ መሰለኝ፡፡ ግን ልክ ነው፡፡ ጭንቅላቴን አልፎ ትከሻዬ ላይ ሲያርፍ ወዲያው ተሸመቀቀ፡፡ ሞት ቀረበኝ፡፡ የገባው ትንፋሽ አልወጣ፣ የወጣው አልገባ አለ፡፡ ሸምቀቆን እንዳች ነገር የኋሊት ይዞ ይጐትተዋል፡፡ ወደሚጐትተው ዞሬ የሞት ሞቴን ተንደረደርኩ፡፡ የተወጠረው እየላላልኝ ሲመጣ ሸምቀቆውን ካንገቴ ላይ ጐትቼ አሰፋሁ፡፡ የገባው አየር ወጣ፣ ሌላ አስገባሁ፡፡ ነፍሴ መለስ አለች፡፡

አይኔን ገልጬ ደካማዋን ጨረቃ የብርሃን እርጥባን ጠየኩ፡፡ አንድ አጭር ሰው ወደ ገመዱ ጫፍ አየሁ፡፡ ሙሉ ሰውነቱን ወደኋላ ለጥጦ ይጐትታል፡፡ እየቀረብኩት ስለመጣሁ ጐታቹ በራሱ ኃይል ወደቀ፡፡ አምጳርጵር እንደሆኑ አልተጠራጠርኩም፡፡ ከወደቁበት ለመነሳት ሲንደፋደፉ ደረስኩባቸው፡፡ እንደልጅ ልቆንጥጣቸው? ወይስ ምን እንዳደረጓቸው ልጠይቃቸው? ግራ ተጋባሁ፡፡

ቁልቁል አየኋቸው፡፡ አምጳርጵር አልነበሩም፡፡ ያ መናጢ የመጣባቸው ልጅ ነበር፡፡ ከእሪበከንቱ ሺ ሞት አንዱ እሱ ነበር? እንደ ድመቱ ሊሸመቅቀኝ?





‹‹ለምን? ደግሞስ እዚህ በዚህ ሰዓት ምን ታደርጋለህ?....›› የምለው ጠፋኝ፡፡

‹‹እዚህ ነው የማድረው›› አለ

‹‹እዚህ? ወንዝ ውስጥ?››

‹‹አዎ››

‹‹ለምን?››

‹‹ሸፍቼ፣ አምጳርጵር ሳላደግ እንዳይገድሉኝ፡፡ እንተስ አባቶው ልከውህ አይደል ልትገድለኝ...››

‹‹ኧረ አይደለም፣ ደግሞ ምን አረከኝ?....›› የምለው ጠፋኝ፡፡ ዝም ብሎ የወደቀበት ቀርቷል፡፡ ‹‹በል ተነስ›› ተነግ፡፡ በደንብ ባይታየኝም ከሩቅ የቀረቡት የእርበኛ ፎቶ ይመስላል፡፡ የእርበኛ ጥላ ፎቶ...

ልብሱን እራገፍኩለት ‹‹ለምን እንዲህ እመፀኛ ትሆናለህ? ያለዕድሜህ? ያለ አቅምህ? ባለፈው ተነጋግረን የለም? ተምረህ አየር ወለድ ለመሆን? ታዲያ...››

‹‹እስከዚያ አምጳርጵር አይተዉኝም››

‹‹ለምን? ካልነካሃቸው አይነኩህም››

‹‹ስላወቅኩባቸው››

‹‹ምኑን?››

‹‹አባቴን እንደገደሉት››

‹‹መጣባቸውን? መቼ? ትናንት...››

‹‹መጣባቸው አባቴ አይደለም፡፡ የእኔን አባት እንደተረገዝኩ ነው አምጳርጵር የገደሉት፡፡ እናቴ ነግራኛለች፡፡››

የምለው ጠፋኝ፡፡ ሁልጊዜም መፍትሔ የማልሰጥበትን ነገር ጉትጉቼ አደምጣለሁ፡፡ እውነትም ያርጌ ልጅ ነኝ፡፡ ጥቂት በዝምታ ቆየን፡፡

‹‹አሁን የት ነው የምታድረው?››



@BOOKALEM

‹‹እዚያ ድልድልዩ ሥር፡፡ ካርቶን እንጥፌአለሁ…››

‹‹በል ዛሬ እዚህ አታድርም አንድ ቤት ወስጄህ…››

‹‹የአምጸርጽር ልጅ ትገድለኛለች››

‹‹እዚያ አይደለም፡፡ ሌላ ቤት አለ፡፡ ጭፍን የምትባል የእኔ ጓደኛ ብቻ ናት ያለችው፡፡››

እንገራገረ ‹‹ግዴለህም…››

‹‹አምጸርጽር ቢሰሙ…››

‹‹ማንም አይነግራቸው፡፡ ቀን ቀን ካልወጣህ ማን ያይሃል? እኔም አልነግርም እምልልሃለሁ፡፡›› መንገድ ልንገባ ስንል…

‹‹ቆይ ገመዴን ልሰብስብ›› አለ፡፡

‹‹ከእንግዲህ ምን ያደርግልሃል?››

‹‹አምጸርጽር ከመጡ እሸመቅቃቸዋለሁ፡፡››

‹‹ጥሩ››

ተያይዘን ወደአከስቴ ቤት ሄድን፡፡ የ'ኳሞቱን ነገር በዚሁ ስለተውኩት የኮፒ ራይቱን ጉዳይ ልግለፅ፡፡ ‹‹ፍቅር እስከ መቃብር›› ገፅ 531፡፡

## 20 - ቢምረው አይማረው

ጭፍን ስመለስ ደስ አላት፡፡ እንዴት ልሂድ? ‹‹ብዙ ሞት ተሰብስቦ የሰፈረበት›› እረበከንቱ ወንዝ አለ፤ አደርኩ፡፡ በዚህ ላይ የመጣባቸው ልጅ በሰዓት ሰስት፣ መቶ መባተት እያስመዘገበ አደረ፡፡ ጠዋት በዚያው ወደ ስራ ሄድኩ፡፡

ይሄኔ የሺ-ትርገጥ ንዴት ተብላልቶ ተብላልቶ ጋን ሆዷን ሊሰብረው ደርሶ ይሆናል፡፡ ወደቤት ስመለስ እንደገመትኩት ነው፡፡ እንደዝሆን እረጋግጣኝ ልታልፍ ከጀላት፡፡ በኩምቢዋ እንስታ ልታፈርጠኝ አሰኛት፤ ግንድ ነቅላ ልትጥልብኝ አቁነጠነጣት፡፡ በመጨረሻ፡-

‹‹አባዬ ይምጣና ሰማኒያውን ቀድዶ ከሱን ያንቀሳቅስ›› አለችኝ፡፡ እንደዝሆን ረግጣኝ፣ አፍርጣኝ፣ ግንድ ጥላብኝ በሆን ጥሩ





ነበር፡፡ ከዳንኩ የትናንቱን የሥጋ እስር ቤት ህይወቴን እቀጥል ነበር፡፡ ከሞትኩም በቃ… ሆዷም፣ ጉንፏ፣ ባቷም… እየተንቀጠቀጡ ወዳባቷ ሄደች፡፡ የፍርዱን እረቂቅ ከግድግዳው ላይ እያነበቡ ጠበኳቸው፡፡ ከአሥራ አራት አመት በታች የለም፡፡ እላት የገባ ቂቤ ሆኛለሁ፡፡ እራሴን ካልገደልኩ በስተቀር ከዚህ ፍርድ አላመልጥም፡፡

አምጸርጽር እየተንጫነጩ ከልጃቸው ፊት ገቡ፡፡ መንግሥት እያለ ‹እንደሌለ…› እያሉ የፍርድ ማከበጃዬን ሊዘረዝሩልኝ ነው ስል ጉዳዩ ሌላ ሆነ፡፡ ጭራሽ ልጃቸው ላይ አፈጠጡ፡፡

‹‹ቅምጥ የወንድ ልጅ ወጉ ነው፡፡ ጥንት አባቶቻችን እስተመቶ እቁባቶች ድረስ ይይዙ ነበር፡፡ ምኑ አዲስ ሆኖብሽ ነው እንዲህ አገር ይያዝ የምትይው?››

ነፍሴ መለስ አለች፡፡ መቼም የአምጸርጽር ነገር እንደሆን ግራ ነው፡፡ ‹‹ሲጠራህ ዝም በል፣ ሳይጠራህ አቤት በል ነገሩ እንዲዘናበል›› ናቸው፡፡

‹‹እንኳን ሁከተኛ ሰው ውሻም ካጥር ውስጥ ከዋለ ነገር አያገኝም፡፡ እዚያም… እዚያም፣ ያቺንም… ያቺንም ሲል ደፋር ነገረኛ ወይም ፈሪ ዝምተኛ ያጋጥመዋል፡፡ እንዴት ነው ነገሩ…››

ሺ-ትርገጥ ለመናገር ሞከረች

‹‹እዚህ እስተኝቶኝኮ ነው…››

‹‹ያደለው ሚስቱ የተኛችበት ቅምጡን ያመጣል፡፡ ማን ተናግሮት? እኔ እናትሽን የሰራኋትን ትረሻለሽ?››

እያልጐመጐመች ወደ ጓዳ፡፡ እንግዲህ እረቂ ልግዛ እንጂ፡፡

* * *

እረቂው ሲደጋገም፣ እንደብረት ስንግል የመጣባቸውን ልጅ ጉዳይ አነሳሁባቸው፡፡

‹‹ጉዳዩ መች የመጣባቸው ልጅ ሆነ?››



@BOOKALEM

«ታዲያ?»

«እረበከንቱ፣ እሱን ንቄ ስተው እሳት ሲያረጅ ገላ ጉቢኛው መስሏቸው አዳሚ እንዳያኮበኩብ እንጂ፡፡ እኔ ነኝ አሁን እሱን ዋና ጠላት አድርጌ...»

«ታ-ዲ-ያ....»

«ያሮጌ ልጅ ሆነህ ብዙ ጊዜ ነገር ትስታለህ...»

እፍ ሲያመልጥ አይደለም ንዴት ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ ነው የማይታወቀው፡፡ «እርሶ ሰውዬ ብዙ ጊዜ አባቴን እያዋረዱና እያበሻቀጡ...» አፈጠጥኩ፡፡ ምን ላይ እንዳፈጠጥኩ እስካስታውስ አፈጠጥኩ፡-

«ኡ-ይ አንተ፣ እሮጌ የሌለበት ቤት አለ እንዴ?» እሱኝ ተለሳልሰው። መቼም እምጳርጵር ሲጠሩዋቸው አቤት አይደሉም፡፡ ይቺን ቀም ይዘው አንድ ቀን ግን ሳልጠራቸው አቤት ብለው ሳልሰናዳ አደጋ ይጥሉብኛል፡፡

«እዘውትሬ የምናገርህ ለመሰለል ነው፡፡ ሴትስ ይሁን፣ ወንድ የወለደ እንዴት ይሰደባል? ዛሬ አባትህ ወንድ ወለድኩ ይበሉ»

ግራ ተጋብቼ ዝም አልኩ፡፡

«የኛ ዘር ጀግንነቱ ሳያንስ እርጅቱ ነው የሚሞት፡፡ ‹ጀግና ብርሌ ነው ቶሎ ይሰበራል› እኛ ዘር ላይ አይሰራም፡፡›»

እንደርስዎ ሲጠሩዋቸው ዝም እያሉ፣ ሳይጠሯቸው አቤት እያሉ ይሆናላ አልኩ በልቤ፡፡

«እንዳባትህ ቁስ ያልክ እንደሆን እኛ ዘር ውስጥ አለ፡፡ ብቻ ቅስናውም ቢኖር ሁከቱ አይቀርም፡፡ እኔ በእድሜዬ የደረሰኩባቸው አለቃ ቢምረው አይማረውን ነው፡፡ አንቱ ናቸው፡፡ የብሉይ ሊቅ ነበሩ፡፡ ታዲያ እዘውትረው ‹በብም ጠረብ አለው› ይሉ ነበር፡፡›»

«እንዴት?» አልኩ፡፡ እንደሀግን የጠማ ትጭልጭልታ ስሰማ የያዝኩትን እለቃለሁ፡፡





«በወረብ ሰዓት ‹አብይ ፅፋት፣ ንዑስ ፅፋት› የሚባለው ስክር ይሁን እንጂ ለፅብም ያገለግላል ባይ ናቸው፡፡›»

«ይገርማል» አረቄዬን ቀመስኩ

«በጣም እንጂ፡፡ መቼም ብዙ ጠላት ነበረባቸው፡፡ ደብራቸውን ነቅቶ ለመውሰድ በዙሪያቸው ያሉ ሁሉ እንክን ፈላጊዎች ነው፡፡ የጠላቶቻቸው አውራ መምሬ ዱባለ እንደሆን ይታወቃል፡፡›»

አረቄያቸውን ፉት እስኪሉ ተቁነጠነጥኩ...

«የብሉይ ሊቅ አይደሉ? አንድ ጊዜ ሊቱ ሁሉ ተሰብስቦ አንድምታውን ይተዳዋል፡፡ እንዲህ ነው፣ እንዲያ ነው እየተባባሉ መምሬ ቢምረው አይማረውን ምስክር ያደርጋሉ፡፡ በመጨረሻ የሙሴ በትር ተነሣች፡፡ እባብ ሆኖ የፈርኦንን በትር የዋጠችቱ፡፡ መምሬ ቢምረው አይማረው መስክሩ ሲባሉ፡-

«በትር እማይሆነው አለ ወይ? እንኳን እራሱ በትሩ ሰውን ወደ እባብ ይቀይር የለም? አሉ፡፡

«እንዴት? እንዴት? አይሆንም!» አሉ እነመምሬ ዱባለ፡፡ የምቶኛ ነው ብለው ሊከሱ እቁብተዋል፡፡ መምሬ ቢምረው አይማረው ይኸን አውቀዋል፡፡

«ተከራካሪዬ ማነው? ሊወቀውና ተወራርጄ ላሳየው-- ታልሆነ አይሆንም አሉ፡፡

«እኔ» መምሬ ዱባለ

ከመጣህ እግዜር ያምጣህ ብለው «ውርርዳችን በምን ይሁን?»

«በባውንድ»

«በስንት ባውንድ?»

«አንዱ መች አንሶ»

«ጥሩ»

«ጥሩ»

«ባውንድ ባውንድ አስያዙ፡፡



@BOOKALEM

‹‹ደበሎ እንግዲህ በበትርዎ ሰው አባብ ያድርጉ›› ብለ መምሬ ዱባለ፡፡ ፈርደበት የለም?

‹‹መምሬ ቢምረው አይማረው ኅሳይህ አይደለ ወይ? ብለው በበትራቸው ይወርዱበት ጀመር፡፡ ሰው ለመገልገል ሲያጀበ ጣሊቃ የገባ ባውንዱን ይከፍላል አሉ፡፡ ያኔ ባውንድ ብዙ ነው፤ ግን ይድፈር፡፡ ሰው ሁሉ ገሸሽ አላለም፡፡ በግላጭ ቦታ ቦታ እየመረጡ እንግባብጠው ወቁትና ሲበቃቸው

‹‹ብል ተነስና ሂድ' አሉት››

‹‹በየት፡፡ ፍስስስስስ አለ፡፡ 'ተነስ እንጂ፡ እኔ ቢምረው አይማረው!' ብለው በትራቸውን ለዳግም ዱላ ሲያመቻቹ የሞት ሞቱን በደረቱ እየተሳበ መሸሸጊያ ፈለገ፡፡

‹‹ከዚህ በላይ አባብ መሆን አለወይ?' ብለው የውርርዳቸውን ተቀበሉ፡፡››

ለጊዜው ሳቅን፡፡





# ምዕራፍ ሰባት

## 21 - የትርኢቱ መዘዝ

ከሁለት አትጣጫ ተገመድኩ፡፡ በሁለት አዳኝ ቆሰልኩ፡፡

ከሁለት አትጣጫ ተገመድኩ፡፡ በሁለት አዳኝ ቆሰልኩ፡፡ ከዮፍን ጋር በጋዱ የሺ-ትርገዋ፡ ነፍሴ ደግሞ የዮፍን ሆንዋል፡፡ ከዮፍን ጋር ጎት እምሽቼ ከሺ-ትርገዋ ጋር ዝሀንም አድራለሁ፡፡ በእኔ ህይወት ገትን ገሃንም ያዋስናታል፡፡ ከገነት ወደገሃንም ለመግባት የሩብ ሰዓት የእግር ጉዞ በቂ ነው፡፡ የሁለቱ እካፋይ ድንበር በእንቅልፍ ልፏ የምታልጎመጉመው ወንዝ ነች፡፡

እምጴርጵር ይሄን ደርሰውበታል፡፡ ትንሽ ቅር የተሰኙት የዮፍን ‹‹ቀትረ-ቀላል›› መሆን ላይ ነው፡፡

‹‹እንደነገሩኝ ከሆንማ ይቺን ቢይዟት ትሞታለች አሉ፡፡ ምን አስመኘህ ልጄ፡፡ ቢገለብጧት ጡት የሌላትቲ ቢደፏት ቂጥ የሌላት ምኑን ሴት ናት?››

የእምጴርጵር በባቸውም ፍትራቸውም ከማይችሉት ጋር መታገል ነው ስል አስቤ ፈገግ አልኩ፡፡

‹‹ሙት እውነቴን ነው፡፡ ሴት ሲሆን ቤት፤ ካልሆነም አልጋ ካልሞላች ምኑን ሴት ናት፡፡››

እምጴርጵር በውጊያ እንዳስለቀቁት ጉብታ ሴታቸው ላይ በደረታቸው እየተንፏቀቁ ወተተው ስንደቅ እላማቸውን ሲተክሉ በአይን ህሊናዬ ታይቶኝ አሁንም ፈገግ አልኩ፡፡



@BOOKALEM

‹‹ሙት፣ የሺ-ትርጉጥ እናትን ያልክ እንደሆን እንደ የምታክል ነበረች፡፡ ገራም ባትሆን ኖሮ ረጋግጣ ትገድለኝ ነበር፡፡ ገና ቆጣ ስል እንደ ግመል በርከክ ብላ የማደርገውን መቀበል ትችልበታለች፡፡››

እምጳርጵርን ክፉኛ እየተላመድኳቸው የሄዱ ይመስለኛል፡፡ እንግዲ የተጠለቀው ሸምቀቆ እሳቸው እጅ ላይ መሆኑን እስከመዘንጋት የሚለኝ ጊዜ አለ፡፡ ምናልባት እሳቸውም አስብቶ አራጅ ናቸውና ያሰቡት አይታወቅም፡፡ ከጨዋታው ቆጠብ ስልባቸው ወደ ጓዳ ገባ አሉ፡፡ የልጅ ልጆቸውን ለመጎብኘት መስሎኝ ነበር፡፡ ጋዜጣ ይዘው ተመለሱ፡፡ ወንጀሉን የሚያስታውስ ታሪክ ለማገበብ ሳይሆን ይቀራል? አጠገቤ ቁጭ አሉና ክስተር ያለ ጨዋታ ጀመሩ፡፡

‹‹እንደምታውቀው እግዜር ይይላቸውና ወረሳዎች የቆሰቆሱት እሳት አልጠፋ ብሏል፡፡ ባረሳሳም አልሆነም፡፡ እረበከንቱዎች የባህልና የታሪክ ትርኢት ካላሳየን ሞተን እንገኛለን እንዳሉ ናቸው፡፡ እንደምታውቀው ደግሞ አሁን እጄ ላይ ብር የለም፡፡ ሂሳብ ይደረግ ከተባለም ሌላ ውርደት ነው፡፡ ስለዚህ ትርኢቱን እኛ እናሳያለን››

‹‹እኛ?››

‹‹አዎ እኛ ምነው?››

‹‹እንዴት?››

‹‹ጥቂት ጦር፣ ጥቂት ጋሻ፣ ጥቂት ፎቶ መፈለግ ነው፡፡ እዚህ ጋዜጣ ላይ የፈረንጆቹን ፎቶ አግኝቻለሁ፡፡››

‹‹የምን ፈረንጅ?››

‹‹አያቴ የማረኳቸውን እንግሊዞች››

‹‹አያትዎ እንግሊዝ ማርከው ነበር እንዴ?››

‹‹ለካ አልነገርኩህም’ና፡፡ አጤ ምኒልክ በእረበከንቱ አትለፉ ማለታቸውን ነግሬህም አልነበር?››

‹‹እሱን ነግረውኛል››

‹‹አንድ ችግር ተፈጠረ...››





‹‹ምን?››

‹‹እስኪ ክልብ ክልብ አትበል!›› ተቆጡኝ፡፡ ‹‹ችግሩ፣ የአጤ ምኒሊክ መልዕክት ለካ በፈረንጅ አፍ አልተጣፈ ኖሮ አንዳንድ ሰላዳቶ በእረበከንቱ አልፋለሁ መስሎት ይመጣ ጀመር፡፡ አያቴ ዝም በሉት ይጠራቀም አሉ ይባላል፡፡

‹‹አንዳንድ ሲል እስከ አምስትም እስከ ስድስትም ፈረንጅ ያልፍ ጀመር፡፡ አንድ ቀን ድንገት ደርሰው ሰባት እንግሊዝ ከበቡ፡፡ አያቴ በምርኳው ደስ ብሏቸው ሲሮክሩ ፈረንጆቹ የባህል ትርኢት እያሳዩ መስሏቸው ፎቶ ያነሱዋቸው ነበር አሉ፡፡ በመጨረሻም ‹‹ቀጥሉ›› ሲሏቸው ፈረንጆቹ ‹‹ተጋበዙልኝ›› መስሏቸው በገዛ እጃቸው ወደ መታሰሪያቸው መጡ፡፡ በዚህ አይነት ምርኮው ተጠናቀቀ፡፡

‹‹ፈረንጆቹ ማልቀስ የጀመሩት የፈረንጅ አፍ የሚያውቅ ተፈልጎ ሲነገራቸው ነው፡፡ እነቡ፣ እነቡ፣ እነቡ፡፡

‹‹ኧረ ይሄ ጭቷም ነጫጭባ ሁሉ፣ ታለቀሰ ለምን ሱሪ ታጠቀ? አሉ ይባላል አያቴ፡፡››

እምጳርጵር ድንገት እንደመባነን ብለው ‹‹ዛሬ አረቄ የለም እንዴ?›› አሉ፡፡

‹‹ተጫወቱ ይገባል›› እምጳርጵር እያመነቱ ቀጠሉ፡-

‹‹ምናጠፉን?›› አሉ ፈረንጆቹ

‹‹ደሞ ምን ልታጠፉ አምሮህ ኑሯል? ካቴም ማጥፋት! እስሬ እሰራሃለሁ፣ እምቢ ካልክ ፍዳህን ትበላለህ›› አሉ አያቴ፡፡

‹‹ምን እንበራ?››

‹‹መድፍ››

‹‹የት እውቀንበት? እኛ ወንጌል አስተማሪዎች ነን፡፡››

‹‹እረበከንቱ ወንጌል አስተማሪ እጥታ ማለት ነው? እንዴት ያላችሁ ቀዘኞች ኑራችኋል፡፡ ንሳ በእግር ብረት አሰርልኝ፡፡›› ታሰሩ፡፡

«ሶስት ቀን እንደታሰሩ እንሞክር አለ::

«እያቴ! ሞክሩ ከተሳካላችሁ ወደ አገራችሁ ካልሆነላችሁ ወደ እግር ብረታችሁ አሉ ይባላል::

«ተሞከረ:: እንደአጋጣሚ መድፉ ግሩም ሆኖ ወጣ:: እያቴ በደስታ ሳይበርድ መድፉን ስለሳሙት ከንፈራቸውን ሞሽለቀው ይባላል::

«ፈረንጆቹ ሊሄዱ ሲሉ እያቴ ድግሙ አሏቸው:: በኛ ባህል ጥፊም ይደገማል::

«ፈረንጆቹ ከእግር ብረት መድፍ መስራት ተሸሎ አገኙት:: ሁለተኛውን መድፍ ለማበጃጀት ላይ ታች ሲሉ እንግሊዝ በወረሳዎች እየተመራ መጣ:: ለእያቴ መልዕክት ላከ::»

«ምን ብሎ?»

«ክንድህን ስጥ»

«ምን ማለት ነው?»

«በእንግሊዝ ምርከኛን ክንዱን ወደኋላ ስለሚያስሩ እንደኛ እጅ ስጥ አይሉም:: ክንድ ስጥ ነው::»

«እ-ሺ?»

«እያቴ ‹ምን ክንድ አለኝ የመብረቅ ክንድ፤ እያውቅም እንዴ እንደሚያሳብድ? ብሎ መድፉን ተኮሰው፤ ደገመው፤ ተሰነጠቀ:: እያቴ በንዴትና በፀፀት ወደወረሳ እያየ...

‹ወረሳ ትዝብት ውረሺ

ሳይመሽ እንዳዘረፍሽኝ

ብሎ ሽጉጡን ጠጣው»

«ምን? ቴአትር...» አልኩ ሳላስበው

«የማን ታሪክ ነው ቴአትር?»

«እ-ይ፤ ቴአትር ሰርተው...»





«ድሮስ ቴአትረኛ ሌላ ምን ስራ አለው! ይልቅ አንድ ጋዜጣ ላይ ሰባቱ ፈረንጆች ከነዘመዶቻቸው የተነሱትን ፎቶ አገኘሁ:: መድፉም አለ»

«እውነት?»

«ይኸው፤ አታየውም? ሰባት የነበሩት አስራ ሶስት ሆነዋል:: ነፃ ከወጡ በኋላ ከዘመዶቻቸው ጋር የተነሱት ነው::»

ጋዜጣውን ተቀብዬ ፎቶውን አየሁት:: ሳቅ እንደደራሽ ፈነቀለኝ::

«ምነው? አሉኝ ቆጣ ብለው «ምን ያስቅሃል?»

«እነዚህኮ እግርኳስ ተጫዋቾች ከሰልጣኞቻቸው ጋር ናቸው:: መድፉ ምልክታቸው ነው» አልኳቸው::

«ፈረንጅ ፈረንጅ ነው:: እኔ ከግልገል ግልገል ሳማርጥ አለገኘም:: ድመት ድመት ነው:: ይልቅ ትከረከም እንደሆን ከርክም» አሉኝ::

## 22 - ትርኢቱ

የእሪበከንቱ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት የባህል ትርኢት ቀኝ አዝማች ማን አህሎህ ግቢ ተዘጋጀ:: መቼም ግቢው የተንጣለለ ሜዳ ነው:: እምጳርጵር ግቢው ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ሲሉ ከዱር ድመትም አንሰው ታዩ:: የባህልና የታሪክ ዕቃዎቹ የሚሰቀሉት ተሰቀሉ፤ የሚደገፉት ተደገፉ፤ የሚዘረጉት ተዘርግተው አለቀ::

ትርኢቱ ከመከፈቱ በፊት ሳየው ዋስትና አጣሁ:: ይሄ ሁሉ የጦር ዕቃ እሪበከንቱ ውስጥ ነበር? እንካሴ፤ ጦር፤ ጎራዴ፤ ሰይፍ፤ ገጀራ፤ ሰሙን የማላውቀው ሽለት... ጋሻ፤ ዋንጫው ደሞ ምንድነው? ጠላት አስከረው የሚማርኩበት?...

የእግር ኳስ ቡድኑ ፎቶ እንደፈራሁት ጥያቄ አላስነሳም:: እኛም እንደውም አንዳንድ የእሪበከንቱ ነዋሪዎች ፎከሩ:: እንዳባቶቻችን ፈረንጅ አስረን መድፍ ካላሰራን ሲሉ ተገለገሉ:: እምጳርጵር ተቆጥተው ዝም እንደማለኝት ጭራሽ አጋጋሉት::



@BOOKALEM

‹‹እኔስ ሀሳቤ ምን ሆነና? ጊዜው መጥፎ ነውና በምስጢር አንድ ሀያውን ሰልዳቶ አሰረን ብናሰራው ባመቱ ስንት መድፍ በኖረን፡፡ ታዲያ ምን ይሆናል...›› እንጠልጥለው ተዉት፡፡

‹‹ታዲያ ሲሉ...?›› ቀኝ አዝማች ጠየቁ፡፡

‹‹ምን እንዳንድ ያልገባው ሂሳብ ወዲት ይደረግ እያለ እንቅፋት ሆነ፡፡ ሁሉ የሚከናወን በሚስጥር መሆኑን እርሱ እያጡትም፡፡››

‹‹መች ጠፍቶኝ!›› እፈጠጡ፡፡ ‹‹ጥንትም የመከላከያ ሂሳብ በምስጢር ነው፡፡ መድፍ ካሰራን ያው ጦር ሚኒስትር መሆናችንም አይደል? አንድ ሰው ሂሳብ እንዳይጠይቅ፡፡ አባ! አባ የታሉ? ገዙ! ሂሳብ የሚጠይቀውን ገዙቱ፡፡››

ተገዙተ፡፡

## 23 - ዳርዳርታ

ቀኝ አዝማች ከአምጳርጵር አፍ ሳይጠፉ ዋሉ፡፡

‹‹እየኸልኝ ትልቅ ሰው! እሱን ነበር እንጂ አጥብቆ መያዝ፡፡ መዛመድ!››

‹‹ታዲያ...›› እኔን አባረው ልጃቸውን ለቀኝ አዝማች ልጅ ቢድሩ የሚል ጉጉት ያዘኝ፡፡

‹‹ታዲያማ የእሱን ዝምድና ለማግኘት ቃል ጠብቆ መገኘት ያስፈልጋል፡፡››

‹‹እና...››

‹‹እናማ ቃላችንን ለመጠበቅ ያህል ሃያም ባይሆን አንድ ሁለት ፈረንጅ ብናገኝና ብንጠልፍ...››

እኔና አምጳርጵር ፈረንጅ ጠልፈን ከፖሊስ ጋር ስንደራደር ታየኝ፡፡ መቼም ፈረንጅ ተጠልፎ የዓለም ህዝብ ዝም አይልም፡፡ ጋዜጠኛው ወደ እሪ በከንቱ ይንጋጋል፡፡ እኚህ ድመት የሆኑ ሰው እንድም ካልሞትኩ ወይም ዘብጥያ ካልወረድኩ መግላግያ የለኝም፡፡ ዝም ብዬ አየኋቸው፡፡





‹‹እስኪ ዞር ዞር እያልክ ቆንስላውን ሁሉ ሰልል፡፡ ማን ያውቃል አንድ ከርፋፋ ፈረንጅ አግተን፣ ይላካልን ይሆናል፡፡››

ከልባቸው እስኪሆኑ ‹‹እሺ›› ከማለት ውጭ መልስ አጣሁ፡፡

‹‹ታዲያ አደራህን ነጭ የመሰሉቱ እንዳያሞኙህ››

‹‹ነጭ የመሰሉቱ የትኞቹ ናቸው?››

‹‹ቱርክ፣ ባኒያን፣ አረብ፣ ቻይና፣ አርመን... እነሱን ከመግረክ እንድያውን የኛኑ ገሌቱ መፈንገል ይሻላል፡፡››

የእንጳርጵርን ልብ መደንደን ስመለከት ፈረንጅ ከገበያ የሚገዙ እንጂ አስገድደው የሚጠልፉ አይመስሉም፡፡ ለመሆኑ በምን መሳሪያ ነው የምንጠልፈው? ትርኢቱ ላይ በተደረደረው?

‹‹እኔ የምለው?››

‹‹እ?››

‹‹ፈረንጅ ከመጥለፉም፣ ስዱ ከመግባቱም፣ ለምን ከቀኝ አዝማች ጋር በጋብቻ አይዛመዱም?››

‹‹ለስሙ የአርጌ ልጅ ነህ፣ ለጋብቻም ቢሆን ቃል ጠባቂነትን ማሳየት ሳይቀድም ይቀራል?››

በአባቱ የሚመጡብኝ ነገር ግልፍ እያደረገኝ ነው፡፡ ‹‹እንቱ ሰውዬ...!›› ለማለት ዳድቶኝ ነበር፡፡ ከከንፈሬ ጫፍ መለስኳት፡፡

## 24 - ቅድመ ዝግጅት

እውጥቼ እውርጂ ፈረንጅ መጥለፍ የተሻለ ሆኖ አገኘሁት፡፡ እንዲት ሴት አስገድዶ በመድፈር ስሜ ከሚብጠለጠልና የሀፍረት ድሪቶ ተከናንቤ ዘብጥያ ከምወርድ አላማ ያለው በሚመስል ተግባር ብሳተፍ ይሻላል፡፡ ሳላስብበት እምጳርጵር ቤት ሄድኩ፡፡

‹‹ት እንጥለፍ›› አልኳቸው

‹‹ምን?›› አሉኝ፡፡

‹‹ፈረንጅ››



@BOOKALEM

ዝም ብለው ያስተውሉኝ ጀመር፡፡ መቼም እምጰርጵር ሲጠሩዋቸው ዝም፤ ሳይጠሩዋቸው አቤት ማለት የሁ... ዘዴያቸው ነው፡፡

«ብሉ እንጂ...» አልኳቸው፡፡

«ለስሙ የአሮጌ ልጅ ነህ፤ ፈረንጅ ጠልፈህ የት ልታስቀምጠው ኑሯል?»

ቡጢ የሚያህል እልህ ደረቴ ላይ ቆመ፡፡ መናገር መተንፈስ ከልክሎ...

«አዙሮ ማየት ነው፡፡ መጀመሪያ አጥሬን ወደነ... እገፋለሁ፡፡ ባሻ ገሩ ከፈቀደ በውድ፤ ካልሆነም በግድ አንድ ሜ... ሜትር ወደግቢው እገፋለሁ፡፡»

የእልሄ ጓል ፈረሰ፤ ተንፈስኩ፡፡

«ከዚያ ፈረንጆቹ ቢመጡ የማያሰማ እስር ቤት እንገነባለን፡፡ ከዚያ ወዲያ ነው ፈረንጅ መጥለፍ፡፡»

እኒህን ሰው ምን ላድርጋቸው? ምንስ ማድረግ ይቻለኛል?... ኡሁሁሁ....!

* * *

ባሻ ገሩ መሬት አልሰጥም አሉ፡፡ እምጰርጵር መጀመሪያ በራሳቸው ስም ዛቱ፡፡ ባሻ ገሩ አልተበገሩ፡፡ እምጰርጵር ቀጥለ... በፓርቲው ስም ዛቱ፡፡ ባሻ ገሩ አሁን የተበገሩ መሰሉ፡ ተንቀጠቀጡ፡፡ አልጋ ያዙ፡፡

በሦስተኛው ቀን እምጰርጵር ባሻ ገሩን ለመጠየቅ ሲነሱ እኔን አስከተሉ፡፡

«የታመሙት ምንድነው?» ስል ጠየኳቸው፡፡

«ደም ብዛት ነዋ! እግዚሐሩም ያበዛዋል እንዳንዴ፡፡ ሰውን በግቢ ብዛትና በደም ብዛት ያንበሸብሸዋል፡፡ እይልኝ ግቢውን፤»

ዝም ያለ ቤት፡፡ ያስፈራል፡፡ ሙጃ የወረረው፡፡ አንዳንድ ሙጃዎች ቀለስ ብለው ወደ ቤት ውስጥ አስግገዋል፡፡ ውስጡም





...የሚሳለመ ነው፡፡ ባሻ ገሩ ሳሎን ውስጥ የተዘረጋ ታጣፊ አልጋ ላይ ተኝተዋል፡፡ እምጰርጵር ድምፅ ሳያሰሙ ሹልክ ብለው ወደአልጋው ተጠጉ፡፡

ባሻ ገሩ እንቅልፍ የወሰዳቸው መስሎኝ ነበር፡፡ ድንገት...

«ውቃ መልአከሞት!!» አሉ፡፡ የሳሳ ብርድ ልብሳቸውን እንደ ጋሻ ገድግደው የእኛን አይን ተከላከሉ፡፡

«ባሻ ገሩ» አሉ እምጰርጵር የእሳቸው ባልሆነ ድምፅ

«እነሆኝ መልአከ ሞት በእርግጥ ልትወስደኝ መጣህን?» የብርድ ልብስ ጋሻቸውን እንደጋረጡ፡፡

«አሁንም በእኔ እጅ ተይዘህ ትከፋለህን? ስለምን እምቢብር ቁራጭ መሬት ሲለምንህ ከለከልከው?»

«መሬትስ ከምስጥ ውሰደኝ!» ብለው የጋረጡትን ብርድ ልብስ አነሱ፡፡ «አንተ ኑረሃል እምጰርጵር?» ተንፈስ አሉ፡፡

«እኔ ነኝ» አሉ ዘዴያቸው ስለከሸፈ ብስጭት ብለው፡፡ እኔ ግን በጅላጅል ዘዴ ላይ የተሳተፍኩ ሆኖ ስለተሰማኝ አፈርኩ፡፡

«ቂምህን ትተህ ልትጠይቀኝ መጣህ? ወይስ ቂምህን ልትወጣ...» ቁልጭ ቁልጭ አሉ፡፡

«ምን በጣኝ! ኧረ ልጠይቅህ ነው እመጣጡ»

«እንግዲያስ ቁጭ በል»

እኔን አላዩኝም

እምጰርጵር ተቀመጡ፡፡ እኔ እንደቆምኩ አለሁ፡፡

«አይ መጨረሻህ» ሲሉ አዘኑ፡፡

«ወይ ጓዴ! ከዛ ሁሉ ልጅ አንድ አጥተህ ባዶ ቤት ታንቋርራለህ!»

«የእግዚሐር ፍርጃ ነው»

«የእግዚሐር ብቻ አይደለም፡፡ ያንተም ጥፋት አለበት» አሉ እምጰርጵር፡፡

«እንዴት?»



@BOOKALEM

‹‹እንዴት ማለት ጥሩ! በዚህ ዕድሜ ላይ ወንድ ላጅ የሐምሌ በሬ ነው፤ አንተ ግን እንዱን ስታባርር መኪና ጸጠው፤

‹‹ምን ላድርግ ልቀጣ ብዬ ነው››

‹‹እ-እንዱን አውጥተህ አባረርከ››

‹‹ምን ላድርግ? ዱርዬ ቢሆን ቢቸግረኝ ነው፡፡››

‹‹በዚህ ዕድሜህ ሴት ልጅ ጠገብ ሳም ማለት ናት፤ ጉልበቷ፣ ሀብቷ... የሚታሰብ፡፡ አንተ ግን መቅጣት ሲገባህ አባልህ አለሌ ሆና እንደሬሬልሌ ዛፍ ላይ ታድር ጀመር፡፡››

‹‹ምን ላድርግ፣ ኧረ ተቃጠልኩ!›› አሉ ባሻ በሁለት እጃቸው አናታቸውን ያዙ፡፡

‹‹በዚህ ዕድሜህ አራስ ልጅ እንደማለት ነህ፤ ሚስቱን ያጣ አዛውንት እናቱ የሞተችበት ጨቅላ ማለት ነው፡፡ እንግዲህ ማን አፍህን ያብስው? ለንገሩ እማበላስ ሲቀርብልህ አይደል እፍህ የሚታብሰው...››

‹‹ኧረ ተቃጠልኩ፡፡›› አሉ ባሻ ገሩ፡፡ ‹‹ተቃጠልኩ፤ ልቤ ላይ ፈላ፤ እናቱ ላይ ተንተከተከ...››

ወደ አምጳርጵር ጠጋ ብዬ ደም ብዛት ካለባቸው ባያናድዷቸው...›› ስላቸው፡፡

‹‹ታዲያ እናቱን በዱላ በተገቢዉ ወንጀል ልግባ? በዚሁ በደ በተን ሶብቱ ደሙን ባፈሳው ሳምንትም ሳይቆይ ፍግም ይላል፡፡ ያኔ 10 ሜትር አይደለም 20 ሜትር መሬት ከግቢዬ ጋር እቀላቅላለሁ፡፡››

## 25 - ምኞት

ባሻ ገሩ ከተገመተው በላይ ፈጥነው ሞቱ፡፡ አምጳርጵርም ከተገመተው በላይ ፈጥነው እጥራቸውን አስፋፉ፡፡ በአፉ የሚደፍር ቢጠፋም በአይኑ የሚወቅስ አልታጣም፡፡

‹‹ምን አድርግ ይሉኛል? ፈረንጆቹ የት ይታሰሩ? መድፉስ የት ይሰራ?›› አሉ ለሚመለከተው ሁሉ፡፡





‹‹ተዉ! ሰው እንዴት ዝም ብሎ ማየት ያቅተዋል?›› አሉ ቀኛዝማች ማንአህሎህ ‹‹ልጅ አስተዋይ ነው፡፡ ተዉ፣ አባ፣ አባ የታሉ የሚያትረመርመውን ገዝቱ!››

ቀኛዝማች ከአምጳርጵር አፍ ሳይጠፉ ዋሉ፡፡

‹‹ይሄ ልጅ፣ አሉ? እንዲህ ሰው ዘመድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡››

ለልጃቸው ሺ-ትርገዋን መዳር፡፡ እኔም ከኚህ ጉንዳን ሰውዬ አገባል ነበር፡፡ አምጳርጵር ግን ‹‹ይሄ ልጅ›› መባላቸውን እያመነዠኩ ዋሉ፡፡

‹‹ይሄ ልጅ አሉ?››

## 26 - ግቢ ለገቢ

በታው ላይ የፈረንጆች እስር ቤት ሲጠበቅ አምጳርጵር በሸንበቆ ሾጣጣ የዶሮ ቤት መሳይ ሰሩ፡፡ የእስር ቤቱ ናሙና ነው ስል እሳቱ ላይ ‹‹የሚከራይ›› ብለው ለጠፉ፡፡

ይኸን ካከናወኑ በኋላ ወደእኔ መጡ፡፡ በኩራት...

‹‹እንደምታየው ከእግዚአብሔር ጋር ይሄን ቤት አጠናቅቄያለሁ›› አሉኝ፡፡

‹‹እሺ›› አልኳቸው በዚህ ሸንበቆ ቤት ስራ ላይ እግዚአብሔር መሳተፉ እየገረመኝ፡፡

‹‹ቤትን መስራት ብቻውን ፋይዳ የለውም፡፡ የእውሬ መፈንጫ ይሆናል፡፡ እንደው እግዚአብሔር ተራድቶኝ ይቺን ቤት አከራይቼ በወር በትንሹ ሦስት ሺ ብር ባገኝ...››

አምጳርጵር ሁለት ነገር ሳቱ፤ የመጀመሪያው ሽኩኮ እንጂ እግዚአብሔር ተከራይ አፈላላጊ አይደለም፡፡ ሌላው ቢያንሱት እንደዶሮ ቤት በትክክ የሚንጠለጠል የሸንበቆ ወጋግራቸውን በዚህ ሁሉ ብር የሚከራይ የለም፡፡ ሳልፈራ ነገርኳቸው፡፡

‹‹ምንም ያሮጌ ልጅ ብትሆን ያንተን ያህል ማሰብ አቅቶኝ ማለት?›› ብለው በነገር ወጉኝ፡፡

ግልፍ አለኝ፡፡ ‹‹እርስዎ ሰውዬ...››



@BOOKALEM

‹‹ከዛሬ ጋር ሁለት ቀን ወንድ ወጣህ፡፡ ወንድነት ግን ያስከፍላል፤ ዋጋ አለው›› ብለውኝ ሾካካ ሰውነታቸውን አሽራመሙ፡፡

እንደ ክፉ በሽታ እጅ እግሬን አስረው እያንዘፈዘፉ ገዙኝ፡፡ እስኪሄዱ ዝም ብዬ አየኋቸው፡፡

ቤታቸው አፍታም ሳይቆይ ተከራይ አገኙ ደላላው ሽኩክ አንድ የኮሰመነ ተማሪ ይዞ መጣ፡፡ ተማሪው ያለው ዕቃ አንድ ፌስታል አልሞላም፡፡ ኧረ እሱ እራሱ ቢታከልበት ፌስታሉ አይሞላም፡፡

ዕቃው አንድ ማዕዘን፣ ተማሪው ሌላ ማዕዘን ላይ ጥግ፣ ጥግ ያዙ፡፡

ሽኩክን ጠጋ ብዬ የኪራዩን ዋጋ ጠየኩት፡፡ እንኳን ሶስት ሺ አንድ ሺም አልሞላም፡፡

እምጵርጵርን በልቤ አሽሟጠጥኳቸው፡፡ በአፌ፡-

‹‹ሦስት ሺ ብሩ ቀረ?›› አልኳቸው፡፡

‹‹ትቸኩላለህ፤ የቸኮለ ጥርሱን አፍስሶ ለቀመ! ሲባል አልሰማህም? ሁከተኛ ሆነህ ብትቸኩል አንድ ነገር ነው፡፡ አንተ…››

ሲናደዱ ደስ ይሉኛል፤ እየተናደዱ የሚናገሩት ከቁብ አይቆጠርልኝም፡፡ ይሄ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ግፍ ከተቆጠረ ከሺ-ትርጉም የምወልደው ልጅ እንደሳቸው የዱር ድመት ይሆን ይሆናል፡፡ ለእሳቸው እግዞ እኔን ይሸመቅቃል፤ ወይም ለእኔ እግዞ እሳቸውን ያንጠለጥላል፡፡

‹‹አትቸኩል፤ ቤቱ እንዴት ሦስት ሺ እንደሚከራይ አሳይሃለሁ፡፡›› ተመናጨቁ፡፡

ምን አስበው ይሆን?

እምጵርጵር የወር ሂሳቡን ተቀብለው ‹‹ይሄ ተማሪ ሳምንት መቆየቱንም እንጃ›› አሉ፡፡ ‹‹ሳምንት ካልቆየ ጥሩ፤ ካልሆነ ግን ለሁለት መቶ ሀምሳ ብር የሱን ትክ ትክ ወር ሙሉ አልሰማም፡፡››

ሽኩክ የድለላውን ለመቀበል ሽኩክ ብሎ ቀረባቸው፡፡





‹‹ምን?›› አሉ እምጵርጵር ‹‹ዕዳ ስላመጣህብኝ ነው የድለላ የምሰጥህ? ይሄ ፈተና አሳትቶ የጨረሰው ተማሪ እሳት እንዳገኘው ፋቲክ ተኮማትሮ ቢገኝ ተጠያቂ የምሆነው እኔ መስሎኝ? እንደውም ይሄ ልጅ አንድ ነገር ይሁንና አንተን ሳልይዝ ከርቸሌ አልወርድም፡፡››

ሽኩክ ሀሳብ እንደገባው ሄደ፡፡

ተማሪው ሶስት ቀን ሞላው፡፡

እምጵርጵር ትዕግስታቸው አለቀ እመሻሽ ላይ ሄደው ‹‹አለህ?›› አሉት፡፡

‹‹አለሁ›› አለ በትክትክ ባንድ ታጅቦ

‹‹እኔስ ሞተሃል ብዬ ነበር››

‹‹እንዴት?›› አለ ግራ ተጋብቶ

ለምን በቅናሽ እከራየሁህ መሰለህ? ሰፈሩ መጥፎ ነው፤ ጨለማ ላይ አድፍጦ ማጅራት የሚመታው ለገንዘብ ሳይሆን ለነፍስ ዝርፊያ ነው፡፡››

ተማሪው ትክ ትክ ጨምሮ ዶቅዶቁ መሰለ፡፡

‹‹…ሙች ይሄ ብቻ! ከጭለማ አምልጠህ በጊዜ ብትገባ በሩን ሰብረው የተኛህበት እንደሙጃ በቆንጨራ ይጨፈጭፉሃል፡፡›› እምጵርጵር የሰቀቃቸው መሰሉ፡፡ ‹‹ስንቱ ጎበዝ እዚችው ቤት በእነሱ ተከታትፎ ሞቶ መሰለህ››

ተማሪው ነፍሱ ከትክትኩ ጋር ለመውጣት የአሰበች መሰለች፡፡ አፉን ያዘ፡፡

‹‹ወዳጄ፤ ለእኔም ኪሳራ ነው፡፡ በዚች ብር የአንተን ትክትክ ወር ሙሉ አልሰማም፡፡ ባይሆን ነገ ተነገወዲያ እኔ እራሴ እጠቁማቸዋለሁ፡፡ ብዙ ብር አለው እላቸዋለሁ፡፡ ይምጡና እነሱ ከትክትክህ ይገላግሉኝ እንጂ››

ተማሪው ያቺን ቀን ሲያድር አይኑ የተርገበገበም አይመስለኝ፡፡ ጠዋት ፌስታሉን ይዞ ሹክክ ብሎ ወጣ፡፡

ቀጣዩ ተከራይ ሲያክ የሚያድር ፎከታም ነበር፡፡

እምጵርጵር ገና በሁለተኛው ቀን ነገር ፈለጉት፡፡



@BOOKALEM

‹‹አንተ ሰው››

‹‹አቤት››

‹‹ቤት ስትጠርግ ነው የምታድረው?››

‹‹እንደውም››

‹‹ታዲያ ሾቅሾቅ የሚለው ምንድነው?››

‹‹እያከከህ ነው››

‹‹በል ደሂን ሮከት ወር ሙሉ አልታገስም፡፡ ካልሆን ማጅራት መቺዎቼን ገላግሉኝ እላለሁ››

ወጣ፡፡

እንዲህ እንዲህ እያሉ አስራ አምስት ቀን ሳይሞላ አራት ተከራይ አባረሩ፡፡ ለአምስተኛ ጊዜ ሁለት ሰዎች መጡ፡፡ እንዱ ወጠምሻ ጎረምሳ ነው፡፡ ሌላኛው የእምጳርጵር መንትያ የመሰሉ ደቃቃ አዛውንት፡፡ እምጳርጵር በክስ ግጠሙ የተባሉ ይመስል አዛውንቱን መረጡ፡፡

አዛውንቱ ተከራይ ቅልብልብ ናቸው፡፡ ቂርጥ እምጳርጵርን፡፡

እምጳርጵር ‹‹ደሂን መቅለብለብ ወር ሙሉ አልታገስም፡፡›› በሶስተኛው ቀን የተለመደ ዘዴአቸውን ለአዛውንቱ አቀረቡ፡፡

አዛውንቱ ተከራይ፣ አዛውንቱ አከራይን በተንኮል እያዩ ‹‹ደግ ነዎ›› አሉ፡፡ ‹‹የምገድለው ወይ የሚገድለኝ ስፈልግ የኖርኩ ሰው ነኝ፡፡ አሁን ካሁን በትንታ እሞት ይሆን? እያልኩ ስጋቼ ነበር፡፡ አይጥ ይመስል በትንታ? በስመአብ! ሰማይ ቤት ዘመዶቼን ሳገኝ ምን ልላቸው?›› አማተቡ፡፡

እምጳርጵር መንትያቸውን እያዩ ፈዘዙ፡፡ ‹‹እንዳሉት ቀላል አይደለም…››

‹‹ግዴለም ተዉት ለእኔ ተዉት፡፡ ለአንበሳ ይመትሯል? ፀብ ለኛ እንደዚያ ነው፡፡››

‹‹እንዴት ነው ተወው?››





‹‹እንደውም›› አሉ ተከራዩ ጭራሮ ‹‹እንደውም ሌላ ጠበኛ የማያት ከርሶ ጋር እንተያያማለን ብዬ ነበር፡፡ ወር ሙሉ ጠብቁ የምገድለው ወይ የሚገድለኝ ባጣ ኪራዩን አልከፍልም፣ ቤቱንም ለለቅም በሚል አምባገሮ ፊጥራ ከእርሶ ጋር እንፋለማለን ብዬ ነበር፡፡ እግዜሀር ደግ ነው፣ እያልቅበትም…››

እምጳርጵር ግራ ተጋቡ፡፡

‹‹ያኔ እኔ ወይም እርሶ እንደ አይጥ በትንታ ከመሞት እንገላገላለን፡፡››

እምጳርጵር አዛውንቱን አይዋቸው፡፡ ፊታቸው ላይ ቀልድ አለ፡፡ ‹‹እና? ወርም ሞልቶ ሂሳብ አይከፍሉም?›› አሉ፡፡

‹‹ምን ሊታሰብ?›› አሉ ተከራዩ አዛውንት፡ በአዛውንት ወኔ፡፡

እምጳርጵር ኸረ መላምታ በሚል እኔን አዩ፡፡ ፊቱን አዞሩባቸው፡፡

‹‹እንግዲያው የተቀመጡበት የሰባት ቀን ሂሳብ ተቀንሶ ገንዘብዎ ይሰጥዎታል፣ ይውጡልኝ›› አሉ እምጳርጵር፡፡

‹‹ምን ሊታሰብ›› አዛውንቱ ጭራሮ ‹‹ያውም ተቀንሶ? ፈጽሞም አልለቅ!››

‹‹ምን አልኩህ ህፃኑ ጨርቆስ? ለፍቼ ለፍቼ የሰራሁትን ቤት ለአዛውንት ጨዋሌሌ ትዳርገው?››

እኔ መካከል ለመግባት ሞከርኩ፡-

‹‹ታዲያ ምን ይሻላል?›› አልኳቸው ተከራዩን አዛውንት፡፡

‹‹ወይ መሞት፣ ወይ መግደል!›› አሉ የተቀመጡበት እየተቁነጠነጡ፡፡

‹‹ተወው አውቄዋለሁ›› አሉ እምጳርጵር ‹‹አስተዛሬ ቤተሰብ ሃብት ያላፈራው ለዚሁ ነው፡፡ እኔም ቤተሰብ ሀብት ባይኖረኝ ዛሬ እዚሁ ይለይልን ነበር፡፡››

እምጳርጵር ጫን ያለ ሲመጣባቸው ለካ ፈሪ ናቸው ስል አሰብኩ፡፡ በመጨረሻም የገላጋይ ሀሳብ አቀረብኩ፡፡

‹‹የሁለት ወር ኪራይ ይሰጥዎትና ይውጡ››

‹‹አልችልም!!›› አሉ አዛውንቱ ተከራይ

‹‹የሶስት ወርስ?››

‹‹አልችልም!!››

‹‹የአራት ወርስ?››

‹‹እሞክራለሁ››

እምጳርጵር ኅብ ኅብ እያሳቸው የተባሉትን ለሞገደኛው አዛውንት ሰጥተው ተገላገሉ፡፡

## 27 - ጥንስስ

ወደቤት ስገባ ሺ-ትርጉጥ ጉብታ መስላ በር ላይ ተቀምጣለች፡፡

‹‹ምነው?›› አልኳት

‹‹ልጄ ፈሪ ሊሆን ነው›› ብላ መነፋረቅ ጀመረች፡፡

‹‹የቱ?››

‹‹ይሄ›› ብላ ሆዷን ተመተመች

‹‹ምን ሆኖ ፈሪ ይሆናል?››

‹‹የመጣባቸውን ልጅ እያየሁ እንዳልወልድ የለም፡፡ አንተን እያየሁ ከወለድኩ እንዴት ፈሪ መሆን ይቀራል?››

እራሴን እስክታዘብ ደነፋሁ፡፡ ደግሞ እራሴን ጠየኩ፡፡ ፈሪ ነኝ? እውነቱ የማልዘልለው ጉድባ ሆኖ ፊቴ ተደቀነ፡፡ እኚያ ኮስማና አዛውንት የነገሩኝ እንጂ ሺ-ትርጉጥ የሰደበችኝ እንዳልሆነ ገብቶኛል፡፡

ምን ላድርግ? እምጳርጵርን ምን ላድርጋቸው ልበል እንጂ…

በሺ-ትርጉጥ አሳብቤ ከቤት በመውጣት ወደ ሠፍን ሄድኩ፡፡

እምጳርጵርን ይሄን ያህል መፍራት አለብኝ? ሰውነቴ ተቆጣ፡፡ ለየትኛው ወንድነቴ ሴት ፍለጋ እሄዳለሁ? የባላጋራ ሙግት ለራሴ አቀረብኩ፡፡ ከልባሙ እንባለሁ? ከእኚያ ሠራሮ አዛውንትስ? ሌላው ይቅር ከመጣባቸው ልጅ ማነስ ነበረብኝ?…





በምቀቆ ይገፍ እረብከንቱ ወንገ ልሸፍት? አይሻልም? በእምጳርጵር የተፈነገለ ባሪያ ከመሆን የማይሻል አለ? የለም! ብዬ ልቆርጥ ስል ለላ ሀሳብ አገተኝ፡፡

እኔ የፈራሁት እምጳርጵርን ነው ወይስ የጠመጠሙብኝን ነገር? እንደልባሙ፣ እንደ ጨፍራራው ሽማግሌ፣ እንደመጣባቸው ልጅ ነገር ባይሰሩብኝ እፈራቸው ነበር?… ለነገሩ እምጳርጵርን የማይፈራ ማን አለ? እምጳርጵርን አለመፍራት ግብታዊነትና ጀብደኝነት አይደለም? እንደ ጨልጨሴ ‹‹አንድ እግር በርበሬ ይፍጃችሁ›› ብዬ መንቀል አቅቷችሁ፣ እምጳርጵር ለብልቦ አንድዶ ይፍጃችሁ›› ብዬ ወኔ ብወርድ ጀግንነት ነው?…

ያም ሆኖ የምክንያት ብዛት ከፈሪነት ዕዳ የሚያወጣኝ አልሆነም፡፡ የፈሪነት ዕዳዬ ዕድሜ ልክ ተገፍግፎ የማያልቅ በደምና በአጥንት ወደ ልጅ ልጆቼ የሚሸጋገር ሆኗል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ የኋልዮሽ በተረት መንዜን ትቼ ወደፊት ያሰብኩ መሰለኝ፡፡ ወደፊት ማሰብ ሠንቀት ይበዛዋል፡፡ መወላወል ያጋጩዋል፣ መድረሻ ይጠፋዋል፡፡ ተረት እና ታሪክ እደጋ የሌለባቸው ጥርጊያዎች ናቸው፡፡

ምንድነው የማስበው? አእምሮዬ ፈሪነቱን እየሸሸ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ፈሪ ነኝ፣ ፈሪ ነኝ…

እክስቴ ቤት ደረስኩ፡፡ ዛሬ የማድረው ሠፍንጋ ነው፡፡ የትናንቱ የእምጳርጵር ፍርድ ለዛሬው መተማመኛ እንደማይሆን አውቃለሁ፡፡ የእሳቸው የማይለወጥ መመሪያ ‹ሲጠራህ ዝም በል ሳይጠራህ እቤት በል ነገር እንዲዘናበል› ነው፡፡

‹‹ሲፈልጉ ያሻቸውን ያድርጉ!››

ወደ ውስጥ ስዘልቅ ሠፍንና የመጣባቸው ልጅ በሁካታ ላይ ነበሩ፡፡ ሠፍን ከእኔ ጋር ስታ በማታውቅበት ሁኔታ ከመጣባቸው ልጅ ጋር ታውካካለች፡፡ ዞርም ብላ አለማየቷ ቆጠቆጠኝ፡፡ ልተና?

ጥቂት ባለሁበት ቆየሁ፡፡ የመጣባቸው ልጅ አይቶኝ ከስሜቱ ሲላቀቅ ሠፍን ግን ሳቋን ማቋረጥ ተስኗት ቀጥላለች፡፡

ፊቴን መልሼ ወደ ውጭ ወጣሁ፡፡ አልተከተለችኝም፡፡ በመሄዴ እፍሬ በመሄዴ ቀጠልኩ፡፡ የተለወጠ የለም፡፡ የሺ-ትርጉጥን



@BOOKALEM

ቤት አፍርሼው እንደመጣሁ ሁሉ አማራጭ ሆኖ አልታይህ አለኝ፡፡ ከንትር ግሮሰሪ ገባሁ፡፡ ጠጪው ሁሉ አፍጥጦ ያየኛል፡፡ በልቤ እኔን እያያችሁ ፈሪ እንዳትወልዱ ብቻ አልኩ ‹‹ደብል ጂን፡፡›› ጠጣሁ ወይም ወደ ውስጤ ደፋሁ፡፡

‹‹ድገም!››

ቀመስ አድርጌ ተውኩት (ፈራሁት?) መቼም ፈሪ ነኝ፡፡

ጠጪ መኖሩን እንጂ ማን ማን እንደሆኑ አላለየሁም ነበር፡፡ ሽኮኮ ከተቀመጠበት ተነስቶ የተደገፍኩትን ባልኮኒ ተደገፈ፡፡

‹‹ምነው?›› አለኝ

‹‹ምነው?›› አልኩ በቁጣ፡፡ (አህያውን ፈርቶ ዳውላውን) የእኔ ነገር ላይሞት ይፈራል፣ ላይድን ይሸሻል እንደተባለው ነው፡፡ (የምን ተረት መጣብኝ?)

ጂኔን አጋመስኩ፡፡ እኔ የጠጣሁትን ሽኮኮ ቀድሞ ሲውጥ አየሁት፡፡ ማንቁርታም፤ ማንቁርቱ ምን ያህላል?

‹‹ድገም! ለእሱም!››

ሽኮኮ የእሱ ጅን እስኪመጣ እኔ የተጎነጨሁትን እየዋጠ ጠበቀ፡፡ የብሶቴን አወራው ጀመር፡፡

‹‹እኚህን ጉንዳን ሰውዬ ምን ማድረግ ይሻላል?››

‹‹ማንን?››

‹‹ሌላ ጉንዳን አለ?››

ከት ብሎ ሳቀና፡፡ ‹‹ስለአምጳርጵር መሆኑን ላረጋግጥ ብዬ ነው እንጂ እኔም ሳስብ የነበረው ስለሳቸው ነበር፡፡ አይገርምም?›› ሲያወራም ማንቁርቱ ከፍ ዝቅ ይላል፡፡

ጅኑ መጣለት፡፡ እንደናፈቀ ዘመዱ ስሞ አስቀመጠው፡፡

‹‹ምንድነው ስለሳቸው ያሰብከው?›› ስል ጠየኩት፡፡

‹‹እስከመቼ ፈንድተውብን ይኖራሉ? ሲፈልጉ የሰራንበትን ይነጥቁናል...››





ደላላ መስዬው ነው እንዴ ስለደለለበት መነጠቅ እኛ እያለ የሚያወራው? አልኩ፡፡

‹‹...ሲፈልጉ ይፈነክቱናል...››

እግዚአብሔር ይመስገን ይሄም ክስ የእኔ አይደለም፡፡

‹‹እ... ሲፈልጉ ልጃቸውን ይድሩልናል...››

ለካ አንደኛዋ ልጅ የሽኮኮ ኑራለች? ልቀና?

‹‹ዝርዝሩን ተውና ምን እናድርጋቸው?›› አልኩ፡፡

‹‹ያሰብኩላቸሁ ነበር..››

‹‹ምን?››

‹‹አንተ መቶ ብር እኔ መቶ ብር ካዋጣን በቃ! ይሳካል!››

‹‹ብሩ አልበዛም?››

‹‹ጉዳዩ ሲከናወን አነስህ ትላለህ፡፡ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል፡፡›› ከደላላ ምላስ ከተነቀለ ከመነቀል ብዛት እራሰ በራ ምላስ ሆነ ማለት ነው፡፡

‹‹ምን እንደምታደርጋቸው ንገረኛ...››

‹‹እሱን ለእኔ ተወው››

‹‹ልወቀው እንጂ›› ብዬ በጅን አይኔ ጅን አይኑ ላይ አፈጠጥኩ ‹‹መቶ ብርን ያህል ነገር ሜዳ ላይ ጥዬ እሄዳለሁ?››

‹‹እንዲህ ነው›› አለና እንደማንኛውም ደላላ ከንፈሩ ዳርና ዳር የደረቀ ምራቁን ጠራርጎ ‹‹አሳስራቸዋለሁ›› አለኝ፡፡

በአረጅሙ ጀምሮ በአጭሩ ጨረሰው፡፡ እንዲህ ነው ካለ የሚብራራ ነገር መኖር የለበትም?

‹‹የፖሊስ ዘመድ አለህ?›› ሳጂን መርጌ ትዝ አለኝ፡፡ ቃልኪዳናችን ከምን ደርሶ ይሆን?

‹‹እሱን ለእኔ ተወው!›› የተደፈቀ ምራቅ መኖሩን አረጋግጦ ሲያበቃ ‹‹መኪናን ቢ.ጨ ዛሬ ሰክሮ በመውደቁ ፈቱ ተላልጧል፡፡



@BOOKALEM

ነገ አምጻርጵር ደበደቡኝ ብሎ እንዲከሳቸው ገንዘብ እንሰጠዋለን፡፡ ባለፈው እንዲሁ አቅደን ገንዘብ ባለማግኘታችን የመከንን ቁስል ደረቀ፡፡ ዛሬ ግን...››

ጥሩ ዕቅድ ይመስላል፡፡ እንደ ልብ ወዳጅ እየሳቅሁ የልቤን እሰራለሁ፡፡ መቶ ብር አወጣሁ፡፡ ሽኮኮ የመንጠቅ ያህል ሞጭልፎ ኪሱ ወሸቀው፡፡ ሌላው አካሉ እንጂ እጁ አልሰከረም ማለት ነው፡፡

## 28 - ኑ! ደባቅመሱ

ጭፍንጋ ገብቼ ስነፋርቅ አደርኩ፡፡

‹‹እኔን አትወጂኝም›› አልኳት፡፡ ‹‹ዛሬ ታወቀብሽ፣ ማሙሽን ነው የምትወጂው››

‹‹እ-ሆሆሆሆይ..› ትልና ቅድም ያባረረኝን ሳቋን ትለቀዋለች፡፡ ሲብሰባት...

‹‹ምን ሳድርግ? እስኪ ንገረኝ?...››

ለካ እውነት ያለው እኔ እጅ ሳይሆን እጿጋ ነው፡፡

ዝም!

‹‹እውነት ምን ታድርግ?››

ዝም! ዝምን ተከትሎ እንቅልፍ መጣ፣ እንቅልፍ ተከትሎ ንጋት መጣ፣ ንጋትን ተከትሎ ንቃት... የአምጻርጵርንና የመቶ ብሬን መጨረሻ ለማየት ወደ እረበከንቱ...

በር ላይ ደርሼ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ በማቅማማት ላይ ሳለሁ ጫጫታ ሰማሁ፡፡ አምጻርጵር እንደጎረምሳ እየደነፉ በፖሊስ ታጅበው ወጡ፡፡

ሺ-ትርገጥ ትቅለበለባለች፡፡ ስትፌጥን ሰውነቷ ተዘርግፎ የሚቀር ይመስላል፡፡ ግርግሩን ተቀላቀልኩ፡፡

መኮንን ቢሮው እየደጋገመ ‹‹እኔ የደበደበኝን አጣሁት እንዴ? እሳቸው!!›› ይላል፡፡

‹‹ደግ አደረኩ!›› ይላሉ አምጻርጵር፡፡ በገዛ እልሃቸው ገደል እየገቡልኝ እንደሆን ጠረጠርኩ፡፡ ‹‹እንኳን ደበደብኩህ! ገና ምን አይተህ? እደግምሃለሁ!››





ግራ ተጋባሁ፡፡ እውነት ደብድበውታል እንዴ?

ሽኮኮ ደላላው በሰዎች መካከል ተወሽቆ ሁኔታውን በንቃት ይከታተላል፡፡

አምጻርጵር እኔን ሲያዩ ቆም አሉና የተንኮል ፈገግታ አሳዩኝ፡፡

ግራ ተጋባሁ፡፡ ‹‹ምንድነው? ማነው? ለምንድነው?..›› እያልኩ ተርበተበትኩ፡፡

አምጻርጵር በአጠገቤ ሲያልፉ ኅተት አድርገውኝ እንዲህ አሉኝ፡-

‹‹የሞኝ ደባ ግንባሩ ላይ የተፃፈ ምስጢር ነው፡፡ ለማንኛውም አመሰግናለሁ፡፡ የልጅ ልጆቼ ነገር እራሴን አዙሮት ነበር፡፡ አሁን ስታሰር ቤቱን አቆልፋለሁ፣ የልጅ ልጆቼን ለእናታቸው እሰጣለሁ፡፡ እናታቸው ሚስትህ ናት፣ ባትወልዳቸውም ልጆችህ ናቸው፡፡ አሳድጋቸው››

እነሆ ዘብጥያ የወረደው ሰው ለየ፡፡ አምጻርጵር ሳይሆን እኔ ነኝ ወህኒ የተወረወርኩት፡፡ ‹ደባ እራሱን፣ ስለት ድጉሱን› ማለት ይሄ አይደል? አምጻርጵር ታስረው ከፈረዱብኝ የኑሮ ዘብጥያ ለማምለጥ ስል ‹‹ፖሊስ!›› ብዬ ተጣራሁ፡፡

ፖሊሱ ታቦት እንደተሸከመ ሁሉ ቀስ ብሎ ዞረ፡፡

‹‹እኔም ከአምጻርጵር ጋር አባሪ ተባባሪ ሆኜ ደብድቤዋለሁ፡፡ ይዘኸኝ ሂድ!›› ስል እራሴን አሳልፌ ሰጠሁ፡፡

ደላላው ሽኮኮ ድንገት ከተፍ ብሎ ‹‹የአንተን አልተነጋገርንም፣ ትጨምራለህ?›› አለኝ፡፡

## 29 - አዲሱ አባባ

አምጻርጵርን ሳጂን መርጌ ‹‹ጀግና እወዳለሁ›› በሚል ተቀበላቸው፡፡ ‹‹ጀግና እወዳለሁ›› በሚል ለቀቃቸው፡፡ አምጻርጵር ለምነው ሁለት ቀን ብቻ ታሰሩ፡፡ ልጆቹ የእኔ መሆናቸውን ማረጋገጫ ሁለት ቀን፡፡



@BOOKALEM

አራቱ ሴት ልጆች አያታቸው ሲፈቱ እንዲያለቅሱ ነገርኳቸው፡፡ አለቀሱ፡፡

‹‹አባዬ፣ አባ፣ አባባ…››

እምጰርጵር ግን ሆዳቸውን አደንድነው፡-

‹‹ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ፣ እሬን ዳባ ዳባ አለኝ›› አሉ፡፡

ሺ-ትርገጥም ልጆቼን እየገሰፀች ‹‹ከእንግዲህ አባባ እሱ ነው›› ብላ ወደእኔ ጠቆመች፡፡

‹‹እዲሱ አባባ፣ አባባ…›› አሉኝ፡፡ የተላጡ ድንች የመሰሉ ጭቃሞች፡፡

ከእንግዲህ በእምጰርጵር ስልት ቅም፣ ቅም፣ ቅም እያቶቼን እያስቆጠርኩ መኖር እጣ ፈንታዬ ሆኗል፡፡

ከዕለት ዕለት በእምጰርጵር እረንቋ እየተዋጥኩ የሚጠብቅ ድውይ ሆንኩ፡፡ እኚህ ጉንዳን ሰውዬ…

## 30 - ተረታማው ኑሮ

እምጰርጵር ወበሩ እጃቸውን በኪሳቸው ከትተው ዞሩ፡፡

እኔ ፈዘዝኩ፣
በገፅታ ወየብኩ፣ (እንደልጆቼ)
በአቅም የደከምኩ፣

ሺ-ትርገጥ ጌታን አመሰገነች

ልጆቿን ሰበሰበች

የቤት እመቤት ሆነች

ህይወቴ ከንብ ቀፎ ወደ ንብ ቀፎ ሆነ፡፡ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እዝዝዝዝዝዝ… ይሉብኛል፡፡ ቤት ውስጥ ልጆቼ እዝዝዝዝዝ… ይደግሙኛል፡፡

እዝዝዝዝ…





ህይወት መሀል ላይ ፍዝዝዝዝ…

ኑሮዬም እጅ እጠረው፣ እስራ አምስት ቀን በጀት፣ እስራ አምስት ቀን ተረት ሆነ፡፡ የተረት ፍጆታዬ ጨምሯል፡፡

- ላያሽንፉ መታገል ትርፉ ገደል›› በሚል ፀፀት መቶ ብር እዋቶቼ የገባሁበትን ገደል እለካለሁ፡፡

- ላይቀር ሞቱ መንጠራወቱ›› በሚል ፀፀት እምጰርጵርን ለመግደል እከጅላለሁ፡፡

- ላሳር የጣፈው ቢነግድ አይተርፈው›› በሚል ቁጭት መጧውን ደሞዝ ለሺ-ትርገጥ ላለመስጠት እወስናለሁ፡፡

- ልጅ እባቱን አይብ እንቱን›› በሚል ጥንታቄ ልጆቼ የሚያሳድሩብኝን ሐዘኔታ እገስፃለሁ፡፡

ተፈጸመ



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ስምንት

## 31 - ተረታማው ቀለብ

ለሚሉኝ መልስ አለኝ፡፡ አይጥ

ትዳር ምንድነው? ሞት መጠበቂያ በወጥመድ ከተያዘች በኋላ ምን አለ? ትዳርም ሞት መጠበቂያ ምፍራ ነው፡፡

ልጆቹ ገና ወፍ ሲንጫጫ ተነስተው የግድግዳ ላይ ጋዜጣ ያነባሉ፡፡ እኔ እፈራለሁ፡፡ በዚች ሰዓት አማራጩ ሁሉ የአስራ አምስት አመት ዘብጥያ ሆኖ ጠዋቱ ይጨልምብኛል፡፡

ልጆቹ በፊደል ክርክር ይገጥሙና የእናታቸውን ዳኝነት ይጠይቃሉ፡፡

‹‹አባታችሁን ጠይቁት›› ትላለች፡፡

‹‹አዲሱ አባባ፡ አዲሱ አባባ...›› ይላሉ፡፡ በገዛ እጄ ፍርዴን ሊያስነብቡኝ፡፡ ልጆቹን ትቼ እናታቸውን ‹‹እስቲ ቁርስ ስጪኝና ወደ ስራ ልሂድ›› እላለሁ፡፡

ሺ-ትርገተ ድንቅ ነገር እንደሰማች ሁሉ በመገረም እጇን አፏ ላይ ትጥላለች፡፡

‹‹ምነው?›› እላታለሁ፡፡

‹‹ለስሙ የተረት አስተማሪ ነህ፡፡ ሳትወልድ ብላ› መባሉን ግን ትዘነጋለህ፡፡››

‹‹መች ወለድኩ?››

‹‹መወለድ ቋንቋ መሆኑን ከዘነጋህ ምኑን አስተማርክ?››

ከተቀማጭ ተረቶቼ ልጅ የሚመለከተውን እመዛለሁ፡፡

‹‹ልጅ ለወለደው ሙቅ ላሞቀው ነው››

‹‹ላም በረቱን፣ ሰው አሳዳጊውን ይበላል፡፡››

አሁን የጠቀሰችውን ተረት አውቀዋለሁ፡፡ ላምበረቱን የሰው ልጅ አባቱን እንጂ እንዳለችው አይደለም፡፡ ተከራከርኳት፡፡

‹‹አባቱን ነው››

‹‹አሳዳጊውን ነው››

‹‹አባቱን ነው››

ልጆቹ የጋዜጣ ንባባቸውን አቋርጠው ያዩናል፡፡

‹‹ይሁንልህ›› አለችኝ፡፡

ኩራት ተሰማኝ፡፡

‹‹ጉዳዩ ያለው ግን እሱ ላይ አይደለም›› አለች መልሳ

‹‹እህስ?›› ስላት

‹‹ላያሸንፉ መታገል ትርፉ ወደገደል የሚለው ላይ ነዋ...›› ሳቀች፡፡ ድምጿን ከፍ አድርጋ አስካካች፡፡

ለካ ገደል አፋፍ ላይ ኖሬአለሁ፡፡ ላላሸንፍ ነው በተረት የታገልኩት፤ ቶሎ ቶሎ ለባብሼ ወጣሁ፡፡

በሬ ሆይ፣ በሬ ሆይ፣ ተረቱን አየህና ገደሉን ሳታይ... በሬው እኔ መሆኔ ነው፡፡

ምሳ ሰዓት እየተሸማቀቅሁ እቤት መጣሁ፡፡ እሊጋ ላይ ወጣሁ፡፡ ተረቶቼን ቆረጣጠምሁ፡፡

ሰላልጠየኩ ሺ-ትርንጉ በዝርግ ሰሀን ምሳ አቀረበችልኝ፡፡ ስበላ ከጉርሻዬ ጋር የምውጠውን ምክር እይሉት መመሪያ ታዥጎደጉዳለች፡፡

‹‹ልጆች ሲያሳድጉ ቀበቶን ጠበቅ አድርጎ ነው፡፡ ያገኘውን የሚያጋብስ ሐሳብ የሌለበት ወንደላጤ ብቻ ነው፡፡››





እንግዲህ አምጳርጵር ያገኙትን ያጋብሱ፡፡ እኔ የእሳቸውን ልጅ ልጆች ቁራኛ... (ብሶት)

‹‹ያለፈው ደሞዝህን ባትዘራ አሁን ማጠፊያው ባላጠረ፡፡ ልጅ ሲያሳድጉ ቆፍጠን ብሎ ነው፡፡ ላለፈው ፀሎት ከንቱ ጨኸት ይባላል፡፡ እወቅበት...››

## 32 - የደሞዝ ውርክብ

ደሞዝ አንድ ቀን ሲቀረው አምጳርጵር ማፏጨት ሲቀራቸው እየወበሩ እንዲህ አሉኝ፡፡

‹‹ውጭ ውጭ ማለት ቤት እየበደሉ አይደለም፡፡ ይሄማ የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ ይሉት ነገር ነው፡፡ እኔስ እነዚህን ሁሉ ማቲዎች አሸክመሃት ምን ትሁነው?››

‹ላያሸንፉ መታገል...› ሆኖብኝ ዝም አልኩ፡፡ ማፈግፈጊያ ቦታ የለኝም፡፡ ገደል አፋፍ ላይ ነኝ፡፡ አምጳርጵር ገገር መሬት ይዘዋልና ማጥቃት ቢሰነዝሩ ተንኮታኳች ነኝ፡፡

የደሞዝ ቀን ጠዋት ሺ-ትርንጉ ‹‹ሳንቲም እንዳይጎድል›› አለችኝ፡፡

ዝም ብያት ወጣሁ፡፡ ማመዬ አይደለም፤ መታከቴ ነው፡፡

ለምሳ ስመጣ እጁ እንደተዘረጋ ጠበቀኝ፡፡ የተዘረጋው እጁ ቁልቁል ሲያዩት ለህፃን ልጅ መታጠቢያ የተዘጋጀ የእንጨት ገበቴ ይመስላል፡፡

ደሞዜን ገበቴዋ ላይ ጣል አድርጌ ተቁለጨለጭኩ፡፡

ቆጠረች፡፡

‹‹አንድ ብር አጉድለሃል››

‹‹በእውቀቢስ መጥቼ ነው፡፡››

‹‹ልጅ ሲያሳድጉ ዘመናይ ሆኖ አይደለም፡፡ አስብበት፡፡››

በቀጣዩ ደሞዝ አሰብኩበት በእግሬ መጣሁ፤ የእንጨት ገበቴዋ ላይ ደሞዜን አስቀመጥሁ...



@BOOKALEM

ብሩን እየቆጠረች ‹‹የምን ማለክለክ ነው?›› አለችኝ፡፡

‹‹አንድ ብሩን ለማትረፍ ከአውቶብስ እኩል እሮጬ ነው?›› አልኳት፡፡

‹‹ልጅ ሲያሳድጉ ዘበናይ ሆኖ አይደለም፡፡ ለምን ከታክሲ እኩል ሮጠህ ሁለት ብር አታተርፍም ነበር?›› አለችኝ፡፡

በቀጣዩ ደሞዝ ከታክሲ እኩል ብሮጥ፡-

‹‹ልጅ ሲያሳድጉ ዘበናይ ሆኖ አይደለም፡፡ ለምን ከአውሮፕላን እኩል በርረህ ሶስት መቶ ብር አታተርፍም?›› ልትለኝ አይደል?

## 33 - ተረታማው ወር

ደሞዝ ምንድነው? ለሚሉኝ መልስ አለኝ፡፡ ደሞዝ ብር ሳይሆን የነፃነት ኩፖን ነው፡፡

- የመብላት ነፃነት ኩፖን
- የመጠጣት ነፃነት ኩፖን
- የመጠጣት ነፃነት ኩፖን ካለ የማምሸት ነፃነት ኩፖን ይዳበላል፡፡
- የማምሸት ነፃነት ኩፖን ካለ ደግሞ ውሽማ የመያዝ ነፃነት ኩፖን ይከተላል፡፡
- ከውሽማ የመያዝ ነፃነት ኩፖን ጋር ቤት ጥሎ የማደር ነፃነት ኩፖን አለ፡፡

ሴቶች ደሞዝህን ሲያገኙ ይሄ ሁሉ ነፃነት ትንፋሽ ያጥረዋል፡፡ ደሞዙን ያስረከበ ወንድ የሚንበሸበሸው በጊዜ እና በተረት ብቻ ነው፡፡ ወር ደረሰ አልደረሰ፣ ደሞዝ መጣ አልመጣ የወንዱ ጉዳይ አይሆንም፡፡ በጊዜ አልጋ ላይ ወጥቶ ሲጋር ተረት መጋለብ፡፡

‹‹ግፍ የተሰራብን እኛ፣ ካሱ ይለናል ዳኛ›› ይሄን ተረት የሰማሁበት ጠፋኝ፡፡

ተረቱን ሳንከላውስ ጩኸት ተሰማ፡፡ ቀጭን የሴት ድምፅ እሪበከንቱን እንደዳቦ ገመሰው፡፡





ሺ-ትርገጥ ግድግዳው እስኪያረገርግ እየተደናበረች ወጣች፡፡

‹‹አባዬን ገደሉት?›› አለች፡፡ ልጆቿ ተከተሏት፡፡

ባደረጉት አልኩ፡፡ የመጣባቸው ልጅ ሽምቅቋቸው ይሆን? የድል በዓል፣ የነፃነት ቀን በሆነ ነበር፡፡ ሺ-ትርገጥ ቆያይታ ተመለሰች፡፡

‹‹ማነው? ምንድነው?...›› አልኳት፡፡

በትዝብት እያየችኝ

‹‹ቀብረው ሲመለሱ እግዜር ይማርዎ›› አለችኝ፡፡

ሺ-ትርገጥ ይሄን ሁሉ ተረት የት ደብቃው ኖራ ነው?

‹‹ትንሽ እንኳን ልብህ አይደነግጥም?››

‹‹ምን ቀረኝና?›› ልላት አፌ አድርሼ መለስኩት፡፡

‹‹ሆዱ ፈሪ እግሩ ዳተኛ፣ አዳም ሲዋጋ እሱ ይተኛ ይባል አባዬ እውነቱን ነው፡፡ አልጋው የት ይሄድብሃል ወጣ ብለህ ብትመለስ?››

ሺ-ትርገጥ ወጣ እንድል ባልተጋለጠ ሁኔታ መጎትጎት ከጀመረች ሰነባብታለች፡፡ አንድ ነገር እየገባኝ ነው፡፡ ምን?

ሴቶች የወንድ ደሞዝ ሲያገኙ አየር የሚያጥረው የወንዱ ነፃነት ብቻ አይደለም፡፡ የእነሱም ነው፡፡ ወንዱ ቁጭ ብሎ የማሰሩትን ሲያይ፣ ነፃነት አይሰማቸውም፡፡ ፈለጉም አልፈለጉ የመንደር አውደልዳይ ለከፍ አድርጓቸው የሚያልፈው ባል ቤት ከሌለ ነው፡፡ ቤት ለቤት አፍ ለአፍ ገጥመው በነፃነት ማውራታቸው በወንድ የቤት ውስጥ ውሎ ይስተጓጎላል፡፡

እንደውም የአመት ፈቃድ ወጥቼ ቀኑን ሙሉ ቤት ቁጭ ባልኩ፡፡

* * *

ለምናልባቱ የትምህርት ቤቱን አስተዳዳሪ የዓመት ፈቃድ ጠየኩት፡፡ እየተሽቆጠቆጠ...



@BOOKALEM

‹‹በጋው ተገባዷል፡ ክረምቱ ደርሷል፡፡ ተማሪዎቹን ከፈተንኳቸው በኋላ ውጤት መስጠት ብቻ ነው፡፡ ከዚያ የሁለት ወር እረፍት አለህ…››

እኔ የማስበው በጋ፣ ክረምት የተሰኙት ቃላቱን ብቻ ነበር፡፡ መሄድ በጋ ነው፣ መቀመጥ ክረምት ነው የሚል ተረት አለ፡፡

‹‹አንድ ወር አትታገስም? አስቸኳይ ነገር ነው እንዴ? ሳጂን መርጌ በያዘው የነፍስ ማጥፋት ጉዳይ ነው?››

‹‹አዎን›› አልኩት ሳላስብበት፡፡

‹‹እንደምንም ለአንድ ወር አለዝበውና ክረምቱ ላይ መጥፋት ይሻልሃል፡፡ እኔ ደሞዝህን በመረጥከው ሰው እልክልሃለሁ፡፡ መጥፋት ሳለ መሞት አለች አሉ፡፡››

አሁን ተረቱ ተገላበጠ፡፡ መቀመጥ በጋ ነው፣ መሄድ ክረምት ነው፡፡

እውነት!

እውነት!

እውነት!

## 34 - እጨጌ አምጮች

‹‹አዲሱ አባባ›› ይላሉ ልጆቹ

‹‹አዲሱ አባባ አይደለሁም›› እላቸዋለሁ፡፡

‹‹ታዲያ ማነህ?››

‹‹ጊዜአዊው አባባ››

‹‹ጊዜአዊ ምንድነው?›› ትንሿ ጠየቀች፡፡ በመጣባቸው ልጅ የተሞከረችው ይቺ ደዘደዝ ሳትሆን አትቀርም፡፡ ለጠየቀችኝ የሚሆን ምላሽ አጣሁ፡፡ አሁን እኔ የአማርኛ መምህር ነኝ? ዝም!

‹‹ስንት ገድለሃል?›› ትልቋ ቀጠለች፡፡

‹‹ምን?››





‹‹ሰው›› ደነገጥኩ

‹‹ምንም!››

‹‹ምንም?›› ሁሉም በድንጋጤ ጠየቁ፡፡ ‹‹ትልቁ አባባ ግን አስር ገድሏል፡፡››

ያልተወለደው ልጄ አሳዘነኝ፡፡ እነዚህ ለማዳ አውሬዎች መካከል እድጎ ሰላማዊ የመሆን ዕድል የለውም፡፡ ተንከልካይ ደም የጠማው መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ የአያቱን የአምጳርጵርን ሪከርድ ይሰብር ይሆናል፡፡ እኔ ግን የለሁም…

ሺ-ትርገጥ ድንገት መጥታ ‹‹አባትና ልጆች! ምን ትዶልታላችሁ?›› አለች፡፡

‹‹ጊዜአዊ አባትና ልጆች›› የሚል አእምሮዬ ላይ መጣ፡፡ አፌን አልፎ አልሄደም'ንጂ፡፡

‹‹አባዬ ይፈልግሃል››

‹‹ምነው? ለምን?…››

‹‹ብቻውን ሆኖ መሰለኝ…››

‹‹ለምን ልጆቹን አይወስዱም?››

‹‹ልጆቹንማ አልሰጥም!!›› ደረቷን በመጅ እጇ ደቃችው፡፡ ‹‹ምንስ አባዬን ብትወደው ከልጆችህ ታስበልጠዋለህ? ምን አይነት ጨካኝ ነህ ግን?››

እምጳርጵር ጋ ስደርስ ሁለት ሰካራም አዛውንቶች ቀድመውኝ ነበር፡፡ ጠላ የያዘ ብርጭቆ ይጠባሉ፡፡ አምጳርጵር ያንጠለጠሉት ማንቆርቆሪያ እየታጠበ ነው፡፡

መጀመሪያ እምጳርጵር ወንደላጤነቱ ሰለቸቷቸው ደግሰው ከሰው ጋር ለመዋል የፈለጉ መስሎኝ ነበር፡፡ በኋላ ግን ተጠራጠርኩ፡፡ ጠላው ተቀዳልኝ፣ ስቀምሰው ደም ደም አለኝ፡፡ ‹‹አለ ነገር!››

እጃችንን እራሳቸው አስታጠቡን፡፡ አምጳርጵር ፃድቅ ሆኑ፡፡ ከፃድቅነት በስተጀርባ ምን ክፋት ይኖር ይሆን?



@BOOKALEM

የተሞናሞን እንጀራ በዶሮ ወጥ ቀረበ፡፡ ነገሩ እየከበደ ሲሄድ ታወቀኝ፡፡

እምጽርጽር መልካም አሳላፊ ሆነው ነጠላቸውን አደግድገው ‹‹ብሉ እንጂ! አልጣፈጣችሁምንዴ?›› ይላሉ፡፡

‹‹ወይ ዛሬ!›› አልኩ ያላወኩት ዕዳ በቁሜ ሲቀብረኝ እየታየኝ፡፡ አልፎ አልፎ እያጎረሱን በልተን ጨረስን፡፡

ከጠላ ጋር የእምጽርጽር ነገር ይንቆረቆርልን ጀመር፡፡

‹‹ወዳጆቼን እንዲህ አክብሬ ከጋበዝኩ ድፍን አስራ አምስት አመቴ፡፡ ባለቤቴ ከመሞቷ በፊት…››

ዝም አልን፡፡

‹‹ጉዳይ ስጉዳይ እንፈልግሃለን ስትሉኝ በምን አባቴ ጠርጥሬ፡፡›› ድምፃቸው ከፍ አድርገው ለጎረቤት ማቀበል ያዙ፡፡

‹‹እርግጥ አንተ ባለፈው ጊዜ የነገሩን ዳር ዳር ነካክተህልኝ ነበር›› ብለው ወደ እኔ ጠቆሙ፡፡ ‹‹ቀኛማች ማንአህሎህን በጋብቻ ብንዛመዳቸው ስትል ነገር ማዞር ሳይሆንልኝ ቀርቶ ነገሬም አላልኩት ነበር፡፡››

ልቤን ደስ ደስ አለው፡፡ የእግዚአብሔር መምጪያ ማሳለጪያ ብዙ ነው፡፡ የቀኛዝማች ማንአህሎ ወንድ ልጅ የእምጽርጽርን ብቸኛ ሴት ልጅ… መቼም የልጅ ልጆቻቸውን አይድሩ…

‹‹አዎ አንስቼብዎ ነበር›› አልኩ፡፡

‹‹እ-ይ፤ እኔን አለማወቅህ ነበር ይፈፀማል ብለህ ማንሳትህ››

‹‹እንዴት? ከቀኛዝማች ማን አህሎህ በላይ ማን እርስዎን ሊያህል?…››

‹‹እሱስ እርግጥ ብለሃል፡፡ ማን ደኅ ሚስቴ አፈር ገብታ እኔም እንዲሁ እከተላታለሁ እንጂ ዳግመኛ ሚስት የሚሉት አልሞከረውም፡፡ ማተቤስ? ክሬስ? ቃሌስ? ወዳጆቼ አትቀየሙኝ ጥያቄያችሁን አልቀበለውም፡፡››





እንደጉልቻ ሶስት ማዕዘን ሰርተን የተቀመጥን ባለሰዳዎች ተያየን፡፡ እምጽርጽር የሚያወሩት ግራ አጋብቶናል፡፡

‹‹እስከዛሬ፣ አስራ አምስት ዓመት ሙሉ የት ከርማችሁ ነው ዛሬ አግባ ብላችሁ የምትፈትኑኝ?››

ሰዳችንን አወቅነው፡፡

‹‹እርግጥ እናንተም እንዳላችሁት ቀኛዝማችና እኔ በትዳር መዛመዳችን ለፓርቲያችን ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡›› ትንሽ ዝም ብለው ‹‹ምን ላድርግ? በፓርቲዬ መጣችሁብኝ፡፡ ይሁን!››

ፈዘን ቀረን፡፡

‹‹ይሁን ካላችሁ ጊዜ ማባከን ደግ አይደለም፡፡ እንዱ ከለብላባ ቀድሞን ማፈር ይከተላልና ነገውኑ ሂዳችሁ የቀኝ አዝማችን የልጅ ልጅ ጋብቻ ጠይቁ፡፡››

በተስፋ የተወጠረች ልቤ እንደፈኛ ‹‹እድው›› ብላ ፈነዳች፡፡ ሚሸሽኩ፡፡ ግልፍ አለኝ፡፡

‹‹እምጽርጽር›› አልኩ፡፡

‹‹ስሜ እምበርብር ነው ከንቱ!›› ሲሉ ተነሚነጡ፡፡ ‹‹ይሄ አፍህ ለምዶብህ ሙሽራዎም ፊት እምጽርጽር ብትለኝ በነፍስ እንፋለማለን››

እንደሊላው ጊዜ አልበረገግኩም፡፡ በተረጋጋ መንፈስ አቤቱታዬን አቀረብኩ፡፡

‹‹በመጀመሪያ ደረጃ አሁን እርሶ ያሉዋት ልጅ ገና ልጅ ናት፡፡ አስራ ስድስት ቢሆናት ነው፡፡ ይልቅ ወንድም ካላት፣ ወይም እናት…››

‹‹የእሮጌ ልጅ ሆነህ ነገር ታጠፋለህ፡፡ ሴት አስር ዓመት ከሞላት ሃያ እንደማለት ነው፡፡ ስድስት ስታክልማ ሰላሳ በላት፡፡››

ግንባሬን አላጠፍኩም፡፡

‹‹ሰላሳ ብትሆን እንኳን ከእርስዎ እድሜ ጋር ሲነፃፀር…››

‹‹እየህ ከንቱው፣ ወንድ ልጅ ሚስቱ የማለችበትን ዕዳ ተወጥቶ ልጇን ትዳር ካስያዘ፣ እልፎ ተርፎ የልጅ ልጆቹን ቦታ ቦታ አስይዞ ቤት ንብረቱን ካፀዳ በኋላ ክበሌ እንደማለት ነው፡፡



@BOOKALEM

አዲስ ጎጆ ወጪ» አሉና የክርክሩን እውድ በመቀየር «አባቴ ቢኖር ይሄኔ እንዴት ይደሰት ነበር?» አይናቸው እንባ አቅርሮ ባደገደጉት ኩታ አባበሱት፡፡

«እኔ እዚህ ውስጥ እጄን ማስገባት ይከብደኛል» አልኩ፡፡

«እጅህን የዶሮ ፍትፍት ውስጥ ማስገባት ግን አይከብድህም፡፡ ሀፍረተ ቢስ!» አሉኝ፡፡

«እከፍላለሁ!» አልኩ፡፡

«አትችለውማ» አሉኝ፡፡

«መላላጫ ነው የበላሁት መላላጫ እከፍላለሁ፡፡»

«ሰማህ ወይ» አሉኝ ያዝኩህ በሚል ጣታቸውን ወዝውዘው «የዶሮ ብልት ገበያ አይሸጥም፡፡ የግድ ከነነፍሷ መግዛት አለብህ፡፡ ወዲህ ደግሞ የተሰራ ዶሮ ያልተሰራ በግ ከነነፍሱ እንደማለት ነው፡፡»

ደነገጥኩ፡፡ የዶሮ መላላጫ የበግ ሒሳብ ላይ ደረሰች፡፡ ቢሆንም «እከፍላለሁ» አልኩ ድርቅ ብዬ፡፡

«እስቲ ክልብ ክልብ አትበል፡፡ መች ጨረስኩና፡፡ አደግድጌ ሳስተናግድህ ነበር፡፡ ያለኝን ክብር ሳልቆጥር፣ ፓርቲዬ አምኖብኝ ገንዘብ ያዥ ያደረገኝን ስሙ-ጥርነት ከግምት ሳልከት ከፍ ዝቅ ማለቴ ስንት ያውጣ? በቀላሉ የበሬ ዋጋ በለው፡፡»

«ይተዉ እንጂ አምጸርጵር» አልኩ የምለው ጠፍቶኝ፡፡

«አንተ ድሮውንም ሲያዝሉህ ነካሽ፣ ሲያወርዱህ አልቃሽ መሆንክን አውቃለሁ፡፡ እንደተከበርክ በአማጭነት ብትሄድ ይሻልሃል፡፡ ዕድላችን ከቀናን ልጅቷን ከነውርሷ በወግ በማዕረግ እንረከባለን፡፡ ካልሆነ ሌላ ዘዴ ይፈለጋል፡፡»

## 35 - ተረታማ ጎዳና

የአማጭነቴን ዜና ለፎፍን ስነግራት ከልቧ ተንከተከተች፡፡ አይኗ ጠፍቶ ያምራል፡፡ የሌለ ያምራል?





«ልጅቷን አወቅሃት? ገላጭ እኮ ናት»

«መፅሐፍ ትገልጣለች?»

በእንም አይኗን አጥፍታ ሳቀች፡፡

«ትቀመቅማለች ነው ያለችህ» አለኝ የመጣባቸው ልጅ፡፡ ገና አሁን መኖሩን ልብ አልኩ፡፡

«ታንጋቀለች፡፡»

አምጸርጵር ጋቢ ለብሰው ሲጠብቁት ውጭ ማደራቸው ታይቶኝ ለማጭነቴን ወደድኩት፡፡

ፎፍን በመቆርቆር እያየችኝ «ዕዳቸውን ሁሉ ወዳንተ አስተላልፈው ‹ፀዴ› ትዳር ሊይዙ ነው አይደል?» አለችኝ፡፡

የምመልስላት ግራ ገባኝ፡፡

«ተረት መፃፍህን ጨረስክ?»

ከየት ወዴት ሄደች? ሳላስብበት መልስ ሰጠኋት «ጉሮዬ እራሱ ተረት ሆኗል፡፡»

«ተረት መፃፍ ፈልገህ የነበረው ለምንድነው?»

ተረት የመፃፍ ፍላጎት ለሌላ የሚነገር ምክንያት አለው? በቃ ዝም ብዬ፣ የአማርኛ መምህር ስለሆንኩ…

«ተረቱን ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙበት ነው አይደል?»

አዎ እንደማለት እራሴን ነቀነኩላት፡፡

«እስኪ መጀመሪያ እራስህ ተጠቀምበት፡፡» ፊቷ ላይ ቁጣ ያነበብኩ መሰለኝ፡፡

ፎፍን አንድ ነገር እንድረዳ አደረገችኝ፡፡ ተረት ቅርስ ሳይሆን ሲፈልጉ የሚመዙት የነገር ጎራዴ ነው፡፡ እኔ ግን እስከዛሬ እንደ ከበረ ድንጋይ ቆፍሬ አግኝቼ ለጆሮ ጌጥ አበጀዋለሁ፡፡ ምን ማለቱ ይሆን?

* * *

ሦስታችን በአማጭነት እየተንጋፈፍን ሄድን፡፡ እቴቴ ሙሽራቷን እየናት፡፡ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ቢሆንም ገና ከእንቅልፏ [illegible]ት ፊቷን ቧንቧ ሥር እየታጠበች ነበር፡፡

‹‹ምነው? ምነው?›› አሉ ቀኛዝማች፡፡ ‹‹መቼም የዛሬ ልጅ ወጉን ትቶታል፡፡ እንዲህ ነው ሽምግልና? እናንተ እንኳን ዕድሜያችሁ ገፋ ያለ ነው፤ ሳታስታውቁኝ ሽምግልና ትመጣላችሁ?››

‹‹ይቅርታ›› አልን፡፡

‹‹በፊት ቢሆን በእረበከንቱ ደንብ ሰድባችሁኛልና እንፋለም እላችሁ ነበር፡፡ እስቲ ይሁን! ይቺ የልጅ ልጄ አፏም ሰው ሆና ሽማግሌ መላኩም አንድ ነገር ነው፡፡ ጊዜ እናጠፋም፤ የዛሬ ሳምንት ስለሙሽራው ዘር የሚያውቅ ይዛችሁ ኑና ዘሩ ከዘሬ የሚቀላቀል ከሆነ...››

ይሄን ለአምጳርጵር ወስደን ነገርናቸው፡፡

‹‹እንኳን ለራሴ ለሌላም ይዘፍናል እንግቴ፡፡ እኔ ምን ሆኜ ሌላ እልካለሁ? ሳምንት እንሄዳለን›› አሉ፡፡

በሳምንቱ ሄድን፡፡

የቀኝ አዝማች ቤተ-ሰው ተቸምችሞ ባዩ ጊዜ አንዳች ነገር አልጎመጎሙ፡፡ በደንብ ተጠግቼ ስሰማቸው ፀሎት መሰል ነው፡፡

‹‹ከቀኝ አውለኝ፣ ከቀኝአማች አውለኝ›› ቀጭን ኩታቸውን አደገደጉ፡፡

የቀኝአዝማች ማንአህሎህ ታናሽ ወንድም ግራአዝማች ድሩ እንዲህ ሲሉ ጠየቁ...

‹‹መቼም ደርሶ ፊጥ የለም፡፡ ልጃችንን ስትጠይቁ ልደታችሁ ተየት ነው? ሐረጋችሁ ተምን ተመዘዘ? ዘራችሁ እንዴት ፈለቀ?››

አምጳርጵር የተጣፋ ኩታቸውን ተርትረው ዳግም አጣፉና ጎኛችን ትኒያዊ ፀሎት አደረሱ ‹‹ከቀኝ አውለኝ››

‹‹ይቀጥሉ እንጂ...››

‹‹አባቴ እኔን አስከትሎ ወደኮሪያ ሲዘምት እውነቱን ለመናገር ማዕረግ የለውም ነበር›› ብለው አምጳርጵር ጀመሩ፡፡ ‹‹ነገር ግን ጥሩ ተዋጊ መሆኑን በአይኑ ስጋ ለመመልከት ችያለሁ፡፡





በዚህ ላይ በአፍላ ጦርነት ወቅት ዘወትር የጠሩን ቀኝ ይዞ ስለሚዋጋ ቀኝ አዝማች ብንለው አያንሰውም፡፡ ይበዛበታል ካላችሁም ቀኝ ዘማች ልንለው እንችላለን፡፡››

‹‹ቀኝ አማች ብለናቸዋል ቀጥሉ...›› አሉ ግራአዝማች ድሩ

‹‹የአባቴ አባት መራዥ ተኳሽ ነበሩ፡፡ አጤ ምኒልክ ከንጉስ ተክለሃይማኖት ጋር እምባቦ ላይ ጦርነት ሲገጥሙ ንጉሱን ያቆሰላቸው ይሄው አያቴ ነበር፡፡ ታዲያ ምን ይሆናል ውለታውን አጤ ምኒልክ ልብ ሳይሉ ቀሩ፡፡ ይባስ ብለው ከንጉስ ተክለ ሃይማኖት ጋር አፍ ለአፍ ገጥመው ሲያወሩ በማየታቸው ብስጭት ተሰማቸው፡፡ ይሄን የሰሙት አባታቸው (የአባቴ አያት) የልጃቸውን በደል አልታገስ ብለው በዘጠና አመታቸው ሸፍተው ዱር ገቡ፡፡ በዙም ሳይርቁ የምኒልክ ጦር የገዛ ልጃቸውን ልክ ማረካቸው፡፡››

አምጳርጵር ሲወናጨፍ የፈረሰ ቀጭን ኩታቸውን አጣፍተው ቀጠሉ፡፡ የሚሉት አቅጣጫ ጠፋኝ፡፡ ዞረብኝ፡፡

‹‹ዕድል ተርታዬ ዕጣ ፈንታዬ ሁለቱንም ያጣቀሰ ነው፡፡ አንዱ አንዱ ማራኪ ሌላው ተማራኪ፡፡ አንዱ ታማኝ ሌላው ከጂ፡፡ አንዱ ሀጥዕ ሌላው ፃድቅ ቅም አያቴ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ከገቡት ሀዋርያት አንዱ ነው ይባላል፡፡ ይሄ ቅም አያቴ ሀዋርያነቱን ከመቀባቱ በፊት ወጋሪ፣ ሰቃይ ነበር፡፡ ጌታችን ተሰቅሎ ተጠማሁ ባለጊዜ ቅም አያቴ የኖረ ቡሆ ሆምጣጣውን ከባልቴት ቤት፣ ከርቢ ከሆክል፣ እምቡላ ከናግሬ ከነግስታቱ ቤት፣ የገዞን ሀሞት ከአዳኝ ቤት ሰብስቦ በማሰሮ አንድነት ሰብቆ ችቦ ሙሉ የሀር ጎፍላ ነክሮ መስቀሉ እርቆት ነበርና በዘንግ አስሮ በቁልስሁስጳ ደግፎ ጌታችንን አጠጣው፡፡››

አምጳርጵር የሚሉትን ለመረዳት ስሞክር የበለጠ ዞረብኝ፡፡ እነቀኝ አማችም ሳይዞርባቸው አልቀረም፡፡

‹‹የዘር ሆኖብኝ እኔም አሻፈረኝ ያለኝን እንዲሁ ሰፍነግ አጠግሰሁ፡፡ ወዲህ ያየኝ እንደሆነ ከጌታችን ግራና ቀኝ የተሰቀሉት ጥጦስና ዳክርስ የቅም አያቴ የወንድም ልጆች ነበሩ፡፡ ጥጦስና ዳክርስ የዘራችን ተምሳሌት ናቸው፡፡ በቀኝም በግራም የተሰቀልን እኛ ነን፡፡ ዘራችን በጂ ካሉት በጄ የሚል በቀኝ የሚያውል ነው፡፡



@BOOKALEM

አሻፈረኝ ካሉት አሻፈረኝ የሚል በግራ የሚያውል ነው፣ ጨረስኩ!» ብለው ተጉረጠረጡ፡፡

የቀኝ አማች ማንአህሎ ቤተ-ሰው ተቁለጨለጨ፡፡ ከጥቂት ፀጥተኛ ቆይታ በኋላ ግራዝማች ድሩ ጉሮሮአቸውን ጠራረጉ፡፡

«ዘራችን እንዲህ ካለ ዘር ጋር መቀላቀሉ ያኮራናል፡፡ ልጃችንን ለልጅዎ ሰጥተናል፡፡፡»

አምጸርጽር «ለልጅዎ?» ብለው ፍስስ አሉብን፡፡ ልብ ድካም ይሆን? እንኳን ልብድካም ልብም ያላቸው አይመስለኝ ነበር፡፡ ልብ የሌለ እኔ ነኝ እንጂ...

## 36 - የማጠላለፍ ወግ

የአምጸርጽርን የልጅ ልጆች ልብ ብዬ ሳያቸው በጣሊያን የተወረርኩ መሰለኝ፡፡ ብስል ቀያዮች ናቸው፡፡ ቀያይነታቸው ሄዶ ሄዶ ወደ ነጭነት አድልቷል፡፡ አምጸርጽር ፈረንጅ ለመጥለፍ ኢምባሲ ለኢምባሲ ከሚዞሩ እነዚህን ቢያቀርቡ ይቃመኑ ነበር፡፡ ለመሆኑ የፈረንጆቹ ጉዳይ ከምን ደረሰ? የእስር ቤቱ ማንባታስ?... አምጸርጽር እንዲዘነጋ መፈለጋቸው ስለገባኝ ላነሳባቸውና በጥቂቱም ላበሳጫቸው ወደቤታቸው ሄድኩ፡፡

«ጎሽ ጎሽ ልንልክብህ ስናስብ መጣህ» አሉኝ፡፡

ሁለቱ ሽማግሌዎች በሁለት ጉልቻ ቅርፅ ተቀምጠዋል፡፡ ሶስተኛው ጉልቻ እየተጠበቀ ነበር ማለት ነው፡፡ አምጸርጽር ሶስት እባል ያለው ቡድን ያቋቋሙት ለምን ይሆን?

በታመመ አውራ ዶሮ ጠባይ እየተራመዱ፣ በተራቆተ ኩራት ተልዕኮው ላልታወቀ ጓድ እንዲህ አሉ፡፡

«እንደምታውቁት የቀኝአማች ማንአህሎን የልጅ ልጅ ለጋብቻ ጠይቀን ብዙ ደጅ ጠናን፡፡ ጤናችንንም አደጋ ላይ ጣልን፡፡፡» ከንፈራቸውን በቀጭር ቀረጣጠፉና ቀጠሉ፡-

«አልሆንልንም፡፡ ተንቀናል፡ ተደፍረናል ብታምኑም ባታምኑም በቁም ሞተናል፡፡ እዚህ ባፍንጫችን ስር ሙሽሪት እየተመላለሰች ቤተሰቦቿ እንድርላችሁም ማለታቸው ንቀት ካልሆነ ሌላ ምንድነው?





አንድ ፍሬ ልጅ ለአዛውንቱ ሙሽራዎች ጠይቀን መልሰላችን እንዴት ንቀት ሊሆን እንደቻለ አልገባኝም፡፡ በስብሰባ ሥነ-ሥርዓት እጄን አወጣሁና እንዲህ አልኩ፡፡

«እራሳችንን የሰደብን እራሳችን ነን፡፡፡»

«እንዴት?» አሉ አምጸርጽር የፉከራ መንጎራደዳቸውን ሁሉ አድርገው፡፡

«ቀድሞውኑ መጠየቅ አልነበረብንም» አልኩ በድፍረት፡-

«አፌ ቁርጥ ይበልልህ» ሲሉኝ ድንግርግር አለኝ

«መጥለፍ ነበረብን»

አመዴ ቡን አለ፡፡

«ክኛ ይለፍ፡ ሽማግሌ ልክን የወጉን ሞልተናል፡፡ አሁን ወደ ጠለፋው!»

«ወንጀል ነው!» አልኩ ተሽቀዳድሜ፡፡ እንዲያግዙኝ ወደ ጠላፊው ጓድ አባላት ተመለከትኩ፡፡ አደጋው የታያቸው አይመስልም፡፡ የቀረበላቸውን የግብስ ጠላ በግብስ ቆሎ እያመሳጠሩ ወደ ሆዳቸው ይልካሉ፡፡

«ወንጀልስ ወንጀል ነው፡፡፡» አሉ አምጸርጽር «ግና የእናንተ ወንጀል በኔ ላይ ነው፡፡፡»

«እርስዎ የጠላፊነትዎ ድርሻ አልዎት፡፡ እኛ ደግሞ የአጠላላፊነታችን አይቀርልንም፡፡፡»

«ወንጀሉን የማይችል አንገት የለኝም፡፡ ፊታችሁን በሽማ ሸፍኑና ጥለፏት፡፡ እንዲ ለኔ ካስተላለፋችሁ በኋላ ነገሩን በሽማግሌ እይዘዋለሁ፡፡ ባይሳካልኝ እንኳን ብቻዬን ወደከርቸሌ! እናንተን ማን ቢያጋልጣችሁ ትወነጀላላችሁ?»

በመቀበልና ባለመቀበል መካከል ስንጠራወዝ...

«ትፈጭ የነበረች ታንጓልል ተሳናት አሉ፡፡ ምነው ልጄ? ለጠለፋ እንኳን አዲስ አይደለህ፣ ልጄን ስትጠልፍ ወንጀልነቱ ያኔ እንዲህ ቢታይህ ደግ ነበር፡፡፡»



@BOOKALEM

ይሂን ጠለፋ ተቀበልኩ አልተቀበልኩ ወህኒ ፊቴ የተደነቀረ ዕጣ-ፈንታዬ ነው፡፡ እምጳርጵር ያቀዱት ጠለፋ ላይ ተሳትፌ የማምለጥ ዕድል ከገጠመኝ ደግ፤ ካልሆነም….

….መጥፎ ዕድሌን እያማረርኩ ፊቴን በነጠላ ሸፍኜ ለጠለፋ ተሰማራሁ፡፡

እምጳርጵር ሁሉን አጥተው ጨርሰዋል፡፡ እንዲህ አሉን፡-

‹‹ልጅቷ እንደ እያቷ ቀኞማች ማንአህሎ ሌሊት መጓዝ ታበዛለች፡፡

መቼም የዘርነውና አትነቀፍም፡፡ ልጅቷ እንደአያቷ ቀኞማች በእጭሩ መታጠቅ ታበዛለች፡፡ ጭኗ ቢታይም የአርበኛ ዘር ናትና ከጀግንነት እንጂ ከዝሙት አይቆጠርባትም፡፡ ልጅቷ እንደ አያቷ ቀኞማች ማንአህሎ ፀጉሯን ታንጨፈርራለች፡፡ መቼም የፋኖ ዘር ናትና ከቅሬዎች የሚመድብባት የለም፡፡››

እኩለ ሌሊት ሲሆን ሸማችንን ተከናንበን መተላለፊያዋ ላይ ገበቃ ወጣን፡፡ ልጅቷ ሲነጋጋ ሲል ሲነጋጋ ባሰበ አካሄድ መጣች፡፡

እንደጠላፊ ሳይሆን እንደመልካም አሳላፊ ቀረብኳት፡፡

‹‹ምንድነው?›› አለች፡፡

የዘር ሆኖባት እንደአያቷ ትቆጣለች ማለት ነው፡፡

‹‹እንደጠለፋ አትቁጠሪንና የምንመራሽ ቤት ሂደሽ ትገቢያለሽ እንደ ጠላፊ አትቁጠሪያቸውና እዚያ አንድ ሰው ይጠብቁሻል›› አልኳት፡፡

ግራ የተጋባች መሰለች፡፡ በኋላ ነገር ሲገለጥላት ለማምለጥ ተወለካከፈች፡፡ እኛ ሳንሆን ጫማዋ ጠልፎ ጣለልን፡፡ በገመድ ለማሰር ስንሰናዳ ድንገት ከጥሻ ውስጥ ብቅ ያሉ የሰው ጥላ ሁለቱን የጠላፊ ጓዶች በዱላ ጠለፏቸው፡፡ እኔ ላይ ያረፈው ዱላ ጭንቅላቴን ሰቶ ትከሻዬን አበረየኝ፡፡

ተበራይተን ተረፈረፍን፡፡

በዚህ መካከል የእምጳርጵርን ድምፅ ሰማሁ፡፡





‹‹እዚህ እያደፈጡ ቤት መጥለፍ ወግ አድርገው ይዘውታል›› ይላሉ፡፡

ግራ ተጋባሁ፡፡

እምጳርጵር ጋቢያቸውን እንደተከናነቡ ዱላቸውን አስቀምጠው የወደቀችውን ልጅ በክብር ደግፈው አነሱና ‹‹አይዞሽ አይዞሽ›› አሏት፡፡

ወደእኔ ጠጋ አሉና ልጅቷ እንዳትሰማ እያንሾካሾኩ ‹‹መቼም ይቅርታ እንደምታደርግልኝ አይጠረጠርም፡፡ ጠለፋ ወንጀል ነው፡፡ የሚያቀጣው ለልጅቷ ውለታ ውሎ መለማመጥ ነው፡፡ ከዚህ መአት ስላዳንኳት ከወንደላጤነት አደጋ እንደምታድነኝ አይጠረጠርም›› አሉ፡፡

ልጅቷን አቅፈው እያባበሉ፡- ሲሄዱ እንደሰመመን ታየኝ፡፡

## 37 - ፍንገላ

እምጳርጵር ወበሩ፡፡ በፍቅር መሰል ነገር ተጠምደው ታዩ፡፡ ልጅቷን እኩለ-ሌት ጠብቀውም ወደቤቷ ይሸኝዋታል ይባላል፡፡

እኔ ትከሻዬን እያስታመምኩ ቆየሁ፡፡ በእኔ መታመም የደነገጠ እሪበከንቱዋዊ ባለመኖሩ አንድ ነገር ተረዳሁ፡፡ የእምጳርጵር አስፈሪነት እየደበዘዘ መሄዱን፡፡

ለእኔ ግን እምጳርጵር መቼም እምጳርጵር ናቸው፡፡ አይሰንፉልኝም፡፡

በደህናው ጊዜ እምጳርጵር እናቴን በዱላ ሲበጠብጡኝ የነበረውን የምግብ ግትልትል እያሰብኩ ምራቄን እውጣለሁ፡፡ ሌላ የለም፡፡ ከምግብ ጋር የተያያዘ ኩርፊያ እንኳን አይፈቀድልኝም፡፡ ሺ-ትርገጥ አባቷን አጣቅሳ ትተርትብኛለች፡፡

‹‹ሆድ ሲሞላ ፍቅር ሌላ፣
ሆድ ሲጎድል ሰው ያጋድል፡፡››

እንደጋለ ብረት ሆድ ከሚተረትር ተረት ሸሽቼ እምጳርጵር ጋ እሄዳለሁ፡፡ ጥቂት ቆሎና ጥቂት ጠላ፣ ብዙ ደባ፡፡ ወጥመዳቸውን



@BOOKALEM

እያወቅሁ ዘው እንድል ሆን ብለው በልጃቸው የሚያስርቡኝ እየመሰለኝ መጥቷል፡፡ ‹‹ምነው እጋደልክ?›› ሲሉ በነገር ተቀበሉኝ፡፡ ትከሻዬን በዱላ እንደነረቱኝ ጠፍቷቸው ነው? ብሶት ብሶት ሲሰማኝ የእምጳርጽር ተረት ከብቦ እንደ እውሬ ጥርሱን ያገጥብኛል፡፡

‹‹ያገባ ወንድና

የታሰረ እንበሳ

በብላሽ እገሳ››

እውነታቸውን ነው ማግባት መታሰር ነው፡፡ ከሁለት መታሰር እንዱን ነበር የመረጥኩት፡፡

ስድስት ኪሎ የታሰረ እንበሳ ብቻ ለምን ይጎበኛል? እንደ እኔ አይነቱም ያገባ እንስሳ መጎብኘት አለበት፡፡

‹‹እምጳርጽር…››

‹‹ክንቱ! እፍህን እንኳን መግዛት አቅቶህ ያስቸግርሃል፡፡››

‹‹ይልቅ ወሬ እንዳያመልጥዎ…››

‹‹ምን?››

‹‹ዛሬ ሰዎች ሰብሰብ ብለው ስለፈረንጆቹ ጠለፋና ስለመሬቱ እያወሩ ነበር፡፡››

‹‹እና?››

‹‹እናማ ፈረንጆቹን ለምን እንጠልፍም?›› ብቻዬን ከምታሰር እሳቸውን ይዤ…

ሳቁ፡፡

ግራ ገብቶኝ እየኳቸው፡፡ ሲጠሩዋቸው ዝም ማለት የእምጳርጽር ዘዴ ነው፡፡ እንዲህ አሉ፡-

‹‹ሁሉ ሆነ ቃልቻ፣ ማን ሊሸከም ስልቻ፣ አሉ፡፡ ለአንተ ያዘጋጀሁልህ ሌላ ስራ አለ፡፡››

‹‹ምን?››





‹‹ቆይ አጋሮችህ ይምጡ››

እነዚያን ጉልቻዎች መሆን አለበት፡፡ እኔስ ማን ሆኜ? ያው የእምጳርጽር ጉልቻ አይደለሁ?

መጡ፣ ሁለቱ የጉልቻ ድንጋዮች መጡ፡፡ እኔ ከእነሱ ተደምሬ ሶስተኛው ማዕዘን ላይ ተቀምጫለሁ፡፡ እምጳርጽር ዘራቸውን ይጥዱብን ጀመር

‹‹የቀኝ አዝማች ማንአህሎ የልጅ ልጅ…›› ብለው በጉጉት ‹‹ሔ?›› እስክንላቸው ጠበቁ፡፡ ዝም አልኩ፡፡

‹‹ምነው በዚያ ሰሞን ልትጠልፏት ስትሉ በዱላ አልገላገልኳችሁም?›› የእፀፉ ማጥቃት መሆን ነው አልኩ፡፡ ‹‹…መቼም የትልቅ ሰው ዘር ትልቅ ነው ውለታዋን ቆጥራ ጥሩ ወዳጄ አድርጋኛለች፡፡ ዛሬ ውጭ ውጭ ማለት አብቅቶ ቤት የተፈአለታለሁ፡፡ ለጋብቻ የምጠይቅበት ጊዜ እንዲሆን ወስኛለሁ፡፡››

እምጳርጽር መቼም ጥሩ ወዳጅ አድርገውን የደስታቸው ተካፋይ እንድንሆን አልነገሩንም፡፡ ለምን ይሆን?

‹‹ጥሩ›› አልኩ

‹‹ጥሩነቱስ ጥሩ ነበር፡፡ ብቻ…›› ብለው ዝም አሉ፡፡

እኔም ዝም አልኩ፡፡ ጉልቾቹ የሚሰሙም አልመሰሉ፡፡ እንደጋሪ ፈረስ የቀረበላቸውን የገብስ ቆሎ አቀርቅረው ወዳፋቸው ይላሉ፡፡

‹‹ብቻ ልጅቷ የጌታ ልጅ ናት፡፡ በተቸመቸመ እሽክር መካከል ስትሽለከለክ ያደገች፡፡ እንደሰማሁትማ ልጅ ሆና ሰኞ ማክሰኞ ትጫወት የነበረው በከሰል መሬት ላይ እስምራ ሳይሆን ጥቋቁሮቹን እሽክሮች እጋድማ ነበር አሉ፡፡ ታዲያ ይቺ ልጅ እኔ ቤት ለእንግድነት ስትመጣ ‹‹እልቦ እሽክር›› ቢጠብቃት እንዴት እደናን ይቀለው? ምንኛስ ይበርዳት? እንዴትስ ትታዘበኝ?…››

የፈለጉት አልገባኝም፡፡

‹‹አየህ፣ እሽክር የሌለው ቤት ለባለቤቱ ግርማ ሞገስ ጠር ነው፡፡ ያለግርማ ሞገስ በምን አባቷ ልጅቷን እጄ አገባለሁ?›› ድምፃቸው ሙሾ ወደማውረድ እዘነበለ፡፡



@BOOKALEM

‹‹በነገራችን ላይ›› አሉ አምጻርጽር ነገራቸውንና ድምፃቸውን እጥፍ አድርገው ‹‹በነገራችን ላይ ልጅቷ ውለታዬ ቢከብዳት ብዬ የጠለፋችሁን አውቃቸዋለሁ ከሰሺና እመሰክርልኝ ለሁ፡፡ ማስረጃም አይጠፋም ብያታለሁ፡፡ ስትጠልፏት የመታቿችሁ ቁስላችሁ ደረቀ እንዴ?›› አሉን፡፡

እኔ፣ ክፉኛ ደነገጥኩ፡፡

ሁለቱ አሮጌ ጌኞች የቀረበላቸውን የገብስ ቆሎ ከማጥቃት ለአፍታም አልተገቱም፡፡

‹‹ቢበዛ አስር አመት ነው፡፡ ምንም አይደል? አስር አመት ምን አላት? ነገ ናት! ያኔ እኔ አሽከር ባይኖረኝም በውለታ ግርማ ሞገስ ልቧን እራርቼ ወልጄ ከብጄ እጠብቃችኋለሁ፡፡ ዕድላችሁ ከቀና በልጅቷ ውርስ በየሳምንቱ ዳጠሮ ሰንጋ ይላክላችኋል፡፡››

‹‹እንዴት ይሆናል?›› ስል ጮህኩ

‹‹እንዴት አይሆንም?›› ሲሉ ጮሁ

‹‹ይሄ ግፍ ነው!›› የምለው ባጣ

‹‹ግፍስ የምወዳት ልጅ ስትመጣ አሽከር እያጣሁ እያየችሁ ጥላችሁኝ መሄዳችሁ…››

‹‹አመዛዝኑ እንጂ አምጻርጽር…›› የምለው ባጣ

‹‹አሽከር ያጣ ወንድ ያው ቀለበ ቢስ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ምን ቀልብ አለውና ያመዛዝናል?››

‹‹አዙረው እዩ እንጂ አምጻርጽር››

‹‹እሱስ አዙሬ ሳይ ነው ያደርኩት የተሻለም አስቤአለሁ፡፡ እንዚህን ልጆች አስር ዓመት ከማሳሰራቸው አንድ ዓመት አሽከር ቢሆኑኝ አይሻልም? ስል እራሴን አማክሬአለሁ፡፡ እናንተ ምን ትላላችሁ?

ዞረው ዞረው ወደ ፍላጎታቸው መጡ፡፡ ተቁለጨለጭኩ፡፡ አምጻርጽር ለባርነት ፈነገሉኝ፡፡ መቁለጭለጬ ወጥመድ ውስጥ መውደቄን ስላረጋገጡ፣ አምጻርጽር ወደጓዳ ገብተው ያሰናዱትን ሶስት የአቡጀዲ ቁምጣና ጥብቆ አመጡ፡፡ አደሉንም፡፡ በ…





ድልድሉ እኔ በር ላይ ዘብ እንድቆም፣ ከጠገበ ዱላ ጋር ተዘየነብኝ፡፡ ግቢው መስፋቱ አሁን ጠቀመኝ፡፡ እባሬ አግዳሚ አያዩኝም፡፡

ድንገት የግቢው በር ተበረገደ፡፡ የአምጻርጽር እጮኛ ዘረች፡፡ የበሩን ጓጓታ ሰምተው አምጻርጽር ወጡ፡፡ ‹‹ማነው? ማነው?›› አሉና ልጅቷን ሲያዩ ወደኔ ዞሩ፡፡

‹‹አሽከር መቀጠሩ እኔ ከጓዳ ማነው እያልኩ እንድወጣ ኖሯል?›› አሉኝ፡፡

ልጅቷ እየተግለበለበች መጥታ አምጻርጽር አፍንጫ ስትደርስ ፍሬን ያዘች፡፡ አፈጠጠች፡፡ አምጻርጽር እፍኝ ጥሬ አከሉ፡፡

‹‹አንቱ? ምን አይነት ትሊታም ነዎት ግን? እርስዎ አይደለም አባባ ጋ አማላጅ የላኩት? እኔን ይመኛሉ? ትንሽ አያፍሩም? የልጅ ልጅ የለዎትም?››

‹‹የጭፍንና የልባሙ ፀብ ትዝ አለኝ፡፡ እንደ ልባሙ ልብ እራቃቸው፡፡ እኔን አዩኝ፡፡ እናቷን በላት ሊሉኝ ይሆን? ወይስ ጥለፋት? ፈራሁ፡፡ እሷ ስትግለበለብ እሳቸው አይናቸውን እኔ ላይ እንደተከሉ ልባቸውን ደግፈው ቁጭ አሉ፡፡ የአምጻርጽር ሰሞንኛ ዘዴ መሆኑ ነው፡፡ ነገር ሲከብድ መልሳቸው ‹‹ልቤን›› ማለት ሆኗል፡፡

## 38 - ስንብት

መቼም አምጻርጽርን ማመን ቢያዳግትም በጠና መታመማቸው ታየ፡፡ ልጅቷን አምጣልኝ በሚል ግድ ውስጥ እንዳይከቱኝ በመፍራት አልጠየኳቸውም፡፡

በሶስተኛው ቀን እስከዛሬ የበደሉትን ሁሉ ሲያስጠሩ እኔም ጥሪው ደረሰኝ፡፡ ሄድኩ፡፡

በደከመ ድምፅ ‹‹በድዬአችኋለሁ ይቅር በሉኝ›› አሉ፡፡

እኔን ጨምሮ የተበደልን ሁሉ እንባችን አይናችን ላይ …ንቸረፈፈ፡፡



@BOOKALEM

ጠጅ ቀጂው ገብሩማ ቢጫ እጁን ቢጫ ፊቱ ላይ ከልሎ ተንሰቀሰቀ፡፡ ያንባውም ቢጫ ሳይሆን አይቀርም፡፡

‹‹የጊዜ እንጂ የሰው ጀግና የለውም›› አልኩ በልቤ፡፡ የሰው እጅ ቢያጠብቅ ይላላል፣ ቢቆልፍ ይፈታል፡፡ እሳቸውን ጊዜ ጣላቸው ብዬ እኔም እንዲህ መታበይ አለብኝ?

‹‹ገብሩ›› አሉ አምጻርጵር ‹‹በድዬሀለሁ፣ በዚህ በረጋ ጉልበቴ ተመክቼ ልቡናህ እያወቀ ዘወትር አንድ ብርሌ ጠጅ እከድህ ነበር፡፡ ይቅር በለኝ፡፡››

‹‹ይቅር ብያለሁ›› አለ ገብሩ፡፡

‹‹የተነጠቅኸው ጠጅ ሰማይ ቤት ድኝ ሆኖ ነፍሴን ይለበልባታል አሉ፡፡ ያኔ ኡ! ኡ! ብለህ፣ በህግ ይዘህ ብታስከፍለኝ ኖሮ ምን ነበረበት? እማኝ አታጣ፡፡ ሳይቸግርህ በጠጅ ድኝ ነፍሴን ለበለብካት፣ የእሳት እቀብ አጠማኸኝ፡፡ የእሳት እቀብ ጠጣና›› ድንገት ብልጭ አለባቸው፡፡

ቢሆንም አልተቀየምናቸውም፡፡

እኔን ጠሩኝ፡-

‹‹እነሆኝ አምጻርጵር›› አልኳቸው፡፡

‹‹ስሜ አምበርብር ነው ከንቱ›› አሉኝ፡፡

ድንግጥ አልኩ፡፡

‹‹ያም ሆነ ይህ አጭበርብሬ ልጄን ድሬሃለሁ፡፡ እርግጥ ተጠቅመሃል፡፡ ታዲያ እግዜር ማጭበርበሬን እንጂ አንተ መጠቀምህን አይቆጥርም፡፡ ነፍሴ ባንተ የተነሳ ለእሳት ትዳራለች አሉ ለእሳት ተዳርና፡፡››

አልተቀየምኳቸውም፡፡

‹‹ለማንኛውም ይሄን ጥቅምህን እየነገርክ እግዚሀርን በጸሎት ወትውትልኝ፡፡››

‹‹እሺ›› አልኩ

‹‹እሺ ትላለህ እንጂ አታደርገውም፡፡ ልብህ ዳተኛ ነው፡፡ ለእኔማ ቢሉህ አለህ ነገር፡፡ ደግነቴ ልጄ ዘወትር በሎቱ





እንድታደርስ ልታስገድድልኝ ትችላለች፡፡ እንደውም ለእሷው አነግራታለሁ፡፡›› ተመናፈሩ፡፡

አሁንም አልተቀየምናቸውም፡፡

በመጨረሻ ጫማ ሰፊውን ጠሩት

‹‹ብሻህ?››

‹‹አቤት››

‹‹መተከሻ አድርጌህ ነበር፡፡ ሰወጣ ስገባ ይሄ ያልሞተ በትሬን ከጀርባህ ጋር እዋድዱው ነበር፡፡ እንደምትሰራው ጫማ በትሬ ኩርንችት ሚስማር ቢኖርበት ኖሮ ከጀርባህ ጋር ተሰፍቶ ይቀር ነበር፡፡ አሁን ምን አደረከኝ? ሰማይ ቤት ‹‹ብሻህ ምን አድርጎህ ነው?›› ብባል ምን እመልሳለሁ?... አንተማ እንደ ሲጋሚ አድርገህ ነው?›› ብባል ምን እመልሳለሁ?... አንተማ እንደ ሲጋሚ እሪኛ ወደገደል ስሄድ እያየህ ዝም አልከኝ፡፡ ገደል ገባሁልህ... ገደል ገባና፣ አንተ ልግመኛ፡፡ ስመታህ ብትሰድበኝ እንኳን ቅጣቱ በቀለለልኝ ነበር›› አሉና እንዲህ አሳረጉ፡፡

‹‹ሁላችሁም፣ ይህ ቃሌ የስንብት ነው፡፡ ወደውጭ ሊሆዱ ከተሰናበቱ በኋላ ከቦሌ እንደሚመለሱት ድንገት ከሞት ከተመለስኩ ይሄ ሁሉ ቃሌ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡ በነባሩ ተግባሬ እቀጥላለሁ፡፡

## 39 - ራዕዩ

‹‹ባለፈው ጊዜ በየፊናው እየጠራሁ ይቅርታ ጠየኳችሁ፡፡ እናንተ ግን ታበያችሁ›› አሉን አምጻርጵር፡፡

‹‹ለመሃን እምዬ፣ ለአገልጋይ እትዬ ብርቋ ነው አሉ፡፡ አሁን የጠራኋችሁ የእኔን ወቀሳ ላሾነደጉድ አይደለም፡፡››

‹‹እንደኪያንስ አምጻርጵር?›› አልናቸው፡፡ እኚህ ቆጭባራ የሆኑ ሰውዬ ምን ሊሉን ይሆን?

‹‹ራዕይ አየሁ››

‹‹ምን?›› አልናቸው

‹‹ኡም፣ ራዕይ አየሁ፣ ምነው?››

ምንም!›› የእሪበከንቱ ሰው ጉድ ለመስማት እቆብቁበ አልጋቸው ዙሪያ ተኮለኮለ፡፡ አምጻርጵር ውሉ ባልለየ መንገድ



@BOOKALEM

እግዚሀር እጅ ተይዘው ሁለት ሳምንት እልጋ ቁራኛ መሆናቸውን እናውቃለን፡፡ እኛ የማናውቀው እግዚሀር በእሳቸው በኩል ለአራ በከንቱ ህዝብ መልዕክት መላኩን ነው፡፡

እምጳርጵር በአንድ ጎናቸው ከተጋደሙበት ትከሻቸውን ቀና አድርገው ትራስ አንረሱና...

‹‹ስላየሁት ራዕይ ከመመስከሬ በፊት ራዕይ ምን ማለት እንደሆን አብራራለሁ›› አሉን

‹‹ደግ፣ ይሁን›› አልናቸው፡፡

‹‹እግዚሐር በሶስት መንገድ ህዝቦቹን ይቀርባል፡፡›› አገዳደማቸውን አመቻችተው ቀጠሉ ‹‹እነሱም ትንቢት፣ ራዕይ እና መነጠቅ›› ናቸው፡፡

‹‹ትንቢት ማለት ሌላ ሳይሆን እንደ ሰው የእግዚሀር ራዲዮ መሆኑ ነው፡፡ ራዕዩ ከፈለጋችሁ ደግሞ ከእግዚሀር በኩል ተዘጋጅቶ የሚላክ ማስጠንቀቂያ በቴሌቭዥን እንደማየት ነው፡፡ እግዚሀር ይሄ አይበቃም ካለ እንደ ነብዩ ኤልያስ በእሳት ሰረገላ ነድቶ ነድቶን ይነጥቅና ትርኢቱን በገሃድ ያሳያል›› ብለው ወደእኔ ዞሩና ‹‹በቴሌቭዥኝ ቀጥታ የሚተላለፍ ፕሮግራም ምንድነው የሚባለው?›› አሉኝ፡፡

‹‹ላይቭ›› አልኳቸው

‹‹መነጠቅ እንዲያ ነው፡፡ የእግዚሀር ራዕይ ለስላሳ አዝዘህ እንደምታየው እግር ኳስ አይደለም፡፡ የሚታይብትን ሰው ይመርጣል፡፡ ንፁህ መሆን ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ጦም ጠሎት ያስፈልጋል፡፡ እንደምታዩት ታምሜ አልጋ ከያዝኩ በኋላ ምንም እንኳን ወድጄ ባይሆንም ከሰው ጋር ተገናኝቼ አላውቅም፡፡ ምንም እንኳን ወድጄ ባይሆንም ይርበኛል፡፡ ሲርበኝ ፈጣሪዬን እወቅሳለሁ፡፡ ታዲያ እግዚሀር ታምሜ ያልጠየቃችሁኝን እንደ ሱባኤ፣ እጦቼ ያልበላሁትን እንደ ጦም፣ ያማረርኩትን እንደ ጦለት ቆጥሮ ራዕይ ገለጠልኝ፡፡››

ሳይታሰብ እልልታው ቀጠለ፡፡ ‹‹ብእርስዎ ጦም ጠሎት እግዚሀር ቀረበን፣ ቀርበንም አዘዘን፡፡ እንታዘዛለን!›› አልን፡፡

‹‹አዳሜ! ባትታገርማ ከጎንሽ ታገኚዋለሽ›› አሉ እምጳርጵር ‹‹አሁን ወደራዕይ እገባለሁ፡፡››





ቤቱን ፀጥታ መታው፡፡

‹‹እንዲህ ነው›› አሉና እንደ ተረት አባት፣ አይናቸውን አቦዘዙ፡፡ ‹‹አንድ የብርሃን ብሉኮ የተጎናጠፈ ሰው የመልአክት ጋሻ ጃግሬዎቹን ይዞ እዚህ እኔ ደጅ ግራዋዋ ሥር ቆሞ ይጠራኛል፡፡››

‹‹የትኩሳት ቅዠት ነው›› አለ አንዱ ልብ ያላልኩት ሰው

‹‹የእግዚሐር ራዕይ ነው ቅዠት?›› ገመምተኛው ቁጣ ተናነቃቸው፡፡ ‹‹አልተኛሁ! ቅዠትኮ ተኝቶ ነው፡፡ እንዲሁ ነው በገሃድ የታየኝ፡፡››

‹‹ይቀጥሉ እምጳርጵር›› የሴት ድምፅ ነበር፡፡

‹‹ተውኩት!›› አሉ በገመምተኛ ኩርፊያ

ተለመኑ

ተጠሩ፡-

‹‹በኋላ ያ በብርሃን ድርና ማግ የተሸመነ ብልኮ የተከናነበ ሰው ሲጠራኝ አመንታሁ፡፡ ‹ና ወዲህ› አለኝ፡፡ ‹ና ወዲህ አምበር ብር አትፍራ ጠሎትህ ተሰምቷል፣ ጦምህ ተመዝግቧል› አለኝ፡፡

‹‹እነሆኝ አልኩ እንደውሻ እግሩ ስር እየተልወሰወስኩ፡፡ መቼም ለፈጣሪ ውሻ መሆን አያስንቅም፡፡

‹‹ብድግ በል ዋሻ!' አለኝ፡፡ የሰፈርህ ሰዎች እምጳርጵር የሚሉህ ለምን ሆነና አሁን ታስመስላለህ? ቀጣፊ!›› አለኝ፡፡ ኢየችሁ ይሄ ተበስተጀርባዬ የምታሽሟጥጡኝ ስሜ ሁሉ እሱ ዘንድ ደርሷል፡፡ ለማንኛውም አባት አስቸጋሪ ልጁን እንደሚወድ እግዚሀር እኔን መውደዱን አሳየኝ፡፡››

‹‹መዘባቱን ትተው ይቀጥሉ›› አንድ ሰጋጋ ድምፅ

‹‹አመት አሳወራ!›› አሉና ቆጣ ብለው ‹አምበርብር› አለኝ እንደ ሐምሌ ነጎድጓድ በሚያስገመግም ድምፅ፡፡ የጎረቤቶችህ ክፋት አንተን አነፃህ፡፡ ታመህ ባይጠይቁህ፣ ርበህ ባያበሉህ፣ ሰላላ ድምፅህ ፈጣሪህ ደጅ ስትንፏቀቅ ደረሰች፡፡ ለማንኛውም አንተም የእግዚሀር ሰብል ነህና መታጨጃህ ደርሷል፡፡ ወደእርሱ ትሰበሰባለህ፡፡ ሶስት ቀን ያለበሽታ ቆይተህ እኑጉት ላይ ትሞታለህ አለኝ፡፡››

‹‹እና ሊሞቱ ነው?›› አለ የእሪበከንቱ ህዝብ፡፡ እውነቱን ለመናገር እኔ ግን ደስ ደስ አለኝ፡፡ የተበተበኝ የነገር ድር እንዲህ መበጣጠሻው ደረሰ፡፡



@BOOKALEM

‹‹የእሪበከንቱ ህዝብ ለእኔስ አታልቅስ፣ ለእራስህ አልቅስ›› አሉ፡፡

‹‹እንዴት?››

‹‹እኔን የጎዳችሁ መስሏችሁ ሳትጠይቁኝ ቀራችሁ፡፡ የታመመ ሰው መጠየቅም አለመጠየቅም ከበሽተኛው ጋር አይያያዝም፡፡ እግዚሐርን ነው ያልጠየቃችሁት፡፡ የራዕዩ ምልክትም እዚህ ላይ ነው፡፡ ሂድ ንገራቸው የተባልኩትም ይሄንኑ ነው፡፡ የእሪ በከንቱ ሰው ታምሜ ጠየከኝን? ተርቤ አበላኸኝን? ታርዤ አለበስከኝን? ይላል እግዚአብሔር፡፡››

‹‹እግዚኦ!›› አሉ እሪበከንቱዎች

‹‹አዳሜ የት ትገቢ ይሆን?›› አሉ በገመምተኛ ቃቻ ‹‹ከእን ግዲህ አምበርብር ወኪሉ እግዚሀር ነው፡፡ አምበርብርን የበደለ እግዚሀርን በደለ፡፡ አምበርብርን የተተናኮለ እግዚሀርን ተተናኮለ፡፡ ለአምበርብር ያልታዘዘ በእግዚሀር ላይ ጠመመ ይኸው ነው!!››

የእሪ በከንቱ ሰው የእግዚአብሔርን አፍ ያገኘ መስሎት እምጳርጵርን በመልካም ምግብ ጠቀጠቀ፡፡ የሚፈልጉትን መጠጥ እየጠየቀ ጠመቀ፡፡ እምጳርጵርን ሲከፋቸው እግዚሀርን አስቀየምኩ እያለ ተንቀጠቀጠ፡፡ እግዚሀርን የሚያስተናግደው የእሪበከንቱ ነዋሪ የድርጊቱ መልካምነት ጊዜውን ልብ እንዳይለው ጋርዶበታልና የእምጳርጵር ሽኝት ከሰስት ቀን አልፎ ሰስት ሳምንቱን ደፈነ፡፡ ይሄን ከእኔ በስተቀር ማንም ልብ አላለውም፡፡ ያበቃለት ችግሬ ከእምጳርጵር ጋር በእሪበከንቱዎች እንክብካቤ እንሰራራ፡፡ የእሪበከንቱ ህዝብ ደሜ ባንተ ላይ ነው!!

## 40 - ከራዕዩ ባሻገር ምን አለ?






Description

የተለያዩ መፅሐፍትን በአነስተኛ ሜጋባይት
የሚያገኙበት ቻናል····· @BOOKALEM

t.me/BOOKALEM

@BOOKALEM